# ታጋሽ ሁን!

## በአስቸጋሪ ጊዜያት እግዚአብሔርን መጠበቅ

**የብሉይ ኪዳን ትርጓሜ**

**መጽሐፈ ኢዮብ**

ዋረን ዌንደል ዌርዝቢ

BIBLE BASED BOOKS

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት
የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
የፖ.ሣ. ቁጥር 127
አዲስ አበባ

የመጀመሪያ እትም 2004 ዓ.ም (2012 G.C)

Copyright © 2009 by SIM Ethiopia.
Originally published in English under the title of
BE PATIENT.
Copyright © 2009 by Warren Wiersbe.
David C. Cook, 4050 Lee Vance View, Colorado Springs,
Colorado 80918 U. S. A.
All rights reserved.

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
በመጻሕፍት ውስጥና በሂሳዊ ጽሑፍ ውስጥ ከሚወሰዱ አጫጭር ጥቅሶች በቀር ያለ አሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ የዚህ መጽሐፍ የቱም ክፍል ሊወሰድ አይገባም።

ትርጉም፡- ዳንኤል ተሾመ
እርማት፡- ኃይሉ ጀናይ
ዋና አርታዒ፡- ዘነበ ገብረሐና
የኮምፒዩተር ለቀማ፡- ዓለምፀሐይ እውነቱ
የገጽ አቀማመጥ፡- ጥሩወርቅ በቀለ
የሽፋን ሥዕል፡- ካንቺወዲያ መሳፍንት

ለተጨማሪ መረጃ
ለኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
የፖ.ሣ. ቊጥር 127፣ አዲስ አበባ ብለው ይጻፉ።



*የዚህ መጽሐፍ መታሰቢያነት*
*ጥልቅ ከሆነ አድናቆታችን ጋር የጸሎት እገዛቸውና*
*ማበረታቻቸውን እግዚአብሔር ታላቅ*
*በሆነ ሁኔታ ለተጠቀመበት*
*«ለጸሎት አጋሮቻችን» (እነማን እንደ ሆናችሁ*
*ታውቃላችሁ) ይሁን።*
*«ባስታወስናችሁ በእያንዳንዱ ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔርን*
*እናመሰግናለን።»*
*ደግሞም እየጸለይንላችሁ ነው!*

## ማውጫ


ትልቁ አሳብ፡- 'ታጋሽ' ሁን ለሚለው መጽሐፍ

በኬን ባፍ የተሰጠ መግቢያ ........ 5

አንድ መልእክት ከደራሲው ........ 11

1. ድራማው ተጀመረ (ኢዮብ 1-3) ........ 14

የዕረፍት ጊዜ ........ 29

2. ውይይቱ ጀመረ (ኢዮብ 4-7) ........ 32

3. ውይይቱ ቀጠለ (ኢዮብ 8-10) ........ 43

የዕረፍት ጊዜ ........ 56

4. የተቈጣ «ወጣት» (ኢዮብ 11-14) ........ 57

5. ውይይቱ ወደ ክርክር ተለወጠ (ኢዮብ 15-17) ........ 72

የዕረፍት ጊዜ ........ 85

6. እውነተኛው ጠላት፣ እባክህን ልትቆም ትችላለህን? (ኢዮብ 18-19) ........ 86

7. ሁሉም ነገር በአመለካከትህ ይወሰናል (ኢዮብ 20-21) ........ 101

የዕረፍት ጊዜ ........ 114

8. በችሎቱ ውስጥ ሥነ ሥርዓት ይከበር! (ኢዮብ 22-24) ........ 115

9. እንዴት ያለ ደካማ ሹክሹክታ! (ኢዮብ 25-28) ........ 131

10. ነገሬን አቅርቤአለሁ! (ኢዮብ 29-31) ........ 145

11. ኤሊሁ መልሶቹ አሉት (ኢዮብ 32-33) ........ 161

12. ኤሊሁ ስለ እግዚአብሔር አብራራ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ጥብቅና ቆመ (ኢዮብ 34-37) ........ 175

የዕረፍት ጊዜ ........ 191

13. የመጨረሻው ፈተና (ኢዮብ 38-42) ........ 192

መደምደሚያ ........ 204




# ታላቁ አሳብ

«ታጋሽ ሁን!» ለሚለው መጽሐፍ
በኬን ባፍ የተሰጠ መግቢያ

ሥቃይ ሁሉም የሰው ልጆች የሚለማመዱት ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮ ነው:: ሰዎች ሁሉ በሕይወታቸው ውስጥ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ሥቃይን ይለማመዱታል፣ ደግሞም በዚያ የመከራ ወቅት፣ ዘወትር ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ:: እነዚህም፡- «ለምን? እግዚአብሔር ሆይ፣ ለምን? አሁን ስለ ምን ሆነ? ይህን ለመቀበል ያደረገኝ ያደረግሁት ነገር ምንድን ነው?» የሚሉት ናቸው:: እነዚህ በአእምሮአችን ውስጥ የሚያስተጋቡ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ አያገኙም::

እውነት ለመናገር፣ አንዳንድ ጊዜ በእራሳችን ላይ የመከራን ወቅቶች እናመጣለን፣ እናመጣም እንዴ? ቀዩን መብራት ከጣስን ቲኬት እናገኛለን:: ከግብራችን ላይ ብናስቀር እና ብንያዝ፣ የሂሳብ ቁጥጥር ይደረግብንና እንቀጣለን:: ጥርሶቻችንን ለዓመታት ቸል ብንላቸው፣ የጥርስ መቦርቦር እና የድድ እብጠት ይመጣብናል ደግሞም የጥርስ ሙሌትም ሊያስፈልገን ይችላል:: እነዚህ የመከራ መቀበያ ጊዜያት እራሳችን ያነሣሣናቸው በገዛ እራሳችን ግድ የለሽነትና ቸልተኝነት ምክንያት ብቻ የሚመጡ ናቸው::

ይሁን እንጂ፣ ባልተጠበቀ ሁኔታና የማይገባን ሆኖ እየተሰማን በሕይወታችን ውስጥ ሥቃይ በር የሚያንኳኳበት ጊዜያት አሉ፣ ደግሞም ለምን እንደ ሆነ ሳይገባን በሆነ አጣብቂኝ ስፍራ ላይ እራሳችንን እናገኛለን:: ኢዮብን የምናገኘው ልክ እንደዚህ ባለው ሁኔታ ውስጥ ነው:: በአንድ ወቅት ጤናማ፣ ሀብታም፣ ስኬታማ የሆነ ነጋዴ እንዲሁም ሁለንተናውን ለቤተሰቡ የሰጠ አባት ነበር:: በቀጣዩ ወቅት፣ ሽፍቶች (አደጋ ጣዮች) መጥተው ያለውን ንብረት ሁሉ ወሰዱ፣ ደግሞም ቋሚ የሆኑ ንብረቶችን አወደሙ:: ልጆቹ ሁሉ ተገደሉ፣ እንደዚሁም አካሉ አሰቃቂ በሆነ ቁስል ተመታና የሚመግልም ሆነ:: ይህ ስለ ምን እንደ ሆነ ኢዮብ የሚያውቀው ነገር አልነበረም:: ምንም የሠራው ስሕተት

አልነበረም። በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን አላደረገም፤ በሚስቱ ላይ አልማገጠም ወይም ልጆቹን አልበደለም። ከደረሰበት ከእነዚህ ነገሮች አንዱም የሚገባው አልነበረም።

በመቀጠልም፣ ጉዳዩን ከዚህ የከፋ የሚያደርገው ይህ ሁሉ ሥቃይና መከራ፣ እግዚአብሔር ከሰይጣን ጋር ያደረገው ውርርድ ውጤት ይመስላል። (ኢዮብ 1:19፤ 2:1-9 ተመልከት።) ይሁንና፣ ከዚህ ሁሉ ሰቆቃ ባሻገር፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «በዚህ ሁሉ፣ ኢዮብ አልበደለም፤ በእግዚአብሔርም ላይ ክፉ አልተናገረም።» (ኢዮብ 1:22፣ አ.መ.ት)። ኢዮብ በተፋፋመ መከራ ውስጥ ታላቅ የጽናት እና የትዕግሥት ሰው ነበር፣ ደግሞም የእርሱን ምሳሌነት ብንከተል እንደዚሁ መሆንን ልንማር እንደምንችል እምናለሁ። ከኢዮብ ሕይወት ምሳሌነት ስለ መከራ ምን ልንማር እንደምንችል እንመልከት።

ሀብቱንና ልጆቹን ካጣ በኋላ ኢዮብ በመጀመሪያ ያደረገው ነገር እግዚአብሔርን ማምለክ ነበር፦ «ኢዮብም ተነሣ፤ ልብሱንም ቀደደ፤ ራሱን ተላጨ፤ በምድርም ላይ ተደፍቶ ሰገደ፤ እንዲህም አለ፤ ዕራቁቴን ከእናቴ ማሕፀን ወጣሁ፤ ዕራቍቴንም እሄዳለሁ። እግዚአብሔር ሰጠ፤ እግዚአብሔርም ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም ቡሩክ ይሁን» (ኢዮብ 1:20-21፣ አ.መ.ት)። የእርሱ የነበረ ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር መሆኑን ኢዮብ ተገንዘበ። እግዚአብሔር ቤተ ሰቡን፣ ቁሳዊ ሀብቶቹን ሁሉ እንዲሁም ስኬቱን እንኳ ሰጥቶት ነበር። ደግሞም እግዚአብሔር ሰጥቶት ከሆነ፣ መልሶ ሊወስደውም ጭምር እንደሚችል ኢዮብ ያምን ነበር። በዚህ ሁሉ ኢዮብ ጥያቄ አላነሣም። በሕይወቱ ያለውን የበላይነቱን ተገነዘበ፣ ስለዚህም ደግሞ በአምልኮ ወደ ምድር ሰገደ። ኢዮብ ምድራዊ (አካላዊ) በሆኑ መከራዎቹ መካከል እግዚአብሔርን አመለከ ደግሞም ለሚስቱ እንዲህ አላት፦ «መልካሙን ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀበልን፣ ክፉውንስ አንቀበልምን?» (ኢዮብ 2:10፣ አ.መ.ት)። ኢዮብ በጥላቻ መካከል እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ያለውን የበላይነት በተመለከተ ያለውን ድፍረት ለመጠበቅ ችሎ ነበር። ይህ ድፍረት (መተማመን) ሊታመን የማይቻል ትዕግሥት ሰጠው። የመከራ ወቅቶችን በትዕግሥት ለማሳለፍ የምትችል መሆን ከፈለግህ፣ ልክ እንደ ኢዮብ እግዚአብሔር በሕይወትህ ውስጥ የበላይ እንደ ሆነ በዚህም ደግሞ እያንዳንዱን ነገር እንደ ፈቃዱ ለሕይወትህ የሚሠራ መሆኑን ልትገነዘብ ያስፈልጋል።

ሁለተኛ፣ እንደ ኢዮብ መከራን በትዕግሥት ለማሳለፍ የምትችል መሆን ከፈለግህ፣ ስለሚያደርገው ነገር ማብራሪያ እንዲሰጥህ እግዚአብሔርን አትጠይቅ። ኢዮብ እንደ እኛው ሰው ነበር፣ ደግሞም እነዚህ አሳዛኝ ክስተቶች በሕይወቱ ውስጥ እንዲመጡ በመፍቀዱ ምክንያት አንዳንዴ በእግዚአብሔር ላይ ይቈጣ ነበር። ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ የነበረው መተማመን የሚዋዥቅ አልነበረም። በመከራ መካከል በእግዚአብሔር ላይ የመታመን ችሎታ አስቸጋሪ የሆነ ተግባር ነው፣ ይሁንና እግዚአብሔር ባለፉት ጊዜያት ለእኔ የነበረውን ታማኝነት ከሚያስታውሱኝ ነገሮች አንዱ ነው። ዛሬ ወደ ኋላ ተመልሼ በሕይወቴ ከዓመታት በፊት የገጠመኝን የመከራ ጊዜያት መመልከት እንዲሁም በዚያ ሁሉ ውስጥ የእግዚአብሔርን ታማኝነት መመልከት እችላለሁ። ልክ እንዳሁኑ ጊዜ ግልጥ በሆነ መልኩ መመልከት አልችልም ነበር፤ ነገር ግን ዛሬ ሁሉንም ነገር እጅግ በተሻለ መንገድ እረዳለሁ። እግዚአብሔር ባለፉት ጊዜያት ለእኔ ያሳየውን ታማኝነት የማይበት ይህ ችሎታ፣ እርሱ ታማኝ እንደ ሆነ በማወቅ ዛሬ በማልፍባቸው አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እግዚአብሔርን በትዕግሥት እንድጠብቀው ይረዳኛል። እርሱ ልክ ባለፉት ጊዜያት እንዳደረገው ሁሉ፣ በዚህ የወቅቱ ቀውስ መካከል እየሠራ እንደ ሆነ አውቃለሁ፣ ደግሞም በእርሱ መታመን ያስፈልገኛል።

ይህን የመታመን ጉዳይ ብሬናን ማኒንግ የገለጠበትን መንገድ እወደዋለሁ፦

> ዘወትር ጀግኖች ከሚያሳዩት ጋር የተቀራረበ የድፍረት መጠንን የሚሻ በመሆኑ የማይነቃነቅ መታመን ብዙም የማይገኝና ውድ የሆነ ነገር ነው። የኢየሱስ መስቀል ጥላ በውድቀት፣ በተቃውሞ፣ በመተው፣ በመካድ፣ ሥራ በማጣት፣ በብቸኝነት፣ በድብርት፣ የሚወዱትን ሰው በማጣት መልኩ በሕይወታችን በኑሮአችን ላይ በሚያጠላበት ወቅትና ለሁሉም ነገር ደንቆሮዎች በምንሆንበት ጊዜ፣ ነገር ግን የገዛ እራሳችን ሥቃይ

> በሚሆንበት ጊዜ፤ በዙሪያችን ያለው ዓለም የተቈጣ ስፍራ በሚመስልበት ጊዜ በእነዚያ ጊዜያት በኀዘን እንዲህ ብለን እንጮኽ ይሆናል፡- «አፍቃሪ የሆነ አምላክ ይህ እንዲከሰት እንዴት ሊፈቅድ ይችላል?» እንዲህ ባሉት ቅጽበቶች ያለመታመን ዘሮች ይዘራሉ። ምንም ነገር በእኛ ላይ ይከሰት በእግዚአብሔር ፍቅር ለመታመን የጀግንነት ድፍረት ያስፈልጋል። (*Ruthless Trust* [New York: Harper-Collins, 2000], 3-4)

ከባድ የሆኑ የሥቃይና የመከራ ጊዜያት ጥልቀት የሌለው፣ ላይ ላዩን የሆነ «በእርግጥ፣ በእግዚአብሔር እታመናለሁ» የምንልበትን ሁኔታ ያስወግዱታል። አሁንም እግዚአብሔርን ለመውደድ እንዲሁም በመከራ መካከል ለእርሱ ሙሉ በሙሉ የተሰጠ መሆን፣ እርሱ አድሎአዊነት እና ወገንተኝነት እንዳለበት በሚመስለን ጊዜ እንኳ እርሱን መውደድ እውነተኛ ፍቅር፣ እውነተኛ አምልኮ፣ እውነተኛ መታመን ነው።

በመጨረሻም፣ ልክ እንደ ኢዮብ መከራን በትዕግሥት መቋቋም ለመቻል ዓይኖችህን በዘላለማዊ ነገሮች ላይ አሳርፍ። በመከራ ወቅቶች በማልፍበት ጊዜ፤ ሥቃዬ መላው ትኩረቴን ለመውሰድ እጅግ በጣም ይቀልለዋል፣ ስለዚህ ምናልባት ይህ ወቅት እጅግ አስቸጋሪ ቢሆንም መንግሥተ ሰማይ ትመጣለች የሚለውን እንዲያስታውስ እራሴን እጫኑዋለሁ። በመከራዎቹ መካከል ሊመጣ ያለውን ስለሚያውቅ በዚህ ደስታ ላይ በማተኮሩ ምክንያት ኢየሱስ መከራውን በትዕግሥት ለመቋቋም ችሎአል። የዕብራውያን ጸሐፊ እንዲህ ሲል ይጽፋል፡-

> የእምነታችንን ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና። በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳትደክሙ ከኃጢአተኞች በደረሰበት እንዲህ ባለ መቃወም የጸናውን አስቡ። (ዕብ. 12:2-4)

አዎን፣ እግዚአብሔር አስቸጋሪ ነገሮች በሕይወታችን ውስጥ እንዲከሰቱ ይፈቅዳል፤ ነገር ግን በእነዚህ ጊዜያት ለብቻችን አለመሆናችንን ልናውታውስ ይገባናል። ልክ እንደ ኢዮብና እንደ



ኢየሱስ ሁሉ ከእኛ በፊት ብዙዎች የመከራን መንገድ ተጉዘዋል፣ ደግሞም በትዕግሥት መቋቋም ችለዋል።

አንድ የመጨረሻ አሳብ። እግዚአብሔር በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ላይ መከራ እንዲወርድ የሚያደርግባቸው ወቅቶች እንዳሉ እኔ አውቃለሁ፣ ይህም የእምነታቸውን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን፣ ለእርሱ ያላቸውን ፍቅርንም ደግሞ ለመፈተን ነው። በሥቃይ ላይ ሳለህ ፍቅርህን የሸንገላ ማድረግ ትችላለህ። እኔ በእውነት በልቤ የማምነው እንዲሁም ስለ እግዚአብሔር በእውነት የሚሰማኝ ነገር፣ እኔ እውነት እወደው እንደ ሆነ እና እንዳልሆነ ሁሉም ነገር በመከራ ወቅቶች ግልጽ ይሆናሉ። ለእግዚአብሔር ያለኝ የፍቅሬ የመጨረሻው ማረጋገጫ በመከራ ወቅቶች ፍጹም በሆነ መታመን እና መገዛት ጉልህ ሆኖ ይታያል። እነዚህ እውነተኛ መሆናቸው የሚረጋገጠው አይቀሬ በሆነው ወሳኝ ፈተና (መከራ) ብቻ ነው። «ቢገድለኝም እንኳ፣ በእርሱ ተስፋ አደርጋለሁ» (ኢዮብ 13:15፣ አ.መ.ት) ማለትን በምንችልበት ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር ያለህ ፍቅር እውነተኛ እንደ ሆነ ታውቃለህ።

ይህን ትርጓሜ በምታነብቡ ጊዜ እግዚአብሔር ማን ስለ መሆኑና እንዲሁም ምን ያህል እንደሚወዳችሁ ደግሞም ማንኛውም ነገር ቢከሰት እናንተም በምላሹ በፍጹም ልባችሁ፣ በፍጹም አሳባችሁ፣ እንዲሁም በፍጹም ኃይላችሁ እንድትወዱት ምን ያህል በጥልቀት እንደሚሻ ሥር የሰደደ ግንዛቤ እንዲኖራችሁ እጸልያለሁ።

የዶ/ር ዌርዝቢ ትርጓሜዎች (ማብራሪያዎች) ለብዙ ዓመታት በመጋቢነት ሳገለግል የምሪትና የጥንካሬ ምንጭ ሆነውኛል። የእርሱ የሆነ የተለየ ሥልቱ እጅግ ሥነ ትምህርታዊ ከመሆን ይልቅ በሥነ መለኮታዊ ትምህርቱ ረገድ ጤናማ ነው። ጥልቅ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል እውነት እያንዳንዱ ሰው ሊረዳውና ተግባራዊ ሊያደርገው በሚችልበት መንገድ አብራርቶታል። የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎችም ሁኑ ወይም ገና ጀማሪ የሆናችሁ አዳዲስ ክርስቲያኖች፣ ልክ እንደ እኔው ሁሉ ከዋረን አዳዲስ አሳቦችን ትማራላችሁ። መጽሐፍ ቅዱሳችሁን በአንድ እጃችሁ የዋረንን (ትርጓሜ/ማብራሪያ) መጽሐፍ በሌላው እጃችሁ

አድርጋችሁ ጥልቀት ያለውን የእግዚአብሔርን እውነት በትክክል ልትገልጡት እንዲሁም በሕይወታችሁ ውስጥ እንዴት እንደምትተ ገብሩት ልትማሩ ትችላላችሁ።

ወዳጄ ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል እውነታዎችን በጥልቀት ተ መገብ፣ በእነርሱ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስን ታገኛለህ፣ ደግሞም ነፃነት፣ ሰላም፣ ዋስትና እና ደስታ በእነርሱ ውስጥ አሉ።

- ኬን ባፍ

የኮስት ሂልስ ኮሚዩኒቲ ቸርች ፓስተር

አሊሶ ቬጆ፣ ካሊፎርኒያ



# አንድ መልእክት ከደራሲው

«ኢዮብ እንዴት እንደ ታገሠ ሰምታችኋል» (ያዕቆብ 5:11)።

አዎን፣ ብዙ ሰዎች ስለ ኢዮብና ፈተናዎቹ ሰምተዋል፤ ነገር ግን እነዚያ ፈተናዎች በአጠቃላይ ምን እንደ ሆኑ ደግሞም እግዚአብሔር እያከናወነው ስለ ነበረው ነገር አልተገነዘቡም ነበር። አሊያም ኢዮብ ያንን ሁሉ ፈተና የተቀበለው ዛሬ ከእርሱ ተሞክሮ ዎች የእግዚአብሔር ሕዝቦች በመከራ ውስጥ እንዴት ታጋሾች እንደሚሆኑና እስከ መጨረሻውም ድረስ መጽናት እንዴት እንደሚችሉ ይማሩበት ዘንድ እንደ ሆነ አልተገነዘቡም።

ስለ መጽሐፈ ኢዮብ ለመጻፍ በወሰንሁ ጊዜ፣ ለባለቤቴ እንዲህ አልኳት፣ «ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ እንድችል፣ በምን ያህል መከራ ውስጥ ማለፍ ይኖርብኝ ይሆን? የሚለውን አሳብ እያውጠነጠንሁ፣ እደነቃለሁ» (ግላዊነት በማይኖረው እና ሥነ ትምህርታዊ በሆነ መንገድ ብቻ ለመጻፍ ወይም ለመስበክ አልፈልግም። ቃሉ ለእኔ የተጨበጠ እውነት መሆን አለበት፣ ወይም ይህ ካልሆነ፣ ለሌሎች የተጨበጠ እውነት እንዲሆንላቸው ማድረግ አልችልም።) እግዚአብሔር እንድንለማመዳቸው ፈቅዶ ከመጡ መከራዎች እኛ የምንገነዘበው ጥቂቱን ነው! ነገር ግን እግዚአብሔር ታማኝ መሆኑንና ጸሎትን የሚመልስ መሆኑን፣ እንዲሁም ስለ እኛ ሁልጊዜ በአእምሮው አስደናቂ የሆነ ዓላማ እንዳለው (ኤር. 29:11) መመስከር እንችላለን።

መጽሐፈ ኢዮብን ለማጥናትና በእውነትም መልእክቱን ለመገንዘብ አንተም እንደዚሁ «በ ሳት» ውስጥ ማለፍ ይኖርብህ ይሆናል። እያለፍህም ከሆነ፣ አትፍራ! በእምነት ከኢዮብ ጋር ይህን ብቻ ተናገር:- «ግን እኔ የምሄድበትን መንገድ ያውቃል፤ ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ» (ኢዮብ 23:10፣ አ.መ.ት)። ወርቅ እሳትን አይፈራም። ማንኛውም የተቃጠለና በምድጃው ውስጥ የተተወ ነገር ቢኖረን ምንም የሚጠቅመን ነገር አይኖርም።

መጽሐፈ ኢዮብን በአንድነት እያጠናን ሳለን በሕይወታችን ውስጥ ሁለት ነገሮች እንደሚከናወኑ አምናለሁ:: በምታልፉበት መከራ ውስጥ ታጋሽ መሆንን ትማራላችሁ ደግሞም በምታልፉበት መከራ ውስጥ እንዴት ሌሎችን መርዳት እንደምትችሉ ትማራላችሁ:: ዓለማችሁ መበረታታትን (መጽናናትን) በሚሹ ሰዎች የተሞላች ናት፣ እንዲሁም ምናልባት እግዚአብሔር እናንተን ለዚያው አገልግሎት እያዘጋጃችሁ ይሆናል:: በሁለቱም መንገዶች ይህ መጽሐፍ እንደሚረዳችሁ ተስፋ አደርጋለሁ::

- ዋረን ዌንደል ዌርዝቢ



# ለመጽሐፈ ኢዮብ ጥናት የሚረዳ አስተዋጽኦ

ፍሬ ነገሩ:- እግዚአብሔር በሚያመጣችው መከራዎች ውስጥ ጽናና በሳል ሁን

ቊልፍ ጥቅስ:- ኢዮብ 23:10

I. የኢዮብ ኃዘን (ኢዮብ 1-3)

1. ንብረቱ (ኢዮብ 1-5)
2. መጥፎ ገጠመኙ (ኢዮብ 1:6-2:13) (የሀብት፣ ቤተሰብ፣ ጤና መጥፋት)
3. ግራ መጋባቱ (ኢዮብ 3:1-26)

II. የኢዮብ መከላከያ (ኢዮብ 4-37)

1.የመጀመሪያው ዙር (ኢዮብ 4-14)
   ሀ. ኤልፋዝ (ኢዮብ 4-5)፤ የኢዮብ ምላሽ (ኢዮብ 6-7)
   ለ. በልዳዶስ (ኢዮብ 8)፣ የኢዮብ ምላሽ (ኢዮብ 9-10)
   ሐ. ሶፋር (ኢዮብ 11)፣ የኢዮብ ምላሽ (ኢዮብ 12-14)
2. ሁለተኛ ዙር (ኢዮብ 15-21)
   ሀ. ኤልፋዝ (ኢዮብ 15)፤ የኢዮብ ምላሽ (ኢዮብ 16-17)
   ለ. በልዳዶስ (ኢዮብ 18)፤ የኢዮብ ምላሽ (ኢዮብ 19-20)
   ሐ. ሶፋር (ኢዮብ 20)፤ የኢዮብ ምላሽ (ኢዮብ 21)
3. ሦስተኛው ዙር (ኢዮብ 22-37)
   ሀ. ኤልፋዝ (ኢዮብ 22)፤ የኢዮብ ምላሽ (ኢዮብ 23-24)
   ለ. በልዳዶስ (ኢዮብ 25)፤ የኢዮብ ምላሽ (ኢዮብ 26-31)
   ሐ. ኤሊሁ (ኢዮብ 32-37)

III. የእግዚአብሔር ነፃ አውጪነት (ኢዮብ 38-42)

1. እግዚአብሔር ኢዮብን ትሑት አደረገው (ኢዮብ 38:1-42:6) (40:3-5 እና 42:1-6 ተመልከት)
2. እግዚአብሔር ኢዮብን አከበረው (ኢዮብ 42:7-17)
   ሀ. እግዚአብሔር የሚተቹትን ሰዎች ገሠጻቸው (ኢዮብ 42: 7-10)
   ለ. እግዚአብሔር ሀብቱን መለሰለት (ኢዮብ 42:11-17)

ምዕራፍ አንድ

# ድራማው ተጀመረ

## (ኢዮብ 1-3)

ሎርድ ባይኖርን «እውነት ሁልጊዜ እንግዳ ናት፣ ከልብ ወለድ ይልቅ እንግዳ ናት» ብሎ በጻፈ ጊዜ ዒላማውን መትቶ ነበር።

መጽሐፈ ኢዮብ ሃይማኖታዊ የሆነ ልብ ወለድ አይደለም። ኢዮብ በገሃዱ ዓለም ውስጥ የነበረ ሰው ነው እንጂ፣ በምርኮ የተፈጠረ ገጸ ባሕርይ አይደለም፤ ሕዝቅኤል (14:14፣ 20) እና ያዕቆብ (5:11) ሁለቱም ምናባዊ አስተሳሰብን አይቀበሉም። ኢዮብ በገሃዱ ዓለም የኖረ እውነተኛ ተሞክሮ የነበረው ሰው በመሆኑ፣ ስለ ሕይወት እንዲሁም በዚህች ገሃድ ዓለም ሕይወት ስላለበት ችግር ልናውቀው የሚያስፈልገንን ሁሉ ሊነግረን ይችላል።

እነዚህ የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ምዕራፎች ኢዮብ የተባለውን ሰው ያስተዋውቁናል፣ ደግሞም ስለ እርሱ አራት ጠቃሚ እውነቶችን ይገልጹልናል።

### 1. የኢዮብ ብልጥግና (1:1-5)

ዖፅ የምትባለው አገር ምናልባት በኤዶም ውስጥ ወይም አቅራቢያ ሳትሆን አትቀርም (ሰቆ. 4:21)። ከኢዮብ ወዳጆች አንዱ የሆነው፣ ኤልፋዝ ከኤዶማውያን ጋር ትስስር ከነበራት ከቴማን መጣ (ኢዮብ 2:11፤ ዘፍጥ. 36:11)።

**የእርሱ ባሕርይ (ኢዮብ 1:1)።** ኢዮብ «ፍጹምና ቅን ነበር» (ኢዮብ 1:1)። እርሱ ኃጢአት-አልባ አልነበረም፤ ምክንያቱም እንደዚያ ያለውን የተለየ ባሕሪ ማንም የእኔ ነው ሊል አይችልምና፣ ነገር ግን እርሱ በባሕርይው ምሉዕና በጠባዩም «ቅንና ቀጥተኛ» ነበር። «ፍጹም» የሚለው ቃል «ከታማኝነት» ጋር የተገናኘ ሲሆን፣ ይህ ቃል በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ ያለ ሌ



ላው ጠቃሚ ቃል ነው (2:3፣ 9፤ 27:5፤ 31:6)። ታማኝነት ያላቸው ሰዎች ከግብዝነት ውጭ የሆኑ ወይም የሌላውን ባሕርይ ከመኰረጅ የጸዱና ምሉእነትን የተላበሱ ሰዎች ናቸው። በጓደኞቹ ክስና በእግዚአብሔር ዝምታ ፊት ኢዮብ ታማኝነቱን ጠብቋል፣ ደግሞም ጌታ በመጨረሻ እርሱን ነፃ አውጥቶታል።

ለኢዮብ ባሕርይ መሠረት የሆነው «እግዚአብሔርን መፍራቱና ከክፉ መራቁ ነበር።» «እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብ ነው ከኃጢአትም መራቅ ማስተዋል ነው» (28:28)። እግዚአብሔርን መፍራት እርሱን ስለ ማንነቱ ማክበር፣ የሚናገረውን፣ እንዲሁም የሚደርገውን ማክበር ማለት ነው። አንድ ባሪያ በጌታው ፊት በመሽማቀቅ የሚያሳየው ፍርሃት አይደለም ነገር ግን አንድ ልጅ ለአባቱ የሚያሳየው የአክብሮት ዓይነት ፍርሃት ሲሆን፣ ወደ መታዘዝ የሚመራ አክብሮት ነው። ኦስዋልድ ቻምበርስ እንዲህ አለ፣ «እግዚአብሔርን ስለ መፍራት አስደናቂ የሚያደርገው ነገር፣ እግዚአብሔርን በምትፈሩበት ጊዜ፣ ሌላ የምትፈሩት ምንም ነገር የማይኖር መሆኑ፣ ግን ደግሞ እግዚአብሔርን የማትፈሩ ከሆናችሁ ሁሉንም ነገር የምትፈሩ መሆናችሁ ነው።»

**ቤተሰቡ (ኢዮብ 1:2)።** ኢዮብ በቤተሰቡ ውስጥ ባለጠጋ ሰው ነበር። በኢዮብ ላይ የተከናወኑ ክስተቶች በአባቶች ዘመን ትልቅ ቤተሰብ ከእግዚአብሔር እንደ ተሰጠ በረከት የሚቈጠርበት ሁኔታን ያሳያሉ (ዘፍጥ. 12:2፤ 13:16፤ 30:1)። ልጆቹ የልደት በዓላቸውን ለማክበር በተደጋጋሚ ስለሚገናኙ፣ አንዱ ከሌላው ጋር ያላቸውን ወዳጅነት እያጠናከሩ ይደሰቱበት ነበር። ይህም ኢዮብ ልጆቹን በደንብ አድርጎ እንዳሳደጋቸው ይናገራል። ከእያንዳንዱ የልደት በዓል ግብዣ በኋላ አባታቸው ልዩ መሥዋዕቶችን የሚያቀርብበት እውነታ የሚያከብሩት በዓልና ግብዣቸው ክፋት ያለበት ነበር ማለት አይደለም። ኢዮብ ጻድቅ ሰው እንደ ሆነና ቤተሰቦቹም ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት የተስተካከለ መሆኑን ለማወቅ/ለማረጋገጥ የሚፈልግ መሆኑን ብቻ ያሳያል።

**ቍሳዊ ሀብቶቹ (ኢዮብ 1:3)።** በዚያን ዘመን ሀብት በቀዳሚነት በመሬት፣ በእንስሳት እንዲሁም በአገልጋዮች ባለ ይዞታነት ይለካ ነበር። እነዚህ ሦስቱ ለኢዮብ በተትረፈረፈ ሁኔታ ነበሩት። ነገር ግን ባለጠጋ መሆኑ ከእግዚአብሔር እንዲርቅ አላደረገውም። ጌታ

እግዚአብሔር ይህን ሀብት እንደ ሰጠው ተገነዘበ (ኢዮብ 1:21)፣ ደግሞም ሀብቱን ለሌሎች በመለገስ ተጠቀመበት (4:1-4፤ 29:12-17፤ 31:16-34):: ኢዮብ ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 6:6-19 የጻፈውን በመታዘዙ ችግር አልነበረበትም::

**ወዳጆቹ (ኢዮብ 2:11)::** እነዚህ ሦስት ወዳጆቹ ኢዮብን በጥልቀት የጎዱትና በታላቅ ሁኔታ እርሱን በተመለከተ የተናገሩት ነገር ስሕተት መሆኑ እውነት ሆኖ እያለ፣ አሁንም የእርሱ ጓደኞች ነበሩ:: የኢዮብን መከራ በሰሙ ጊዜ፣ እርሱን ለመጐብኘት ረጅም ርቀት ተጉዘው መጥተዋል፣ ደግሞም ከእርሱ ጋር በኀዘን ስሜት ተቀምጠዋል:: ስሕተታቸው ኢዮብ ያለበትን ሁኔታ ማብራራታቸውና ይህን ሁኔታ እንዴት ሊለውጥ እንደሚችል ለእርሱ መንገራቸው ነበር::

ሄነሪ ፎርድ እንዲህ አለ፣ «ምርጥ ጓደኛዬ በእኔ ውስጥ ያለን ምርጥ ነገር ቈፍሮ የሚያወጣ ነው::» ነገር ግን የኢዮብ ጓደኞች በእርሱ ዘንድ ያለን ደካማ ጐን ነቅሰው አወጡ:: ይሁን እንጂ፣ በመጨረሻው ኢዮብ እና ወዳጆቹ ታረቁ (42:7-10)፣ ደግሞም የነበራቸው ግንኙነት ከዚህ ቀደም ከነበረው የጠለቀ ነበር ልል እፈልጋለሁ:: እውነተኛ ወዳጆች ያሉት ሰው መሆን፣ በእውነትም ባለጠጋ መሆን ነው::

## 2. የኢዮብ ባላንጣ (1:6-19)

በአንድ ቀን ኢዮብ ሀብቱን አጣ:: አራት ከተከሰተው ሁኔታ በፍርሃት አምልጠው የመጡ መልእክተኞች አንድ በአንድ እየሆኑ ወደ ኢዮብ በመቅረብ 500 ጥማድ በሬዎች፣ 500 አህዮች፣ እንዲሁም 3000 ግመሎችን አደጋ ጣዮች ማርከው ወሰዱዋቸው፤ 7,000 በጎች በመብረቅ ተመትተው ሞቱ፤ እንዲሁም በተነሣው ዐውሎ ንፋስ 10 ልጆቹ መሞታቸውን አረዱት:: ንጉሥ ሰሎሞን እንዲህ ብሎ የተናገረው ትክክል ነበር፣ «ደግሞም የራሱን ጊዜ የሚያውቅ ሰው የለም፤ ዓሦች በክፉ መረብ እንደሚያዙ፣ ወይም ወፎች በወጥመድ እንደሚጠመዱ፣ ሰዎችም ሳያስቡት በሚመጣባቸው፣ በክፉ ጊዜ ይጠመዳሉ» (መክ. 9:12፣ ዓ.መ.ት)::

ኢዮብ የደረሰበትን *ነገር* ያውቃል፣ ነገር ግን *ለምን* እንደ ተከሰተበት አያውቅም ነበር፤ ደግሞም ያ የጉዳዩ አንኳር ነበር:: ደራሲው የመንግሥተ ሰማይ ዙፋን ያለበትን ክፍል እንድንጐበኝ እና ሰይጣንና እግዚአብሔር ሲነጋገሩ እንድንሰማ ስለ ፈለገ፣ እኛ ጥፋቱን ማን እንዳመጣውና ይህ እንዲመጣም የፈቀደ ማን እንደ ሆነ እናውቃለን:: ነገር ግን ይህ መረዳት ከሌለን፣ ምናልባት እንደ ኢዮብ ወዳጆች ያለ ተመሳሳይ የሆነ ዝንባሌ ይኖረን ይሆናል ደግሞም ለገጠመው ኀዘን (ችግር) እንከሰንነው ይሆናል::



ብዙ ጠቃሚ እውነቶች ከዚህ ሁኔታ ይነሣሉ፣ *እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ላይ ሉዓላዊ (የበላይ)* ነው የሚለው፣ ከሁሉ የሚያንሰው አይደለም:: እርሱ በመንግሥተ ሰማይ ዙፋን ላይ አለ፣ መላእክት ፈቃዱን ያደርጋሉ ኀላፊነታቸውንም የተወጡበትን ሁኔታ በዝርዝር ያቀርባሉ፣ ደግሞም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ሰይጣን በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ ምንም ሊያደርግ አይችልም:: በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ ካሉ ቍልፍ ስሞች አንዱ «ሁሉን ቻይ» የሚለው ነው፤ ሠላሳ አንድ ጊዜ ተጠቅሷል:: ገና ከመነሻው፣ በዚህ ዓለም ላይ እንዲሁም በኑሮአችን ውስጥ ምንም ነገር ይከሰት፣ እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ነው ደግሞም እያንዳንዱ ነገር በቍጥጥሩ ሥር ነው የሚለውን ጸሐፊው ያስታውሰናል::

ሁለተኛው እውነታ-ምናልባትም ያስገርማችሁ ይሆናል- *ሰይጣን በሰማይ ወዳለው ወደ እግዚአብሔር ዙፋን የሚቀርብበት ሁኔታ አለው:: ፓራዳይዝ ሉስት (Paradise Lost)* ለተባለው ለጆን ሚልቶን መጽሐፍ ምስጋና ይግባውና ብዙ ሰዎች ሰይጣን ከገሃነም ሆኖ ይህችን ምድር እየገዛት ነው የሚል የተሳሳተ አሳብ አላቸው («በሰማይ ከማገልገል ይልቅ፣ በገሃነም ሆኖ መግዛት ይሻላል»):: ነገር ግን የመጨረሻው ፍርድ (ራእይ 20:10) እስኪደረግ ድረስ ሰይጣን ወደ ገሃነም አይጣልም:: ዛሬ በምድር ሁሉ ላይ ለመመላለስ ነፃ ነው (ኢዮብ 1:7፤ 1ኛ ጴጥ. 5:8) ደግሞም በሰማይ ወዳለው ወደ እግዚአብሔር እንኳ መሄድ ይችላል::

ይህ ሦስተኛው እውነታ እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው:- *እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ ምንም ስሕተት አላገኘበትም፣ ነገር ግን ሰይጣን አግኝቶበታል::* በኢዮብ 1:8 ላይ እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ኢዮብ በቍጥር 1 ላይ የነበረበትን ሁኔታ ያስተጋባል፣ ነገር ግን ለሰይጣን ጥያቄ አሳድሮበታል:: *ሰይጣን* የሚለው ቃል ሕጉን የሚቃወም «ባላንጣ» ማለት ነው:: ይህ የፍርድ ቤት ትዕይንት

ነው፣ ደግሞም እግዚአብሔር እና ሰይጣን እያንዳንዳቸው ስለ ኢዮብ የተለያየ ቃል ተናገሩ:: ይህን መጽሐፍ ስታነብቡ ሳላችሁ እግዚአብሔር «ነቀፋ የሌለበት!» (1:8፤ 2:3፤ 42:7) ማለቱን ልብ በሉ:: እግዚአብሔር ኢዮብን እንዲሠቃይ ለማድረግ የሚያስገድድበት ምንም ነገር አልነበረም:: ነገር ግን ሰይጣን «በድሎአል!» አለ፣ ምክንያቱም እርሱ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከሳሽ ነው ደግሞም በእግዚአብሔር ሕዝቦች ዘንድ የሚያገኘው ምንም መልካም ነገር የለም (ዘካ. 3፤ ራእይ 12:10)::

ሰይጣን ኢዮብን መክሰሱ በእውነቱ እግዚአብሔርን ማጥቃቱ ነበር:: ምናልባት እንደዚህ አሳጥረን ልናቀርበው እንችላለን:- «ኢዮብ አንተን የሚፈራበት ብቸኛው ምክንያት፣ ይህን እንዲያደርግ አንተ ብዙ ነገሮችን መስጠትህ ነው:: አንተም ውል ገብተሃል:- እስከ ታዘዘህና እስካመለከህ ድረስ ታበለጽገውና ትጠብቀዋለህ:: አንተ አምልኮ የሚገባህ አምላክ አይደለሽም! እንዲያከብሩህ ለሰዎች ትከፍላቸዋለህ::»

ሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች ኃጢአት በመሥራቱ ምክንያት ኢዮብ እየተሠቃየ እንደ ሆነ ተናገሩ፣ ይህ ግን እውነት አልነበረም:: ኹሊሁ የተሻለ ሰው እንዲሆን እግዚአብሔር ኢዮብን እየቀጣው ነው አለ፣ ይህ በከፊል እውነት ነበር:: ነገር ግን የኢዮብ መከራ ዋነኛ ምክንያት የሰይጣንን ስድብ የምላበት ክስ ጸጥ ለማሰኘት፣ እንዲሁም ሰው ሁሉንም ነገር ቢያጣ እንኳ እግዚአብሔርን ማክበር ያለበት መሆኑን ለማረጋገጥ ነበር:: ይህ «በሰማያዊ ስፍራ» የሚደረግ ጦርነት ነበር (ኤፌ. 6:12)፣ ነገር ግን ኢዮብ አያውቀውም ነበር:: የኢዮብ ሕይወት «ያህዌ እግዚአብሔር ከሰው የሚቀርብ አምልኮ ይገባዋል ወይ?» የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የእግዚአብሔር ኃይላትና የሰይጣን ኃይላት በመንፈሳዊ ትግል የተሳተፉበት የጦር ሜዳ ሆኖ ነበር::

አሁን ኢዮብ የጓደኞቹን ምክር ከቶ ያልተቀበለበትን ምክንያት እንረዳለን:: ኃጢአቱን እንዲናዘዝና ንስሐ እንዲገባ በዚህም መከራው እንዲወገድና እንደ ገና ባለ ጸጋ እንዲሆን ይፈልጋሉ:: ኢዮብ ንስሐ መግባት እንዲችልና የእግዚአብሔርን በረከቶች እንዲያገኝ ሲል ብቻ ኃጢአትን በሕይወቱ ውስጥ መፍጠር



የለበትም:: ያንን ማድረግ በከሳሽ እጅ ውስጥ መውደቅ ነው! በዚህ ፈንታ ኢዮብ ምንም እንኳ እግዚአብሔር እያደረገው የነበረውን ነገር ባይረዳም፣ ለእርሱ ያለውን ታማኝነት ጠብቋል ደግሞም እግዚአብሔርን አመስግኖአል:: ለጨለማው ልዑል እንዴት ያለ ሽንፈት ነው!

አራተኛው እውነታ ይህ ነው:- ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሕዝቦች መንካት የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ነው፣ ደግሞም እግዚአብሔር ለጥቅማቸውና ለክብሩ ይጠቀምበታል:: ፊሊፕ ብሩክስ እንዲህ አለ:- «የሕይወት ዓላማ በእውነት አማካይነት ባሕርይን መቅረጽ ነው::» የበለጠ ኢየሱስ ክርስቶስን እንድንመስል እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ እየሠራ ነው (ሮሜ 8:29)፣ ደግሞም እኛን ፍጹም ለማድረግ የሰይጣንን ጥቃት እንኳ መጠቀም ይችላል:: አንተ በመታዘዝ መንገድ ላይ በምትሆንበት ጊዜ እንዲሁም በብዙ ፈታኝ የሆኑ መከራዎች ውስጥ ስትሆን፣ ከእርሱ ፈቃድ ውጭ የሆነ ምንም ነገር ወደ ሕይወትህ እንደማይመጣ አንተው ራስህ አስታውስ::

በእግዚአብሔር ሕዝቦች ሕይወት ውስጥ ከሚመጡ አንዳንድ መከራ ከተባሉ ነገሮች መካከል አንዳንዶቹ እግዚአብሔር «ጠላትን እና ቂመኛን ጸጥ ለማሰኘት» ነው (መዝ. 8:2):: መላእክት ቤተ ክርስቲያንን ይመለከታሉ ደግሞም እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚያደርገውን ነገር ይማራሉ (1ኛ ቆሮ. 4:9፤ ኤፌ. 3:10):: መንግሥተ ሰማይ እስከምንደርስ ድረስ እግዚአብሔር አንዳንድ ነገሮች እንዲከሰቱ የሚፈቅደው ለምን እንደ ሆነ አናውቅ ይሆናል:: በመሀሉ፣ በእምነት እየተመላለስን ከኢዮብ ጋር «የጌታ ስም የተባረከ ይሁን!» እንላለን::

## 3. የኢዮብ እምነት (1:20-22)

የመንግሥተ ሰማይና የገሃነም ሠራዊቶች ለብልጥግናውና ለልጆቹ መጥፋት ኢዮብ የሚሰጠውን ምላሽ ይመለከቱ ነበር:: ኢዮብ በዚያ ዘመን የተለመደ በሆነ መልኩ ኀዘኑን ገለጠ፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሰው እንድንሆን ይጠብቅብናልና (1ኛ ተሰ. 4:13):: ለነገሩ፣ ኢየሱስ እንኳ አልቅሷል (ዮሐንስ 11:35):: ነገር ግን ከዚያ መልስ ኢዮብ እግዚአብሔርን አመለከ ደግሞም መሠረታዊ የሆነ

የእምነት ንግግር አደረገ (ኢዮብ 1:21)::

በመጀመሪያ *ወደ ኋላ ተመልሶ* የተወለደበትን ቀን ተመለከተ:- «እራቁቴን ከእናቴ ማኅፀን ወጥቻለሁ::» ኢዮብ የነበረው ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ነበር፣ ደግሞም ይኸው አምላክ መልሶ ሊወስደው መብቱ ነበረው:: ኢዮብ እርሱ የሀብቱ መጋቢ ብቻ መሆኑን አስታወቀ::

ከዚያም ኢዮብ *ወደ ፊት* ስለ ሞቱ *ተመለከተ*:- «እራቁቴንም ወደዚያው እመለሳለሁ::» እርሱ ወደ እናቱ ማኅፀን ከቶ አይመለስም፣ ምክንያቱም ያ የማይቻል ነገር ነው:: እርሱ ወደ «እናት ምድር» ይሄዳል፣ ይቀበራል፣ ደግሞም ወደ አፈርነት ይለወጣል:: («በመወለድ» እና «በእናት ምድር» መካከል ያለው ትስስር ጭምር በመዝ. 139:13-15 ይታያል):: በመወለዱና በሞቱ መካከል ያገኘው የቱም ነገር ወደሚቀጥለው ዓለም ከእርሱ ጋር አይሄድም:: ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፎአል፣ «ወደ» ዓለም ምንም እንኳ አላመጣንምና አንዳችንም ልንወስድ አይቻለንም» ( 1ኛ ጢሞ. 6:7)::

በመጨረሻም፣ ኢዮብ *ወደ ላይ ተመለከተ* ከዚያም ውብ የሆነ ንግግር አደረገ:- «እግዚአብሔር ሰጠ፤ እግዚአብሔርም ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን» አለ (ኢዮብ 1:21):: ኢዮብ ያደርገዋል ብሎ ሰይጣን እንደ ተናገረው እግዚአብሔርን በመርገም ፈንታ፣ ኢዮብ እግዚአብሔርን ባረከ! የቱም ሰው፣ «እግዚአብሔር ሰጠ» ወይም «እግዚአብሔርም ነሣ» ማለት ይችላል፤ ነገር ግን በኀዘን እና በመከራ መካከል «የጌታ ስም የተባረከ ይሁን» ለማለት እምነትን ይጠይቃል::

«በዚህ ሁሉ ኢዮብ አልበደለም፣ ለእግዚአብሔርም ስንፍናን አልሰጠም» (ቍ. 22)::

## 4. የኢዮብ ሰቆቃ (2:1-3:26)

በዚህ ክፍል፣ አራት የተለያዩ ድምፆችን ትሰማላችሁ::

**(1) የከሳሹ ድምፅ (ኢዮብ 2:1-8)::** ሰይጣን በቀላሉ ተስፋ አይቆርጥም፣ ምክንያቱም ኢዮብን ዳግመኛ ሊከስ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ይሄዳልና:: ልክ እንደ መጀመሪያው ስብሰባ ሁሉ (1:8)፣ የአገልጋዩን የኢዮብን ጉዳይ ያነሣው እግዚአብሔር ነበር፤ ደግሞም ሰይጣን የቀረበለትን ተግዳሮት ተቀብሎታል:: አገልጋዩ በፈተናው ባለመውደቁ እግዚአብሔር የመተማመን ስሜት የተሰማው መሆኑን እንረዳለን::

«እያንዳንዱ ሰው የገዛ እራሱ የሆነ ዋጋ አለው፣» አለ ሰይጣን:: «ኢዮብ ሌላ ቤተሰብ ሊመሠርት እንዲሁም ሌላ ሥራ ሊጀምር ይችላል፣ ምክንያቱም አሁንም ጤናማና ጠንካራ ነው:: ሥጋውን እንድነካና ጤናውን እንድወስድ ፍቀድልኝ፣ ፊጥኖም በፊትህ ሲረግምህ ታያለሁ::»

በእግዚአብሔር ፈቃድ (1ኛ ቆሮ. 10:13)፣ እኛ ልንለየው በማንችል በሽታ ሰይጣን ኢዮብን መታው:: በሽታው ምንም ይሁን፣ ምልክቶቹ አስፈሪ ነበሩ:- እነዚያም ከባድ እከክ (ኢዮብ 2:8)፣ የእንቅልፍ እጦት (ቍ. 4)፣ የሚመግሉ ቁስሎችና እስከ (ቍ. 5)፣ የሌሊት ቅዠት (ቍ. 13-14)፣ መጥፎ ትንፋሽ (19:17)፣ የክብደት መቀነስ (ቍ. 20)፣ የመንቀጥቀጥ ስሜት እና ትኩሳት (21:6)፣ ተቅማጥ (30:27)፣ እና የቆዳ መጥቆር (ቍ. 30) ናቸው:: ሦስቱ ጓደኞቹ ኢዮብን መጀመሪያ ባዩት ጊዜ አላወቁትም ነበር (2:12)!

ሁሉም አካላዊ ችግሮች ከክፉው የሚመጡ አይደሉም፣ ምንም እንኳ የሰይጣን አጋንንት (ከሌሎች ነገሮች ጋር) ዕውርነትን (ማቴ. 12:22)፣ ዲዳነትን (9:32-33)፣ የአካል ቅርጽ መበላሸትን ጉዳት (ሉቃስ 13:11-17)፣ የማያቋርጥ ሕመምን (2ኛ ቆሮ. 12:7)፣ እንዲሁም ዕብደትን (ማቴ. 8:28-34) የሚያመጡ ቢሆኑም:: አንዳንድ ጊዜ አካላዊ ሕመም ከእኛ በሚሆን ግድለሽነት የተነሣ የሚመጣ ተፈጥሮአዊ ነገር ነው፣ ደግሞም እራሳችንን እንጂ ማንንም መኰነን የለብንም:: ነገር ግን፣ ሰይጣን ሥራውን የበለጠ ለማስፋት የእኛን ከንቱነት (ተላላነት) እንዴት እንደሚጠቀምበት ያውቃል::

ስለዚህ የኢዮብ ገጽታ አስቀያሚ ስለ ነበረ ከማኅበረሰቡ ተለየ (ኢዮብ 19:13-20) ደግሞም ከከተማይቱ ውጭ ሄዶ በአመድ ላይ ተቀመጠ:: በዚያ የከተማይቱ ቈሻሻ ይጣልና ይቃጠል ነበር፣ ደግሞም በዚያ ከተማይቱ የጣለቻቸው ሰዎች በዚያ ከሚያልፉ ሰዎች ምጽዋት እየለመኑ ይኖሩ ነበር:: በአመድ ቁልሉ ላይ ውሾች ስለሚበሉት ነገር ትንቅንቅ ይገጥሙ ነበር፣ ደግሞም የከተማይቱ

እበት በዚያ ይጣልና ይቃጠል ነበር። የከተማይቱ ዋና ዜጋ በችጋር፣ በድኅነት እና በእፍረት ይኖር ነበር።

**(2) የልግመኛው ድምፅ (ኢዮብ 2:9-10)።** በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረው የቁም አማኝ በክርስቶስ መከራ ተካፋይ ሆነ የሚባል ካለ፣ እርሱ ኢዮብ ነበር። እርሱ የቀሩት ሰዎች ሚስቱና ሦስቱ ጓደኞቹ ነበሩ፣ እነርሱም እንኳ በተቃውሞ ውስጥ ነበሩ። ኢዮብ እግዚአብሔር የተወው እንደ ሆነ ቢሰማውም አያስደንቅም።

«እግዚአብሔርን እርገምና ሙት!» የሚለው በትክክል ሰይጣን ኢዮብ እንዲያደርገው የሚፈልገው ነገር ነበር፣ ደግሞም የኢዮብ ሚስት ፈተናውን በባልዋ ፊት አስቀመጠች። አዎን፣ ሰይጣን ለእኛ የተወደዱ በሆኑ ሰዎች በኩል ሊሠራ ይችላል (ማቴ. 16:22-23፤ የሐዋ. 21:10-14)፤ እንዲሁም እኛ በጣም የምንወዳቸው በመሆኑ ፈተናው ጠንካራ ይሆናል። አዳም ሔዋንን አዳመጠ (ዘፍጥ. 3:6፣ 12)፣ ደግሞም አብርሃም ሣራ ያለችውን ሰማ (ዘፍጥ. 16)፤ ነገር ግን ኢዮብ የሚስቱን ምክር አላዳመጠም።

በእርግጥ፣ እርሷ ተሳስታለች፣ ነገር ግን በተቻለን ሁሉ እርሷ የነበረችበትን ሁኔታ ከግምት ማስገባት ይኖርብናል። አሥር ልጆችን በአንድ ቀን አጥታለች፣ ደግሞም ይህ የትኛዋንም እናት ተስፋ ሊያስቆርጥ በቂ ምክንያት ነው። የቤተሰቡ ብልጥግና ተወስዷል፣ ደግሞም ከዚህ በኋላ እርሷ «በምድርዋ ላይ የመሪነት ሚና» የምትጫወት አትሆንም። በምሥራቅ ካሉ ሰዎች ሁሉ የላቀው ባልዋ (ኢዮብ 1:3)፣ አስከፊ በሆነ በሽታ እየተሠቃየ በከተማይቱ ቈሻሻ መጣያ ተቀምጧል። ምን የቀራት ነገር አለ? ባልዋ በሥቃይና በእፍረት ተውጦ ያለበትን ሁኔታ ከማየት ይልቅ እግዚአብሔር በሞት እንዲመታው፣ ይህንንም ነገር ደግሞ ቶሎ እንዲያደርገው ትመርጣለች። ምናልባት ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚረግም ከሆነ፣ እግዚአብሔር ይህን ያደርገው ይሆናል።

ከባድ በሆኑ ፈተናዎች ወቅት፣ የመጀመሪያው ጥያቄአችን፣ «ከዚህ የምወጣው እንዴት ነው?» የሚል መሆን የለበትም፣ ነገር ግን «ከዚህ ምን አገኛለሁ?» የሚል መሆን አለበት። የኢዮብ ሚስት ችግሩን እንዳስወገደችው አሰበች፤ ነገር ግን ኢዮብ የእርሷን ምክር ተቀብሎ ቢሆን ኖሮ፣ ነገሮች የተባባሱ ብቻ ነበር የሚሆኑት። እምነት ለራስ ጥቅም በምሥጢር ሳያቅዱ መኖር



ነው። ከስሜቶች፣ ሁኔታዎች ወይም ውጤቶች ባሻገር፣ እርሱ በእራሱ መንገድና ጊዜ ፍጹም የሆነ ዕቅዱን እያከናወነ እንደ ሆነ በማወቅ፣ እግዚአብሔርን መታዘዝ ነው።

ኢዮብ ተስፋ ያልቈረጠባቸው ሁለቱ ነገሮች በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነት እና ለእግዚአብሔር ያለው ታማኝነት ነበሩ፣ ደግሞም እንዲጥላቸው ሚስቱ የፈለገቻቸው ነገሮች እነዚህ ነበሩ። ክፉ ወደ ሕይወቱ እንዲመጣ ቢፈቅድም እንኳ፣ ነገሮችን በማዛባት ኢዮብ በእግዚአብሔር ላይ አላመጸም። ኢዮብ የሳሙኤል ራዘርፎርድን ደብዳቤዎች ከቶ አላነበባቸውም፣ ነገር ግን በታላቅ ሁኔታ የተሠቃየውን መንፈሳዊ የሆነውን ስኮትላንዳዊ መጋቢ ምክር ተከትሎ ነበር፡- «እጅግ አስቸጋሪ ከሆነው የእግዚአብሔር በትር አፍቃሪ የሆነ ደግነትን ለማግኘት መጠበቅ የእምነት ሥራ ነው።» ኢዮብ በእግዚአብሔር መታመኑን ቀጠለ፡- ከእግዚአብሔር ጋር መከራከሩንም ቀጠለ! ደግሞም መከራዎቹን ወይም አጋጣሚ ዎቹን እግዚአብሔር ለእርሱ የሚሰጣቸውን ነገሮች ለመቀበል በሚሆን ሩጫ አላባከናቸውም።

ሕይወት አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ፣ ተስፋ መቁረጥ ቀላል ነው፤ ነገር ግን ተስፋ መቁረጥ ልናደርጋቸው ከሚገቡ ነገሮች ሁሉ እጅግ የከፋው ነው። አንድ የታሪክ አስተማሪ እንዲህ አለ፡- «ኮሎምበስ ወደ ኋላ ተመልሶ ቢሆን ኖሮ፣ ማንም ባልወቀሰውና እንዲሁም ማንም እርሱን ባላስታወሰው ነበር።» መታወስ የምትፈልጉ ከሆናችሁ፣ አንዳንድ ጊዜ ኀዘንተኞች መሆን ሊኖርባችሁ የግድ ነው።

በመጨረሻም፣ የኢዮብ ሚስት ከባልዋ እና ከእግዚአብሔር ጋር ታረቀች ደግሞም እግዚአብሔር ለእርሷ ሌላ ቤተሰብ ሰጣት (42:13)። ከመከራዎችዋ ምን ያህል እንደ ተማረች አናውቅም፣ ነገር ግን ለእርሷ ይህ እያደገ የሚሄድ ተሞክሮ መሆኑን መገመት እንችላለን።

**(3) የአስተዛዛኞቹ ድምፅ (ኢዮብ 2:11-13)።** «የኢዮብ አጽናኞች» የሚለው አባባል እርዳታቸው የባሰ ስሜት ብቻ እንዲሰማችሁ የሚያደርጉ ሰዎችን ለመግለጥ የሚያገለግል የተለመደ ሐረግ ነው። ነገር ግን ኢዮብን ከማሳደዳቸው ባሻገር እነዚህ ሦስት ሰዎች ጥቂት የሚወደድ ባሕርይ አላቸው።

የመጀመሪያው ነገር፣ እርሱን ለመጎብኘት ረጅም ርቀት ተጉዘው በመምጣታቸው ለኢዮብ እንክብካቤ አድርገውለታል:: ደግሞም ከእርሱ ጋር ሆነው በሚያጽናኑት ጊዜ፣ በተመቻቸ ቤት ወይም በሆስፒታል ክፍል ውስጥ አልነበረም የተቀመጡት:- አስወጋጆች በጣሉት የዐመድ ቁልል ተከብበው ከእርሱ ጋር ተቀምጠዋል:: ኀዘናቸው እጅግ ታላቅ በመሆኑ፣ ለሰባት ቀናት ምንም መናገር አልቻሉም:: (በእርግጥ፣ ከዝምታቸው በኋላ ብዙ ተናግረዋል::) እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ኀዘናቸውን የገለጡበት መንገድ ለአንድ ታላቅ ሰው ሞት እንደሚደረግ ያለ ነው (ዘፍጥ. 50:10)::

የተጐዱ ሰዎችን የምንረዳበት ምርጡ መንገድ ከእነርሱ ጋር ብቻ መሆን ነው፣ ጥቂት ብቻ መናገር ወይም ከቶ አለመናገር፣ ደግሞም እየተንከባከባችኋቸው እንዳላችሁ እንዲያውቁ ማድረግ ነው:: እያንዳንዱን ነገር ለማብራራት አትሞክሩ፤ ማብራሪያዎች የተሰበረ ልብን አይጠግኑም (አይፈውሱም):: ጓደኞቹ አድምጠውትና ስሜቱንም ተረድተው ቢሆን ኖሮ፣ እንዲሁም ከእርሱ ጋር ባይከራከሩ ኖሮ፣ በታላቅ ሁኔታ ይረዱት ነበር፣ ነገር ግን ከምስክሮች ይልቅ ተሟጋች ዐቃቤ ሕግ ሆነው ነበር:: በመጨረሻም፣ እግዚአብሔር ገሠጻቸው፣ ደግሞም ይቅርታን ከኢዮብ መጠየቅ አስፈለጋቸው (ኢዮብ 42:7-10)::

**(4) የመከራ ተቀባዩ ድምፅ (ኢዮብ 3:1-26)::** ከሰባት ቀናት የጸጥታ መከራ በኋላ፣ ኢዮብ እግዚአብሔርን ለመርገም ሳይሆን የተወለደበትን ቀን ለመርገም ተናገረ:: «ስለ ምን ተወለድሁ?» ነቢዩ ኤርምያስን ጨምሮ (ኤር. 20:14-18)፣ ከአንድ በላይ የሆኑ የተጐዱ የእግዚአብሔር ልጆችን ሲያስለቅስ የኖረ አባባል ነው:: ምንም እንኳ ኢዮብ ያንን ፍላጎት ከአንዴ በላይ የገለጸው ቢሆንም (ኢዮብ 6:9፤ 7:15-16፤ 14:13)፣ ይህ «መቼ በሞትሁ» ከሚለው ጋር አንድ ዓይነት አይደለም:: ኢዮብ በየትኛውም ጊዜ የገዛ ሕይወቱን ማብቂያ በተመለከተ አልተናገረም:: የኢዮብ «የልደት እሮሮ» እራስን ስለ ማጥፋት የቀረበ/የተነገረ ምክንያታዊ የሆነ መከላከያ ወይም «የምሕረት ግድያ» የሚሉት አልነበረም:: ከመከራው መብዛት የተነሣ ከቶ አለመፈጠሩን/አለመወለዱን የሚሻ ሰው ንግግር ነው::



በምትጐዱበት ጊዜ፣ በኋላ የምትጸጸቱባቸውን ነገሮች ትናገራላችሁ፣ ወይም ድርጊቶችን ትፈጽማላችሁ:: የኢዮብ መከራ እጅግ ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ እርሱና ቤተሰቦቹ ለብዙ ዓመታት በደስታ የተቀበሉዋቸውን በረከቶች እረሳቸው:: ከቶ ያልተወለደ ቢሆን ኖሮ፣ በምሥራቅ ካሉ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ታላቁ ሰው ባልሆነም ነበር! ነገር ግን መከራ ያለፈውን ዘመን ደስታ ያስረሳናል፤ በዚህ ፈንታ፣ በወደፊቱ ጊዜ ተስፋ-አልባ ሁኔታ ላይ ትኩረታችንን እናደርጋለን:: የኢዮብ ጓደኞች ቃሎቹን ሰምተዋል፣ ነገር ግን የልቡ ኀዘን አልተሰማቸውም፣ ደግሞም መከራዎቹን በሚረሳበበት ሁኔታ ላይ እርሱን ለመርዳት የተሳሳተ አቀራረብን ተግባራዊ አድርገዋል:: ስሜቱን በመረዳት ከማገልገል ይልቅ፣ በሚናገራቸው ቃሎች ላይ ክርክር ገጠሙ::

ኢዮብ ሁለት ምሽቶችን ረገመ:- የተፀነሰበትን ምሽት እና የተወለደበትን ምሽት (3:1-13):: ፅንስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣ በረከት ነው [ዘፍጥ. 30:1-2፤ መዝ. (138) 139:13-16]፤ ስለዚህ በረከትን በምንረግምበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን መልካምነት ጥያቄ ውስጥ እያስገባን ነው::

እዚህ ላይ ቁልፉ ቃል ጨለማ የሚለው ነው:: አንድ ልጅ በሚወለድበት ጊዜ፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን እየመጣ ነው፤ ነገር ግን ኢዮብ በጨለማ ውስጥ መቆየትን መረጠ:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በሚወለድበት ጊዜ ሞቶ ቢሆን ኖሮ፣ የተሻለ እንደ ነበረ አሰበ! ከዚያም ወደ ሙታን ዓለም (ሲኦል) ይሄድ ስለ ነበረ ይህን ሁሉ አሳዛኝ ነገር አይመለከትም::

ንግግሩንም አራት «ለምን» የሚሉ እግዚአብሔር ብቻ የሚመልሳቸውን ጥያቄዎች በማቅረብ ይቋጫል:: ለምን ብሎ መጠየቅ ቀላል ነው፣ ነገር ግን ትክክለኛውን መልሱን ማግኘት አስቸጋሪ ነው:: እግዚአብሔር መልስ ሊሰጠን ይገባል እስካላልን ድረስ ለምን ብሎ በመጠየቅ ውስጥ ምንም ስሕተት የለም:: ጌታችን እንኳ እንዲህ ብሎ ጠይቋል፣ «ስለ ምን ተውኸኝ?» (ማቴ. 27:46):: ነገር ግን ነገሮች እየሆነ እንዳሉት ለምን እንደሚከሰቱ ነግሮን ከሆነ፣ በውኑ ያ ሥቃያችንን ያቃልልልናል ወይም የተሰበረ ልባችንን ይጠግንልናል? ኤክስሬይን ማንበብ የተሰበረ እግር ሥቃይን ያስወግደዋል ወይ? የምንኖረው በማብራሪያዎች ሳይሆን፣

በተሰፋ ቃሎች ነው፤ ስለዚህ ስለ ምን ሆነ በሚል እግዚአብሔርን በመጠየቅ እጅግ ብዙ ጊዜን ማባከን አይኖርብንም።

የመጨረሻው የሰቆቃው ክፍል የሙታን ዓለም፣ አይሁድ ሲኦል ብለው የሚጠሩት ስፍራ (ኢዮብ 3:13-26)፣ መግለጫ ነው። ኢዮብ ሊኖርበት የፈለገው ስፍራ ያ ነው! ብሉይ ኪዳን ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት ሙሉ የሆነ መገለጥን አይሰጥም፤ ያ ደግሞ የአዳኙን መምጣት የሚጠባበቅ ርእስ ጉዳይ ነው (2ኛ ጢሞ. 1:10)። ኢዮብ ሲኦልን ታላላቆችም ሆኑ ታናናሾች በምድር ላይ ካሉ መከራዎችና ሸክሞች ሁሉ በመገላገል በአንድ ላይ የሚያርፉበት ጥላማ ቦታ አድርጎ ነበር የሚመለከተው። ኢዮብ በሕይወት ኖሮ ወደ እርሱ ሊመጣ ያለውን ኀዘን ከመሸከም ይልቅ መሞትንና ማረፍን ይመርጥ ነበር። ለነገሩ፣ የወደፊት ጊዜውን በተመለከተ በጨለማ ውስጥ ነበር (ኢዮብ 3:23)፣ ስለዚህ በሲኦል ጨለማ ውስጥም ይኖር ይሆናል።

ኢዮብ በሰቆቃው ማብቂያ ላይ አንድ ምሥጢርን ያካፍላል (ቍ. 25-26)፡- መከራዎቹ ሁሉ ከመጀመራቸው በፊት፣ የሚሰማውና የሚፈራው ነገር፣ ማለትም አንድ በጣም አስፈሪ የሆነ ነገር ይመጣል የሚል ፍርሃት ነበረው። ይህ ከጌታ የተሰጠ ስሜት ነበርን? አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንደዚህ ያሉ ስሜቶች ይኖሯቸዋል፣ ደግሞም የእግዚአብሔርን ፊት እንዲሹና የእርሱን እርዳታ ለመጠየቅ እንዲጸልዩ ያነሣሣቸዋል። ኢዮብ እያደረገው የነበረው ይህንን ነበር ወይ? እኛ የምናውቀው ነገር የለም፣ ነገር ግን እርሱ የተሰበረ ሰው እንደ ነበረና እጅግ ይፈራው የነበረ ነገር አሁን ገሃድ እንደ ወጣ እናውቃለን።

ሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች ኢዮብ እምነቱን ከገለጠበት ንግግር (1:21፤ 2:10) ይልቅ የምሬት (ሰቆቃ) ንግግሩ ላይ ማተኮራቸው የሚያሳዝን ነው። የተወለደበትን ቀን ሲረግም ከሰሙት በኋላ፣ እርሱን መገሠጽ አስፈላጊ እንደ ሆነና ለእግዚአብሔር ጥብቅና መቆም አስፈላጊ እንደ ሆነ ተሰማቸው።

እዚህ ላይ ነው ውይይቱ የጀመረው። ወዲያውም ውይይቱ ክርክር ይሆናል፣ ከዚያም ጠብ ይነሣል፤ ደግሞም ነገሮችን ወደ ፍጻሜአቸው ለማምጣት ጌታ እግዚአብሔር ጣልቃ ይገባል።



## ለግል ምልከታ እና ለቡድን ውይይት የሚሆኑ ጥያቄዎች

1. በሕይወታችሁ ስለ ኢዮብ የሰማችሁትን ሁሉ አስቡ። አሁን ይህን ዓረፍተ ነገር በዘመናዊ አባባል ጨርሱት፡- «እርሱ እንደ . . . ያለ ዓይነት ሰው ነው።»

2. የኢዮብ ጓደኞች ኢዮብ ላለበት ተጨባጭ ሁኔታ ማብራሪያ መስጠት አለብን እንደሚል ዓይነቱን ስሕተት ፈጸሙ። አንድ ሰው ሲሠቃይ በምንመለከትበት ጊዜ ያ ግፊት የሚሰማን ለምን ይመስላችኋል?

3. ኢዮብ ሁሉን ነገር አጣ። በመጥፋታቸው ምክንያት እግዚአብሔርን ተጠያቂ ለማድረግ የምትፈተኑባቸው የትኞቹ ነገሮች ናቸው በሕይወታችሁ የላቀ ስፍራ ያላቸው?

4. ሰይጣን በምድር ሁሉ መዞር ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ወደ እግዚአብሔር ዙፋን መቅረብ ዕድሉ እንዳለው ስለሚናገረው እውነት ምን ይሰማችኋል?

5. ኢዮብ 1:22ን አንብቡ። በእጦት መካከል የእውነትን ሴላ ገጽታ ለመጠበቅ ኢዮብን ያስቻለው ምሥጢር ምንድን ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ?

6. በድንገት በመጣበት እጦት ከተሠቃየ በኋላ፣ ኢዮብ በከባድ ሕመም ተሠቃየ። የእግዚአብሔርን መልካምነት ከመጠራጠር ፈተና አኳያ በእጦትና በሕመም መካከል ያሉ ልዩነቶች እና ተመሳሳይነቶች ምንድን ናቸው?

7. የኢዮብ ጓደኞች ይህ መከራ በሙላት በእርሱ ስሕተት የመጣ መሆኑን መናገራቸውን ገፋበት። እኛ እንደ ሰው ለምንቀበለው መከራ አንድ ሰው ሊነቀፍበት ይገባል የሚል ስሜት የሚሰማን ለምንድን ነው?

8. ልክ እንደ ኢዮብ፣ ባልተወለድሁ ብለው ለሚመኙ ሰዎች እኛ መጽናናትን ልናመጣላቸው የምንችልባቸውን ጥቂት ነገሮች ዘርዝር።

9. በእጦት የተሠቃየህባቸውን ጊዜያት አስብ። ሙሉ በሙሉ በእርሱ ከመጥፋት የጠበቀህ ነገር ምንድን ነበር?



# የዕረፍት ጊዜ

ከሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች ጋር መልካም ጊዜ ታሳልፋላችሁ፣ ስለዚህም ከእነርሱ ጋር የበለጠ ትተዋወቃላችሁ።

ሦስቱም ሰዎች ያረጁ ሰዎች ናቸው (ኢዮብ 32:6)፣ ከኢዮብም በዕድሜ የሚበልጡ ናቸው (15:10)፣ ነገር ግን *ኤልፋዝ* ከሁሉም በዕድሜ የሚበልጥ እንደ ሆነ እንገምታለን። ስሙ በመጀመሪያ ተጠቅሷል (2:11)፣ በመጀመሪያ ተናግሮአል፣ ጌታ እግዚአብሔር እርሱን ከሦስቱ አባላት ታላቅዬው እንደ ሆነ አድርጐ ተቀብሎታል (ኢ.ር. 42:7)። በጥበቧ ታዋቂ ከሆነችው ስፍራ ከቴማን ጋር ግንኙነት ነበረው (49:7)። ኤልፋዝ ንግግሩን በሁለት ነገሮች ላይ መሠረተ:- እነዚህም የገዛ እራሱ የሕይወት ምልከታው («እንዳየሁ» ኢዮብ 4:8፤ 5:3፣ 27) እንዲሁም አስፈሪ የሆነ አንድ ምሽት የገጠመው የግል ተሞክሮ (4:12-21) ናቸው። ኤልፋዝ በትውፊት ላይ ታላቅ እምነት አሳድሮአል (15:18-19)፣ ደግሞም እርሱ የሚያመልከው አምላክ ግትር የሆነ ሕግ ሰጪ ነበር። «ንጹሕ ሆኖ የጠፋ ማን ነው?» ሲል ጠየቀ (4:7)፤ ደግሞም የሰማዕታቱ ሠራዊቶች «እኛ አለን!» ብለው መመለስ በቻሉ ነበር። (የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ጉዳይስ?) ኤልፋዝ ለእግዚአብሔር ጸጋ ኢምንት ወይም ምንም ስፍራ የሌለው ግትር ሥነ መለኮታዊ አስተሳሰብ (መረዳት) ነበረው።

*በልዳዶስ* ስሙ ሁለተኛ ስለ ተጠቀሰ እንዲሁም ቀጥሎ ስለ ተናገረ በዕድሜ ሁለተኛ መሆን አለበት። በአነጋገሩ በልዳዶስ ወግ አጥባቂ ነበር። የሕይወት መሪ ጥቅሱ እንዲህ የሚል ነበር:- «እነሆ፣ እግዚአብሔር ፍጹሙን ሰው አይጥለውም፤ የኃጢአተኞችንም እጅ አያበረታም» (ኢዮብ 8:20)። ጥንታውያን ምሳሌዎችን መጥቀስ ይችላል፣ ደግሞም ልክ እንደ ኤልፋዝ ለትውፊት ታላቅ አክብሮት አለው። በአንዳንድ ምክንያቶች፣ በልዳዶስ የኢዮብ ልጆች የሞቱት እነርሱም ጭምር ኃጢአተኞች ስለሆኑ እንደ ሆነ እርግጠኛ ነበር (ቊ. 4)። ሰውዬው ስለ ተጐዳው ወዳጁ ምንም የሚሰማው ነገር ያለ አይመስልም።

ሶፋር ከሦስቱ መካከል ታናሽዬው ነበር። ደግሞም በእርግጠኝነት ከሁሉ የላቀ ነገር አወሳሰቢ (አካባጅ) ነበር። እርሱ ይናገር የነበረው አላዋቂ ለሆኑ አዲስ ሰዎች ትምህርት እንደሚሰጥ መምህር ነበር። «ይህን እወቁ!» የሚለው ሌሎችም ቢሆኑ የእራሳቸው መረዳትና ግንዛቤ ያላቸው መሆኑ የማይሰማው እንደ ሆነ ያሳያል (11:6፤ 20:4)። እርሱ ምሕረት-የለሽ ነው ደግሞም እግዚአብሔር ለእርሱ ስለ ኃጢአቶቹ ሊከፍለው ከሚገባው በእጅጉ ያነሰ እንደ ሰጠው ለኢዮብ ነገረው (11:6)! የእርሱ ቀልፍ ምንባብ፡- «ሰው በምድር ላይ ከተቀመጠ፣ ከድሮ ዘመን ጀምሮ የኃጢአተኛ ፉከራ አጭር መሆኑን የዝንኮዎችም ደስታ ቅጽበት መሆኑን አታውቁምን?» (20:4-5)። የሚገርመው፣ ሶፋር ለኢዮብ የተናገረው ሁለት ጊዜ ብቻ ነው። ወይ የኢዮብን ክርክሮች ለመመለስ እንደማይችል ተረድቶአል አሊያም ደግሞ ኢዮብን ለመርዳት መሞከር ጊዜን ማባከን እንደ ሆነ ተሰምቶታል።

እነዚህ ሦስቱ ሰዎች ጥቂት መልካም እና እውነት የሆኑ እንዲሁም ደግሞ ጥቂት የስንፍና ነገሮችን ተናግረዋል፤ ነገር ግን አመለካከታቸው እጅግ ጠባብ በመሆኑ ምክንያት ለኢዮብ ምንም አልጠቀሙትም። ሥነ መለኮታዊ መረዳታቸው መሠረታዊ እና ጥልቀት ያለው አልነበረም። ነገር ግን ሙትና ጠባብ ነበር፣ እንዲሁም ጥብቅና ሊቆሙለት የሞከሩት አምላካቸው ሊረዱትም ሆነ ስለ እርሱ ሊናገሩለት በጣም ያነሰ ነበር። እነዚህ ሰዎች የዶሮዚ ሲየርስን አባባል በሙላት በምሳሌነት ያሳያሉ፣ «አመለካከታችሁ በቂ በሆነ መልኩ ውሱን ከሆነ፣ ልታረጋግጡት የምትችሉት ምንም ነገር የለም።»

እነዚህ ሰዎች ለኢዮብ እንደ ተናገሩት ሦስት ሰዎች ሆነው ለወዳጃቸው የሚናገሩበት ምክንያት ምንድን ነበር? ለምንድን ነበር እጅግ የተናደዱት? በኢዮብ ንግግሮች ውስጥ መልስ የሚሆን ጥቆማ አለ፡- «አሁንማ እናንተ እንደዚያ ሆናችሁብኝ፣ መከራዬን አይታችሁ ፈራችሁ» (ኢዮብ 6:21፣ አ.መ.ት)። ሦስቱ ሰዎች እንደዚሁ ያለ መከራ እንዳይመጣባቸው ፈርተው ነበር! ስለዚህ እግዚአብሔር ጻድቃንን ይሸልማል እንዲሁም ኃጢተኞችን ይቀጣል የሚል መሠረታዊ አቋማቸውን መጠበቅ ፈለጉ። «ጻድቅ» እስከ ሆኑ ድረስ፣ በዚህ ሕይወት ሳሉ ምንም ክፉ ነገር በእነርሱ



ላይ አይከሰትባቸውም።

ፍርሃትና ቍጣ ብዙውን ጊዜ አብረው ይጓዛሉ። ታማኝነቱን በመጠበቁና ኃጢአት ሠርቼአለሁ ማለትን ባለመቀበሉ ኢዮብ የጓደኞቹን ሥነ መለኮታዊ አስተሳሰብ ናቀው፣ ደግሞም ሰላማቸውንና መተማመናቸውን ሰረቀው፤ እንዲሁም ይህ እንዲቈጡ አደረጋቸው። ጥልቀት የሌለውን ሥነ መለኮታዊ ግንዛቤያቸውን ለማጥፋትና በጥልቀት ወደ እግዚአብሔር ልብና አሳብ እንዲገቡ ለማድረግ እግዚአብሔር ኢዮብን ተጠቀመበት። ይሁንና፣ ጥልቀት ካለው ምሥጢር ይልቅ፣ ላይ ላዩን የሆነውንና ምቹ የሆነውን መረጡ።

ኤልፋዝ፣ በልዳዶስ እና ሶፋር በዛሬው ጊዜ ብዙ ደቀ መዛሙርት አሏቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንዲሁም እያንዳንዱን ችግር ለመፍታት ቀመር ማበጀትና እያንዳንዱን ነገር ለማብራራት የሚገደድ የሚመስለው ሰው በምታገኙበት ጊዜ፣ እናንተ ያላችሁት ከኢዮብ ጓደኞች ጋር በዐመድ ቁልሉ ላይ ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ፖል ተርኒር የተባለውን ስዊዘርላንዳዊ የሥነ ልቡና ባለሙያ ቃሎች አስታውሱ፡-

> እኛ ሁልጊዜ ማለት ይቻላል፣ ሊረዱትና ሊከተሉት ቀላል የሆነና ምሥጢራት የሌሉበት ሃይማኖት፣ መልስ የማይገኝላቸው ጥያቄዎች፣ አስቸጋሪ ነገሮች የሌሉበት ሃይማኖት፣ አሰቃቂ ከሆኑ ሰብአዊ ሁኔታዎቻችን እንድናመልጥበት የሚፈቅድልንን ሃይማኖት፤ ከእግዚአብሔር (ከአምላክ) ጋር ያለ ግንኙነት ከሁሉም ጠብ፣ ከሁሉም እርግጠኝነት ማጣቶች፣ ከመከራዎች ሁሉና ከጥርጣሬዎች ሁሉ ማምለጥ እንድንችል የሚናገር ሃይማኖት፣ በአጭሩ፣ ከመስቀል ውጭ የሆነ ሃይማኖትን እንናፍቃለን። (*Reflections* [New York: Harper and Row. 1976], 142)

ሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች ለሁለቱ በኤማሁስ መንገድ ላይ ይጓዙ ለነበሩት የጌታ ደቀ መዛሙርት እንዴት አድርገው ስለ መስቀሉ ሊነግሩዋቸው እንደሚችሉ ስናስብ እንገረማለን (ሉቃስ 24:ከ13 ጀምሮ)! የመጀመሪያው ዙር ንግግራቸውን እናዳምጥ።

ምዕራፍ ሁለት

# ውይይቱ ጀመረ

## (ኢዮብ 4-7)

*ነገር ግን ሰይጣን የእርሱ በሆኑ በእነዚያ ሳባውያን፣ እንዲሁም የእርሱ በሆኑት ከለዳውያን እና እርሱን ለመርዳት ከምድረ በዳ በመጣው ንፋስ ሁሉ ሊያከናውነው ያልቻለውን ነገር በኤልፋዝ፣ በሶፋር እና በበልዳዶስ ክርክራዊ ጥቃት እና በክርክራዊ አቀራረብ ሊተገብረው ሞከረ:: አ፣ ያልለዘበ የክርክር እርግማን ነበር!*

- አሌክሳንደር ኋይት

ሦስቱ ጓደኞች ለሰባት ቀናት ዝም ብለው ነበር (ኢዮብ 2:13)፣ ደግሞም በኋላ ላይ ኢዮብ በዚህ መልኩ ዝም ቢሉ እንደሚመርጥ ምኞቱን ተናግሮአል (13:5):: «ከዚያም ቴማናዊው ኤልፋዝ ለኢዮብ መለሰለት::» ነገር ግን የመለሰለት ምንድን ነበር? በኢዮብ ልብ ውስጥ ያለውን ሥቃይ ነበር? አይደለም፣ እርሱ የመለሰለት ከኢዮብ ከናፍርት ላይ ለተገኙት ቃሎች ነበር፤ ይህ ደግሞ ስሕተት ነበር:: ብልህ የሆነ አማካሪ እና አጽናኝ ከልብ ማዳመጥ ከዚያም ደግሞም ለውስጣዊ ስሜቶችና ለንግግሮች መልስ መስጠት ይኖርበታል:: የተሰበሩ ልቦችን፣ በሥነ አመክንዮ መፈወስ አልቻሉም:: አዎን፣ እውነቱን መናገር አለባችሁ፣ ነገር ግን እውነቱን በፍቅር እንደምትናገሩ እርግጠኞች ሁኑ (ኤፌ. 4:15)::

### የኤልፋዝ ተግሣጽ (4-5)

**የእርሱ አቀራረብ (ኢዮብ 4:1-4)::** የኤልፋዝ አቀራረብ አጀማመሩ አምንታዊ፣ እንዲሁም ረጋ ያለ እንኳ ይመስል ነበር፤ ነገር ግን ቀጥሎ ላለው መራራ ነገር ኢዮብን ለማዘጋጀት የታለመ ማር ብቻ ነበር:: «አንድ ሰው ከአንተ ጋር ለመናገር ቢሞክር፣ ቅር ይልሃልን?» ሲል ጠየቀ (ቊ. 2፣ አ.መ.ት)::

«ኢዮብ ሆይ አትናደድ!» እያለው ነበር:: «ባለፉት ጊዜያት ቃሎችህ ብዙ ሰዎችን ይረዱ ነበር፤ ደግሞም የእኛ ቃሎች አንተን እንዲረዱህ እንፈልጋለን::»

በሕይወት ትግል ውስጥ የቃል ኃይል ሰዎችን የሚያበረታታ መሆኑን አስመልክቶ ዝቅተኛ ግምትን ከቶ አትስጡ:: ጄምስ ሞፋት ኢዮብ 4:4ን፣ «ቃላችሁ ሰዎች በእግሮቻቸው እንዲቆሙ ያደርጋሉ» በማለት ተረጐመው:: በትክክለኛው ጊዜ በትክክለኛ የልብ አሳብ የተነገሩ ትክክለኞቹ ቃሎች በሌሎች ሕይወት ላይ አስገራሚ ተጽዕኖ ሊያደርጉ ይችላሉ:: ቃሎቻችሁ የደከሙትን ሊመግቡ እና እነዚያ የተሸነፉትን ሰዎች ሊያበረታቱ ይችላሉ፣ ነገር ግን የምትናገሩትንና እንዴት እንደምትናገሩ ተጠንቀቁ::

**ያቀረበው ክስ (ኢዮብ 4:5-11)::** ከዚያም ኤልፋዝ ወደ ክሱ አመራ:: ኢዮብ ሊሰማው ይችል ነበር፣ ነገር ግን ሊቀበለው አይችልም! መከራቸውን እንዴት መመልከት እንዳለባቸው ሊነግራቸው ይችላል፤ ነገር ግን መከራ በሕይወቱ በሚመጣበት ጊዜ የሚሰብከውን ነገር አይኖርበትም:: «እግዚአብሔርን መፍራት መታመኛህ ቀና አኪያሄድህም ተስፋህ አይደለምን?» (ቊ. 6፣ አ.መ.ት):: ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ሕይወትን የሚኖር ከሆነ፣ እንግዲያውስ ኤልፋዝ የሚፈራው ምንም ነገር አይኖርም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁልጊዜ ጻድቃንን ይባርካል በክፉዎች ላይ ይፈርዳል::

ይህ የሦስቱም ጓደኞች መሠረታዊ የሆነ አቋም ነው:- ትክክለኞቹን ነገሮች አድርግ ደግሞም ነገር ሁሉ ለበጐነትህ ይውላል፤ ስሕተት የሆነውን አድርግ፣ እግዚአብሔር ፍርድን ይልካል:: ፍርዱ አንዳንድ ጊዜ ልክ ሰብል ወደ መከሩ እንደሚያድግ ቀስ ብሎ የሚመጣ ይሆናል (ቊ. 8)፤ ወይም ልክ እንደ ነጐድጓድ አመጣጥ እና እንደ አንበሳ ጥቃት ቅጽበታዊም ሊሆን ይችላል (ቊ. 9-11):: ነገር ግን ፍርድ እንደሚመጣ እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ ነው::

ብዙ ሰዎች በመጨረሻ እግዚአብሔር ጻድቃንን የገዛ እራሱን ሕዝቦች እንደሚባርክ በክፉዎችም ላይ እንደሚፈርድ

ይስማሙበታል፤ ነገር ግን በኢዮብ መጽሐፍ ላይ ውይይት እየተደ ረገበት የነበረው ጥያቄ ይሄ አልነበረም:: ስለ መጨረሻው ሳይሆን፣ ስለ አሁኑ ነበር ኢዮብና ወዳጆቹ ግድ ይሰኙ የነበሩት፣ እነርሱ ብቻም ሳይሆኑ፣ ዳዊትም ጭምር ግድ ይሰኝ የነበረው ስለ አሁኑ ነው [መዝ. (36) 37]፣ አሳፍም እንደዚሁ [መዝ. (72) 73]፣ ደግሞም ነቢዩ ኤርምያስ እንኳ ግድ ይሰኝ የነበረው ስለ አሁኑ ነው (ኤር. 12:1-6)::

***ያቀረበው መከራከሪያ ነጥብ* (ኢዮብ 4:12-5:7)::** ኤልፋዝ ነጥቦቹን በማስረጃ ለማስረገጥ ሁለት መከራከሪያዎችን ያነሣል እነዚህም:- ተሞክሮ (4:12-21) እና እይታ (5:1-7) ናቸው:: የመጀመሪያው ተሞክሮ በአንድ ሌሊት ያየው ራእይና የሰማው ድምፅ ነው:: ሁለት ጥያቄዎች መመለስ አለባቸው:- የመልእክቱ ይዘት ምንድን ነበር፣ እንዲሁም መልእክቱ በቀጥታ ከእግዚአብሔ ር የመጣ መገለጥ ነበር ወይ? በብሉይ ኪዳን የዕብራውያን ጥንታዊ ጽሑፎች ውስጥ ምንም ዓይነት የሥርዓተ ነጥብ ምልክቶች ባለመኖራቸው ጥቅሶች የት ጀምረው የት እንደሚያቆሙ ሁል ጊዜ እርግጠኞች አይደለንም:: ብዙዎቹ የእንግሊዝኛ ትርጓሜዎች 4:17-21ን «የመንፈሱ» ሙሉ ዐረፍተ ነገር ያደርጉታል፤ ነገር ግን አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎች ዓረፍተ ነገሩ ከቁጥር 7 ላይ የተገደበ እንደ ሆነ ይሰማቸዋል:: ቀሪው ደግሞ በኤልፋዝ የተሰጠ ማብራሪያ ነው:: በዚህም ሆነ በዚያ፣ መልእክቱ አንድ ነው:- የሰው ሕይወት አጭርና መከራ የበዛበት ነው፣ ደግሞም እግዚአብሔርን ለማስደሰት በእራሱ ክቶ በበቂ ሁኔታ ጻድቅ ሊሆን አይችልም::

ነገር ግን መጠየቅ ያለበት ጥያቄ ይህ ዓረፍተ ነገር በቀጥታ ከእግዚአብሔር የመጣ ዓረፍተ ነገር (ንግግር) ነበር ወይ? የሚለው ነው:: ምናልባት መልሱ አይደለም የሚለው ነው:: መላው መዋቅር እግዚአብሔር እውነቶችን የሚገልጥበት የእርሱ አሠራር አይመስልም:: አንድ ምሳሌን እንይ ከተባለ «የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ» ወይም «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» የሚለው የቃሉ ሥልጣን ይጐድለዋል:: ደግሞም እግዚአብሔር በአብዛኛው በሰዎች ላይ አያደባም እንዲሁም ተስፋ እንዲቈርጡ አያደርግም:: በእርግጠኝነት የምናውቀው ነገር የለም፣



ነገር ግን ኤልፋዝ ሕልም ማለሙ የሚቻል ነገር ነበር፣ ደግሞም ሕልሙ ቀስ በቀስ ወደ ራእይነት ይቀየራል::

አንድ ነገር እርግጥ ነው:- ኤልፋዝ ስለ እግዚአብሔርና ሰው መሉውን ታሪክ እየተናገረ አልነበረም:: አዎን፣ ሰው ፈጥኖ ወደ አፈርነት በሚቀየርበት በሸክላ ቤት ውስጥ ይኖራል፤ ደግሞም የሰው ሕይወት ልክ እንደ እሳት ራት ተጨፍልቆ የሚጠፋ ይሆናል ወይም ድንኳንን ወደ ታች ጐትተው እንደሚያፈርሱት ይፈርሳል:: ነገር ግን ደግሞ ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ጭምር የተፈጠረ ነው፤ እንዲሁም የሠራው አምላክ የጸጋ እና የምሕረት ደግሞም የፍትሕ አምላክ ነው::

የኤልፋዝ ሁለተኛ ክርክር በግል የሕይወት እይታው ላይ የተ መሠረተ ነበር (5:1-7):: ኃጢአተኞች በልጥገውና ሥር ሰድደው ተመልክቶአል፣ ይህም ደግሞ ለጥፋትና የያዙትን ነገር ሁሉ ለማጣት የሆነ ብልጥግና ነበር:: ይህ የኢዮብ ሁኔታን በተ መለከተ ቅን ያልሆነ መግለጫ ነበር:: ልጆቹን የገደላቸው ኃጢአቱ እንደ ሆነ መስማቱ ኢዮብን በጣም ሳይጐዳው አልቀረም:: ነገር ግን በመዝሙር (72) 73 ላይ፣ አሳፍ ሙሉ በሙሉ ከዚህ የተለየ አመለካከት ይዞአል:: እግዚአብሔር ክፉዎች በዚህ የምድር ላይ ሕይወት እንዲበለጽጉ ፈቅዶላቸዋል፣ ምክንያቱም የሚያውቋት ብቸኛዋ «መንግሥተ ሰማይ» ይህችው ምድር ናት:: እግዚአብሔር ለሚቀጥለው ሕይወት ነገሮችን ያበጃጃል ደግሞም በዚያ የእርሱን ሕዝቦች ይሸለማሉ ክፉዎች ደግሞ ይቀጣሉ::

ከእይታ ተነሥቶ የሚደረግ ክርክር ችግሩ፣ እይታችን እጅግ ውስን መሆኑ ነው:: በተጨማሪም፣ እግዚአብሔር ሊያይ በሚችልበት መልኩ የሰው ልብን ማየት አንችልም ደግሞም በእግዚአብሔር እይታ ማን ጻድቅ እንደ ሆነ መናገር አንችልም:: ሌሎች በብልጥግና ኖረው በሰላም የሚሞቱ ሆነው ሳሉ (መክ. 8:10-14)፣ አንዳንድ ኃጢአተኞች፣ በቅጽበት ማለት ይቻላል፣ ፍርድ ያገኛቸዋል::

ችግር እንደ አረም ከምድር አይበቅልም፣ የሰው ውልደት አንዱ አካል ነው፣ ምክንያቱም ሰው ኃጢአተኛ ሆኖ ነው የሚወለደው (ኢዮብ 5:6-7):: ኢዮብ በመከራ ውስጥ በመሆኑ፣ ኤልፋዝ የደ ረሰበት ድምዳሜ፣ እርሱ እራሱ ነው ለዚህ ምክንያት የሆነው፣

ምክንያቱም በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርቷልና:: ስለዚህ ኢዮብ ኃጢአቱን ተናዝዞ እግዚአብሔርን ይቅርታ ሊጠይቀው ይገባዋል::

**ያቀረበው አቤቱታ (ኢዮብ 5:8-17)::** ይህም ኢዮብ እግዚአብሔርን እንዲሻ ደግሞም እራሱን ለእግዚአብሔር እንዲያስገዛ ይጠይቀው ዘንድ ኤልፋዝን መራው:: ተአምራትን የሚያደርገው እንዲሁም ፍጥረቱን የሚንከባከበው አምላክ እራሱን የሚያዋርድና ኃጢአቱን የሚናዘዝ ከሆነ በእርግጥኝነት ኢዮብን ይረዳዋል:: ኢዮብ ፈተናዎቹን እርሱን የተሻለ ሰው ለማድረግ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣ ተግሣጽ መመልከት አለበት (ቍ. 17-18)፣ ይህማ ኤሊሁ በስተኋላ ላይ ወስዶ ያንጸባረቀው ዓላማ/አሳብ ነበር:: እግዚአብሔር የኢዮብን ሀብት እና ቤተሰቡን እንዲሁም ጤናውን ሊወስድበት፣ የቻለበት ኢዮብ ስለ እርሱ ያልተስተካከል አሳብ ሳይኖረው አልቀረም:: ደግሞስ ተግሣጽ የእግዚአብሔር የፍቅር መሣሪያ አይደለም (ምሳሌ 3:11-12፤ ዕብ. 12:1-11)?

**እስረግጦ የሚናገረው ነገር (ኢዮብ 5:17-27)::** ኤልፋዝ ንግግሩን የማስረገጫ ቃላትን በማምጣት ይደመድማል:: ያቈሰለው አምላክ እራሱ ይፈውሳል (ዘዳግ. 32:39፤ ሆሴዕ 6:1-2):: ከመከራ ነፃ ያወጣችኋል፤ ከጠላቶቻችሁ ያድናችኋል እንዲሁም እረጅም እና የደስታ ሕይወት ይሰጣችኋል እንዲሁም የሰላም ሞትን ትሞታላችሁ:: «እነሆ ይህን ሁሉ መርምረናል፤ እውነት ሆኖ አግኝተነዋል ስለዚህ ልብ በል፤ ተቀበለውም» (ኢዮብ 5:27፤ አ.መ.ት)

*ነገር ግን ይህ በተለየ ቃል የተነገረ የሰይጣን ፍልስፍና ነው!* « በውኑ ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራ በከንቱ ነውን? . . .ቍርበት ስለ ቍርበት ነው፤ ሰው ያለውን ሁሉ ስለ ሕይወቱ ይሰጣል» (1:9፤ 2:4):: ኤልፋዝ ከእግዚአብሔር ጋር ድርድር እንዲያደርግ ኢዮብን እየጠየቀው ነበር፣ ደግሞም እግዚአብሔር ያጣኸውን ነገር ሁሉ ይመልስልሃል አለው:: ኢዮብ ያንን አድርጎ ቢሆን ኖሮ፣ እግዚአብሔርን ያስቈጣውና ሰይጣንን ደግሞ ነፃ ያደርገው ነበር፤ ኢዮብ ግን ይህን ለማድረግ ዝግጁ አልነበረም::



## የኢዮብ ምላሽ (6-7)

ኢዮብ ሁለት ከስሜት የሚወጡ ነገሮችን አቀረበ:: የመጀመሪያው ለሦስቱ ጓደኞቹ የበለጠ ግንዛቤንና ኀዘኔታን እንዲያሳዩ ጠየቀ (ኢዮብ 6):: ከዚያም ከመሞቱ በፊት መከራውን እንዲያቀልልለት እግዚአብሔርን ጠየቀ (ኢዮብ 7)::

**(1) ኢዮብ ለወዳጆቹ ያቀረበው አቤቱታ (ኢዮብ 6)::** እስከ አሁን እየተናገረ የነበረው ኤልፋዝ ብቻ ነበር፤ ነገር ግን፣ በልዳዶስና ሶፋርም እንደዚሁም ከእርሱ ጋር የሚስማሙ መሆናቸውን ኢዮብ ሊናገር ይችላል:: ከኢዮብ ጓደኞች አንዱ እንኳ ከሚሰማው አካላዊና ስሜታዊ ሁኔታ ጋር እራሱን ያቆራኘ አልነበረም:: እርሱ በተቀመጠበት ቦታ ላይ መቀመጥ፣ እርሱም የሚሰማውን ማወቅና ስሜቱን መረዳት ለእነርሱ አንድ ነገር ነበር (ሕዝ. 3:15):: «ኀዘኔታን» ልክ «በልቤ ውስጥ ያለ የአንተ ሥቃይ» በሚል የሚተረጉም አንድ ሕፃን ልጅ እነዚህ ሦስቱ ካደረጉት ይልቅ ማጽናናትን ያውቃል::

ለመጀመር ያህል፣ የመከራው ከባድነት ሊሰማቸው አልቻለም (ኢዮብ 6:1-3):: ኢዮብ እጅግ ትዕግሥት-የለሽ በሆነ መልኩ መናገሩ አያስደንቅም! እርሱ የተሸከመውን ሸክም ተሸክመው ቢሆኑ ኖሮ ጓደኞቹም ተመሳሳይ ነገር ያደርጉ ነበር:: ኢዮብ ዛሬ አማኞች ያላቸው የመንግሥተ ሰማይ ሙሉ መገለጥ አልነበረውም፣ ስለዚህ የወደፊት ዕድል ፈንታው የጨለመ ነበር:: 2ኛ ቆሮንቶስ 4:16-18ን ልናነብብና ልናስተውል እንችላለን::

የመከራውን መራርነት ሦስቱ ጓደኞቹ አይረዱም ነበር (ኢዮብ 6:4-7):: ኢዮብ ልክ እግዚአብሔር በመርዝ የተበከለ ቀስት የወረወረበት ያህል ሆኖ ይሰማው ነበር፣ ስለዚህ መርዙ የኢዮብን መንፈስ መራራ አደረገው:: እግዚአብሔር ሠራዊቱን ደረደራቸው፣ እነርሱም በአንድ ደካማ ሰው ላይ ይተኩሱ ነበር፣ ደግሞም የኢዮብ ጓደኞች በዚህ መርዝ ላይ ይጨምሩበት ነበር:: ለኢዮብ የሚያስፈልገው ነገር መንፈሱን የሚመግብለትና ጥንካሬ የሚሰጠው የማጽናኛ ቃል ነበር፣ ነገር ግን ጓደኞቹ ሁሉ የመገቡት ነገር ጥቅመ-ቢስ እና ጣዕም-አልባ የሆኑ ቃሎችን ነበር:: እርሱ ያሰማው ማጉረምረም እንደ አህያ ማናፋት ወይም እንደ በሬ ጩኸት (ግሳት) ከሆነ፣ የዚህ ምክንያቱ ልክ እንደ ተራ እንስሳ ፍቅርንና ችግሩን የሚረዳለትን አጥቶ መራቡ ነበር::

ኢዮብ የነበረበትን ተስፋ የመቍረጥ ሁኔታ እንዲረዱት ለማድረግ ጣረ (ቍ. 8-13):: የተራዘመና ከባድ መከራ አንድን ሰው ሕይወትን በአግባቡ ለመምራት ኃይል-አልባ መሆኑ እንዲሰማው ሊያደርግ ይችላል:: ሕይወትን የሚያበጁ አንዳንድ ግብዓቶችን መቈጣጠር ካልቻልህ፣ ስለ ወደፊቱ እንዴት ማቀድ ትችላለህ? ኢዮብ እንዲህ ሲል ይጠይቃል፣ «አሁንም ተስፋ አደርግ ዘንድ ብርታቴ፣ እታገሥስ ዘንድ አለኝታዬ ምንድን ነው?» (ቍ. 11፣ አ.መ.ት):: በሌላ አነጋገር፣ «ምንድን ነው የምትጠባበቀው? ሕይወት እንዲሁ እየከፋ ነው!» ማለት ነው::

ተስፋ ማጣት ጥቅም-አልባ ነኝ ወደሚል ስሜት ሊመራ ይችላል፤ ጥቅም-አልባ እንደ ሆንህ በሚሰማህ ጊዜ፣ መኖርን አትፈልግም:: ይህም ኢዮብ፣ እግዚአብሔር ለምን ሕይወቱን እንዲወስድ እንደ ፈለገ ያብራራልናል (3:20-23፤ 6:8-9፤ 7:15-16፤ 10:18-19፤ 14:13):: ኢዮብ ይህን በእራሱ ለማድረግ አልሞከረም፣ ምክንያቱም እራስን ማጥፋት ስሕተት እንደ ሆነ ያውቃል:: ነገር ግን ከዚህ መከራው በማውጣት እንዲወስዳት እግዚአብሔርን ጠየቀ:: የኢዮብ ጓደኞች ጤናማና በምቾት ውስጥ ያሉ ናቸው:: ዕለት ዕለት የመከራን ሸክም ተሸክሞ ከእንቅልፍ መንቃትን አያውቁም ነበር:: ኢዮብ ጥንካሬ ርቆታል፣ ደግሞም እርሱ ጥቅም-አልባ እንደ ሆነ ይሰማዋል (6:12-13)::

በድፍረትም፣ የእርሱ አገልግሎት ውጤታማ አለመሆኑን ኢዮብ አመለከተ (ቍ. 14-30):: አላሳዘኑትም ወይም የእርሱን ፍላጎት ለመሙላት አልሞከሩም:: እነርሱ በበረሃ እንዳለ የተጠሙ ተጓዦችን ተስፋ እንደሚያስቈርጥ ደረቅ ጅረት ነበሩ:: እርሱ ባለጠጋ እስከ ሆነ ድረስ ወዳጆቹ ነበሩ፤ ነገር ግን ችግር በሚመጣ ጊዜ፣ በእርሱ ላይ በተቃውሞ ይነሣሉ::

ኢዮብ ለወዳጆቹ ሁለት ጥያቄዎችን አቀረበላቸው:- እነዚህም «አስተምሩኝ» እና «ወደ እኔ ተመልከቱ» የሚሉ ነበሩ (ቍ. 28):: ክስ አያስፈልገውም፤ እርሱ የእግዚአብሔር ቃል መረዳት ነበር የሚስፈልገው! ነገር ግን ፊቱንና አቤቱታውን እንኳ አልተመለከቱም ነበር:: በአካል፣ ሦስቱ ሰዎች ከኢዮብ ጋር ተቀምጠዋል፣ ነገር ግን በስሜት ልክ እንደ ካህኑና ሌዋዊው «በሌላው የመንገዱ ጠርዝ የሚጓዙ ነበሩ» (ሉቃስ 10:30-37)::



በመጋቢነት አገልግሎቴ በበሽታ፣ በአደጋ፣ ወይም በቀዶ ጥገና ምክንያት ሲያዩአቸው አስቸጋሪ የሚሆኑ የሆስፒታል ሕሙማንን መጐብኘቴን አስታውሳለሁ፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከመመረራቸው የተነሣ ሊያዳምጡዋቸው አስቸጋሪዎች ይሆናሉ:: ከአይታዬና ለቃላቸው ከሰጠሁት ምላሽ እኔ በእውነት ስለ እነርሱ ግድ እሰኝ እንደ ሆነ ወይም እንዳልሆነ ማወቅ ይችላሉ:: በመጀመሪያ በልቦቻችን ድልድይን ካልገነባን በስተቀር፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ መጥቀስና መጸለይ እምብዛም ጥሩ አይሆንም:: ከዚያም እያንዳንዱን ማገልገል እንችላለን::

ኢዮብ ለጓደኞቹ መናገርን የእርሱን ተጨባጭ ሁኔታ ልብ እንዲሉ ደግሞም የበለጠ የፍቅር አቀራረብን እንዲይዙ በኃዘኔታ በመናገር ደመደመ:: «መለስ በሉ፤ ፍርደ ገምድል አትሁኑ፤ ጽድቁ ጸንታ ቆማለችና መለስ ብላችሁ አስተውሉ» (ኢዮብ 6:29፣ አ.መ.ት):: ሦስቱ ሰዎች እራሳቸውን በመከላከል ረገድ እጅግ ከመዋጣቸው የተነሣ ባልንጀራቸውን ማጽናናቱን ረስተውታል!

**(2) ኢዮብ ለጌታ ያቀረበው አቤቱታ (ኢዮብ 7)::** ኢዮብ የሕይወትን *ከንቱነት* ለማብራራት ብዙ ጉልህ ሥዕላዊ መግለጫዎችን ተጠቅሞአል:: እርሱ ከፈቃዱ ውጭ ወደ ጦር ሠራዊት እንዲቀላቀል የተደረገ ሰው ስሜት ይሰማዋል (ቍ. 1ሀ) «ወራቱ»፣ ደግሞም ልክ እንደ የጉልበት ሠራተኛ (ቁ. 1ለ) ወይም እንደ ተቀጠረ ሰው የፀሐይን መውጣትና የዕለት ምንዳውን ይጠባበቅ ነበር (ቍ. 2):: ቢያንስ ቢያንስ እነዚህ ሰዎች አሻግረው የሚመለከቱት አንድ ነገር ይኖራቸዋል፣ ነገር ግን የኢዮብ የወደፊት ሁኔታ ተስፋ የሌለበት ነበር:: ምሽቶቹ እንቅልፍ-አልባ ነበሩ፣ ቀኖቹም ከንቱ ነበሩ (ዘዳግ. 28:67)፣ ደግሞም ጌታም ግድ ያለው አይመስልም ነበር::

ከዚያም በሕይወት ቀጭነት ላይ ያተኩራል:: ጊዜ እንደ ዘበት እያለፈ ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር የትኞቹንም ነገሮች ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ቢሆን፣ ፈጥኖ ቢያደርገው ይመረጣል! የኢዮብ ሕይወት ልክ እንደ ሸማኔ መወርወሪያ (ኢዮብ 7:6)፣ ክሩን እያደራ በፍጥነት የሚጓዝ ነበር:: (በ6:9 ላይ «አድቅቆ ያጠፋኝ ዘንድ» (አ.መ.ት) የሚለው ሐረግ «ከመጥለፊያ ላይ ድርን/ፈትልን መቁረጥ ማለት ነው::» ኢሳ. 38:12ን ተመልከት):: ሕይወት ልክ

እንደ ፌትል ናት፣ ደግሞም አጠቃላዩን መዋቅር ደግሞም ሥራው መቹ እንደሚጠናቀቅ የሚያይ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

በተጨማሪም ኢዮብ ሕይወቱን እንደ ትንፋሽ ወይም ደመና ተ መልክቷት ነበር፣ እዚህ ላይ ሕይወት ለአጭር ጊዜ ታይታ እስከ ወዲያኛው የምትሄድ ከቶም የማትመለስ መሆንዋ ተመልክቶአል (ኢዮብ 7:7-10፤ ያዕቆብ 4:14)። እግዚአብሔር እርሱን ይመለከተ ው የነበረው በእያንዳንዱ ደቂቃ ሊጠበቅ የሚገባ አደገኛ አውሬ አድርጎ ነበር (ኢዮብ 7:11-12)። እግዚአብሔር እርሱን ዘወትር ስለ መጠበቁ ኢዮብ መመረሩ አያስደንቅም። ኢዮብ ያምን («ባሕርን») እና ታሚን («ዓሣ ነባሪን») የመጥቀሱ እውነታ ለምሥራቁ ዓለም ምናባዊ እውነታ (አባባል) ማረጋገጫን መስጠቱ አይደለም። እነዚህን ታዋቂ የሆነ ገጸ ባሕርያት የተጠቀመው ሊያስጨብጠው የፈለገውን ነጥብ በምሳሌ ለማቅረብ ነበር።

ኢዮብ «ሰውን የሚከታተል» (ቍ. 20፣ አ.መ.ት)፣ እግዚአብሔ ርን የሚያመልጥበት ምንም መንገድ የለም። ኢዮብ ቢያንቀላፋ፣ እግዚአብሔር በሕልሞቹ ያስፈራራዋል፣ ቢነቃ ደግሞ የእግዚአብሔር ዓይኖች በእርሱ ላይ እንዳሉ ያውቃል (10:14፤13:27፤ 31:4)። እግዚአብሔር ሳያውቀው ምራቁን እንኳ መዋጥ አይችልም ነበር! እግዚአብሔር ለአንድ ሰው ይህን ያህል ለምን ትኩረት ሰጠ (7:17-18፤ መዝ. 8:4)?

ኢዮብ አቤቱታውን በይቅርታ ጥያቄ ያጠናቅቀዋል (ኢዮብ 7:20 -21)። «ኀጢአት ብሠራ፣ አንተን ምን አደርግሃለሁ? ለምን ዒላማህ አደረግኸኝ? ለምንስ ሸክም ሆንሁብህ?» ጊዜ ፈጥኖ እንደ ዘበት ያልፋል፣ ስለዚህ በተቻለ መጠን በፍጥነት ነገሮችን እንቋጭ! ይህ የኃጢአት ኑዛዜ አይደለም፣ ምክንያቱም ኢዮብ አሁንም ታማኝነቱን ጠብቋል፤ ነገር ግን እርሱ ስለማያውቀው የሕይወት ክፍሉ እግዚአብሔር የሚናገርበት መልካም አጋጣሚ ነበር [መዝ. 18 (19):12-14]።

ከዚያም ኢዮብ ጸጥ አለ። ሥቃዩንና ፍርሃቶቹን እንዲረዱትና እንዲያጽናኑት እንዲሁም ለጓደኞቹ ያቀረበውን ልመና አቆመ። ይቀበለው ይሆን?

ቀጥለን በእግዚአብሔር ፍትሕ ላይ አጠር ያለ ሥነ መለኮታዊ ትምህርት የሰጠውን ሹሐዊው በልዳዶስን እናድምጥ።



# ለግል ምልከታ ወይም ለቡድን ውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. አንድ ሰው አስቸጋሪ እውነት አንሥቶ ጥያቄ በመጠየቅ አጣብቂኝ ውስጥ ሊጨምራችሁ ቢመጣ (ብትመጣ)፣ በዚህ ዓይነት እንዲቀርባችሁ (እንድትቀርባችሁ) ትፈልጋላችሁ?

2. መታዘዝ በረከትን ያመጣል፣ ከሚለው ጋር የኢዮብን መከራ እንዴት ታስታርቁታላችሁ?

3. ሕይወት አጭርና በመከራ የተሞላች ናት፣ ከሚለው ከኤልፋዝ ነጥብ ጋር የትኞቹ ክስተቶች ናቸው ፊት ለፊት ያገጣጠሙዋችሁ?

4. በመከራ ውስጥ አልፋችሁ ከሆነ፣ ጠንካራና የተሻለ ሰው ሆናችሁ ከትግሉ ጊዜ የወጣችሁት በየትኞቹ መንገዶች ነው?

5. ልክ እንደ ኢዮብ ጉዳይ ሁሉ፣ እኛ ከቶ ያልተጋፈጥናቸውን መከራዎች ለተቀበለው ሰው የምንሰጠው መጽናናት ምንድን ነው?

6. ኢዮብ ከጓደኞቹ ጋር ለሰባት ቀናት በጸጥታ ተቀምጦአል።

እርሱን እንዲመለከቱት በተናገራቸው ጊዜ የጠየቃቸው ምንድን ነበር?

7. ላለበት ተጨባጭ ሁኔታ የኢዮብ ጓደኞች የትኞቹን እውነተኛ መጽናናቶች ሊያመጡለት ይችሉ ነበር?

8. ከቶ ባልተወለድሁ ብሎ በመመኘቱ ለኢዮብ ኃጢአት ነበር ወይ? የእራስህን ምክንያቶች ስጥ::

9. ኢዮብ ሲፀነስ በሕይወቱ ውስጥ ያን እያንዳንዱን ዝርዝር እግዚአብሔር ያውቃል:: ይህ ለኢዮብ መጽናናት የሚሆነው በምን መልኩ ነበር?



**ምዕራፍ ሦስት**

# ውይይቱ ቀጠለ

**(ኢዮብ 8-10)**

«ምናልባት አንተም እንደ ሰይጣን ልክ የሆነ አሳብን ይዘህ የምትመጣ፣ እንዲሁም ክፉ ልትሆን ትችላለህ::»

- ጆን ዌስሊ

ውይይቱ እንደ ቀጠለ፣ ኢዮብ ኃጢአተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ በልዳዶስ ሦስት ሥነ አመክንዮታዊ ክርክሮችን አቀረበ፤ እንዲሁም ኢዮብ እርሱ በእውነት ምን ያህል ግራ እንደ ተጋባ እና የተሠቃየ እንደ ሆነ እንዲረዱት ጓደኞቹን ለመርዳት ከሦስት የሚያስቸግሩ ጥያቄዎች ጋር መቃወሚያውን አቀረበ::

## ሦስት ሥነ አመክንዮታዊ ክርክሮች (8:1-22)

«ቃልህም እንደ ብርቱ ነፋስ የሚሆነው እስከ መቼ ነው?» (ኢዮብ 8:2፣ አ.መ.ት):: ሊሞት ለሚፈልግ በመከራ ውስጥ ላለ ሰው አንድ አማካሪ እንዲህ ይላል ብላችሁ ታስባላችሁ? በልዳዶስ ይህን አደረገው፣ በእርግጥ በሚቀጥለው ንግግሩም ተመሳሳይ ዝንባሌን ነበር የተጠቀመው (18:2):: ኢዮብ ኀዘኑን አፈሰሰ ደግሞም የኀዘኔታን ቃል ለመስማት እየተጠባበቀ ነበር፣ ነገር ግን ጓደኛው የኢዮብ ቃሎች ልክ እንደ ሞቀ አየር ናቸው አለ::

ለበልዳዶስ አቀራረብ መነሻ የሆነ ምክንያት አለ:- የጓደኛውን ፍላጎት እስኪረሳ ድረስ የእግዚአብሔርን ፍትሐዊነት በተመለከተ መከላከያ ለማቅረብ እጅግ አትኩሮት ሰጥቶ ነበር:: «በውኑ እግዚአብሔር ፍርድን ያጣምማልን? ሁሉንም የሚችል አምላክ ጽድቅን ያጣምማልን?» (ኢዮብ 8:3):: በልዳዶስ በእግዚአብሔር

ፍትሐዊነት ላይ ስብከት አቀረበ፣ ደግሞም ምንባቡ የተወሰደው ከኤልፋዝ «ራእይ» ነበር:- «በውኑ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሊሆን. . .ይችላልን?» (4:17)፡፡ ለእግዚአብሔር ፍትሐዊነት ጥብቅና ለመቆም፣ በልዳደስ ሦስት ሥነ አመክንዮታዊ ክርክሮችን አቀረበ፡፡

**(1) የእግዚአብሔር ባሕርይ (ኢዮብ 8:1-7)፡፡** እግዚአብሔር የትኛውንም ስሕተት አይፈጽምም የሚለው የኢዮብ ንግግር ይልቁንም በልዳደስን አስቈጣው፡፡ ኢዮብ በጥፋት ጊዜ የነበሩ ኃጢአተኞችን ረሳቸው፣ ወይስ እግዚአብሔር በሰዶምና በገሞራ ላይ ያደረገውን ረሳ? እርሱ ቅዱስ አምላክ አይደለምን፣ ቅዱስ የሆነ ባሕርይው ትክክለኛውን ነገር ብቻ እንዲያደርግ የሚፈቅድ አይደለምን? በእርሱ ላይ ጥያቄን በማንሣት እርሱንም ስለሚያደርጋቸው ስሕተቶች በመክሰስ በእግዚአብሔር ላይ የስድብን ቃል እየተናገረ ነበር፡፡

እግዚአብሔር ጻድቅ ነው የሚለው የበልዳደስ ሥነ መለኮታዊ አሳብ ትክክል ሆኖ ሳለ፣ ሥነ መለኮታዊ አሳቡን ከሕይወት ጋር የሚያዛመድበት ሁኔታ የተሳሳተ ነበር፡፡ በልዳደስ የእግዚአብሔርን አንድ ባሕርይ-የቅድስናውንና ፍትሐዊነቱን ገጽታ ብቻ ይመለከት ነበር፤ ታዲያ ፍቅሩን፣ ምሕረቱን እና መልካምነቱን ረስቶ ነበር፡፡ አዎን፣ «እግዚአብሔር ብርሃን ነው» (1ኛ ዮሐንስ 1:5)፣ ነገር ግን «እግዚአብሔር ፍቅር መሆኑን» (4:8፣ 16) አትርሳ፡፡ የእርሱ ፍቅር ቅዱስ የሆነ ፍቅር ነው፣ ደግሞም ኃጢአትን በሚቀጣበት ጊዜ እንኳ የእርሱን ቅድስና ሊለማመዱት የሚችሉት በፍቅር ነው፡፡

እነዚህ ሁለት የእግዚአብሔር ባሕርያት እንዴት ነው የሚታረቁት? መልሱ በመስቀል ላይ ነው፡፡ ኢየሱስ ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት በሞተ ጊዜ የእግዚአብሔር ጽድቅ ተረጋግጦአል፣ ምክንያቱም ኃጢአት ተፈርዶበታልና፤ የእግዚአብሔርም ፍቅር እንዲሁ ተገልጦ ታይቷል፣ ምክንያቱም አዳኝ ተሰጥቶአልና፡፡ በቀራኒዮ እግዚአብሔር ሁለቱንም፣ ማለትም «ጻድቅም አጽዳቂም» ነው (ሮሜ 3:24-26)፡፡ የእግዚአብሔር ሕግ እንዲህ ይላል:- «ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ ትሞታለች» (ሕዝ. 18:4፣ 20)፤ ደግሞም እግዚአብሔር ልጁን በመሠዋቱ የገዛ እራሱን ሕግ አከበ



ረው፡፡ ክርስቶስ በትንሣኤው ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ጸጋ በኃጢአትና በሞት ላይ ድል አደረገ ደግሞም ንስሐ የሚገቡ እና በኢየሱስ ክርስቶስ የሚታመኑ ሁሉ ይድናሉ፡፡

በብሉይ ኪዳን ዘመን፣ አማኞች ወደ ፊት ወደ መስቀሉ አሻግረው ይመለከቱ እና ሊመጣ ባለው አዳኝ ላይ በሚሆን እምነት ይድኑ ነበር (ዮሐንስ 8:56፤ ሮሜ 3:25፤ ዕብ. 11)፡፡ ኢዮብ አማኝ ነበር፤ ስለዚህ ስለ ኃጢአቱ ስርየት የሚሆን መፍትሔ በእግዚአብሔር ይዘጋጅለታል፡፡ ኢዮብ በእግዚአብሔር ላይ በሆነ ታላቅ ሁኔታ ኃጢአት ሠርቶ ቢሆን እንኳ፣ እግዚአብሔር ከልጁ ጋር ጉዳዩን የሚያከናውነው በጸጋ እና በምሕረት መሠረት ነው እንጂ፣ በፍትሕ መሠረት አይደለም፡፡ ኃጢአታችንን በምንናዘዝበት ጊዜ እግዚአብሔር ይቅር ይለናል፣ ምክንያቱም ለተስፋ ቃሉ እንዲሁም ለእነዚያ ኃጢአቶች ለሞተው ልጁ ታማኝ ነው (1ኛ ዮሐንስ 1:9)፡፡

በልዳደስ የኢዮብ ልጆች የሞቱት ኃጢአትን ስለ ሠሩ ነው ብሎ በተናገረ ጊዜ፣ ኢዮብ ክፉኛ መጐዳቱ የማይቀር ነው (ኢዮብ 8:4)፡፡ ምናልባት በልዳደስ ኢዮብን እያጽናና እንደ ሆነ ሳያስብ አልቀረም፡፡ «ምናልባት የሞቱት *በአንተ* ኃጢአት ሳይሆን፣ ነገር ግን በገዛ እራሳቸው ኃጢአት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ እነርሱ አሁን ሊያመጡት የሚችሉት ለውጥ የለም፣ ነገር ግን አንተ ለውጥ ልታመጣ ትችላለህ፤ ስለዚህ ለውጥ ለማምጣት እጅግ አትዘግይ!»

በቍጥር 5-7 ላይ በልዳደስ ያቀረበው ልመና የሰይጣንን ፍልስፍና ሌላው የሚያስተጋባ ነገር ነው፡፡ «አንተ እኔ ኃጢአት አልሠራሁም ብለሃል፡፡ እንግዲያውስ ብልጥግናህን እንዲመልስልህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ፡፡ አንተ በእግዚአብሔር ፊት ልክ ከሆንህ፣ እርሱ ለአንተ ታላቅ ነገርን ያደርግልሃል፡፡ ብልጥግና ከሥቃይ አይሻልምን?» ቃሉቹ እንደሚፈጸሙ ደግሞም የኢዮብ ፍጻሜ ከመጀመሪያው ይልቅ የሚበልጥ መሆኑን በልዳደስ እምብዛም አልተገነዘበም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ በመጨረሻ የኢዮብ ጸሎት ለበልዳደስና ለሌሎቹ ሆነ፣ ምክንያቱም እነርሱ ነበሩ ከእግዚአብሔር ጋር በትክክል ይሄዱ ያልነበሩት (42:7-13)፡፡

**(2) የቀደመው ዘመን ጥበብ (ኢዮብ 8:8-10)፡፡** ኤልፋዝ አስተ

ሳሰቡን በእይታውና በተሞክሮው ላይ መሠረተ፣ ነገር ግን በልዳዶስ ከጥንት ያለውን ጥበብ የሚመለከት ትውፊታዊ ነበር:: «ጥንታውያን ሰዎች ስለ እርሱ ምን ይናገራሉ?» የሚለው ለእርሱ ቁልፍ ጥያቄ ነበር:: እርግጠኛ ለመሆን፣ ዛሬ እኛ ካለፈው መማር እንችላለን:: «ካለፈው የማይማሩ ሰዎች ደግመው ሊኖሩት የተረገሙ ናቸው፣» ሲሉ ጆርጅ ሳንታይና ጻፉ:: ነገር ግን ካለፈው ዘመን ሊመራን የሚገባ ራዳር መሆን ይገባዋል እንጂ፣ ወደ ኋላ የሚጐትትና የሚይዘን መልኅቅ መሆን የለበትም:: «ያለፈው ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለበት ሁኔታ የወደፊቱን ዘመን ይወስናል፣» አለ አልፍሬድ ኖርዝ ኋይትሄድ የተባለው ፈላስፋ::

ከዓመታት በፊት የተባለ ወይም የተጻፈ ነገር የመኖሩ እውነታ አሁን እውነት ስለ መሆኑ ዋስትና አይኖርም:: ጥንታውያን የሮምና የግሪክ ጽሑፎችን ማንበብ እንደሚወድድ ሰው፣ ብዙ ጥበብን የመያዛቸውን ያህል ብዙም ከንቱነት በመያዛቸው እገረማለሁ፤ ደግሞም ዘወትር እርስ በርስ ይጋጫሉ:: *«ዘ ግሬት ቡክስ ኦፍ ዘ ዌስተርን ወርልድ»* የተባለው መጽሐፍ አራሚ ሮበርት ሁቺንስ፣ በመቅደሙ ውስጥ እንዲህ የሚለውን ጽፎአል፣ «ለሃያ አምስት ምእተ ዓመታት በተደረገ ቃላት መለዋወጥ፣ የመሠረተ እምነት ድንጋጌዎችና አመለካከቶች ሁሉ ተገለጡ:: እዚህ ላይ ታላላቅ ስሕተቶች እንደዚሁም ታላላቅ እውነቶች አሉ::»

«ትውፊት» እና «ትውፊታዊነት» ሁለቱ የተለያዩ ነገሮች ናቸው:: ጂሮስላቭ ፔሊካን የተባለው የታሪክ ጸሐፊ እንዲህ ብሎ በተናገረ ጊዜ ይህን ልዩነት ገልጾታል:- «ትውፊት የሙታን ሕያው እምነት ነው፤ ትውፊታዊነት የሕያዋን ሙት እምነት ነው::» ለበልዳዶስ፣ ያለፈው ጊዜ እንደ መኪና ማቆሚያ ነበር፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያለፈው ጊዜ የመነሻ እንዲሆን ነው የሚፈልገው:: እነርሱ ይሹት ወደ ነበረው ግብ መራመድ እንችል ዘንድ፣ ከጥንታውያን ሰዎች ጋር እንቆማለን:: ይህ ስለ እግዚአብሔር ያለን ግንዛቤ እንዲሁም ደግሞ ስለ ሰዎች ያለንን እውቀት ያካትታል:: ጆን ሮቢንሰን ወደ አዲሱ ዓለም ሲያመሩ የመናኝ ጕዞ ለሚያደርጉቱ እንደ ተናገሩት፣ «ጌታ ከቅዱስ ቃሉ ገና የሚወጡ ብዙ እውነቶች አሉት::»



በልዳዶስ ከጥንታውያን ሰዎች ንግግር/አባባል አልጠቀሰም፤ እርሱ ልክ እንደ እርሱ ሁሉ እነዚህን አባባሎች ኢዮብ እንደሚያውቃቸው ተገንዝቦአል:: ነገር ግን በልዳዶስ በእርሱ ዘመን ከነበሩ አስተማሪዎች ይልቅ፣ የጥንታውያኑን ጥበብ የበለጠ ያከብር ነበር:: «ገና ትላንትና ከተወለዱ ሰዎች» ቃል ይልቅ በዘመናት መካከል የተከማቸ ጥበብ ይሻላል:: እነርሱ ሊያስተምሩን የሚችሉትን ሁሉ ለመማር ሕይወት ለእኛ አጭር ናት:: እኛ እንደ ጠፊ ጥላዎች ነን፣ ስለዚህ ባገኘነው አጋጣሚ ሁሉ ጥበብን ብንማር የተሻለ ነው::

**(3) በተፈጥሮ ውስጥ ያለ ማረጋገጫ (ኢዮብ 8:11-22)::** በዚህ «የጥበብ ግጥም»፣ በልዳዶስ በምክንያትና ውጤት ሕግ ላይ ተመሥርቶ ክርክር ባቀረበበት ጊዜ ከጥንታውያን ሰዎች አባባሎች መካከል አንዳንዶቹን አሳጥሮ አቅርቧቸዋል:: ይህ ሕግ በተፈጥሮ ተግባራዊ የሚሆን ከሆነ፣ በሰው ሕይወት ውስጥስ ለምን አይተገበርም?

የፓፒረስን ተክል እንደ ምሳሌ እንውሰድ:- ውኃ ከሌለው ይደርቅና ይሞታል (ቍ. 11-13):: ኢዮብ እየደረቀና እየሞተ ነበር፣ ስለዚህ ለዚህ የሚሆን መነሻ የግድ መኖር አለበት:- እርሱ ግብዝ ነበር፣ እንዲሁም ተስፋውም በመጥፋት ላይ ነበር::

ከዚያም በልዳዶስ ከዕፀዋት ወደ ሸረሪቶች አመራ (ቍ. 14-15):: በሸረሪት ድር ላይ ጋደም ልትል እና እንዳትወድቅ ሊይዝህስ ይችላልን? በእርግጥ ይህ ሊሆን አይችልም! አንተ ምንም ያህል የተማመንህ ሁን፣ ድሩ ይበጣጠሳል:: የኢዮብ መተማመን ልክ እንደዛ ያለ ነበር:: በጊዜውም፣ ተበጣጥሷል፣ ደግሞም ኢዮብ ወድቋል::

ሦስተኛው ምሳሌ የተወሰደው ከአትክልት ስፍራ ነበር:- አንድን ተክል ብትነቅለው፣ የቱንም ያህል ለም ቢሆንም፣ በመጨረሻ ይሞታል (ቍ. 16-22):: በኢዮብም «ሥር ሥርዓት» ላይ እንዲሁ አንድ ነገር ተከስቷል፣ እርሱም እየጠወለገ ሄደ፤ ስለሆነም፣ ምክንያቱ ኃጢአት ነበር:: ማንም ሰው መልካም የሆነ ተክልን ነቅሎ ሊያወድመው አይሻም፣ ስለዚህም እግዚአብሔር የኢዮብን ሥር እንደዚህ አድርጎ ለመንቀል፣ ኢዮብ የፈጸመው አንድ የሆነ ስሕተት መኖሩ አይቀሬ ነው:: እግዚአብሔር አረሞችን

እያሳደገ መልካም ተክሎችን አይጥልም! ኃጢአት መሥራቱን አምኖ ከእግዚአብሔር ጋር መንገዱን ካስተካከለ፣ የወደፊት ዘመኑን እግዚአብሔር እንደሚያድስለት በልዳዶስ ለኢዮብ በድጋሚ ያረጋግጥለታል። ይህም ደግሞ በድጋሚ ለኢዮብ የቀረበ የዲያብሎስ ግብዣ ነበር!

## ሦስት አሳማሚ ጥያቄዎች (9:1-10:22)

ከዚህ ነጥብ ጀምሮ፣ በውይይቱ ላይ ያለው አጽንዖት *በእግዚአብሔር ፍትሕ* ላይ ነው፤ ደግሞም በኢዮብ አእምሮ ውስጥ ላቅ ብሎ ያለው ምስል *የፍርድ ክርክር ሂደት* ነው። እግዚአብሔርን ፍርድ ቤት ሊወስደውና *ታማኝነቱን* በፍርድ ቤት ሙግት ሊያረጋግጥ ፈለገ። በአንዳንድ ቃላት ላይ የምናደርገው ምልከታ ይህን ያመለክታል:-

*ክርክር* (ኢዮብ 9:3፤ 10:2) = ወደ ሙግት መግባት
*መልስ* (9:3፣ 16) = በፍርድ ቤት መመስከር
*ዳኛ* (ቍ. 15 ) = በሕግ የሚቃወም፣ ከሳሽ
*ጊዜን መወሰን* (ቍ. 19) =ወደ ፍርድ ቤት መውሰድ
*ገላጋይ* (ቍ. 33) = ወሳኝ፣ ዳኛ
*አመክንዮ* (13:3) = በአንድ ጉዳይ ላይ መከራከር
*ጭብጥ* (ቍ. 18) = ነገርን ማቅረብ
*አቤቱታ* (ቍ. 19:23:6) = በፍርድ ቤት የሚደረግ ክርክር
*አድምጠኝ* (31:35) = በሕግ ሂደት ላይ ስማኝ
*ባላንጣ* (ቍ. 35) = በፍርድ ቤት ከሳሽ

በኢዮብ 9 እና 10፣ ኢዮብ ሦስት ጥያቄዎችን ይጠይቃል:- «በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ጻድቅ መሆን እችላለሁ?» (9:1-13)፣ «እግዚአብሔርን በፍርድ ቤት እንዴት ላገኘው እችላለሁ? (ቍ. 14-35) እንዲሁም «ስለ ምን ተወለድሁ?» (10:1-22፤ ቍ. 18ን ተመልከት)። እነዚህ ጥያቄዎች እንዴት እንደሚያያዙ መመልከት ትችላላችሁ። ኢዮብ ጻድቅ ነው፣ ነገር ግን ጻድቅነቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል። ሟች የሆነ ሰው ጻድቅ መሆኑን በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ማረጋገጥ ይችላል? እግዚአብሔርን ወደ ፍርድ ቤት መውሰድ ይችላል? ነገር ግን እግዚአብሔር በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ካልገባና ለኢዮብ ካልመሰከረለት በስተቀር፣ የዚህ መከራ ሁሉ



ዓላማ ምንድን ነው? ኢዮብ ስለ ምን ተወለደ?

**(1) «እኔ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ጻድቅ ልሆን እችላለሁ?» (ኢዮብ 9:1-13)**። ይህ ስለ (ደህንነት) የቀረበ ጥያቄ («እንዴት ልጸድቅ እችላለሁ?») አይደለም፣ ነገር ግን ነፃ ስለ መውጣት («ነፃ መውጣቴ እንዴት ሊታወጅልኝ ይችላል?») የሚናገር ነው። አንድ ሰው እግዚአብሔርን ወደ ፍርድ ቤት ለመውሰድ ከሞከረ፣ እግዚአብሔር የሚያነሣቸውን ከአንድ ሺህ ጥያቄዎች ውስጥ አንዷን እንኳ ለመመለስ አይችልም! ይሁንና በጓደኞቹ ፊት ነገሩን ግልጥ ለማድረግ ኢዮብ የሚያውቀው ሌላ ምንም መንገድ አልነበረም።

የዚህ አብዛኛውን ክፍል በእግዚአብሔር ችሎታዎች፣ በተለይም ምድርንና ሰማይን የሚቆጣጠር የማይበገር ጥበቡና ኃይሉ ላይ የሚያተኩር አዋጅ ነው። ማንስ ቢሆን ምድርን ለማንቀጥቀጥ፣ ከዋክብትን ለመሥራት እንዲሁም በማዕበል ውስጥ ለመራመድ ኃይለኛ ከሆነ ተቃዋሚ ጋር ፍርድ ቤት ለመሄድ ይደፍራልን? (ኢሳ. 44:24 እና አሞጽ 4:13ን ተመልከት)።

እግዚአብሔር የማይበገር ብቻ አይደለም፣ እርሱ *የማይታይም* ጭምር ነው። ኢዮብ ሊያየው ወይም የፍርድ ቤት መጥሪያ ሊሰጠው በማለት ሊያስቆመው አይችልም። እግዚአብሔር የቱንም ደስ የሚያሰኘውን ነገር ማድረግ ይችላል፤ ደግሞም ማንም ሊጠይቀው አይችልም! ረዓብ የተባለውን ጭራቅ እንኳ (ኢዮብ 9:13፣ ይህ ደግሞ ልክ እንደ ያም እና ታኒን ሁሉ ሌላው ምናባዊ ፍጡር፣ 7:12 ነው) በእግዚአብሔር ኃይል ፊት መስገድ አለበት።

**(2) «እግዚአብሔርን በፍርድ ችሎት እንዴት አገኘዋለሁ?» (ኢዮብ 9:14-35)**። እራሱን በጻድቅነቱ ለማረጋገጥ እግዚአብሔርን ወደ ፍርድ ቤት መውሰድ ነበረበት። ነገር ግን እግዚአብሔር መጥሪያውን ተቀበለ እንበል። ኢዮብ ምን ይናገራል ወይስ ምን ያደርጋል? አራት ሁኔታዎችን በአእምሮው በማውጠንጠን ይህን ያብራራዋል።

*ሀ. «እግዚአብሔር ቢመጣ ምን እላለሁ?»* (ቍ. 14-19)። ኢዮብ የእግዚአብሔርን መስቀለኛ ጥያቄ እንዴት ሊመልስ ይችላል? እግዚአብሔር መመለስ የሚገባው ከሆነ፣ ኢዮብ በእውነት የእግዚአብሔር ድምፅ መሆኑን አያምንም፤ ደግሞም ኢዮብ የተ

ሳሳተ ነገር መናገር የግድ የሚያስፈልገው ከሆነ፣ እግዚአብሔር ሊያደርግ የሚችለው መከራውን መጨመር ብቻ ነበር:: በመጨረሻ ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር በተገናኘ ጊዜ (ኢዮብ 35-41)፣ እግዚአብሔር ሰባ ሰባት ጥያቄዎችን ጠየቀው! ኢዮብ ደግሞ አንዱንም እንኳ አልመለሰም ነበር! ብቸኛው ምላሹ አለማወቁን አምኖ መቀበል ደግሞም አፉን በጸጥታ መዝጋት ነበር::

ለ. *«ንጽሕናዬን ማወጅ ብችል፣ ከዚያ ምን ይከሰታል?»* (ቍ. 20-24):: ይህ እግዚአብሔር ኢዮብን በነፃ ስለ መልቀቁ ዋስትና አይሆንም:: ኤልፋዝም ሆነ በልዳዶስ ሁለቱም እግዚአብሔር ጻድቃንን እንደሚባርክና በኃጢአተኞች ላይ እንደሚፈርድ ይናገራሉ፣ ነገር ግን ኢዮብ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ጻድቁንም ሆነ ኃጢአተኛውን ሁለቱንም ያጠፋል ይላል:: ክፉ የሆኑ ዳኞች በጻድቃን ላይ ይፈርዳሉ ደግሞም በመልካም መንገድ የማይሄዱትን ሰዎች ይረዳሉ፣ ደግሞም ይህን በተመለከተ እግዚአብሔር ፈጥኖ የሚያደርገው ነገር የለም:: ኢዮብ እራሱንና ቤተሰቡን ብቻ በተመለከተ ሳይሆን፣ ነገር ግን በምድሪቱ ላይ የሚኖሩ ሌሎች ንጹሐን ሰዎችን ሁኔታ ጭምር በተመለከተ እግዚአብሔርን በኢፍትሐዊነት ላይ ስለማይወስደው እርምጃ ይከሰስ ነበር::

ሐ. *«ደስተኛ ለመሆን ብሞክር፣ ምን መልካም ነገር ይኖራል?» (ቍ. 25-31)::* ልክ ወደ ተላኩበት ለመድረስ እንደሚቸኩሉ የንጉሥ መልእክተኞች፣ እንዲሁም ፈጠን ብለው በወንዙ ቍልቍል የሚወርዱት በግብፅ ያሉ የፓፒረስ ጀልባዎች፣ ደግሞም ከሰማይ ወደ ምድር ዥው ብለው እንደሚወርዱ ንስር አሞራዎች፣ ለኢዮብ ጊዜው በፍጥነት እየሄደበት ነበር:: ምናልባት ኢዮብ ለመከራው የበለጠ አዎንታዊ የሆነ ዝንባሌ ሊያሳይ፣ ሥቃዩን ሊረሳ፣ እንዲሁም ፈገግ ሊል ይገባዋል (ቍ. 27):: ነገር ግን በውኑ የሚለውጠው ነገር አለን? የለም! አሁንም በእግዚአብሔር ፊት በደለኛ ይሆናል፣ በወዳጆቹ የተጣለ፣ እንዲሁም በበሽታና በሥቃይ በዐመድ ላይ ይቀመጣል:: የመንጻትና በአደባባይ የሚደረግ የጸጸት ተግባር የሆነውን ታጥቦ ልብስ መለወጥን ቢያደርግ እንኳ፣ እግዚአብሔር ሊያደርገው ስላለ ነገር አሁንም በመፍራት ውስጥ መሆኑን ይቀጥላል:: ኢዮብ



ለግዚአብሔር በእርሱ ላይ እንደ ተነሣ ከዚህም በተነሣ ደግሞ እርሱ በምድር ላይ የሚወስደው የቱም እርምጃ በሰማይ ከንቱ (ባዶ) እንደሚደረግበት ወደ ማመኑ መጥቷል:: ተከሳሽ ፈገግ ሊል እንዲሁም በችሎት ስፍራ በድፍረት ሊቀርብ ይችላል፣ ነገር ግን ይህ ዳኛውን («በደለኛ ነህ!») ከማለት ሊከለክለው አይችልም::

*መ. «እኔ አማላጅ ብቻ ቢኖረኝ ኖሮ!» (ቍ. 32-35)::* እግዚአብሔር ሰው ቢሆን ኖሮ፣ እንግዲያውስ ኢዮብ ሊቀርበው እና ስለ ጉዳዩ አቤት ሊል ይችል ነበር:: ወይም በእግዚአብሔርና በኢዮብ መካከል ገላጋይ (አማላጅ) ቢኖር ኖሮ፣ እርሱ የፍርድን በትር ባነሣና ኢዮብና እግዚአብሔርን ባቀራረባቸው ነበር:: ነገር ግን እግዚአብሔር ሰው አይደለም፣ ደግሞም መካከለኛ/አስታራቂ የለም! *እዚህ ላይ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ትዕይንቱ ውስጥ ሊገባ የሚችለው!* ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው ደግሞም አብን ለመግለጥና (ዮሐንስ 14:7-11) ኃጢአተኞችን ወደ እግዚአብሔር ለማምጣት (1ኛ ጢሞ. 2:5-6፤ 1ኛ ጴጥ. 3:18) ሰው ሆነ:: እርሱ ኢዮብ ከሺህ ዓመታት በፊት ይፈልገው የነበረው ገላጋይ ዳኛ ነበር (ኢዮብ 16:21)::

**(3) «ስለ ምን ተወለድሁ?» (ኢዮብ 10:1-22)::** እዚህ ላይ የኢዮብ ክርክር እግዚአብሔር የፈጠረው ሕይወትንም የሰጠው (ቍ. 3፣ 8-12፣ 18-19) ሲሆን፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እርሱን ከፍጡራኑ እንደ አንዱ እየተመለከተው ያለመሆኑ ነው:: ኢዮብን በመሥራት ጊዜንና ጉልበትን ካወጣ በኋላ፣ እግዚአብሔር ኢዮብን እያጠፋው ነበር! በተጨማሪም፣ በእርሱ ላይ የቀረበው ክስ ምን እንደ ሆነ (ቍ. 2) እንኳ ሳይነግረው እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ እየፈረደበት ነበር:: ኢዮብ ቢቈጣ፣ ቢመረር እና ግራ ቢጋባ አያስደንቅም (ቍ. 1፣ 15):: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ኢዮብ በቀጥታ ለእግዚአብሔር እንጂ ለወዳጆቹ እንደማይናገር ልብ በሉ::

እግዚአብሔር እንደ ሰው ነገሮችን መመርመር እና ከጊዜ ጋር መሽቀዳደም የለበትም (ቍ. 4-6):: እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው ደግሞም ያሻውን ያህል ሰዓት ሊጠቀም ይችላል:: ደግሞም እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ስለሆነ ልክ በግል ወንጀልን እንደሚመረምሩ ባለሙያዎች ያለ ምርመራ ማድረግ አያስፈልገውም:: ኢዮብ ከዚህ ቀድሞ ዳኛ ይፈልግ ነበር (9:33)፣ ነገር ግን አሁን ነፃ

የሚያወጣውን (10:7) ለማግኘት ይጠይቃል። ስለዚህ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ የሚገኝ ጠባቂ ነው፣ እያንዳንዱንም የኢዮብን እንቅስቃሴ ይመለከታል (ቍ. 14)። ልክ እንደ አንበሳ በኢዮብ ላይ ያደባበታል (ቍ. 16) እንዲሁም በሠራዊቶቹ ያጠቃዋል (ቍ. 17)። ኢዮብ ተከቧል፣ ደግሞም ምንም መውጪያ አልነበረም።

ስለዚህ የኢዮብ ጥያቄ ምክንያታዊ ይመስላል፦ «ታዲያ ለምን ከማኅፀን አወጣኸኝ?» (ቍ. 18)። የኢዮብ በምድር ላይ መኖር እጅግ ዓላማ-ቢስ ይመስላል፤ ሕይወቱ ከማለፉ በፊት ጥቂት የሰላምን የደስታ ጊዜ እንዲሰጠው እግዚአብሔርን ጠየቀ። ሕይወቱ በፍጥነት ስትጓዝ ማየት ችሎ ነበር (7:6-7፤ 9:25-26)፣ ደግሞም ሊባክን የሚገባው ጊዜ የለም። «ወደ ጨለማው ዓለም ከመሄዱ በፊት ትንሽ እጽናና ዘንድ ተወኝ» ብሎ ጸለየ።

ኢዮብ እግዚአብሔር እያደረገው የነበረውን ነገር መረዳት አልቻለም፣ ደግሞም መረዳት አለመቻሉ አስፈላጊ ነገር ነበር። እግዚአብሔር ሰይጣንን ለማሸነፍ እርሱን እንደ መሣሪያ እየተጠቀመበት እንደ ሆነ ኢዮብ ቢያውቅ ውጊያው እስኪያልቅ ድረስ በመታመን ቁጭ ብሎ ይጠባበቃል። ነገር ግን ኢዮብ እራሱንና ሁኔታዎቹን ሲቃኝ ማርያም ጌታን ሽቱ በቀባችው ጊዜ፦ «ስለ ምን ይህን ማባከን አስፈለገ?» ብለው ደቀ መዛሙርቱ የጠየቁትን ዓይነት ጥያቄ ጠየቀ (ማር. 14:4)። እጅግ ክፉኛ ኢዮብን ከመተቸታችን በፊት፣ ሕፃን ልጅ በሚሞትበት ጊዜ ወይም ተስፋ ያለው ወጣት ሰው በመኪና አደጋ በሚሞትበት ወቅት ምን ያህል ጊዜ ይህን ጥያቄ እንደ ጠየቅን እናስታውስ።

*በእምነትና በፍቅር ለክርስቶስ የተሰጠ የቱም ነገር ከቶ አይባክንም። ማርያም ኢየሱስን የቀባችው ሽቱ መዓዛ ከምእተ ዓመታት በፊት ተንኖ ጠፍቷል፣ ነገር ግን የአምልኮዋ ጉልህነት በሁሉም ዘመን ያሉ ክርስቲያኖችን ይባርካል እንዲሁም ይህን ማድረጉን ይቀጥላል።* ኢዮብ በኪሣራና በሕመም ውስጥ ነበር፣ ደግሞም ለጌታ ሊሰጠው የሚችለው ነገር በመከራው ውስጥ በእምነት መመላለስ ብቻ ነበር፤ *ነገር ግን ያ ሰይጣንን ጸጥ ለማሰኘት እግዚአብሔር የሚፈልገው ነገር ነበር።*

ዊሊያም ኋይቲንግ ቦርደን (እ.ኤ.አ) በ1913 ዓ.ም ወንጌል ወደሚያዳርስበት ጣቢያ ሲሄድ ግብፅ ውስጥ በሞተ ጊዜ፣ አንዳንድ



ሰዎች፣ «ይህ መባከን ስለ ምን አስፈለገ?» በማለት ሳይጠይቁ አልቀሩም። ነገር ግን እግዚአብሔር አጭር የሆነውን ሕይወቱን በመጠቀም ሰዎች ያላቸውን ሁሉ ለክርስቶስ እንዲሰጡ አሁንም እየተጠቀመበት ነው።

ጆን እና ቤቲ ስታም በ1934 ዓ.ም በቻይና ሰማዕት በሆኑበት ጊዜ፣ «ይህ ማባከን ስለ ምን አስፈለገ?» በማለት የሚጠይቁ ጥቂት ሰዎች ነበሩ። ነገር ግን በሚስ ሀዋርድ ቴይለር *«ዘ ትራይምፍ ኦፍ ጆን ኤንድ ቤቲ ስታም»* በሚል ርእስ የተጻፈው መጽሐፍ ከታተመበት ከ1935 ዓ.ም ጀምሮ ሕይወትን የሚለውጥ መጽሐፍ ሆኖአል። እጮኛዬ (የአሁንዋ ባለቤቴ) በሃያ አንደኛው የልደት በዓሌ ላይ አንድ ቅጅ ሰጠችኝ፣ የመጽሐፉም መልእክት አሁንም ድረስ ልቤን ይነካዋል።

አምስቱ የወንጌል መልእክተኞች በኤኳዶር አውካ ኢንዲያንስ በሚባሉ ጎሳዎች እጅ በተሠዉበት ጊዜ፣ አንዳንዶች ክስተቱን «አሰቃቂ የሆነ የሰው ኃይል ብክነት» ብለውታል። ነገር ግን እግዚአብሔር በተለየ መልኩ አስቦታል፣ ደግሞም የእነዚህ አምስት የእምነት ጀግኖች ታሪክ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያንን እያገለገለ ነው።

ኢዮብ፣ «ስለ ምን ተወለድሁ?» ሲል ጠየቀ። ያጣቸውን ነገሮችና በግልም የተቀበለውን መከራ ከግምት ባስገባ እይታ ስንመለከተው፣ ሁሉም ነገር ከንቱ የሆነ ብክነት ይመስላል! ነገር ግን እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ ምን እያደረገ እንዳለ ከዚያም በኋላ ምን እንደሚያደርግ ያውቅ ነበር።

«ኢዮብ እንዴት ታግሦ እንደ ጸና ሰምታችኋል፤ ጌታም በመጨረሻ ያደረገለትን አይታችኋል» ብሎ ያዕቆብ ጻፈ (ያዕቆብ 5:11)። ያንን ለኢዮብ ነግራችሁት ቢሆን ኖሮ፣ ባላመነውም ነበር፤ ግን ነገሩ አሁንም እውነት ነው።

ይህ ለእርሱ እውነት ነበር፣ ደግሞም ዛሬ ለእኛም እውነት ነው።

እመኑት!

# ለግል ምልከታና ለቡድን ውይይት
# የተዘጋጁ ጥያቄዎች

1. በልዳዶስ በሥነ አመክንዮ ንግግር በኩል ኢዮብን ሊያጽናናው ሞከረ። በተሞክሮአችሁ መጽናናት በምትፈልጉበት ሁኔታ ውስጥ ሳላችሁ ሥነ አመክንዮታዊ ንግግሮች እንዴት ጉድተዋችኋል?

2. ስለ እግዚአብሔር ፍትሐዊነት ያስተማሯችሁ በሕይወታችሁ ያገኛችኋቸው ተሞክሮዎች ምንድን ናቸው?

3. በልዳዶስ ካለፉት ዘመናት በወሰዳቸው የጥበብ ንግግሮች ኢዮብን ለማጽናናት ሞከረ። አንዳንድ ጊዜ እነዚያን ጥበባዊ ንግግሮች «መፈክሮች» እንላቸዋለን። ሰዎች በመከራዎች ውስጥ በሚያልፉ ጊዜ፣ የትኞቹ ዓይነቶች መፈክሮች ወይም አጠቃላይ የሆኑ ጥበባዊ ንግግሮችን ነው አንዱ ለሌላው የሚጥልለት?

4. የበልዳዶስ መሠረታዊ ክርክር፣ «አንድ መጥፎ የሆነ ነገር እየተ ከሰተብህ ነው፣ ስለዚህ አንድ መጥፎ የሆነ ነገር ሳትፈጽም አልቀረህም።» የሚል ነበር። በዚያ ክርክር ውስጥ ያለው ስሕተ ት ምንድን ነበር?



5. በልዳዶስ በእግዚአብሔር ፍትሕ ላይ ብቻ አተኮረ። እርሱ ዝቅ አድርጎ የተመለከታቸው የትኞቹን የእግዚአብሔር ባሕርያት ነበር?

6. ስለ መከራ የትኞቹን ጥያቄዎች ለእግዚአብሔር ታቀርባለህ፣ ኢዮብ እንደ ገለጸው ምስክሮችን ያቆማልን?

7. ማቴዎስ 5:44-45ን አንብብ። እግዚአብሔር በክፉዎችም ሆነ በመልካሞች ላይ አንድ ዓይነት ሁኔታን ቢልክ፣ ያ መከራን በተ መለከተ የሚሰጠን መረዳት ምንድን ነው?

8. መከራ ልክ ለኢዮብ የሚመስለውን ነው ለእኛም የሚመስለን - ይህም ከንቱ ለሆነ ነገር የጠፋን ያህል ነው የሚመስለን። መከራችን ለእግዚአብሔር የተለየ ሆኖ የሚታየው እንዴት ነው?

9. የሕይወት ተልዕኮአችንን መገንዘብ መከራን ከመቀበል ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

## የዕረፍት ጊዜ

በኢዮብ 9:33 «ዳኛ» በሚል የተተረጐመው የዕብራይስጡ ቃል ትርጕሙ እንደ ውሳኔ ያለ ድርጊትን መፈጸም ነው። «ዳኛ» የሚወዛገቡ ወገኖች በአንድ ላይ በሚመጡበት ጊዜ ውሳኔ በመስጠት ሁኔታውን ሰላማዊ ለማድረግ ሥልጣን ያለው ሰው ነው። በምሥራቅ አገሮች ለጥያቄው መፍትሔ የሚሰጥ እርሱ መሆኑን ሊያስታውሳቸው ዳኛው በሁለቱ የሚከራከሩ ሰዎች ራስ ላይ እጆቹን ያስቀምጣል (ይጭናል)። ኢዮብ በእርሱና በእግዚአብሔር ላይ እንዲህ የሚያደርግ ዳኛ ለማግኘት ናፈቀ።

ምንም እንኳ የሚወክለው ማንም ባይኖረውም፣ ኢዮብ እግዚአብሔርን በችሎት ላይ ለመግጠም በመፈለጉ ረገድ ክልቡ ነበር። «ነገር ግን ሁሉን ከሚችል አምላክ ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ፤ ከእግዚአብሔርም ጋር መዋቀስ እሻለሁ» (13:3)። «ቢገድለኝም እንኳ በእርሱ ተስፋ አደርጋለሁ፤ ስለ መንገዴም ፊት ለፊት እከራከራዋለሁ» (ቊ. 15)። «እንግዲህ ጕዳዬን ይገፍ ቀርቤአለሁ፤ እንደሚፈርድልኝም አውቃለሁ» (ቊ. 18)። እግዚአብሔር በፍትሕ እንዳልያዘው ተሰምቶታል። «ተበደልሁ ብዬ ብጮኽ ምንም አይመስለኝም» (19:7)። እግዚአብሔር «መብቱን» ወስዶበታል (27:2)፣ ደግሞም በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት የመሰማት ዕድል እንዲፈጠርለት ፈልጓል። ነገር ግን ዕድሉ በተፈጠረለት ጊዜ፣ ኢዮብ የሚናገረው ምንም ነገር አልነበረውም።





## «የተቈጣ ወጣት»

### (ኢዮብ 11-14)

«ለምን እንደምሠቃይ ለማወቅ የምሻ አይደለሁም፣ ነገር ግን ለማወቅ የምሻው ስለ አንተ መሆኑን ነው።»

- ቤርዲቻራዊው ሌቪ ይትዝሃቅ

የኢዮብ ሦስቱ ጓደኞች ሽማግሌዎች ነበሩ፣ ሶፋር ከሁላቸው ትንሹ ነበር። ስለዚህም ነበር ሶፋር በስተ መጨረሻ ይናገር የነበረው። የመጀመሪያ ንግግሩ ረጅም አልነበረም፤ ነገር ግን በእርዝመት ያልታየው ነገር፣ ለጥላቻ የሚያነሣሣ ነበር፣ ምክንያቱም ሶፋር መናደዱን ይገልጥበታል። ጽድቅ ያለበትን ቍጣ መግለጫ ተገቢ የሆነ ጊዜና ስፍራ አለ (ኤፌ. 4:26)፣ ነገር ግን ኢዮብ የተቀመጠበት የዐመድ ቁልል ስፍራው አይደለም፣ ደግሞም ትክክለኛው ጊዜ አይደለም። «የሰው ቍጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራም» (ያዕቆብ 1:20)። ለኢዮብ የሚያስፈልገው ነገር ፊቱን በጥፊ መምታት ሳይሆን፣ የሚረዳው እጅ ነበር።

ሶፋር በኢዮብ ላይ ሦስት ክሶችን አቀረበ፦ ኢዮብ ኃጢአትን ሠርቷል (ኢዮብ 11:1-4)፤ ኢዮብ እግዚአብሔርን አያውቅም (ቊ. 5-12)፤ ደግሞም ኢዮብ ንስሐ ለመግባት እንቢ ብሎ ችክ ብሎ ነበር (ቊ. 13-20)። በምላሹ፣ ኢዮብ ለሦስቱም ክሶች መልስ ሰጠ፤ የእግዚአብሔርን ታላቅነት አስመልክቶ አጽንቶ ተናግሮአል (ኢዮብ 12)። እንዲሁም የገዛ እራሱን ንጽሕና (ኢዮብ 13) ተናግሮአል፣ ነገር ግን እርሱ ምንም ተስፋ አልነበረውም፣ ስለዚህ ስለ ምን ንስሐ መግባት ግድ ይለዋል (ኢዮብ 14)?

## የሶፋር ሦስት ክሶች (11:1-20)

ኤልፋዝ እና በልዳዶስ ሲከሱት ከሰማ በኋላ፣ ሶፋር በአዲስ አቀራረብ ለመቅርብ በቂ የሆነ መረዳትም ሆነ ርኅራኄ ሲኖረው የተገባ ነበር። እግዚአብሔር የቱንም ነገር ያድርግ ወይም ጓደኞቹ የቱንም ነገር ይናገሩ፣ ኢዮብ ታማኝነቱን ጠብቋል፣ ስለዚህ ያንን ውይይት መቀጠል ለምን አስፈለገ? የሚያገለግሉ ሰዎች የአገልግሎታቸው መጨረሻ ኀዘንን ማምጣት በሚሆንበት ጊዜ ምንኛ ያሳዝናል። «ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ፣ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ» (ሮሜ 12:15) የሚለው ሊከተሉት የሚገባ መልካም ምክር ነው።

**(1) ኢዮብ ኃጢአተኛ (በደለኛ) ነው (ኢዮብ 11:1-4)።** ልክ እንደ በልዳዶስ ሁሉ (5:2)፣ ሶፋርም እንደዚሁ ንግግሩን የጀመረው ኢዮብን «በነፋስ የተሞላ ቦርሳ» ብሎ በመጥራት ነው። እነዚህ ሦስት ጓደኞቹ ከንግግሩ በስተጀርባ ባለ ስሜት ላይ ከማተኮር ይልቅ፣ በንግግሩ (ቃሎቹ) ላይ ማተኮራቸው ምንኛ አሳዛኝ ነበር። አንድ የቻይና ምሳሌአዊ አነጋገር እንደዚህ ይላል፡- «ምንም እንኳ ፊት ለፊት ተገናኝተው ቢነጋገሩም፣ ልቦቻቸው አንድ ሺህ ማይል ያህል ተራርቀዋል።» ይህም በዚያ የዐመድ ቁልል ምን ያህል እውነት ነው! ለነገሩ፣ መረጃ ከመግባባት ጋር አንድ አይደለም። ሲድኔ ጄ. ሀሪስ እንዲህ ሲል ያስታውሰናል፡- «መረጃ ማስወጣት ነው፣ መግባባት ግን በውስጥ ማለፍ ነው።»

የኢዮብ ንግግር ብዙ ንፋስ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ሐሰትም ማሾፍም ጭምር ነበር። ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር የተናገራቸው ነገሮች እውነት አልነበሩም፣ ስለዚህ ሳያስቡ ዝም ብለው ከሚናገሩ ሰዎች ንግግር ጋር ብቻ የሚመሳከር ነበር። ደግሞም ኢዮብ ስለ እራሱ የሚናገረው ነገር የለየለት ውሸት ነበር፣ ምክንያቱም እርሱ በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ አይደለምና። ታማኝነቱን በመጠበቅ፣ ኢዮብ እርሱ ኃጢአት-አልባ፣ ማለትም በእርግጠኝነት እውነት ያልሆነ ኃጢአት-አልባነቱን አስመልክቶ ፍንጭ ሰጥቶ ነበር (6:30፤ 9:20-21፤ 10:7 ተመልከት)።

**(2) ኢዮብ እግዚአብሔርን አያውቅም (ኢዮብ 11:5-12)።** በቁጥር 5 ላይ የሶፋር ጥያቄ እግዚአብሔር በተገለጠ ጊዜ ተመለሰ (38:1)፤ ነገር ግን በኋላ በእግዚአብሔር የተገሠጹት ሶፋር እና ሁለቱ ጓደኞቹ ነበሩ እንጂ፣ ኢዮብ አልነበረም! ኢዮብ



እውነቱን ስለ ተናገረ እግዚአብሔር አመስግነው። አንተ ልታውቀው የምትሻውን ነገር እንዲያሳይህ ፈቃደኛ ካልሆንህለት በስተቀር፣ ለሌሎች በምትናገርበት ጊዜ ምን ሊያውቁ እንደሚገባቸው እግዚአብሔርን መጠየቅ እንዳትረሳ ተጠንቀቅ። ሶፋር፣ ኢዮብ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ጥበብ ከፍታ፣ ጥልቀት፣ ስፋት እንዲሁም ርዝመት እንዲጨብጥ ፈለገ (11:8-9)። ይህን በማለቱም እርሱ ቀድሞውኑ ሰፊ የሆኑ ፈርጆች (አቅጣጫዎች) ያሉትን የእግዚአብሔርን ጥበብ እንዳወቀው፣ ደግሞም የሚያደምጠው ከሆነ፣ ኢዮብን ሊያስተምረው እንደሚችል ፍንጭ ሰጠ። ሶፋር ሰፊ የሆነ የእግዚአብሔርን ፍቅር ፈርጆች (አቅጣጫዎች) አለማወቁ (ኤፌ. 3:17-19) እንዲሁም ጥቂት ፍቅርን ለኢዮብ አለማካፈሉ እጅግ የከፋ ነገር ነው።

ሶፋር የእግዚአብሔር ጥበብ ምሥጢራት «ብዙ» (ኢዮብ 11:6) ብሎ በተናገረበት ጊዜ፣ ምን ማለቱ ነበር? የእግዚአብሔር ጥበብ ሙሉና ፍጹም (ኢሳ. 40:2) ነው፣ ወይም እግዚአብሔር ኢዮብ ስለ እርሱ ከሚያስበው ሁለት እጥፍ የሆነ ጥበብ አለው ማለት ነው። አዲሱ መደበኛ ትርጉም እንዲህ ይላል፣ «እውነተኛ ጥበብ ባለ ብዙ ፈርጅ ናትና» (ኢዮብ 11:6)። እኛ የምንመለከተው ትንሽ ክፍል (ገጽታ) አለ ደግሞም እግዚአብሔር ብቻ ሊመለከተው የሚችል ትልቅ ክፍል (ገጽታ) አለ።

እግዚአብሔር ሁሉን የሚያውቅ ስለሆነ፣ ስለ ኢዮብ ሁሉንም ነገር ያውቃል ደግሞም ካደረገው በላይ ሊቀጣው ይችላል። «የባሰ ሊሆን ይችል ነበር!» የሚለው ቤተሰቡን፣ ብልጥግናውን እንዲሁም ጤንነቱን ላጣ ሰው የሚሰጠው መጽናናት አይኖርም። ምርቶችን በገበያ ማዕከላት በምትመዝኑበት መልኩ መከራን ከብዛት አንጻር መመዘን አትችሉም። እርሱ ስላለበት ሁኔታ የኢዮብ ጓደኞች በማንጓጠጥ የሚናገሩበት ሁኔታዎች ግንዛቤ የጐደላቸው መሆናቸውን ያሳያል። «ኀዘኑ እየጠለቀ በሄደ ቁጥር፣» ይላል የአይሁዶች ታልሙድ፣ «ምላሱ ይቀንሳል።»

በቁጥር 7 ላይ ያሉት ሁለቱ ጥያቄዎች አሉታዊ መልስን ይጠብቃሉ። ምንም ሰው «የእግዚአብሔርን ምሥጢር መለካት» ወይም «ሁሉን የሚችለውን አምላክ መመርመር» አይችልም

(ኢ.መ.ት)። በእርግጥ፣ ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር አውቃለሁ አላለም፤ ነገር ግን የሚያውቀው ነገር ታማኝነቱን እንዲጠብቅ እንዲሁም ተስፋ እንዳይቈርጥ አበረታትቶታል።

እግዚአብሔር ለእኛ ተጠያቂነት ያለበት አይደለም። እርሱ የመረጣውን ሰው መያዝና ማሰር፣ ችሎት መሰየምና ፍርድ ማስተላለፍ ይችላል፣ ደግሞም ምንም ሰው የተቃውሞ ቃል መናገር አይችልም (ቊ. 10፤ ደግሞም 9:12 ተመልከት)። እግዚአብሔር የቱ ጠቢብ የቱ ሰነፍ፣ የቱ ንጹሕ የቱ ኃጢአተኛ እንደ ሆነ ያውቃል። እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ ፍርድን ስላስተላለፈ፣ ኢዮብ ኃጢአተኛ መሆን አለበት።

ሶፋር ክሱን የሚዘጋው አንድ ጥቅስን በመጥቀስ ነው (11:12)። ትርጕሙን በእርግጠኝነት መናገር ቀላል አይደለም። ሰው የቱንም ያህል በሚወለድበት ጊዜ፣ እንደ የሜዳ አህያ፣ ምንም የማይገባው ቢሆን እንኳ፣ አዋቂ የመሆን ተስፋ አሁንም አለው። ወይም ምናልባ ው ልክ አዲሱ መደበኛ ትርጒም እንደሚናገረው ተቃራኒውን የሚገልጽ ሳይሆን አይቀርም፦ «ጅል ሰው ጥበበኛ ከሚሆን ይልቅ፣ የሜዳ አህያ ሰው ሆኖ ቢወለድ ይቀላል።» ደግሞም የቀድሞው (የ1954ቱ ትርጒም) እንዲህ በሚል ይስማማል፣ «የሜዳ አህያ ግልገል ሰው ሆኖ ቢወለድ፣ ያን ጊዜ ከንቱ ሰው ጥበብን ያገኛል።» የሶፋርን ቊጣ እና የስድብ ቋንቋ ከግምት ስናስገባ የአዲሱ መደበኛ ትርጒምና የ1954ቱ ትርጒም ትክክለኞች እንደ ሆኑ እንረዳለን።

**(3) ኢዮብ ችክ ያለ ሰው ነው፣ ንስሐ መግባትም ይገባዋል (ኢዮብ 11:13-20)።** «ተስፋ አለ!» የሚለው ሶፋር ለኢዮብ ያቀረበው የመጽናኛ ቃል ነው (ቊ. 18)፣ ደግሞም እየገለጸ የነበረው ኢዮብ ሊለማመደው የሚችለውን ነገር ነበር። እግዚአብሔር በተትረፈረፈ ሁኔታ ሊባርከው ይችላል፣ ችግሮቹም ይጠፋሉ (ቊ. 15፤ 10:15)። ውኃ ከግድቡ ወጥቶ እንደሚያልፍ እንዲሁ መከራውን ይረሳል (11:16)። እግዚአብሔር ረጅም የሆነ የሕይወት ዘመንን ይሰጠዋል፣ ይህም ደግሞ አዲስ ቀን የሚያይበት ይሆንለታል (ቊ. 17)። በብርሃን ውስጥ እንጂ፣ በሲኦል ጨለማ ውስጥ አይኖርም (10:20-22)፤ ደግሞም የእግዚአብሔር ጥበቃ ፍርሃቶቹን ሁሉ ያስወግድለታል።

ነገር ግን ኢዮብ እነዚህን ነገሮች የሚፈልጋቸው ከሆነ፣ ሶፋር



በሚለው መንገድ ሊያገኛቸው ግድ ነው። አዎን፣ ከእርሱ ጋር ከተገናኘ ቅድመ-ሁኔታ ጋር ተስፋ አለ፤ ኢዮብ ንስሐ ሊገባና ኃጢአቱን ሊናዘዝ ያስፈልጋል (ቊ. 13-14)። *ካለበት ነገር ሁሉ መውጣት ይችል ዘንድ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲደራደር ሶፋር ኢዮብን እየፈተነው ነው።* ይህ ደግሞ በትክክል ኢዮብ እንዲያደርገው ሰይጣን የሚፈልገው ነገር ነው! «በውኑ ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራው በከንቱ ነውን?» ሲል ሰይጣን ጠይቆ ነበር (1:9)። ሰይጣን ለመታዘዝ የብልጥግናን ተስፋ ሊሰጠው የሚችል «የንግድ እምነት» አለው። ብሎ ኢዮብን ከሶት ነበር። ኢዮብ የሶፋርን ምክር ተቀብሎ ቢሆን ኖሮ፣ በቀጥታ በጠላት እጅ ውስጥ ይወድቅ ነበር።

ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲደራደሩ «የንግድ እምነት» አልነበረውም። «ቢገድለኝም እንኳ እርሱን በትዕግሥት እጠባበቃለሁ» (13:15)። ይህ ደግሞ ከችግሮች ውስጥ ለመውጣት ቀላል መንገድን የሚሻ ሰው ድምፅ (ንግግር) አይመስልም። «ኢዮብ ጌታ የሚሠራባቸውን ወቅቶች አያውቅም ነገር ግን በመልካምነቱ መጽናቱን ቀጠለ፣» በማለት ሲ. ኤች. ስፐርጀን ተናግሮአል።

## የኢዮብ ሦስት ማረጋገጫዎች (12-14)

የሶፋር ንግግር አጠር ያለ ነበር፣ ነገር ግን የሶፋርን ጥያቄዎች አንድ በአንድ ለመመለስ ለኢዮብ ረጅም ጊዜ ወስዶበታል። ኢዮብ እርሱ ስለ እግዚአብሔር እንደማያውቅ ሶፋር ባቀረበው በሁለተኛው ክስ ላይ መናገር ጀመረ (ኢዮብ 11:5-12)። እነርሱ እንዳላቸው ሁሉ እንዲሁ እርሱም እውቀትና መረዳት እንዳለው ኢዮብ አረጋገጠላቸው (ኢዮብ 12)። ከዚያም ኢዮብ በደለኛ የሆነ ኃጢአተኛ ስለ መሆኑ (11:1-4) ሶፋር ላቀረበው የመጀመሪያ ጥያቄ ምላሽ ሰጠ። ኢዮብ በድጋሚ ታማኝነቱን አጸና (ኢዮብ 13)። ከዚያም ኢዮብ የሶፋርን ሦስተኛ ክስ፣ ማለትም አሁንም ተስፋ አለ የሚለውን (11:13-20)፣ አጣብቂኝ ውስጥ በመጨመር ንግግሩን ደመደመ። በኢዮብ 14፣ ኢዮብ ተስፋው መትነኑን ተቀበለ።

**(1) የእግዚአብሔር ታላቅነት (ኢዮብ 12)።** በመጀመሪያ፣ ኢዮብ ከእርሱ ይልቅ እነርሱ ብዙ እውቀት እንዳላቸው የተናገሩበትን

የጓደኞቹን አሳብ አጣብቂኝ ውስጥ ጨመረው:: እውነት ነው፣ በዕድሜ ከኢዮብ የሚበልጡ ታላላቆቹ ነበሩ፤ ነገር ግን ዕድሜ ለጥበብ መኖር ዋስትና አይደለም:: የወጣቶች ጅሎች እንዳሉ ሁሉ፣ የሽማግሌዎች ጅሎችም እንዲሁ አሉ::

ከዚያም፣ ኢዮብ የእርሱ ስሜት ሊሰማቸው ባለመቻሉ እንዲሁም እርሱን መሳለቂያ ስለ ማድረጋቸው ገሠጻቸው:: እርሱ ጻድቅና ቅን እንደ ሆነ ይሰማዋል፣ ይህም ደግሞ እግዚአብሔር ስለ ኢዮብ የተናገረበት መንገድ ነው (1:1፤8፤ 2:3):: «የደላቸው በመከራ ያፌዛሉ፤ እግሩ የተንሸራተተውንም ይገፈትራሉ:: የቀማኞች ድንኳን አይታወክም፤ አምላካቸውንም በእጃቸው ይዘው አይዞሩም፣ እግዚአብሔርንም እያስቈጡ በሰላም ይኖራሉ» (12:5-6):: ሶፋር ጥበብ ለሰው ቅርብ አይደለችም ብሎ ተናግሮ ነበር (11:7-9)፣ ነገር ግን ኢዮብ የእግዚአብሔር ፍጥረታት ሊያውቁት የሚስፈልጓቸውን ነገሮች ሊያስተምሩዋቸው እንደሚችሉ ተናገረ (12:7-11፤ ዘፍጥ. 1:26-28 ተመልከት):: የእግዚአብሔር እጅ ሁሉንም ነገር እንደ ሠራ ደግሞም ሁሉንም ነገር ደግፎ እንደ ያዘ «ያልሠለጠኑ» እንስሳት እንኳ ያውቃሉ:: በእርግጥ፣ ኢዮብን ለመክሰስ የሚጠቀሙበት ያው እስትንፋሳቸው ለእነርሱ የተሰጠ የእግዚአብሔር ስጦታ ነበር፣ ደግሞም ያለ ፈቃዳቸው ሊያስወግደው ይችላል:: እግዚአብሔር ለወንዶችና ለሴቶች ምግብን ቀምሰው የሚያጣጥሙበትን ችሎታ ሰጣቸው:: ቃሎችን ለመገምገም እንዲሁም እውነትን ለመለየት የበለጠ ችሎታ እንኳ አይሰጣቸውምን (ኢዮብ 12:11)?

በቍጥር 12-25፣ ኢዮብ የእግዚአብሔርን ጥበብና ኃይል ይዘረዝራል:: ቍጥር 12 እግዚአብሔርን የሚጠቅስ ይመስላል፣ ይህም «ከጥንት የነበረው» «ረጅም ዘመናትን የኖረው» በሚል ተገልጾአል:: እነዚህን የመለኮት ስሞች የተሞክሮ ዘመናቸው እጅግ ብዙ እንዳስተማራቸው የሚያስቡትን የዕድሜ ባለጸጋ የሆኑትን የኢዮብን ጓደኞች የሚገሥጹ ናቸው!

ኢዮብ እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ በሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ባለ ሥልጣን (ቍ. 14-15) እንዲሁም በሰዎች ላይ የሚያደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ (ቍ 16-25) ነቅሶ አወጣ:: እርሱ ያፈረሰው ነገር ተመልሶ ሊገነባ አይችልም፣ እርሱ



የቈለፈው ነገር መከፈት አይችልም (ራእይ 3:6-8):: እርሱ ጽድቅን ወይም ጕርፍን ሊልክ ይችላል፣ ደግሞም ማንም ሰው ሊገታው አይችልም (ኢዮብ 12:15):: የሚያደርገውን ነገር የሚያሳውቀው ጥበብ አለው፣ ደግሞም ሊያከናውነው ኃይሉ አለው (ቍ. 13፣ 16)::

በሰዎች ላይ ባለው የበላይነት፣ ደረጃቸው የቱም ይሁን፣ እግዚአብሔር ሁሉን የሚቈጣጠር ነው:: የኢዮብ ክርክር በሕይወት ውስጥ ያሉ ሁሉም ዓይነት ሰዎች አስቸጋሪ ሁኔታ ዎችን ይለማመዳሉ፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ደስ የሚያሰኘውን ነገር ማድረግ ይችላል:: እርሱ በሰዎች መካከል አያደላም፣ ደግሞም በሰዎች መካከል ፣ ሀብትና ምኅበረሰቡ ውስጥ ባላቸው ደ ረጃ ሥልጣን የሚደነቅ አይደለም::

ለምሳሌ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ፣ የንጉሥ አማካሪዎች ሥልጣናቸውንና ሀብታቸውን ሊያጡ ይችላሉ፣ ደግሞም ፈራጆች/ ዳኞች ሊነሆልሉና ሊያብዱ ይችላሉ:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የእራሳቸው የነገሥታት እስራት ይፈታል፣ (ይህም የሥልጣናቸው ምልክት ነው):: ደግሞም ካህናት («መሳፍንት» ቍ. 19) ይገለበጣሉ:: ደግሞም ምርኮኞች ይሆናሉ:: ልክ እንደ አማካሪ ዎችና ሽማግሌዎች ያሉ ጠቢባን ሰዎች ጸጥ እንዲሉ ይደረጋል (ቍ. 20)፣ ደግሞም ልዑላን እና ኃያላን (ቍ. 21) ክብራቸውንና ብርታታቸውን ያጣሉ::

ነገር ግን እግዚአብሔር በሕዝቦችም ሆነ በግለሰቦች ላይ ሉዓላዊ (የበላይ) ነው (ቍ. 23-25፤ ዳን. 2:20-22፤ የሐዋ. 17:24-28):: አንድን ሕዝብ (አገር) ሊያሳድገው ወይም ሊያጠፋው ይችላል፣ ወይም ነፃነት ሊሰጠው አሊያም በባርነት ሊተወው ሥልጣን አለው:: እርሱ ይህን ለማድረግ የሚወስደው እርምጃ ጥበብን ከመሪዎች በመንጠቅ ነው፣ ደግሞም የአገሩ/ሕዝቡ ጥፋት የተረጋገጠ ይሆናል:: ኩሩ ሕዝቦች ይህን መልእክት መስማት አይወድዱም:: ከሄኖክ ከተማ ጀምሮ (ዘፍጥ. 4:16-18) የባቢሎንን ግንብ ጨምሮ (11:1-9)፣ የሰው ልጅ ነገሮችን ከእግዚአብሔር ውጭ ለመገንባትና ለማስተዳደር እየሞከረ ቆይቷል፤ ፍጻሜው ግን ሁልጊዜ፣ ውድቀትና ፍርድ ሆኗል::

**(2) የኢዮብ ታማኝነት (ኢዮብ 13)::** በዚህ የመከላከያው

ክፍል፣ ኢዮብ በመጀመሪያ በሦስቱ ጓደኞቹ የተሰማውን *ተስፋ መቍረጥ* ይገልጻል (ቍ. 1-12)፣ ከዚያም በጌታ ላይ ያለውን እምነት *ዐወጀ* (ቍ. 13-17)፣ በመጨረሻም ደግሞ እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንዲመጣ እንዲሁም ጉዳዩ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲቋጭ ያለውን *ምኞት* ያቀርባል (ቍ. 18-28)::

*ብስጭት (ቍ. 1-12)::* የኢዮብ ጓደኞች ለእርሱ መጽናኛዎቹ አልነበሩም:: ከኢዮብ በተሻለ እግዚአብሔርን እንደሚያውቁ በማሰብ እንደ ዳኞች የላቀ ስፍራን ወሰዱ:: በኀዘኑና በሥቃዩ ከእርሱ *ጋ*ር አልቆሙም:: ኢዮብ «ሐሰትን የሚለብጡ»፣ «ጥቅም የሌላቸው ሐኪሞች»፣ እንዲሁም «አሳች በሆነ መልኩ ለእግዚአብሔር ጥብቅና የቆሙ» ብሎ ጠርቷቸዋል::

*የምትለብጡ* (ቍ. 4) የሚለው ቃል «የሚሸፋፍኑ» ማለትም ጭምር ነው:: ትውፊታዊ አሳባቸውን አጽንተው ሲጠብቁ ሳሉ አስቸጋሪ ዕንቆቅልሾችን ያስወግዱ ዘንድ በውይይታቸው (በንግግራቸው) ላይ የሕይወታቸው ሁኔታን ሐሰታቸውን ይሸፋፍናሉ [መዝ. 118 (119):69]:: አንድ ነገር ላይ ላዩን ይመለከቱታል ደግሞም ወደ እግዚአብሔር እውነት ጠልቀው አይገቡም ወይም የኢዮብን ስሜት በጥልቀት መረዳት አይችሉም:: ላይ ላዩን በሚደረግ ቅኝት ላይ የተመሠረተ ማማከር የሚፈይደው ኢምንት ነው:: ሰዎችን የምንረዳ ከሆነ፣ በጥልቀት መዝለቅ አለብን፤ ነገር ግን ይህ ፍቅርን፣ ድፍረትን፣ እና ትዕግሥትን ይጠይቃል::

ልክ እንደ ሐኪሞች፣ ያደረጉት ምርመራ ስሕተት ነበር፣ ስለዚህም ደግሞ መድኃኒታቸው ጥቅመ-ቢስ ነበር (ኤር. 6:14፤ 8:11):: ደግሞም «ለእግዚአብሔር ጥብቅና እንደ መቆማቸው»፣ ጸጥ ቢሉ ይሻላቸዋል፣ ምክንያቱም ስለሚነጋገሩት ነገር ምንም አያውቁምና:: እንደዚህ ያለ የተገደበና ጠባብ አስተሳሰብ (አመለካከት) ስለ እግዚአብሔር አሳቸው፣ ደግሞም ስለ ኢዮብ እንዲህ ያለው በእውነት ላይ ያልተመሠረተ አመለካከታቸው፣ ነገራቸውን ሁሉ የሐሰት ፋብሪካ እንዲሆን አድርጎታል:: እግዚአብሔር ገበታቸውን በሚገለብጥበትና በሚመረምራቸው ጊዜ ምንድን ነበር የሚሆኑት? (ሮሜ 14:1-13):: «ምሳሌዎቻችሁ የዐመድ ምሳሌዎች ናቸው፤ መከላከያችሁም የጭቃ ምሽግ ነው»



(ኢዮብ 13:12፣ አ.መ.ት):: ሦስቱ ጓደኞች ያስቡዋቸው የነበሩት የእውነትን መሠረታዊ አባባሎች ነው፤ እነዚህም የጥንት እሳቶች ከሚሞቁበት፣ ከሚሰባበሩ የሸክላ ዕቃዎች ዐመድ ብቻ የሚገኙ ነበሩ:: ጥሩ አማካሪ ከመልካም ትውስታ የሚበልጡ ብዙ ነገሮች ያስፈልጉታል:: እርሱ ወይም እርሷ ዛሬ ላሉ ሰዎች ፍላጎቶች እውነቱን እንዴት ማዛመድ እንደሚችሉ ለማወቅ ጥበብ ያስፈልጋቸዋል::

*አዋጅ* (ቍ. 13-17):: ይህ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከምናገኘው የእምነት አዋጆች ትልቁ ነው፣ ነገር ግን በእራሱ ዐውድ ሊረዱት ያስፈልጋል:: ኢዮብ እንዲህ እያለ ነበር፡- «ነገሬን በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር አቀርባለሁ ደግሞም ታማኝነቴን አረጋግጣለሁ:: እግዚአብሔርን በመቅረቤ ሕይወቴን በእጆቼ ላይ አድርጌአለሁ፣ ምክንያቱም እኔን ሊገድለኝ ይችላል:: ነገር ግን የማይጥለኝ ከሆነ ግብዝ እንደ ሆንሁ የተናገራችሁት ከንቱ ነው::» በኋላም፣ ኢዮብ መሐላ ያደርጋል ደግሞም ፍርድን እንዲያስተላልፍ እግዚአብሔርን አጥብቆ ይጠይቃል (ኢዮብ 27):: እግዚአብሔርን በግል መቅረብ ትልቅ የእምነት ተግባር ነው (ዘጸአት 33:20፤ መሳ. 13:22-23)፣ ነገር ግን ኢዮብ የሚያገኛቸውን መልካም ዕድሎች በመጠቀም ረገድ ያለውን ታማኝነቱን እርግጠኛ ነበር:: ለነገሩ፣ ምንም ባያደርግም፣ ይሞታል፤ ደግሞም በእግዚአብሔር የተጣለ ከሆነ፣ ይሞታል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የእርሱን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥበት ዕድል አለ::

*ፍላጎት (ቍ. 18-20)::* እነዚህ ቃሎች ለእግዚአብሔር የቀረቡ ናቸው:: ኢዮብ ነገሩን አዘጋጅቶአል (ቍ. 18፣ አ.መ.ት) ደግሞም እንደሚያሸንፍ እርግጠኛ ነበር:: ኢዮብ ሁለት ፍላጎቶች ነበሩት፡- እነርሱም የቅጣት እጁን እንዲያስወግድለትና ለእርሱ ዕረፍትን እንዲሰጠው፣ ደግሞም እንዲህ ባለ በማያስፈራ መንገድ እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንዲመጣ መፈለጉ ነበር:: ኢዮብ በፍርድ ችሎት ላይ እንዲገናኙ፣ እግዚአብሔርም በኢዮብ ላይ ያለውን ነገር እንዲያቀርብ፣ ኢዮብም በእግዚአብሔር ላይ ያለውን ነገር እንዲያቀርብ እየጠየቀው ነበር:: በቍጥር 22 ላይ፣ ኢዮብ በመጀመሪያ የመናገርን አማራጭ ለእግዚአብሔር ይሰጠዋል!

ኢዮብ እግዚአብሔርን ስለ ምንድን ነው በፍርድ ችሎት ሊያገኘው የፈለገው? እግዚአብሔር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በኢዮብ ላይ ያለውን ነገር እንዲያቀርብ ኢዮብም በሕይወቱ ያለና እንደዚህ ያለ ብዙ መከራ ለመቀበል ያደረገውን ኃጢአት ያውቅ ዘንድ ነው:: «እግዚአብሔር ስለ ምንድን ነው እጅግ በጣም የሚከታተለኝ?» ሲል ኢዮብ ጠየቀ:: «እንደ ጠላት ይመለከተኛል፣ ነገር ግን እኔ፣ በንፋስ ውስጥ ያለሁ፣ የቅጠል ግንጣይ፣ ለምንም ነገር የማይጠቅም ገለባ ነኝ:: እኔ የበሰበሰ እንጨት ቍራጭ እንዲሁም ብል የበላው ጨርቅ ነኝ፣ ይሁንና እግዚአብሔር እኔን እንደ ጦር ምርኮኛ ይመለከተኛል ደግሞም በየደቂቃው ይጠባበቀኛል::» በሂደቱ የገዛ ሕይወቱን እንኳ የሚያጣ ቢሆንም፣ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት ጊዜው እንደ መጣ ተሰምቶታል::

**(3) የኢዮብ ተስፋ ቢስነት (ኢዮብ 14)::** ኃጢአቱን በማወቅና ንስሐ በመግባት ብቻ ተስፋ እንዳለው ለኢዮብ ሶፋር አረጋግጦለታል (ኢዮብ 11:13-20):: ነገር ግን ሶፋር በኢዮብ ሁኔታ ውስጥ አልነበረም! ከኢዮብ አመለካከት አንጻር፣ የወደፊት ጊዜው ደማቅ አልነበረም:: ከቍጥር 1-12፣ በዚህ ዓለም የሰው ተስፋ-ቢስ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ብዙ ሥዕላዊ መግለጫዎችን በመጠቀም አሳይቷል:: እርሱ በቅርቡ እንደሚቈረጥ አበባ ነው፣ ቀስ በቀስ እንደሚጠፋ ጥላ ነው፣ በጊዜው የተቀጠረና በሌላ እንደሚተካ ቅጥረኛ ሰው ነው:: እግዚአብሔር የዘመናችንን ወሰን ያውቃል [7:1፤ 14:5፤ መዝ. (138) 139:16]:: እራስን መግደል የሞትን ቀን ያሳጥር ይሆናል፣ ነገር ግን ማንም ሰው እግዚአብሔር ለእርሱ/ለእርሷ ያበጀላቸውን ወሰን ማለፍ የለባቸውም::

ሰው አበባ፣ ጥላ እና አገልጋይ ብቻ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ስለ ምን ትኩረት ሰጠው? ሕይወት እጅግ አጭር ስለ ሆነች፣ የሰውን አጭር ዘመን የኀዘን እና የሥቃይ እንዲሆን እግዚአብሔር ለምን ይፈቅዳል? «ከእርሱ ራቅ ደግሞም ብቻውን እንዲሆን ተወው» በማለት ኢዮብ ይጸልያል (ኢዮብ 14:6፣ አ.መ.ት):: «አጭሩ ዘመኔ ከማለቁ በፊት ጥቂት የደስታ ጊዜ ይኑረኝ!» (አጠር ባለ መልኩ የተቀመጠ)::

የኢዮብ ጠንካራ የሆነ ሥዕላዊ መግለጫው ዛፍ ነው (ቍ. 7-12):: ቍረጡት፣ ሥሩ በውስጡ ይኖራል፣ ደግሞም ዛፉ እንደ ገና



የሚለመልምበት ዕድል አለ:: ለዛፉ ተስፋ አለ፣ ለሰው ግን የለም:: በሚሞትበት ጊዜ፣ የሚተወው ምንም ምልክት የለም:: ሰው እንደሚተንን እና ወደ መሬት እንደሚሰርግ ውኃ ነው፣ እንደገና ተመልሶ አይመጣም (ቍ. 11፤ 2ኛ ሳሙ. 14:14):: ሰው በምሽት ይተኛ ይሆናል ደግሞም በማለዳ ይነቃል፤ ነገር ግን ለሞት በሚተኛበት ጊዜ፣ እንደ ገና ለመንቃቱ ዋስትና የለውም::

እያንዳንዱ አማኝ ልክ እንደ ኢዮብ የወደፊቱን ሕይወት ምን እንደሚመስል የሚያሳይ አሁን እኛ በክርስቶስ እንዳለን ያለ መገለጥ የለውም (2ኛ ጢሞ. 1:10):: በብሉይ ኪዳን ያሉ አንዳንድ ምንባቦች ወደ ፊት ትንሣኤ እንዳለ ፍንጭ ይሰጣሉ (መዝ. 16:9-11፤ 17:15፤ ኢሳ. 26:19፤ ዳን. 12:2)፣ ነገር ግን ያነበባቸውና ይደነቅባቸው ዘንድ ከእነዚህ መጻሕፍት አንዳቸውም አልነበሩትም:: «በውኑ ሰው ከሞት በኋላ ተመልሶ ሕያው ይሆናልን?» (ኢዮብ 14:14):: ኢዮብ ይህን ጠቃሚ ጥያቄ ጠየቀ፣ ነገር ግን አልመለሰውም:: በኋላም፣ ኢዮብ ስለ መጪው ትንሣኤ አንድ ትልቅ ዓረፍተ ነገር ያበጃል (19:25-26)፤ ነገር ግን እዚህ ነጥብ ላይ በተስፋ መቍረጥና ተስፋ በማድረግ መካከል እየዋዠቀ ነው::

በ14:13፣ ኢዮብ ከሙታን ዓለም፣ ከሲኦል እንዲመልሰው ለእግዚአብሔር ማሳሰቢያን ሰጠ:: ምናልባት ኢዮብ ስለ ትንሣኤ እያሰበ አልነበረም፣ ነገር ግን በከሳሾቹ ፊት እግዚአብሔር ነፃ እንደሚያወጣው ለአጭር ጊዜ ወደ ምድር መመለስን እያሰበ ነበር:: በእርግጥ፣ ዛሬ አንድ አማኝ እስከ መቤዠት ቀን ድረስ በመንፈስ ቅዱስ የታተመ ነው (ኤፌ. 1:13-14)፤ ደግሞም እግዚአብሔር በትንሣኤ ቀን ከልጆቹ አንዱን አይረሳም (1ኛ ቆሮ. 15:50-58)::

ኢዮብ እርሱ የእግዚአብሔር እጆች ሥራ እንደ ሆነ ጌታን ያስታውሰዋል (ኢዮብ 14:15)፣ ይህም ከዚህ ቀደም ያቀረበው መከራከሪያ ነበር (10:3):: ለፍጥረቱ እንክብካቤ በማድረግ ፈንታ፣ እግዚአብሔር የእርሱን ኃጢአቶች ከመዘገብ በቀር፣ ምንም እንደማያደርግ ለኢዮብ የሚሰማው ይመስላል:: እግዚአብሔር እርሱን እስከ መረመረውና በእርሱ ላይ የጥፋተኝነት ማስረጃ እስካሰባሰበ ድረስ፣ ኢዮብ ምንም ዓይነት ተስፋ ሊኖረው ይችላል?

የኢዮብን ኃጢአት በማንጻት ፈንታ፣ እግዚአብሔር እየከደናቸው ነበር ደግሞም ምን እንደ ሆኑ ለኢዮብ እንኳ አይነግረውም!

«እንዲሁ የሰውን ተስፋ ታጠፋዋለህ» በማለት ኢዮብ አጉረመረመ (14:19)፣ ደግሞም ነጥቡን ለማስጨበጥ ሁለት ምሳሌዎችን ተጠቅሞአል። ሰው ጠንካራ ተራራን ይመስላል፣ ነገር ግን ውኃው ቀስ በቀስ ዐለቱን ይሸረሽረዋል፣ በመጨረሻም ደግሞ ተራራው ይናዳል። ወይም የመሬት መንቀጥቀጥ በድንገት ዐለቶቹን ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ ያንቀሳቅሳቸዋል ደግሞም ተራራውን ይለውጠዋል። ሞት ቀስ በቀስ ወይም በድንገት ሊመጣ ይችላል፣ ነገር ግን ይመጣል፤ እንዲሁም ሰው ቤተሰቦቹ ምን እያደረጉ እንዳሉ ምንም ነገር እስከማያውቅ ወደ ዓለም ይሄዳል። ኢዮብ ከዚያ ኀዘንና ሥቃይ ነፃ እንዲሆን አጥብቆ ተመኘ።

ሰዎች ኃይለኛ ኀዘንና ሥቃይ በሚሰማቸው ጊዜ፣ የወደፊቱ ጊዜ ተስፋ-ቢስ እና እግዚአብሔርም እነርሱን የጣላቸው ስለ መሆኑ በቀላሉ ይሰማቸዋል። ዝነኛው አሜሪካዊ የሥነ ልቡና ባለሙያ ካርል ሜኒንገር፣ ተስፋን «እራስን የመግደል ስሜት ዋና ጠላት የሆነ መሣሪያ» ብሎ ጠርቶታል። ተስፋ-አልባ ሰዎች ወደፊት የሚመለከቱት ነገር ስለሌለ፣ ነገር ግን የሚመለከቱት መከራንና ውድቀትን ስለሆነ፣ ሕይወት ሊኖሩት የሚያስችል ጥቅም የለውም የሚል ስሜት ይሰማቸዋል። ከመኖርና ለእራሳቸውም ሆነ ለሌሎች ሸክም ከመሆን ይልቅ መሞት ለእነርሱ የተሻለ ነው ሲሉ ይደመድማሉ።

ጀርመናዊው ፈላስፋ ፍሬድሪች ኒቼ ተስፋን «የሰው ልጆችን ሥቃይ የሚያስረዝም በመሆኑ፣ ከክፉዎች ሁሉ የባሰ ክፉ» ሲል ጠርቶታል። ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ግለሰብ በየዕለቱ የበለጠ አስደናቂ በሆነ ሁኔታ እያደገ በሚሄድ «ሕያው ተስፋ» ተካፋይ ይሆናል (1ኛ ጴጥ. 1:3።)

ሙት የሆኑ ተስፋዎች ይደበዝዛሉ፣ ምክንያቱም ሥር የላቸውም፣ ነገር ግን ሕያው የሆነ ተስፋችን እየታደሰ ይሄዳል፣ ምክንያቱም ሕያው በሆነው በክርስቶስ እና በሕያው ቃሉ ሥር የሰደደ ነው። የትንሣኤና በክርስቶስ ያለው የክብር ሕይወት ጉዞአችንን ለመቀጠል መጓዝ አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ እንኳ ለእኛ ጠንካራ የሆነ መነሣሣት ነው (1ኛ ቆሮ. 15:58)።



ቻርለስ ኤል. አለን እንዲህ ሲል ጽፎአል፣ «አንድ ሁኔታ ወይም ሰው ተስፋ-ቢስ ነው በምትሉበት ጊዜ፣ በእግዚአብሔር ፊት በሩን በኃይል እየዘጋችሁት ነው።» ኢዮብ ገና አሁንም በሩን አልዘጋም፣ ነገር ግን ወደ መዝጋቱ ተቃርቧል፤ ደግሞም ጓደኞቹ ከቶውንም አልረዱትም።

«የተስፋ አምላክ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተስፋ እንድትበዙ በማመናችሁ ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ» (ሮሜ 15:13)።

# ለግል ምልከታ ወይም ለቡድን ውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ዌርዝቢ እንዲህ አሉ፤ «መረጃ ከመገናኛ ጋር አንድ አይደለም።» ይህ እውነት ሶፋር በቀጥታ በኢዮብ ላይ ተነሥቶ በተናገረው ስሕተት ላይ እንዴት ተግባራዊ ይሆናል?

2. እርሱ አንዳንድ ጊዜ በእኛ ላይ መጥፎ ነገሮች እንዲመጡ የሚፈቅድ መሆኑን ካወቅን፤ በእግዚአብሔር ላይ የሚኖረን መተማመን ምንድን ነው?

3. ልክ እንደ ሶፋር፤ አንዳንድ ጊዜ እያንዳንዱን የእግዚአብሔርን አቅጣጫ የምናውቅ የሚመስለን ለምንድን ነው?

4. ከእግዚአብሔር ምሥጢራዊ ባሕርይ ጋር መገናኘትን ማጣት አደገኛነቱ ምንድን ነው?

5. እናንተ በሶፋር ስፍራ ብትሆኑ፤ ስለ እግዚአብሔር ለኢዮብ ምን ትሉታላችሁ?

6. ሲሠቃዩ ስላየሃቸው ሰዎች አስብ። ከሥቃያቸው ለመገላገል



በሚጸልዩበት ጊዜ (ኢዮብ እንዳደረገው)፤ ተስፋ የሚያደርጉቱ ምን ዓይነቱን መገላገልን ነው?

7. ኢዮብ ተስፋ ያደርግ የነበረው ምን ዓይነት መገላገልን ነው?

8. ሥቃይ በእውነት ከእግዚአብሔር የመጣ ቅጣት እንደ ሆነ እንዴት ልናውቅ እንችላለን?

9. ኢዮብ ለቀቢጸ ተስፋ ያልተበገረበትን ምክንያት እንዴት ታብራራዋለህ?

10. በመከራና በችግር ፊት እንኳ ቢሆን ተስፋችንን አጽንተን ለመያዝ ከእኛ የሚጠበቅ ነገር ምንድን ነው?

ምዕራፍ አምስት

# ውይይት ወደ ክርክር ተለወጠ

(ኢዮብ 15-17)

«ኀረቤታችንን የምንመዝንበት ሚዛን እራሳችንን ከምንመዝንበት ሚዛን ጋር አንድ ዓይነት የሚሆነው ከስንት አንዴ ነው፡፡»

- ቶማስ ኤ. ኬምፒስ

በዚህ በሁለተኛው ዙር ንግግር ወቅት፣ እነዚህ ሦስት ጓደኞች ኢዮብን ከመርዳት ይልቅ የኢዮብን ስሕተት ለማረጋገጥ ባደረጉት ትኩረት ላይ እሳቱ እየተጋጋለ ሄደ፡፡ ለነገሩ፣ የገዛ አእምሮ ሰላማቸው አደጋ ላይ ነበር፣ ይሁን እንጂ እጃቸውን ወደ መስጠቱ አልተቃረቡም፡፡ ኢዮብ በእግዚአብሔር እየተቀጣ ያለ ኃጢአተኛ ካልነበረ፣ እንግዲያውስ ሦስቱ ጓደኞቹ ስለ እግዚአብሔር የነበራቸው ግንዛቤ ሁሉ ስሕተት ነበር፡፡ *ነገር ግን ይህ በግለሰብ ላይ የሚመጣ መከራን በተመለከተ ለእራሳቸውም ምንም መከላከያ የላቸውም ማለት ነው!* መታዘዝ የጤናና የብልጥግና ዋስትና ካልሆነ፣ እንግዲያውስ በኢዮብ ላይ የደረሰው ነገር በእነርሱም ላይ ሊደርስ ይችል ይሆናል፡፡ አያድርስ ነው!

የማይታወቅ ቀልደኛ በአንድ ወቅት የሥነ መለኮት አዋቂን እንዲህ ሲል ገለጸው፡- «አንድ ዓይነ ሥውር በጨለማ ክፍል ውስጥ የሌለችን ጥቁር ድመት ፍለጋ ውስጥ ገባ ደግሞም አገኛት!» ነገር ግን እውነተኛ የሥነ መለኮት አዋቂ በቃሉ ውስጥ፣ በታሪክ ውስጥ እንዲሁም በፍጥረት ውስጥ ባለ በእግዚአብሔር መገለጥ ውስጥ ይመላለሳል፤ ደግሞም የሚያስከፍለው ዋጋ የቱም ይሁን፣ በትሕትና እውነትን ይቀበላል፡፡

ሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች የሥነ መለኮት አዋቂዎች አይደሉም፤



ምክንያቱም፣ ሊያዩት የሚፈልጉትን የሥዕሉን አንድ ገጽታ ብቻ ተመልክተዋልና፡፡ በረጅሙ የባሕር ዳርቻ የሚኖረው ፈላስፋ፣ ኤሪክ ሆፈር እንዲህ ሲል ጽፎአል፣ «እኛ እጅግ ታላቅ ትኩረት የምንሰጣቸው ነገሮችን በተመለከተ የነጠረ እውቀትን ለመቀበል እናመነታለን፡፡» በተጨማሪም ደግሞ እጅግ የምንፈራቸውን ነገሮችም በተመለከተ ዝንባሌያችን እንዲሁ ነው፡፡

## ኤልፋዝ፡- ሁለት ማስጠንቀቂያዎች (ኢዮብ 15)

በመጀመሪያ ንግግሩ (ኢዮብ 4-5)፣ ኤልፋዝ ለኢዮብ መጠነኛ ርኅራኄን አሳይቶት ነበር፣ ነገር ግን በዚህ በሁለተኛው የንግግር ክፍለ ጊዜ ምንም ዓይነት ትዕግሥትም ሆነ፣ ርኅራኄን አታገኙም፡፡ ምንም አዲስ አሳብም አታገኙም፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው ደግሞም እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን መቅጣት ይኖርበታል የሚለውን የቀደመውን የኤልፋዝን የክርክር አሳብ ብቻ ተደጋግሞ ታገኙታላችሁ (5:17-19)፡፡ ሁለት ማስጠንቀቂያዎችን ለኢዮብ ይሰጠዋል፡፡

**(1) ኢዮብ ጥበብ ይጎድለዋል (ኢዮብ 15:1-16)፡፡** ኤልፋዝ ይህን እንዴት ሊያውቅ ቻለ? የመጀመሪያው ነገር፣ *የኢዮብን ቃል (ንግግር)* መስማቱ ነበር (ቍ. 1-6) ደግሞም ንግግሩ ከንፋስ በቀር ምንም እንዳይደል ደርሶበታል፡፡ የኢዮብ አሳቦች «ባዶ የሆኑ ስሜቶች» እና «ጥቅም-አልባ ቃሎች» ብቻ ነበሩ (ቍ. 2-3፣ አ.መ.ት)፡፡ የኢዮብ ቃሎች ሞቃታማ በሆነ የበረሃ ንፋስ ከተሞላ ሆድ የመጡ ብቻ ነበሩ (ዮናስ 4:8) እንጂ እውነተኛ ጥበብን ከተሞላ ሰው ልብ የሚወጡ አልነበሩም፡፡ ኤልፋዝ በክርክር ወቅት ጥቅም ላይ የሚውለውን ከጥናታውያን ሥልቶች አንዱን እየተጠቀመ ነበረ - ይህም የተቃዋሚዎችህን የመከራከሪያ አሳብ መርታት ካልቻልህ፤ የሚናገራቸው ቃሎችን በማጥቃት እጅግ ብዙ የሆነ «ባዶ ወሬ» ብቻ እንደ ሆኑ አድርጋቸው፡፡

ሳሙኤል ጆንሰን የአሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን የእንግሊዝ «የሥነ ጽሑፍ ንጉሥ» ነበር፣ ይህ ሰው ከጓደኞቹ ጋር ለሰዓታት ቁጭ የሚልና ስለ ሁሉም ርእስ ጉዳዮች የሚያወያይ ሰው ነበር፡፡ ነገር ግን ጆንሰን ትክክልም ይሁን ስሕተት ሁልጊዜ ክርክሩን ማሸነፍ ነበረበት፡፡ ገጣሚውና ቲያትር ደራሲ ኦሊቨር ጎልድ

ስሚዝ እንዲህ አለ፡- «ከጆንሰን ጋር ክርክር ማድረግ አይቻልም፤ ምክንያቱም ሽጉጡ አልተኮስ ካለው በሽጉጡ ሰደፍ መትቶ ይጥልሃል!» ኤልፋዝም ልክ እንደዚሁ ነበር።

ኤልፋዝ የኢዮብን ቃሎች ያደመጠ ብቻ አልነበረም፣ ነገር ግን *እነዚያ ቃላት ወዴት እንደሚመሩም ተመልክቶአል* (ኢዮብ 15:4)። «አንተ ግን እግዚአብሔርን መፍራት ታጣጥላለህ፤ አምልኮተ እግዚአብሔርን ትከለክላለህ» (ቍ. 4፣ አ.መ.ት)። እግዚአብሔር ሁልጊዜ ክፉዎችን አይቀጣም እንዲሁም ቅኖችን አይባርክም ሲል ሁሉም ሰው ልክ ኢዮብ እንደሚያምነው የሚያምን ከሆነ፣ እንግዲያውስ ሰዎች እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የሚኖራቸው ውስጣዊ አሳብ ምንድን ነው? ሃይማኖት ምንም ጠቃሚ አይሆንም! *ነገር ግን ይህ የዲያብሎስ ሥነ መለኮታዊ አስተምህሮ ነው፣ እግዚአብሔር ኢዮብን በመጠቀም የሚዋጋው ዋነኛ ነገር ይህንን ነበር!* ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያገለግሉት ከዚያ ለሚያገኙት ነገር ሲባል ብቻ ከሆነ፣ እንግዲያውስ እግዚአብሔርን ከቶውንም እያገለገሉት አይደለም፤ እግዚአብሔርን አገልጋያቸው በማድረግ እራሳቸውን እየጠቀሙ ናቸው። ሃይማኖታቸው እራስ ወዳድነትን ለማስፋፋት የተበጀ ቅዱስ መሳይ የአሠራር ስልት እንጂ፣ እግዚአብሔርን ማክበሪያ አይደለም።

እግዚአብሔር እስራኤልን በጠራትና ከእርሷ ጋር ቃል ኪዳን በገባ ጊዜ፣ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ መነሻ የሆነው የሕዝቡ ውስጣዊ አሳብ ቅጣትን ማፍራት ነበር። ሕጉን ከታዘዙ እግዚአብሔር ይባርካቸዋል፤ ካልታዘዙ ግን እርሱ ይቀጣቸዋል። ነገር ግን ይህ ሕዝቡ በመንፈሳዊ ረገድ ጨቅላ በነበሩበት ጊዜ ነበር፣ ይህም እግዚአብሔር እነርሱን እንደ ሕፃናት ልጆች አያያዝ በሚያይበት በመጀመሪያው ወቅት (በመንፈሳዊ ሕፃንነት ወቅት) ነበር። ልጆች *ሥነ* ምግባርንና ግብረ ገብነትን ከሚረዱት በላይ ሽልማቶችንና ቅጣቶችን ይረዳሉ። ነገር ግን አዲሱ ትውልድ ከነዓን ለመግባት ዝግጁ በነበረበት ወቅት፣ ሙሴ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ከፍ ያለ ውስጣዊ ስሜትን አሳድሮባቸው ነበር፣ ይህም ለእግዚአብሔር ያላቸው ፍቅርን ነው (ዘዳግ. 6:4-5፤ 7:7፤ 10:12-16፤ 11:1፣ 13፤ 22፤ 19:9)። ከዚህ በኋላ ሕፃናት አይደሉም፣ ደግሞም እግዚአብሔር ይታዘዙት ዘንድ ሊያስፈራራቸው (ወይም



«ጉቦ ሊሰጣቸው») አይገባም። ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው (ሮሜ 13:8-10) ደግሞም ለመታዘዝ የሚሆን የላቀ ውስጣዊ መነሻ ነው (ዮሐ. 14:15)።

ኢዮብ *ክፉ ልብ* እንዳለው የኢዮብ ቃሎች ለኤልፋዝ ነግረውታል (ኢዮብ 15:5-6)። «በደልህ አፍህን ያስተምረዋል!» (ቍ. 5፤ ማቴ. 12:34-37 ተመልከት)። ኢዮብ ንጽሕናውን እያጸና ነበር፣ ነገር ግን ኤልፋዝ የኢዮብን ኃጢአተኝነት ለማረጋገጥ ቃሎቹን ይተረጉማቸው ነበር! እየተናገረው የነበረውን ነገር ወዳጆቹ በማያምኑበት ሁኔታ እንኳ ሳለ ለኢዮብ ምን ተስፋ አለው?

ኢዮብ ጥበብ ይጐድለዋል ምክንያቱም *ተሞክሮ የለውም* (ኢዮብ 15:7-10)። በዚህ ነጥብ ላይ፣ ኤልፋዝ ወደ አሽሙር ተመለሰ፣ ሊናገረው የሚሻውን አንድ ልዩ እውቀት (መረዳት) ለመናገር የፈጠነበት ምክንያት ሌላው ማስረጃ ነበር። ይህ ደግሞ ሌላው የተከራካሪዎች መሸወጃ ነበር፡- አንድን ንግግርን ተቃውመህ መርታት በማትችልበት ጊዜ፣ ተናጋሪውን አፌዝበት። ኢዮብ እግዚአብሔር የፈጠረው የመጀመሪያው ሰው እንደ ነበረ አልተናገረም፣ ወይም እግዚአብሔር የሚተማመንበት መሆኑን፣ ወይም ጥበብ በሞኖፖል እንድይዝ አድርጎኛል አላለም። ኢዮብ ወዳጆቹ ከእርሱ ይልቅ በዕድሜ ባለ ጠጎች መሆናቸውን ያውቃል፣ ነገር ግን ዕድሜ ጥበበኛ ለመሆንህ ዋስትና አይደለም [32:9፤ መዝ. 118(119):97-104]።

በኤልፋዝ መረዳት መሠረት፣ የኢዮብ ዝንባሌ ስሕተት ነበር፣ ምክንያቱም እርሱ የእግዚአብሔርን እርዳታ አሻፈረኝ ብሎአልና (ኢዮብ 15:11-16)። ኤልፋዝ እራሱንና አስፈላጊውን መጽናናት ለኢዮብ ለማምጣት እንደ ተላኩ እንደ እግዚአብሔር መልእክተኞች ይመለከት ነበር። ቃሎቻቸው «በርጋታ የተነገሩ» ነበሩ (ቍ. 11፣ አ.መ.ት)፣ ነገር ግን የኢዮብ ንግግር በቍጣ የሚነገር ነበር። ሦስቱ ጓደኞች እግዚአብሔርን እያገለገሉ ነበር፣ ነገር ግን ኢዮብ እግዚአብሔርን እየተቃወመ ነበር።

ከዚያም ኤልፋዝ በመጀመሪያ ንግግሩ ያቀረበውን መልእክት ደግሞ ተናገረ (ቍ. 14-16፤ 4:17-19)። ኢዮብ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን ለመቀበል እንቢ አለ፣ ነገር ግን የበለጠ እየተሠቃየ ስለ ሄደ ምናልባት አሁን ይቀበለው ይሆናል። ሰማያት በእግዚአብሔር ፊት

ንጹሕ ካልሆኑ፣ በሰማይ የሚኖሩ መላእክትም እንደዚሁ ንጹሕ ካልሆኑ፣ የሰው ልጅ እንዴት ንጹሕ ነኝ ሊል ይችላል? ሰው ከኃጢአተኛ ባሕርይ ጋር ነው የተፈጠረው፣ ኃጢአትንም ይጠማል ደግሞም ኢዮብ ከዚህ የተለየ አይደለም። ይህ ሁሉ ለኤልፋዝ ሁለተኛ ማስጠንቀቂያ በሩን ከፈተለት።

**(2) እግዚአብሔር በክፉዎች ላይ ይፈርዳል (ኢዮብ 15:17-35)።** በመጀመሪያ ንግግሩ ኤልፋዝ የእግዚአብሔር ሰውን በረከት አስ ረድቷል (5:17-26)፣ ነገር ግን አሁን የእግዚአብሔር ሰው ስላልሆነ ሰው ያስረዳል። ኤልፋዝ እነዚህ ነገሮች የእርሱ አሳብ ብቻ እንዳልሆኑ፣ ነገር ግን ጥንታውያን ሰዎች ሁሉም ከእርሱ ጋር እንደሚስማሙ ለኢዮብ በማስታወስ ጥንቁቅ ነበር። ኢዮብ ኤ ልፋዝ የተናገረውን የማይቀበል ከሆነ፣ ከአባቶቻቸው ጥበብ (እውቀት) ጀርባውን መልሶአል ማለት ነበር። ኤልፋዝ፣ «ትውፊት መሪ ነው እንጂ አሳሪ አይደለም» የሚለውን በመርሳት ከትውፊት በጣም ጥንካሬን ያገኘ ሰው ነበር (ደብሊው. ሶመርሴት መውፋም)።

ይህን ስለ ክፉው ሰው የሚናገር ዝርዝር በምታነብበት ጊዜ፣ ኤልፋዝ ስለ ኢዮብ እየተናገረ እንደ ሆነ ታስተውላለህ። ኢዮብ በሥቃይ፣ በጨለማ፣ በችግር፣ በምሬት እና በፍርሃት ውስጥ ነበር። እግዚአብሔርን እየተቃወመ ደግሞም አግኝቶት በደለኝነቱን እንዲያረጋግጥለት እየጠየቀ ነበር። እሳት የኢዮብን በጎች በላች (1:16፤ 15:30፣ 34)፤ አደጋ-ጣዮች ግመሎቹን ወሰዱ (1:17፤ 15:21)፤ ያለውን ሀብት ሁሉ አጣ (ቍ. 29)፤ ደግሞም የትልቁ ልጁ ቤት በዐውሎ ነፋስ ፈረሰ እንዲሁም በዚያ የነበሩ የኢዮብ ልጆች ሁሉ ጠፉ (1:19፤ 15:28)። ኤልፋዝ በአቀራረቡ ሁሉ አሳች አልነበረም፤ ሁላቸውም ስለ ኢዮብ እየተናገረ እንደ ነበ ረ ያውቃሉ።

ነገር ግን በመደምደሚያ ቃሎቹ (ቍ. 34-35)፣ ኤልፋዝ ከሁሉም ከባድ የሆነ ነገር ተናገረ:- ኢዮብን ግብዝና አምላክ የለሽ ሰው ብሎ ጠራው፤ እንዲሁም በእርሱና በአሳቡ ላይ ለመጣው ስቆቃ እርሱን ጥፋተኛ አደረገው። ኢዮብ በምሥጢር ኃጢአትን «ፀንሶአል»፣ ኃጢአት ደግሞ መከራንና ሞትን ወልዳለች (ያዕቆብ



1:14-15፤ ኢሳ. 59:4፤ መዝ. 7:14)። «ማኅፀናቸው ክፋትን ይፀንሳል» የሚለው ለኢዮብ 15:35 አዲሱ መደበኛ ትርጒም የሰጠው ትርጒም ነው፤ ደግሞም «ማኅፀን» በሚል የተተረጐመው ቃል በቍጥር 1 ላይ «ሆድ» ከሚለው ጋር አንድ ነው። በኤ ልፋዝ መረዳት መሠረት ኢዮብን ኤክስሬይ ብታነሡት ልታገኙት የማትችሉት የሞቀ አየርና ኃጢአት ብቻ ነው! በኢዮብ ሦስት ጓደኞች ንግግር ውስጥ ግብዝ የሚለው ቊልፍ ቃል ነው። በልዳዶስ ኢዮብ ግብዝ ነው ብሎአል (8:13)፣ ደግሞም ሶፋርና ኤ ሊሁ ሁለቱም መሪ አሳቡን ይቀበላሉ (20:5፤ 34:30፤ 36:13)። በእርግጥ፣ ኢዮብ ክሱን ክዶአል (13:16፤ 17:8፤ 27:8) ደግሞም ይህ እውነት እንደ ሆነ እግዚአብሔርም ሆነ የእርሱ ጓደኞች ሊያ ረጋግጡት እንደማይችሉ በክርክሩ ላይ ተናግሮአል።

ኤልፋዝ በክፉዎች ላይ ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ አስመልክቶ በተናገረው ንግግር ላይ ያለው ችግር፣ *ይህ በዚህ ሕይወት ሁልጊዜ የሚከሰት አለመሆኑ ነው።* ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች መከራን ሲለማመዱና የወደቁ ሲመስሉ፣ ብዙ ክፉ ሰዎች በዚህ ምድር ደስተኛና ስኬታማ ሆነው ያልፋሉ። *በመጨረሻ* ክፉ ዎች የሚሠቃዩ እንዲሁም የእግዚአብሔር ሰዎች የሚባረኩ መሆናቸው እውነት ነው። ነገር ግን በመካከሉ፣ የዚህ ተቃራኒ ዘወትር ተከስቶ ይታያል (መዝ. 73፤ ኤር. 12:1-4)። በተጨማሪ ም፣ እግዚአብሔር ለመልካም ሰዎችና ለክፉዎች ፀሐይን ይሰጣል ደግሞም በጻድቃንና በኃጢአተኞች ላይ ዝናብን ያዘንባል (ማቴ. 5:45)። እርሱ ስለ ኃጢተኞች ይታገሣል (2ኛ ጴጥ. 3:9) ደግሞም ወደ ንስሐ ሊመራቸው መልካምነቱን ይጠብቅላቸዋል (ሮሜ 2:4፤ ሉቃስ 15:17-19)።

በዚህ ሕይወት እግዚአብሔር በኃጢተኞች ላይ የሚልከው ትልቁ ፍርድ *የገዛ መንገዳቸውን እንዲከተሉ መፍቀድ* ነው። «ዋጋቸውን ተቀብለዋል» (ማቴ. 6:2፤ 5:16)። ከእግዚአብሔር ጋር ያልቆሙ ሰዎች ብቸኛው ሰማይ (*መንግሥተ* ሰማይ) በምድር ላይ ያላቸው ደስታ ነው፣ ደግሞም ይህ ደስታ እንዲኖራቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። የእግዚአብሔር ሰዎች ሊቀበሉት ያለ ብቸኛ መከራ በዚህ ምድር ላይ ያለው ነው፣ ምክንያቱም በመንግሥተ ሰማይ ሥቃይ ወይም ልቅሶ የለም። በተጨማሪም፣

የእግዚአብሔር ሕዝቦች አሁን የሚቀበሉት መከራ ለእነርሱ በጐነት ይሠራላቸዋል ደግሞም አንድ ቀን ወደ ክብር ይመራቸዋል (1ኛ ጴጥሮስ 1:6-8፤ 5:10፤ 2ኛ ቆሮ. 4:16-18፤ ሮሜ 8:18)። ኤልፋዝ እና ጓደኞቹ ሁሉም ግራ የተጋባ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ።

## የኢዮብ፡- ሦስት ጥያቄዎች (16-17)

የኢዮብ ምላሽ ሦስት ልብን የሚነኩ ጥያቄዎችን ማቅረብ ነበር፡- የመጀመሪያው፣ እንዲያዝኑለት ለጓደኞቹ ያቀረበው አቤቱታ ነው (ኢዮብ 16:1-14)፤ ከዚያም ፍትሕን እንዲያሰፍን ለእግዚአብሔር ያቀረበው አቤቱታ ነው (ቍ. 15-22)፤ እንዲሁም በመጨረሻ የሕይወቱ ማብቂያ እንዲሆንና ከመከራ እንዲገላግለው ለእግዚአብሔር ያቀረበው አቤቱታ ነው (17:1-16)።

**(1) እንዲያዝኑለት የቀረበ ልመና (ኢዮብ 16:1-14)።** የኢዮብ ጓደኞች አሁንም እርሱ ካለበት ሁኔታ ጋር እራሳቸውን አላገናዘቡም፤ የሚሰማው ሥቃይ አልተሰማቸውም ወይም የገጠመውን ግራ መጋባት አልተረዱም። ኢዮብ ቀድሞውንም «የማያዛልቁ ጅረቶች» (6:15ን ተመልከት) ደግሞም «የማይረቡ ሐኪሞች» (13:4፣ አ.መ.ት) ብሏቸዋል፣ ነገር ግን አሁን «የምታስጨንቁ አጽናኞች» (16:2) ይላቸዋል። እርሱን ለማጽናናት የሚያደርጉት ጥረት ሁሉ የበለጠ ያስጨንቀው ነበር! «እንደ እናንተ ያሉ ወዳጆች ያሉት ሰው፣ ምን ጠላት ይሻል?» ከሚለው አባባል ጋር የሚሄዱ ናቸው።

ኢዮብ እነርሱ በእርሱ ስፍራ ቢሆኑ ኖሮ፣ ለእርሱ ከሚያሳዩት የበለጠ አያያዝ ያሳያቸው ነበር። ረጅም ንግግር በማድረግ ፈንታ፣ የማጽናኛ ቃሎችን ይሰጣቸው ነበር። ከልቡ ያዳምጣቸውና ሸክማቸውን ለመሸከም ይጥር ነበር። አንዳንድ ጊዜ፣ ሌሎችን እንዴት ማገልገል እንዳለብን ለመማር ኀዘኔታ የሌላቸው ወገኖች እኛን በተሳሳተ መልኩ የሚረዱበትን ተሞክሮ ማግኘት ይኖርብናል። ይህ ለኢዮብ አዲስ ልምምድ (ተሞክሮ) ነበር፣ እንዲሁም ከዚህ የላቀውን ለማግኘት ይጥር ነበር። ይሁን እንጂ፣ ኢዮብ ተናገረም ጸጥ አለም፣ እርሱ በመሠቃየት ላይ ያለ ሰው ነበር (ቍ. 6)።

የፍቅር ርኅራኄ እንዲያሳዩ ሲለምናቸው፣ ከእግዚአብሔር ስለ ተቀበላቸው ነገሮች ኢዮብ ለወዳጆቹ ነገራቸው (ቍ. 7-14)።



ኢዮብ በመከራ ደቅቆአል፤ ቤተሰቡ ጠፍቶአል፤ እርሱ የመነመነ እና በሽተኛ ነው። ሰዎችም እግዚአብሔርም ሁለቱም አጥቅተውታል። ኢዮብ እግዚአብሔር በጀርባው ላይ ዒላማን እንዳስቀመጠና የእያንዳንዱ ሰው ቀስት በእርሱ ላይ እንደሚያርፍ ይሰማው ነበር! ዕረፍት የሚባል ነገር የለም፣ ልክ ዕረፍት እንደ ሌለው ጦረኛ እግዚአብሔር እርሱን በጥብቅ ይከታተለዋል። «እኔ እግዚአብሔርን አላጠቃሁትም እርሱ እያጠቃኝ ነው!» እግዚአብሔር ጠላት ሆኖት ነበር (16:9፤ 13:24)፣ ደግሞም ኢዮብ እውነቱ እንዲወጣ የሚያደርገው ነገር የለም። ኢዮብ ወደ ላይ ቢመለከት፤ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ በተቃውሞ ተነሥቶ ያገኘዋል። ዙሪያውን ቢመለከት፣ ወዳጆቹ በእርሱ ላይ በተቃውሞ ተነሥተው ያገኛቸዋል። ወዴት ይዙር?

**(2) ስለ ፍትሕ የቀረበ ልመና (ኢዮብ 16:15-22)።** ለእግዚአብሔር ጥቃት ኢዮብ እንዴት ያለ ምላሽ ይስጥ? ማቅ ለብሶአል፣ እራሱን በማዋረድና በጸጸት ያለቅሳል፣ ደግሞም ፊቱን በአፈር ውስጥ ቀብሮአል። ከኤልፋዝ ክስ ባሻገር (15:4-6)፣ እርሱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ እንደ ሆነ ደግሞም እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚሰማ (16:17) ያውቃል።

ኢዮብ ግራ ተጋብቷል። መከራው እጅግ ከመብዛቱ የተነሣ፣ መሞትን በጽኑ ተመኝቶአል፣ ነገር ግን እራሱን ነፃ ከማውጣቱ ወይም እግዚአብሔር ነፃ ሲያወጣው ከማየቱ በፊት ለመሞት አይፈልግም። ይህም በቍጥር 18 ላይ ያሰማውን ጩኸት ይገልጸዋል፣ «ምድር ሆይ፣ ደሜን አትክደኚ፣ ለጩኸቴም ማረፊያ አይሁን።» ጥንታውያን ሰዎች የንጹሐን ተጠቂዎችን ደም ስለ ፍትሕ ወደ እግዚአብሔር ይጮኻል (ዘፍጥ. 4:8-15) እንዲሁም የሙታን መናፍስት ሬሳውን በሆነ መልኩ እስከሚቀብር ድረስ (ኢሳ. 26:21) ዕረፍት-አልባ ናቸው ብለው ያምናሉ። ኢዮብ የሞተ ቢሆን እንኳ፣ በኔታ ጻድቅነቱ እስኪመሰከርለት ድረስ ዕረፍት-የለሽ ነበር የሚሆነው።

ኢዮብ በተደጋጋሚ ያሰማው ጩኸት በእግዚአብሔር ፊት ቅን የሆነ ፍርድ እንዲፈረድለት ነበር (ኢዮብ 9:1-4፣ 14-16፣ 19-20፣ 28-35፤ 10:2፤ 13:6-8፣ 19)። በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ወክሎት የሚገኝ ባለ መኖሩ ምክንያት ሰቆቃውን አሰማ (9:33)። ከጓደኞቹ

የቱም ሊረዳው አልቻለም፣ ስለዚህ ብቸኛው ተስፋው፣ በሰማይ ያለ እግዚአብሔር የሚረዳው እንደዚሁም ለታማኝነቱ ምስክርነት የሚሰጥ መሆኑ ነበር (16:19)። ነገር ግን ኢዮብ እርሱን ተክቶ በእግዚአብሔር ፊት የሚለምንለት አንድ ሰው ያስፈልገዋል (ቊ. 21)።

ክርስቲያን የሆኑ አማኞች ይህ ሰማያዊ ጠበቃ በኢየሱስ ክርስቶስ አላቸው (1ኛ ዮሐንስ 2:1-2)። ልክ ለእኛ እንደሚማልድ ሊቀ ካህናት ክርስቶስ በምንፈተንበት ጊዜ የሚያስፈልገንን ጸጋ ይሰጠናል (ዕብ. 2:17-18፤ 4:14-16)። ብንወድቅ፣ ኃጢአታችንን በምንናዘዝበት ጊዜ ይቅር ሊለን እና ሊያድሰን፣ ዝግጁ የሆነ ጠበቃችን ነው (1ኛ ዮሐንስ 1:5-2:2)።

በእርግጥ፣ ኢዮብ ነገሩን በእግዚአብሔር ፊት የሚያቀርብ እና እርሱ ጻድቅ መሆኑን የሚያሳምን ጠበቃ አስፈልጎታል። ኢዮብ አንድ ጊዜ በክርክሩ ከረታ፣ ከዚያ በኋላ በሚነቅፉት ጓደኞቹ ፊት እግዚአብሔር ነፃ ያወጣዋል ደግሞም የኢዮብን ክብር ይመልሳል። የእግዚአብሔር ሰዎች የዚያን ዓይነት ምልጃ አያስፈልጋቸውም፣ ምክንያቱም አብና ወልድ ለእኛ ባላቸው ፍቅር እንዲሁም ለኑሮአችን ባላቸው ዕቅድ ፍጹም የሆነ ስምምነት አላቸው። ጌታ ኢየሱስ ለሕዝቡ ምልጃን ለማድረግ (ሮሜ 8:31-39፤ ዕብ. 7:25) ደግሞም በእግዚአብሔር ፈቃድ እነርሱ ፍጹማን እንዲሆኑ (13:20-21) ምን ጊዜም ይኖራል። እኛ ወደ ጸጋው ዙፋን ወጥተናል፣ ወደ ፍርድ ዙፋን አይደለም፤ እንዲሁም አፍቃሪ አባታችን ለእኛ መልካም የሆነውን እንደሚያደርግልን እናምናለን።

**(3) ለመሞት የቀረበ ልመና (ኢዮብ 17:1-16)።** ኢዮብ ሰማያዊ ጠበቃው ፈጥኖ እንዲሠራ የፈለገበት አንዱ ምክንያት ሞት፣ «ወደማይመለስበት መንገድ መሄጃው» (ኢዮብ 16:22) እየቀረበ መምጣቱ ስለ ተሰማው ነበር። ሰዎች መንፈሳቸው እስኪደክም ድረስ እጅግ በሚሠቃዩበት ጊዜ (17:1)፣ ውጊያቸውን ያበቃሉ ደግሞም ሕይወት እንዲያበቃ ይሻሉ።

የኢዮብ ጓደኞች እርሱን የሚቃወሙ ነበሩ፤ ሁኖም ወደ ችሎት የሚሄዱ አይደሉም። ደግሞም ይህን እርሱ እንዲያደርገው ለሌላ ጊዜ አስተላልፈውታል (ቊ. 3-5)። ሰዎች ኢዮብን የምድር ጭቃ እንደ ሆነ አድርገው ይመለከቱት ነበር (ቊ. 6)። ሰውነቱ ከዚህ



በፊት የነበረው የአካሉ ጥላ ብቻ ነበር (ቊ. 11)። ጓደኞቹ አሳባቸውን ለውጠው እርሱን ወደ መደገፉ አልመጡም (ቊ. 10)። በእርግጥ፣ ያለበትን ሁኔታ በታማኝነት አልተመለከቱትም፣ ነገር ግን ብርሃን ፈጥኖ እንደሚወጣለት መናገራቸውን ቀጠሉ (ቊ. 12)። ኢዮብ ብቸኛው ማምለጫ ሞት እንደ ሆነ መመልከቱ ያስደንቃልን?

ይሁን እንጂ፣ በየትኛውም ጊዜ ኢዮብ የገዛ ሕይወቱን ለማጥፋት ወይም ሌላ ሰው ይህን እንዲያደርግለት አልጠየቀም። ሕይወት ከእግዚአብሔር የተሰጠች የተቀደሰች ስጦታ ናት፤ ስለዚህ ሊሰጣትም ሆነ ሊወስዳት የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። በአንድ በኩል እራሱን ነፃ ወጥቶ ማየት ስለሚፈልግ ረጅም ዕድሜ ለመኖር ይፈልጋል፤ ነገር ግን በሌላ በኩል ለምን ያህል ተጨማሪ ጊዜ መታገሥ እንደሚችል አያውቅም። አንድ ጊዜ በሙታን ዓለም፣ በሲኦል፣ ውስጥ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ካልመለሰው በቀር በምድር ላይ ነፃ መውጣት አይችልም።

`ኢዮብ ሲኦልን፣ በጨለማ የሚተኛበት እና የሚያርፍበት (ቊ. 13) እንደ ቤቱ የሆነ ስፍራ አድርጎ ይሥለዋል። ቤተሰብ የሌለው በመሆኑ፣ ጉድጓድን (ወይም «መበስበስን») እንደ አባቱ እንዲሁም የሚውጥ ትልን እንደ እናቱ ወይም እኅቱ አድርጎ ይወስዳል። እነርሱ ከጓደኞቹ ይልቅ ብዙ መጽናናት ይሰጡታል!

ነገር ግን፣ በመቃብር ውስጥ የሆነ ተስፋ ይኖራልን? ኢዮብ ተስፋውን ከእርሱ ጋር ወደ ሲኦል ይዞት መሄድ ይችላልን? ጳውሎስ ጥያቄውን ይመልሳል፡- «በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ፣ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን። አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል» (1ኛ ቆሮ. 15:19-20)። *ተስፋችን አይሞትም፣ አይቀበርም ደግሞም እንዲበሰብስም አያደርግም፣ ምክንያቱም፣ ክርስቶስ በሞትና በመቃብር ላይ ድልን ስለ ተቀዳጀ ተስፋችን «ሕያው ተስፋ»* ነውና። ክርስቲያኖች ያዝናሉ፣ ነገር ግን «ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች» ማዘን አይኖርባቸውም (1ኛ ተሰ. 4:13)።

እግዚአብሔር ኢዮብ እንዲሞት ያቀረበውን ጥያቄ አልመለሰለትም፤ ምክንያቱም ያቀደለት አንድ የተሻለ ነገር ነበረው። እግዚአብሔር ኢዮብ ከሚያልፍበት ደስታና ምሬት በላይ

ይመለከት ነበር፤ ደግሞም አሁንም እርሱ እምነት እንዳለው አየ:: ወጣት መጋቢ በነበረበት ጊዜ፣ ተሞክሮ ያለው የተቀደሰ ሰው እንዲህ ሲል ሰማሁ፣ «ያልተመለሱ ጸሎቶችን በተመለከተ ምስጋና ለማቅረብ ረጅም ዓመታት ኖርሁ::» በዚያን ጊዜ፣ በዓረፍተ ነገሩ ደነገጥሁ፤ ነገር ግን እኔ እራሴ ጥቂት ዓመታትን ኖርሁ፣ እርስዋ ምን እየተናገረች እንደ ነበረ አውቃለሁ:: በተስፋ መቍረጥ ጨለማና በሥቃይ እስር ቤት ውስጥ፣ ብዙውን ጊዜ በኋላ የምንጸጸትባቸውን ነገሮች እንናገራለን፤ *ነገር ግን እግዚአብሔር ስለ እርሱ ሁሉንም ነገር ያውቃል ደግሞም ደንቆሮ የሆነ ጆሮ ወደ ንግግራችን ይመልሳል ነገር ግን ወደ ቍስላችን ሩኅሩኅ ዓይንን ይመልሳል።*

የሚቀጥለው ተናጋሪ ብቻ ለዚህ ለተጐዳ ሰው ርኅራኄን ቢያሳይ እንዴት ተመራጭ ነበር! ነገር ግን በልዳዶስ በእግዚአብሔር ቃል በሆነ ስፍራ የሚገኝ እጅግ ጉልህ የሆነ ሥዕሎችን ስለ ሞት በማምጣት ኢዮብን ያስፈራው ጀመር::



## ለግል ምልከታ ወይም ለቡድን ውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ኢዮብ በንጽሕናው ላይ ድርቅ አለ፣ ጓደኞቹ ግን በደለኝነቱን በተመለከተ የበለጠ በጽናት መናገራቸውን ቀጠሉበት:: ኢዮብ ንጹሕ ሲሆን ግን ደግሞ መከራ ሊቀበል ይችላል የሚለውን እውነት የፈሩባቸውን ጥቂት ምክንያቶች ጥቀስ::

2. መታዘዝ ሁልጊዜ ወዲያው በረከቶችን የማያፈራ ከሆነ፣ እንግዲያውስ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ መነሻችን ምንድን ነው?

3. ኢዮብ ንጹሕ እንደ ሆነ በመናገር የገዛ እራሱን ጻድቅነት እየተናገረ ካልሆነ፣ ታዲያ ሌላ ምን እያለ ነበር?

4. ኤልፋዝ ክፉ ሰውን ግራ እንደ ተጋባ፣ እንደ ተቸገረ እንዲሁም እንደ ፈራ ሰው አድርጎ ገልጾታል:: የእግዚአብሔር ሰው እንዲህ ባለ መንገድ የሚገለጽበትን አንዳንድ ሁኔታዎች አስ ረዳ::

5. አንድ ሰው የሚሠቃየው እርሱ/እርሷ በመቀባታቸው ነው

ብለን ማሰብ ካልቻልን፣ እንግዲያውስ እየተሠቃየ ስላለ ሰው ምን ማለት እንችላለን?

6. **እግዚአብሔር ለክፉ ነገር ወዲያው ቅጣት ለመስጠት የማይመርጥባቸውን ጥቂት ምክንያቶች ዘርዝር::**

7. ኢዮብ በእግዚአብሔር ፊትና በጓደኞቹ ፊት ነፃ ለመውጣት ፈልጎ ነበር:: የምታምናቸው እና የምትደገፍባቸው ሰዎች ሳይረዱ ሲቀሩ የሚሰማህ ምንድን ነው?

8. አንድ ሰው ሞትን እስኪመኝ ድረስ በሚሠቃይበት ጊዜ ለዚህ እግዚአብሔር እንዴት ያለ ምላሽ ይሰጣል ብለህ ታስባለህ?

9. **እየተሠቃየን ሳለን እንኳ እግዚአብሔርን የምናመልክባቸውን ጥቂት መንገዶች ጥቀስ::**



# የዕረፍት ጊዜ

ተስፋ የቈረጡና የተጐዱ ሰዎችን ለመርዳት ምርጡ መንገድ በጆሮ ብቻ ሳይሆን፣ ከልብ እነርሱን ማድመጥ ነው:: አስፈላጊው ነገር የሚናገሩት ሳይሆን፣ የሚናገሩበት ምክንያት ነው:: ለእናንተ የሚናገሩትን ነገር በተለዩ ቃላት መልሳችሁ ወደ እነርሱ በማምጣት የምትረዷቸው መሆናችሁን እንዲያውቁ አድርጉ:: አትከራከሩ ወይም ሥነ አመክንዮታዊ ምክንያቶችን በመደርደር ልታሳምኑዋቸው አትሞክሩ:: ለኋላኛው ጊዜ ይኖራል፤ እስኪዜወው ድረስ ስሜቶቻቸውን በእግዚአብሔር ላይ የሚናገሩትን የምሬት ቃሎች እንኳ ተቀበሉ ደግሞም አጥርን ሳይሆን፣ ድልድይን ሥሩ::

ስለ ባለቤቱ በጻፈው መጽሐፍ፣ *«ሒ ግሪፍ ኦብዘርቭድ»* በሚለው ሲ. ኤስ. ሌዊስ የገዛ እራሱን አሳማሚ የሆነ ተሞክሮ እንዲህ ሲል ጽፎአል:- «ስለ ሃይማኖት እውነታ ንገሩኝ፣ እኔ ደግሞ በደስታ አደምጣለሁ:: ስለ ሃይማኖት ተግባር ንገሩኝ፣ እኔም በመታዘዝ አደምጣለሁ:: ነገር ግን ሃይማኖት የሚሰጠውን መጽናናት ልትነግሩኝ አትምጡ፣ አለበለዚያ አልተረዳሁም ብዬ እጠራጥራችኋለሁ» (23)::

በእምነታችን ውስጥ እውነተኛ መጽናናት አለ፣ ነገር ግን ልክ እንደ ሳል መድኃኒት ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ አይሰጥም:: *እጅግ ጥልቅ በሆነ ጉድጓድ (ሸለቆ) ውስጥ መግባት ምን እንደሚመስል እግዚአብሔር የተወ እንደሚመስል የተረዱ ሰዎች ብቻ ሊካፈሉት ይችላሉ::* እውነተኛ አጽናኝ ለመሆን የምትፈልግ ከሆንህ፣ ሊከፈል የሚገባ ዋጋ አለ፣ ሆኖም ሁሉም ሰው ሊከፍለው የሚፈቅደው አይደለም:: ጳውሎስ ስለዚህ በ2ኛ ቆሮንቶስ 1:3-11 ላይ ጽፎአል::

ጆን ሄነሪ ጆዌት እንዲህ አለ:- «እግዚአብሔር ምቾት እንዲሰማን አድርጎ አያጽናናንም፣ ነገር ግን አጽናኞች እንድንሆን ያጽናናናል::» የእግዚአብሔር ማጽናናት በስጦታ መልክ ከቶ አይሰጥም፤ ሁልጊዜ *በብድር* መልክ ነው የሚሰጠው:: እግዚአብሔር ለሌሎች እንድናካፍለው ይጠብቅብናል::

## ምዕራፍ ስድስት

# እውነተኛው ጠላት፣ እባክህን ልትቆም ትችላለህን?

(ኢዮብ 18-19)

«ሞት ከእርሱ ውጭ በጨረቃ ያለ የእግር መረገጫ ስፍራ እንዲሁም የህዋ ጉዞ ወደ ኢምንትነት የሚለወጥበት ታላቅ ጀብዱ ነው።»

- ጆሴፍ ባይሊ

በልዳዶስ ሁለተኛውን ንግግሩን በመጀመሪያው ንግግሩ በተጠቀመባቸው በእነዚያው ቃሎች መናገር ጀመረ፡- ይህም «እስከ መቼ?» (ኢዮብ 18:2፤ 8:2) የሚል ነበር፣ ኢዮብም እንደዚሁ ምላሽ በሰጠ ጊዜ፣ ያንኑ ነበር የተናገረው (19:2)። የሚያቀርቡት ንግግር የትም የማይደርስ ስለሚመስል፣ ጓደኞቹ እርስ በርስ ትዕግሥት እያጡ ሄዱ። ጆርጅ በርናርድ ሾው አማካይ የሆነውን ንግግር በመውሰድ «የደርዘን ግማሽ ከሚሆን በመቅረጸ ድምፅ ከተቀዳ ንግግር ጋር አወዳዳረው-ወዲያውም ይህን ስትሰሙ ሁሉንም ትሰለቹአቸዋላችሁ» አለ።

በልዳዶስ ሊግባባ ስላለመቻሉ ኢዮብን ተጠያቂ አደረገው ደግሞም እንዲህ ሲል ገሠጸው፣ «እስኪ ልብ ግዛ፤ ከዚያም በኋላ እንነጋገራለን» (18:2፣ አ.መ.ት)። እርሱም ሆነ ጓደኞቹ አንድን ነገር ደግመው ደጋግመው የሚናገሩ መሆናቸው በበልዳዶስም ላይ ቢሆን ተንጸባርቋል፡- (1) እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፤ (2) እግዚአብሔር ክፉዎችን ይቀጣል ጻድቃንን ግን ይባርካል፤ (3) ኢዮብ እየተሠቃየ ያለው ክፉ ቢሆን ነው፤ (4) እርሱ ከኃጢአቱ



ቢመለስ፣ እግዚአብሔር እንደ ገና ይባርከዋል እያሉ መልሰው መላልሰው ይናገሩ ነበር።

በልዳዶስ ኢዮብ ነገሮችን ልብ የሚል አይደለም፣ አክባሪም አይደለም አለ። ጓደኞቹ በእውነት ጠቢባን ሁነው ሳሉ፣ በዚህ ፈንታ እርሱ ነገር እንደማይገባቸው ከብቶች አድርጐ ይመለከታቸዋል (ቊ. 3)። ኢዮብም እንደዚሁ በትሕትና ፈንታ እየተነጫነጨ ቊጣን የሚገልጽ ሆኖ ነበር (ቊ. 4)። «እግዚአብሔር መላውን ዓለም ለአንተ እንደሚመች አድርጎ እንደ ገና ያስተካክልልህ ወይ?» ሲል በልዳዶስ ጠየቀው። «ስለ አንተ ብቻ ሲል ምድሪቱን በጦርነት ያጥፋ ወይስ የምድር መንቀጥቀጥ ያስነሣ?» አሽሙርን እንዴት መጠቀም እንዳለበት የሚያውቅ ኤልፋዝ ብቻ አይደለም!

ይሁን እንጂ፣ በልዳዶስ ከአሽሙር ይልቅ ጠንካራ መሣሪያ ለመጠቀም ዐቅዷል። የእርሱ *መሣሪያ ፍርሃት* ነበር። ሦስቱ ጓደኞቹ ከኢዮብ ጋር ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ካልተመላለሱ፣ ወይም ንስሐ እንዲገባ የሚያሳፍሩት ከሆነ፣ ምናልባት ክፉዎች በሚሞቱ ጊዜ ምን እንደሚከሰት በማስረዳት ኢዮብን ያስፈራሩት ይሆናል።

አስፈሪውን የበልዳዶስን ንግግር ከማጥናታችን በፊት፣ ፍርሃት ተለምዶአዊ የሆነ የሰው ስሜት መሆኑንና መፍራትም ምንም ስሕተት አለመሆኑን መገንዘብ አለብን። የመታመም፣ የመቊሰል ወይም የመሞት ፍርሃትን ለሕፃናት እጆቻቸውን ስለ መታጠብ፣ ከኤሌክትሪክ መሥመር ስለ መራቅ ደግሞም የመኪና መንገድን ከመሻገራቸው በፊት በጥንቃቄ ስለ መመልከት ለማስተማር እንጠቀምበታለን። የገንዘብ ኪሣራን መፍራት ዋስትና እንዲገዙ ሰዎችን ያነሣሣል፣ ደግሞም የሞት ፍርሃት ዓመታዊ የሆነ የጤና ምርመራ እንዲያደርጉ ሰዎችን ያበረታታቸዋል።

የሞት ፍርሃት (እንዲሁም ተከታዩ ፍርድ) በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመንና ለመዳን ተቀባይነት ያለው መነሣሣት ነው። «ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ። ይልቅስ፣ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ» አለ ኢየሱስ (ማቴ. 10:28)። ኢየሱስ የፍቅርን (የቸርነትን መልእክት) ሰበከ፣ ነገር ግን አስከፊ የሆነውን የፍርድንም

መልእክት ሰበከ:: ጳውሎስ፣ «እንግዲህ የጌታን ፍርሃት አውቀን ሰዎችን እናስረዳለን» (2ኛ ቆሮ. 5:11) ብሎ ጻፈ:: ጆናታን ኤድዋርድስ «በተቈጣ አምላክ እጅ ውስጥ ያሉ ኃጢአተኞች» የሚለውን ስብከቱን በሚሰብክበት ጊዜ፣ የትኛውንም ሥነ ልቡናዊም ሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርኆዎችን አልተላለፈም:: የማያምኑ ሰዎች ስሜት አእምሮአቸው ትምህርትን ከመቀበሉ እንዲሁም ፈቃዳቸውን ተግዳሮት ከመግጠሙ በፊት መነሣሣት አለበት::

ይሁን እንጂ፣ በልዳዶስ ይህን ንግግሩን ከሞት ፍርሃቶች በላይ አድርጐ ባቀረበ ጊዜ ሁለት ስሕተቶችን ፈጽሞአል:: እንዲያው ለመናገር ያህል፣ ይህን ሊነገረው ለሚገባው ሰው አልነበረም የሰበከው፤ ምክንያቱም ኢዮብ ቀድሞውኑ አማኝ ነበርና (ኢዮብ 1:1፣ 8):: ሁለተኛ፣ በተሳሳተ ውስጣዊ አሳብ ነበር የሰበከው፣ ምክንያቱም በልቡ ውስጥ ምንም ፍቅር አልነበረም:: እንግሊዛዊው ሰባኪ ዶ/ር አር. ደብልዩ. ዴል በአንድ ወቅት ወንጌላዊ ዲ. ኤል. ሙዲን በስብከቱ ውስጥ «ፍርሃት በውስጡ የሚይዛቸውን ነገሮች» ተጠቅሞ እንደ ሆነ ጠየቀው:: ሙዲ በእያንዳንዱ የአገልግሎት ወቅት አንድ ስብከትን በመንግሥተ ሰማይ ላይ አንድ ስብከትን ደግሞ በገሃነም ላይ ዘወትር እንደሚሰብክ፣ ነገር ግን የጠፉት ሰዎች ስለሚገጥማቸው ውድቀት በሚሰበክበት ጊዜ የሰው ልብ በጣም ርኅሩኅ ሊሆን ይገባል፣ የሚለውን በመናገር መልስ ሰጠ:: በልዳዶስ ርኅሩኅ የሆነ ልብ አልነበረውም::

## የሞት ፍርሃት (18:5-21)

በዚህ ንግግሩ፣ በልዳዶስ የክፉዎችን ሞት በተመለከተ አራት ጕልህ የሆኑ ሥዕሎችን ያስቀምጣል::

**(1) የጠፋ ብርሃን (ኢዮብ 18:5-6)::** ጨለማ ከሞት ጋር እንደሚያያዝ ሁሉ፣ እንዲሁ ብርሃንም ከሕይወት ጋር ይያያዛል:: እግዚአብሔር የሕይወት ምንጭ ስለሆነ፣ እርሱ ብቻ ነው «ብርሃናችንን ሊያበራው» የሚችለው፤ ምክንያቱም «እርሱም ሕይወትን እና እስትንፋስን ሁሉንም ለሰው ይሰጣልና»፣ ደግሞም «በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን እንኖርማለን» (የሐዋ. 17:25፣ 28):: እዚህ ላይ ያለው ሥዕላዊ መግለጫ በድንኳን ውስጥ የተንጠለጠለ መብራት እንዲሁም መብራቱ እንዲበራ የተ



ለኰሰ እሳት ነው:: ወዲያውም፣ ብርሃኑ ይጠፋል፣ እንዲሁም የእሳቱ የመጨረሻ ብልጭታም ይጠፋል:: ድንኳኑም ሙሉ በሙሉ ጨለማ ይሆናል (ምሳሌ 13:9፤ 24:20)::

ልክ እንደ መብራቱ ነበልባል፣ ሕይወት ውድ ናት:: ነገር ግን በቀላሉ ጠፊ ነገር እንዲያጠፋት ኃይለኛ ንፋስ አያስፈልግም:: «በእኔና በሞት መካከል አንድ እርምጃ ቀረ» (1ኛ ሳሙ. 20:3)::

ዊሊያም ራንዶልፍ ሂርስት የተባለው አሜሪካዊው የጋዜጣ አዘጋጅ፣ በፊቱ ስለ ሞት እንዲያወራ ለማንም ሰው አይፈቅድለትም:: ይሁንና (እ.ኤ.አ) በነሐሴ 14፣ 1951፣ የሕይወቱ ነበልባል ጠፋች እና ሞተ:: «የሰው መንፈስ የእግዚአብሔር መብራት ነው» (ምሳሌ 20:27)፣ ደግሞም እርሱን ደስ ባሰኘው ጊዜ መብራቱን ሊያጠፋው ይችላል::

**(2) ተጓዡ ሰው በወጥመድ ተያዘ (ኢዮብ 15:7-10)::** ከመፍራቱ የተነሣ፣ ሰው ድንኳኑን ለቅቆ ይሄዳል ደግሞም ምቹ ቦታን በመፈለግ ወደ ታች መጓዝ ይጀምራል:: ነገር ግን መንገዱ ከሁሉ እጅግ አደገኛ ስፍራ ይሆንበታል፣ ምክንያቱም ወጥመድ የተደረገበት መንገድ ነውና:: በልዳዶስ ከሞት ለማምለጥ መሸሽ በሚሞክሩበት ጊዜ ሰዎች የሚጋፈጡዋቸውን አደጋዎች ለማብራራት ስድስት ቃሎችን ተጠቅሟል:-

*መረብ* - እርሱን ለመያዝ በመንገዱ ላይ ተዘርግቷል

*ወጥመድ* - ጥልቀት ያለውን ጕድገድ ቅርንጫፎች ሸፍነውታል

*ወጥመድ* - በሚነካበት ጊዜ ተዘርግቶ የሚያጠምድ የሸምቀቆ ወጥመድ ተረከዙ ላይ ይያዛል

*ቀማኛ* - ሌላው ጕድጓድ

*ወጥመድ* - በመሬት ላይ የተደበቀ ሸምቀቆ

*ወጥመድ* - ተጠቂውን ለመያዝ የታለመ የትኛውም መሣሪያ::

እነዚህ መሣሪያዎች ወፎችንና እንስሳትን ለመያዝ እንጂ፣ ሰዎችን ለማጥመድ የሚጠቀሙ አይደለም:: ነገር ግን ክፉ ሰው ልክ እንደ እንስሳ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔርን ከሕይወቱ አስወግዶታልና::

መንገደኛው ምንም ቢዘይድም፣ ከወጥመዱ ማምለጥ አይችልም፤ ብዙ ቢሞክርም እየደከመ ይሄዳል (ኢዮብ 18:7):: ጨለማ እና አደጋ ስለ ከበቡት፣ ተስፋ የለውም::

**(3) ወንጀለኛ ይፈለጋል (ኢዮብ 18:11-15)::** ሞት «የፍርሃቶች ንጉሥ» ነው (ቊ. 14):: እርሱ የትም ቢኖር ወንጀለኛን ለመያዝ የቈረጠ ነው:: ያመለጠ ወንጀለኛ በመንገድ ላይ ቢሮጥ እና ወጥመዶቹን ቢያመልጥ እንኳ፣ እርሱን ለማሳደድ ሞት ከረዳቶቹ አንዳንዱን ይልካል:: ፍርሃት ያስፈራዋል፣ መቅሠፍት ኃይሉን ያደክመዋል፣ ደግሞም ይወድቅ ዘንድ አደጋ ይጠብቀዋል (ቊ. 11-12፣ አ.መ.ት)::

የፈራው ወንጀለኛ እየደከመ እየደከመ ይሄዳል፣ ነገር ግን አሁንም ጉዞውን ለመቀጠል ይሞክራል:: ለመደበቅ ተመልሶ ወደ ድንኳኑ ቢሄድ እንኳ፣ አሳዳጆቹ ያገኙታል፣ ያስሩታል፣ ይጐትቱታል ወደ የፍርሃት ንጉሥም ይወስዱታል:: ሁሉንም ነገር ከድንኳኑ ይወስዳሉ፣ ድንኳኑንም ያቃጥላሉ፣ ከዚያም በዐመድ ላይ ዲንን ይበትናሉ:: የዚያ ሰው ፍጻሜ እሳትና ዲን ይሆናል!

**(4) የተነቀለ ዛፍ (ኢዮብ 18:16-21)::** አንዳንድ ጊዜ ሞት ወንጀለኛን እንደ መያዝ አስገራሚም ሆነ ቅጽበታዊ አይደለም:: ምናልባት ሞት ልክ እንደ ዛፍ መበስበስ ቀስ በቀስ የሚመጣ ሊሆን ይችላል:: ሥሮቹ ይደርቃሉ፣ ቅርንጫፎቹ መድረቅ ይጀምራሉ እንዲሁም የሞቱ ቅርንጫፎች አንድ በአንድ ይወድቃሉ:: ወዲያውም ዛፉ ሙሉ በሙሉ ይሞታል፣ ሰዎችም ይፈልጡታል:: የዛፉ ሞት በምሳሌነት የሚያሳየው የቤተሰብ የዘር ሐረግ ሁኔታን ነው:: ክፉ ሰው እራሱ ብቻ የሚቈረጥ አይደለም፣ ነገር ግን ቅርንጫፎቹ ሁሉም እንደዚሁ ይቈረጣሉ፤ ደግሞም ስሙን የሚሸከሙ ትውልዶች አይኖሩም:: (ሁሉም የኢዮብ ልጆች በዐውሎ ነፋስ እንደ ሞቱ አስታውስ::) በምሥራቅ፣ ቤተሰብን በሞት ማጣት እንደ ታላቅ ሰቆቃ ነበር የሚቈጠረው::

ኢዮብ ዛፍን የትንሣኤ ተስፋ ምሳሌ አድርጎ ነበር የተጠቀመበት (14:7-11)፣ ነገር ግን በልዳዶስ ከእርሱ ጋር አልተስማማም:: እንደ በልዳዶስ ከሆነ፣ ዛፉ አንድ ጊዜ ከተቈረጠ፣ ያ መጨረሻው ነው፤ ክፉ ሰው የወደፊት ተስፋ የለውም::

ምንም እንኳ በልዳዶስ ይህን ሊነግረው ለማይገባው ሰው ቢናገርና መንፈሱም የተሳሳተ ቢሆንም፣ ስለ ሞት የተናገረው ነገር ከልብ ሊወሰድ የሚገባው ነው:: ሞት ለመሞት ባልተዘጋጁ ሰዎች ሁሉ ዘንድ የሚፈራ ጠላት ነው (1ኛ ቆሮ. 15:26)፣ ደግሞም



የመዘጋጃው ብቸኛው መንገድ በኢየሱስ ክርስቶስ መታመን ነው (ዮሐንስ 5:24)::

አማኝ ለሆነ ክርስቲያን፣ ሞት በሰማይ ወዳለ አባት መሄድ ማለት ነው (ዮሐንስ 14:1-6)፤ በምድር ላይ ማንቀላፋትና በሰማይ መንቃት (የሐዋ. 7:60፤ ፊልጵ. 1:21-23) ነው፤ ወደ ዕረፍት መግባት ነው (ራእይ 14:13)፣ ደግሞም ወደ ታላቁ ብርሃን መሸጋገር ነው (ምሳሌ 4:18):: ጌታን ለድነታቸው የታመኑ ሰ ዎችን በልዳዶስ ከተናገራቸው ሥዕላዊ መግለጫዎች አንዱም አይመለከታቸውም::

## የሕይወት ፈተናዎች (19:1-29)

በልዳዶስ የሞት ፍርሃቶችን መዘርዘሩን በጨረሰ ጊዜ፣ ኢዮብ የገዛ እራሱን ሕይወት ፈተና በመዘርዘር ምላሽ ሰጠ:: «ፈተናዎችን ለመለማመድ መሞት አይኖርብኝም፣» ሲል ለጓደኞቹ ነገራቸው:: «እኔ በአሁኑ ሰዓት ፈተናዎቹን እየተለማመድኳቸው ነው፤ እናንተ ም ደግሞ ለዚህ ግድ ያላችሁ አይመስልም::»

**ስድቦች (ኢዮብ 19:1-4)::** ቃሎቻችን ወይ ሌሎችን ይጐዳሉ አሊያም ይፈውሱዋቸዋል፤ እኛ በሸክሞቻቸው ላይ እንጨምራለን ወይም ሸክሞቻቸውን በድፍረት እንዲሸከሙ እንረዳቸዋለን:: የኢዮብ ጓደኞች በቃላቸው ተረባረቡበት፤ በመከራዎቹ ሁሉ ፊት ጥቅም-አልባና ተስፋ-ቢስ እንደ ሆነ እንዲሰማው አደረጉት:: የሌ ሎችን ችግሮችና ትግሎች በተመለከተ ምን ያህል የሚሰማን ሰ ዎች ልንሆን ይገባል! ሰዎች መገሠጽ የሚስፈልጋቸው ቢሆኑ እንኳ በፍቅር ልናደርገው ያስፈልጋል፤ ደግሞም ቃሎቻችን ልባቸውን ሊደግፉ እንጂ፣ ሊጎዱዋቸው አይገባም::

«ኃጢአትን አድርጌ ቢሆን እንኳ የእኔ እንጂ የእናንተ ኃጢአት አይደለም:: እግዚአብሔር እና እኔ ነገሮችን ማስተካከል እንችላለን፣ ስለዚህ እኔን ተዉኝ» አለ ኢዮብ በቍጥር 19:4 ላይ:: ኢዮብ «ተ ሳስቼ» ብሎ የተጠቀመበት ቃል «ሆን ተብሎ ያልተፈጸመ ኃጢአት» የሚል ትርጉም ያለው ነው:: ኢዮብ ታማኝነቱን ጠብቋል ደግሞም እርሱ ለተቀበላቸው መከራዎች ሁሉ በቂ ምክንያት የማይሆኑ ኃጢአቶችን አልሠራም::

**ምሳሌዎች (ኢዮብ 19:5-12)::** በልዳዶስ የሞት ፍርሃትን በተ

መለከተ አራት አስፈሪ ሥዕላዊ መግለጫዎችን ሰጥቶአል፣ ስለዚህም የሕይወት ፈተናዎችን በተመለከተ ኢዮብ ሰባት ጉልህ ሥዕላዊ መግለጫዎችን በመስጠት ምላሽ የሰጠ ሲሆን፣ እነዚህ በዚያ ስፍራና በዚያን ጊዜ እርሱ እየተለማመዳቸው የነበሩ ናቸው!

1 *እንደ ተጠመደ እንስሳ የሆነ ይመስለዋል* (ቍ. 6)። ኢዮብ እራሱን በእግዚአብሔር መረብ እንደ ተያዘ አድርጎ ይመለከታል፣ ይህም በኃጢአቱ ምክንያት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ስላጠመደው ነው። በልዳዶስ የሚያመልጥ ወንጀለኛን የሚይዙ ስድስት የተለያዩ ዓይነት ወጥመዶችን ይዘረዝራል (18:7-10)፣ ነገር ግን ኢዮብ በዚያ ሥዕል ውስጥ እራሱን አላስቀመጠም። እርሱ ከእግዚአብሔ ር አልሸሸም፣ በኃጢአት የሚከሰስ አይደለም። ኢዮብ ሊረዳው በማይችል ምክንያት በቅጽበት በወጥመዱ የያዘው እግዚአብሔር ነበር።

2. *በፍርድ ቤት እንደ ቀረበ ወንጀለኛ የሆነ ያህል ይሰማዋል* (19:7)። እርሱን በመያዝና ፍርድ ቤት በማቅረቡ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ የተሳሳተ ነገር ፈጽሞአል። ምንድን ነው ያደረገው? ክሶቹ ለእርሱ ስለ ምን አልተነበቡለትም? እራሱን እንዲከለክል ለምን አልተፈቀደለትም? «ተበደልሁ ብዬ ብጮኽ ማንም አይመልስልኝም» (ቍ. 7፣ አ.መ.ት)። በመላው መጽሐፉ ውስጥ ኢዮብ ስለ ፍትሕ ይለምናል ደግሞም በእግዚአብሔር ፊት እንዲሟገትለት ጠበቃን ለማግኘት ይጮኻል። ኢዮብ ያልተገነዘበው ነገር ቢኖር *እርሱ ለእግዚአብሔር ለመሟገት ጥብቅና የቆመ መሆኑን* ነበር! ሰይጣን ስሕተት መሆኑን ያረጋገጠውና ለእግዚአብሔር ክብርን ያመጣለት የኢዮብ እምነትና ጽናት ነበር።

3. ኢዮብ እራሱን *መንገዱ በአጥር እንደ ተዘጋበት ተጓዥ* ይመለከታል (ቍ. 8)። ኢዮብንና ቤተሰቡን እግዚአብሔር አጥሮ ከችግር በመጠበቁ ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ አጕረመረመ (1:9-12)። አሁን እግዚአብሔር መንገዱን ስለ ዘጋበት፣ ደግሞም መንቀሳቀስ ስላልቻለ ኢዮብ እያጕረመረመ ነው። እግዚአብሔር መንገዱን ስላጨለመበት፣ ኢዮብ ወዴት እንደሚሄድ ማየት አይችልም ነበር።

አንዳንዴ ልጆቹ ወዴት መሮጥ እንዳለባቸው በማያውቁት በሞት ጥላ መካከል ያለን ጨለማ እንዲለማመዱ እግዚአብሔር



ይፈቅዳል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ *እግዚአብሔር በእራሱ ጊዜ ብርሃንን እንዲለጣችሁ ጠብቁት።* የእራሳችሁን ብርሃን ለማመንጨት አትጣሩ ወይም ከሌሎች ብርሃንን አትዋሱ። የኢሳይያስን ጥበባዊ ምክር ተከተሉ፡- «ከእናንተ እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ የባሪያውንም ቃል የሚሰማ፣ በጨለማም የሚሄድ ብርሃንም የሌለው፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ስም የሚታመን፣ በአምላኩም የሚደገፍ ማን ነው?» (ኢሳ. 50:10)።

ዶ/ር ቦብ ጆንስ ትልቁ እንዲህ ይላሉ፣ «እግዚአብሔር በብርሃን ያስተማራችሁን ነገር በፍጹም በጨለማ አትጠርጥሩት።» እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በብርሃን ያስተማረን ነገር በጨለማ ውስጥ የበለጠ ትርጕም ያለው ነው የሚሆነው።

«አህ፣ በአንደበት ሊነገር የሚያዳግት 'የጨለማው ሀብት'!» በማለት ኦስዋልድ ቻምበርስ ጽፈዋል። «ይህ ፀሐይ የወጣችበት እና የውበት እንዲሁም የነፃነት ቀን አይደለም በነፍስ ላይ እስከ መጨረሻ የሚዘልቅና የማይልቅ ውጤትን የሚተወው፣ ነገር ግን በእነዚያ መንፈስ በሚሠራባቸው ምሽቶች፣ በእግዚአብሔር እጅ ጥላ በተደረገባቸው፣ ደረቅ በሆነ ምድር በጠቋቍሩ ዐለቶች ስንጣቂ ውስጥ በተደበቀ ቀን፣ በፊታችን የገዛ እራሱን ውበት ያሳልፈዋል።»

4. *የኢዮብ መከራ ከዙፋኑ እንደ ተወገደ ንጉሥ ሁኖ* እንዲሰማው አደረገው (ኢዮብ 19:9)። መከራዎቹ ከመምጣታቸው በፊት፣ በምሥራቅ ካሉ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ታላቅ እና በየዕ መሪ የነበረ ሰው ነበር (1:3፤ 29:1-25)፤ ነገር ግን አሁን ክብሩና ሥልጣኑ ሁሉ የለም። እግዚአብሔር ከእርሱ ላይ የእርሱን የነገሥታት አልባሳትና ዘውድ ወስዶበታል፣ ደግሞም ከከፍተኛነት ይልቅ ዝቅተኛው ሰው ሆኖአል። ምን ዓይነት መዋረድ ነው!

5. አምስተኛው *ሥዕላዊ መግለጫው የፈረሰ መዋቅር* ነው (19:10)። የእግዚአብሔር «ሠራዊቶች» ሲያልፉ ያፈረሱትና ከንቱ አድርገውት ያለፉት ቅጥር ወይም ሕንጻ ሊሆን ይችላል። ኢዮብ ተመልሶ የንግድ ሥራውን ጉዳዮች ወይም የቤተሰቦቹን ሁኔታ ይመለከት ይሆናል፣ ወይም ምናልባት የመነመነ ስለሆነው ሰውነቱ እያውጠነጠነ ያሰላስላል። ምንም ሆነ ምን፣ በአንድ ወቅት ጠቃሚና ጠንካራ የነበረው ሰው፣ አሁን ጥቅም-አልባና ደካማ

ሆኖአል። በልዳዶስ ስለ ፈረስ ድንኳን ተናግሮ ነበር (18:15)፣ ደግሞም ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ ኢዮብ ያውቃል።

6. በስድስተኛው *ሥዕል* ላይ፣ ኢዮብ *ከሥሩ የተነቀለ ዛፍ* ምስልን ተጠቅሞአል (19:10፤ 18:16) ተመልከት)። ኢዮብ ዛፉን እንደ ተስፋ ምሳሌ አድርጎ ተጠቅሞበታል (14:7)፣ ነገር ግን አሁን እንደ ጠፋ ተስፋ ምልክት ይመለከተዋል። ነገር ግን እዚህ ላይ ሥሩ ስለ ተነቀለ ዛፍ የሚናገር ሆኖ ሳለ፣ በኢዮብ 14 ውስጥ፣ ኢዮብ የተቈረጠ ዛፍን በተመለከተ ይናገራል። ከሥሩ መዋቅር ውጭ፣ ዛፍ ሊኖር አይችልም።

7. የኢዮብ የመጨረሻው *ሥዕል በጠላት የተያዘች ከተማ ናት* (19:11-12)። እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ ጦርነትን አውጇል (13:24) ደግሞም ልክ እንደ ጠላት ይመለከተዋል። ሠራዊቶቹ እርሱን አጥቅተውታል ደግሞም ለተጨማሪ ሰፋ ያለ ይዞታ በሰፍራው ላይ ተረጋግተው ተቀምጠዋል። አንድን ድንኳን ብቻ ለማጥቃት ስለ ተሰበሰበ ታላቅ ሠራዊት እስኪ አስቡ! እግዚአብሔ ር እጅግ ብዙ መከራ ለምን እንደ ላከ ኢዮብ የሚረዳው ነገር እንደሌለ በድጋሚ እናስታውስ። አንድ ድንኳንን ለማፍረስ አቶሚክ ቦንብ ለምን ያስፈልጋል?

**መገለል (ኢዮብ 19:13-22)**። መከራው ከሰዎች ጋር የነበረውን ግንኙነት እንዴት እንዳበላሸበት ኢዮብ ይገልጻል። ከልክ ያለፈና የተራዘመ *ሥቃይ* የሚሠቃዩ ሰዎችን ዘወትር ከሰዎችና በዙሪያቸው ካሉ ሁኔታዎች እንዲለዩ እንደሚያደርጉዋቸው መገንዘብ ይኖርብናል። ሰዎች በእውነት በሚጐዱበት ጊዜ፣ ገለል ወደ ማለቱና ሰዎች እኛ የምናልፍበትን ሁኔታ አይረዱትም ወደ ማለቱ ያዘነብላሉ። ኢዮብ በሕይወት ካሉት ቤተሰቦቹ፣ ከጓደኞቹ፣ እና ከአገልጋዮቹም እንኳ የተገለለ መሆኑ ይሰማው ነበር።

ነገር ግን ለኢዮብ መገለል ከሥቃይ በላይ የሆነ ምክንያትም ነበር። እርሱ አሁን ችግር ላይ ወድቋል ደግሞም ታሟል፣ በከተማይቱ ቆሻሻ መጣያ ስፍራ እየኖረ ነበር፤ እንዲሁም ማንም ሰው ከእርሱ ጋር መገኘት አይፈቅድም ነበር። ከዚህም በላይ፣ ኢዮብ በእግዚአብሔር ፍርድ እየተሠቃየ ያለ ኃጢአተኛ ነው ብለው ሰዎች ያምኑ ነበር፣ ስለዚህ ለምን ሲባል የእርሱ ጓደኞች ይሆናሉ። መልኩ (ገጽታው) የሚያቀርብ ስላልነበረ፣ እናም ሰዎች እርሱን



መመልከትን ያቆማሉ።

የጌታችንን ርኅራኄ የሚያመለክተው አንዱ ማስረጃ፣ ከተጣሉ ሰዎች ጋር አብሮ መሆኑ ነው። «ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር በልቷል» (ማቴ. 9:9-13)፣ ለምጻሞችን ዳስሷል (ማቴ. 8:1-4)፣ ከሴተኛ አዳሪዎች ስጦታዎችን ተቀብሏል (ሉቃስ 7:36-50)፣ እንዲሁም በሁለት ወንጀለኞች መካከል ተሰቅሎአል (23:32-33፣ኢ.መ.ት)። ኢየሱስ «በሰዎች የተናቀና የተጠላ የሕመም ሰውና ሥቃይ ያልተለየው» ሰው መሆን (ኢሳ. 53:3) ምን ማለት እንደ ሆነ ያውቃል። እኛ ደቀ መዛሙርቱ እንደዚህ ያለ ርኅራኄ ያለን መሆኑ ምን ያህል ጠቃሚ ነገር ነው። በመከራ ውስጥ በሚያልፉበት ጊዜ ከምናውቃቸውና ከምንወዳቸው ሰዎች ጋር አብሮ መሆን ቀላል ነገር ነው፣ ነገር ግን የሚረዳቸው የሌላቸውን፣ ድሆችን እና በመከራቸው ውስጥ ሳሉ ቸል የተባሉትን ዝቅ አድርገን እንመለከታቸዋለን።

በኢዮብ 19:20 ላይ ያለው የኢዮብ ንግግር ታዋቂ ሆኖአል፣ ነገር ግን ምሳሌው በተሳሳተ ትርጉም የሚረዱት ሆኖአል፦ «አጥንቴ ከቁርበቴና ከሥጋዬ ጋር ተጣበቀ፣ ድድ ብቻ ቀርቶልኝ አመለጥሁ»። ይህ ብዙውን ጊዜ «በጥርሴ ቆዳ አመልጣለሁ፣» ማለትም «እኔ ለትንሽ አመለጥሁ!» በሚል ይተረጐማል (ይረዱታል)። (በጥርሳችን ላይ ቆዳ ካለ ምን ያህል ውፍረት ይኖረው ይሆን?) ነገር ግን የዕብራይስጡ ምንባብ «ከ-ጋር» እንጂ፣ «በ» አይልም ደግሞም በትርጉሙ ላይ የመጻሕፍት ትርጓሜ የሚሠሩ ሊቃውንት አይስማሙበትም።

አንዳንዶች ኢዮብ እንዲህ ማለቱ ነው፣ «እጅግ ከመሰለሉ የተነሣ፣ የቀረው ቁርበቴ ብቻ!» ነገር ግን ድድ ሁልጊዜ የጥርስ ቆዳን የሚያመለክት አይደለም። «በጥርሶቼ ላይ ቆዳ ያለ ከሆነ፣ እንዲህ ባለ መልክ ለሞት ቀርቤአለሁ!» ወይም «ሰውነቴ እጅግ ከመበላቱ የተነሣ የቀረኝ ነገር ቢኖር የጥርሴ ቆዳ ነው!» (በእርግጥም እርሱ እየጋነነ ነበር።) የቱም ነገር በኢዮብ አእምሮ ውስጥ ይገኝ፣ ምስሉ አንድ ነገርን በግልጥ ያሳያል፦ ኢዮብ እየኖረ ያለው በተአምር ነበር።

ኢዮብ ንጽሕናውን እንዲቀበሉ ወዳጆቹን እንዲያዝኑለት እየጠየቀ በዚህ ክፍል የሚያቀርበውን መከላከያውን ይደመድማል

(ቍ. 21-22፤ 6:14)። እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ተነሥቷል፣ ቤተ ሰቡ እና ጓደኞቹ ትተውታል፣ አሁን የቀሩት ልክ የዱር እንስሳ ግዳዩን እንደሚያሳድድ እርሱን በተቃውሞ የሚያሳድዱት ሦስት ጓደኞቹ ብቻ ነበሩ። ይህን አቋመው እርሱን መርዳት አይችሉምን? ስለ ምን እንደዚህ ያለ ጨካኝ ልብ ይኖራቸዋል?

**ልዩ መረዳት (ኢዮብ 19:23-29)።** ኢዮብ *ቃሎቹ* በቋሚነት ተ ቀርጸው እንዲቀመጡለት ለምን ፈለገ? እግዚአብሔር እርሱን ነፃ ከማውጣቱ በፊት እንደሚሞት አሰበ፣ ደግሞም እንዴት እንደ ተ ሠቃየ እና ምን እንደ ተናገረ ሰዎች እንዲያስታውሱ ፈለገ። በልዳዶስ እንዲህ ሲል አስጠንቀቃቸው፣ «መታሰቢያው ከምድር ይጠፋል» (18:17)፣ ኢዮብ ግን ስለ እርሱ የጽሑፍ ማስታወሻ እንዲኖር ፈለገ።

በዚህ ጊዜ፣ ኢዮብ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አግንኖ ያስቀመጣቸውን ብዙ የኀዘንና የሥቃይ መግለጫዎቹን የሚመለከት ሌላውን የእምነት ንግግር ተናገረ። ኢዮብ ጥልቅ ከሆነ ተስፋ መቍረጥ ወደ እምነት ከፍታ እየሄደ መሆኑ ጕልህ ነው፣ ከዚያም ደግሞ ተመልሶ ወደ ተስፋ መቁረጥ ይመጣል። *ይህ በታላላቅ መከራዎች ውስጥ የሚያልፉ ሰዎች ዘወትር የሚለማመዱትና የሚያዘወትሩት ነገር ነው።* ሰማያት ጥቁርና ነጕድጓዳማ ይሆናሉ፣ ከዚያም በቅጽበት የብርሃን ጨረር ይወጣል፣ ቀጥሎም ደግሞ ነጐድጓዱ ተመልሶ ይመጣል።

አንዳንድ ሰባኪዎች ምንም ይበሉ፣ ከባድ በሆነ ሥቃይና ፈተና ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ ቋሚ በሆነ የእምነት ከፍታ እና መተ ማመን (ድፍረት) ውስጥ የሚገኙ እጅግ ጥቂት ሰዎች ናቸው። በአንድ ወቅት እንግሊዝኛ ተናጋሪ በሆነው ዓለም ታዋቂ የነበረው ታላቁ ሰባኪ ጆን ሄነሪ ጆዌት፣ ለጓደኛው እንዲህ ሲል ጻፈ፡- «እኔ እንዲህ ያለሁ ቅዱስ እንደ ሆንሁ እንደማታስበኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ውጣ ውረዶች የሌሉብኝ ነገር ግን በማይቋረጥ ደስታና በአስቸጋሪ ወቅትም መረጋጋት ውስጥ ቀጥ ባለ መንፈሳዊ አኪያሄድ የምመላለስ ይመስልሃል። ይህ በምንም ዓይነት የሚሆን አይደለም! እኔ ዘወትር ፍጹም ምስኪን እሆናለሁ፣ ደግሞም ሁሉም ነገር እጅግ ጨለማ ይሆንብኛል» (አርቱር *ፖሪት፣ ጆን ሄነሪ ጆዌት፣ 290)።*



በ19:25-27፣ ኢዮብ ቢሞት እንኳ አንድ ቀን በምድር ላይ የሚፈርድ ቤዛ እንዳለው ይገልጻል። ከዚህም በላይ እርሱ እራሱ እንደሚኖርና ቤዛውን እንደሚያየው ይጠባበቃል! «ቈዳዬ ቢጠፋም፣ ከሥጋዬ ብለይም፣ እግዚአብሔርን አየዋለሁ» (ቍ. 26፣ አ.መ.ት)። ይህም በሥጋ ትንሣኤ ላይ ያለ እምነት ማረጋገጫ ነበር።

በቍጥር 25 ላይ «የሚቤዠኝ» በሚል የተተረጐመው የዕ ብራይስጥ ቃል፣ የወንድሙን ደም የሚበቀል የቅርብ ዘመድ (ዘዳግ. 19:6-12)፣ የወንድሙ ንብረትን የሚወርስና የሚያስተዳድር (ዘሌዋ. 25:23-24፤ 39-55) እንዲሁም ወንድሙን ከባርነት ነፃ የሚያወጣ (25:25) ማለት ነው። የቅርብ ዘመድ የሆነ ተቤዢ ስሕተት የፈጸመ ዘመዱን በመተካት ፍርድ ቤት የሚቆምም ጭምር ነው (ምሳሌ 23:10-11)። በመጽሐፈ ሩት ውስጥ፣ ቦዔዝ ሩትን ለመቤዠት እና በአዲስ ምድር ውስጥ አዲስ ሕይወትን ሊሰጣት ፈቃደኛም መሆን የሚችል የቅርብ ዘመድ የሆነ ተቤዢ ነው።

ቀደም ብሎ፣ ኢዮብ ዳኛ (ኢዮብ 9:33-34) እንዲሁም በሰማይ ጠበቃ ለማግኘት (16:19) መፈለጉን ተናግሮአል። አሁን ይህን አሳብ ባለቀ ሁኔታ አስፋፋው፡- የሚቤዠው አንድ ቀን ነፃ ያወጣዋል፣ ደግሞም ኢዮብ ይህንን ለመመስከር በዚያ ይገኛል! ስለ ወደፊቱ ሕይወት በኢዮብ ዘመን ምን ያህል እምነት የሆነ ነገር እንደ ገለጸ ልብ በምትልበት ጊዜ፣ እነዚህ ቃሎች ሊሰመርባቸው የሚገቡ የእምነት ምስክርነቶች ይሆናሉ። ይህን የኢዮብ ጓደኞች በገለጹበት ተስፋ ማስጨለም እና በገዛ እራሱ ከባድ መከራ ላይ በምትጨምሩበት ጊዜ፣ የኢዮብ ምስክርነት እጅግ አስደናቂ ይሆናል።

በእርግጥ፣ ይህ የቅርብ ዘመድ የሆነ ተቤገር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እግዚአብሔርን ይገልጥልን ዘንድ የሰውን ሥጋ ለበሰ፣ እኛ ልንሠቃየው የሚገባውን ሥቃይ ሁሉ ተቀበለ፣ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፣ ከዚያም ደግሞ በእግዚአብሔር አብ ፊት እኛን ሊወክል ወደ ሰማይ ተመለሰ። እርሱ ለማዳን ፈቃደኛ ነው፤ ይችላልም። አንድ ቀን በምድር ላይ ይቆምና ይፈርዳል፤ ደግሞ የገዛ እራሱ ሕዝቦችን ነፃ ያደርጋል።

ኢዮብ ለሦስት ተቺ ጓደኞቹ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ንግግሩን ይቋጫል (19:28-29)፡- እነርሱም እንደዚሁ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ለፍርድ ይቆማሉ፣ ስለዚህም ቢዘጋጁ መልካም ነው። ኃጢአተኛ ስለ መሆኑ ኢዮብን ከሰውታል፣ *ነገር ግን እነርሱስ* እንደዚሁ ኃጢአተኞች አይደሉም ወይ? እግዚአብሔር ስለ ኃጢአቱ ኢዮብን እየቀጣው ነው ብለዋል፣ *ነገር ግን በእነርሱስ* ላይ አይፈርድባቸውም ወይ? አንድ ቀን ለኢዮብ እና ስለ ኢዮብ በተናገሩት ነገር ላይ ለእግዚአብሔር መልስን ይሰጣሉ፤ ስለዚህ ቢጠነቀቁ ይሻላል። የኢዮብ ቃሎች በሮሜ 14:10-13 ያለውን የጳውሎስን ቃልና በማቴዎስ 7:1-5 ያለውን የጌታችንን ማስጠንቀቂያ ያስታውሱናል።

አብርሃም ሊንከን በአንድ ወቅት እንዲህ አለ፣ «ለመርዳት የሚሆን ልብ ያለው ሰው እርሱ ለመተቸት መብት አለው።»

ይህን ታሚላላችሁን?



# ለግል ምልከታና ለቡድን ውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ፍርሃት ውጤታማ በሆነ መልካም ሆነ ውጤታማ ባልሆነ መልኩ ለመቀስቀሻነት ጥቅም ላይ ውሎ ያየህበትን ጊዜ አብራራ።

2. በሁሉን ቻይነቱ ለእግዚአብሔር ያለንን አክብሮት በምንገልጽበት ፍርሃትና በልዳዶስ የኢዮብን ጭንቀላት በመታበት ፍርሃት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

3. ከተሞክሮህ፣ ሞት ልክ እንደሚጠፋ ብርሃን የሚሆንባቸውን ጥቂት መንገዶች ጥቀስ።

4. ልቡ በመንግሥተ ሰማይ ጉዳይ በተያዘና አማኝ ባልሆነ ሰው አመለካከት መካከል ያለን ልዩነት አብራራ።

5. ኢዮብ የሕይወት ትግሉ በወጥመድ እንደ ተያዡ እንስሳት ወይም እንደ ተነቀለ ዛፍ መሆኑን አብራርቶታል። የሕይወት ትግልን በየትኞቹ ሌሎች መንገዶች ልትመስላቸው ትችላለህ?

6. 1 ለ 10 በሆነ መለኪያ (1=ሙሉ መገለል፣ 10=ከቶ ብቸኛ

አለመሆን) በትግሎች ውስጥ በምታልፍበት ጊዜ፣ ምላሽ የምትሰጠው እንዴት ነው? ከሰዎች ትርቃለህ ወይስ ወደ እነርሱ ትቀርባለህ?

7. እየታገሉ ያሉ ሰዎችን በምትመለከትበት ጊዜ፣ ከእነርሱ ጋር «ወደ እነርሱ ዓለም ዘልቆ ለመግባት» አስቸጋሪ የሚያደርገው ምንድን ነው?

8. በመከራ (በትግል) ውስጥ ያሉ ሰዎች አንዳንዴ በጣም የሚያስፈልጋቸውን ርኅራኄ የሚገፋባቸውን ጥቂት ምክንያቶች ስጥ።

9. 1 ለ10 በሆነ መለኪያ (1= መፍራትና መንቀጥቀጥ፣ 10= እየፈኩ መዘጋጀት) ስለ እራስህ ሞት ከአሥር ዓመታት በፊት ያለህን ዝንባሌ እንዴት ታብራራዋለህ? አሁን ያለህ ግንዛቤስ ምንድን ነው?





# ሁሉም ነገር በአመለካከትህ ይወሰናል
## (ኢዮብ 20-21)

«ለተጠቃ ሰው ልንሰጠው የምንችለው እውነተኛ እርዳታ ሸክሙን ከእርሱ ላይ ማንሣት አይደለም፣ ነገር ግን ሊሸከምበት የሚችለውን የእርሱን ምርጥ የሆነ ጥንካሬ መገንባት ነው።»

- ፊሊፕስ ብሩክስ

ሶፋር ቀጣዩ ተናጋሪ ነው፣ ነገር ግን የሚናገረው አዲስ ነገር የለውም። ያንኑ አሮጌ ታሪክ ነው የሚያወራው፦ ይህም እግዚአብሔር ክፉዎችን ይቀጣል፣ ስለዚህ ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር ነገሩን ቢያስተካክል መልካም ነው የሚል ነበር። ቊልፍ የሆነው ምንባብ ኢዮብ 20:5 ነው፦ «የኃጢአተኞች መፈንጨት ለአጭር ጊዜ፣ የክፉዎችም ደስታ ለቅጽበት መሆኑን አታውቅምን?» ይህን አሳብ ቀድሞውኑ በልዳዶስ (8:11-19፤ 18) እና ኤልፋዝ (15:20-35) ያነሡትና የተናገሩት ነበር። ነገር ግን ሶፋር በኢዮብ የመጨረሻ ንግግር እጅግ በመረበሹ ምክንያት መናገር እንዳለበት ተሰማው። «የሚያቃልለኝን ንግግር ሰምቻለሁ፤ መልስም እሰጥ ዘንድ መንፈስ ገፋፋኝ» (20:3፣ አ.መ.ት)። ሶፋር በኢዮብ የተሰደበ መሰለው፣ ስለዚህም እራሱን ለመከላከል ወሰነ።

### የክፉዎች አስቃቂ ዕጣ ፈንታ (20:4-29)

የክፉዎች ዕጣ ፈንታ በእርግጥ የሚያሳዝን እንደ ሆነ ለማረጋገጥ ሶፋር ሦስት ማረጋገጫዎችን አቀረበ፦ የሕይወት ዘመናቸው

**አለመሆን) በትግሎች ውስጥ በምታልፍበት ጊዜ፣ ምላሽ የምትሰጠው እንዴት ነው? ከሰዎች ትርቃለህ ወይስ ወደ እነርሱ ትቀርባለህ?**

**7. እየታገሉ ያሉ ሰዎችን በምትመለከትበት ጊዜ፣ ከእነርሱ ጋር «ወደ እነርሱ ዓለም ዘልቆ ለመግባት» አስቸጋሪ የሚያደርገው ምንድን ነው?**

**8. በመከራ (በትግል) ውስጥ ያሉ ሰዎች አንዳንዴ በጣም የሚያስፈልጋቸውን ርኅራኄ የሚገፉባቸውን ጥቂት ምክንያቶች ስጥ::**

**9. 1 ለ10 በሆነ መለኪያ (1= መፍራትና መንቀጥቀጥ፣ 10= እየፈኩ መዘጋጀት) ስለ እራስህ ሞት ከአሥር ዓመታት በፊት ያለህን ዝንባሌ እንዴት ታብራራዋለህ? አሁን ያለህ ግንዛቤስ ምንድን ነው?**





# ሁሉም ነገር በአመለካከትህ ይወሰናል

## (ኢዮብ 20-21)

«ለተጠቃ ሰው ልንሰጠው የምንችለው እውነተኛ እርዳታ ሸክሙን ከእርሱ ላይ ማንሣት አይደለም፣ ነገር ግን ሊሸከምበት የሚችለውን የእርሱን ምርጥ የሆነ ጥንካሬ መገንባት ነው::»

- ፊሊፕስ ብሩክስ

ሶፋር ቀጣዩ ተናጋሪ ነው፣ ነገር ግን የሚናገረው አዲስ ነገር የለውም:: ያንኑ አሮጌ ታሪክ ነው የሚያወራው:- ይህም እግዚአብሔር ክፉዎችን ይቀጣል፣ ስለዚህ ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር ነገሩን ቢያስተካክል መልካም ነው የሚል ነበር:: ቊልፍ የሆነው ምንባብ ኢዮብ 20:5 ነው:- «የኃጢአተኞች መፈንጨት ለአጭር ጊዜ፣ የክፉዎችም ደስታ ለቅጽበት መሆኑን አታውቅምን?» ይህን አሳብ ቀድሞውኑ በልዳዶስ (8:11-19፤ 18) እና ኤልፋዝ (15:20-35) ያነሡትና የተናገሩት ነበር:: ነገር ግን ሶፋር በኢዮብ የመጨረሻ ንግግር እጅግ በመረበሹ ምክንያት መናገር እንዳለበት ተሰማው:: «የሚያቃልለኝን ንግግር ሰምቻለሁ፤ መልስም እሰጥ ዘንድ መንፈስ ገፋፋኝ» (20:3፣ አ.መ.ት):: ሶፋር በኢዮብ የተሰደበ መሰለው፣ ስለዚህም እራሱን ለመከላከል ወሰነ::

### የክፉዎች አሰቃቂ ዕጣ ፈንታ (20:4-29)

የክፉዎች ዕጣ ፈንታ በእርግጥ የሚያሳዝን እንደ ሆነ ለማረጋገጥ ሶፋር ሦስት ማረጋገጫዎችን አቀረበ:- የሕይወት ዘመናቸው

አጭር ነው (ኢዮብ 20:4-11)፣ ደስታቸው ጊዜያዊ ነው (ቍ. 12-19)፣ እንዲሁም ሞታቸው ሥቃይ ያለበት ነው (ቍ. 20-29)::

**(1) የሕይወት ዘመናቸው አጭር ነው (ኢዮብ 20:4-11)::** ሶፋር ከሰው ታሪክ ጅማሬ አንሥቶ የክፉዎች ድል መንሣት («ሳቅ») ለአጭር ጊዜ ነው የሚለውን አወጀ:: ይህን መረጃ ከየት አገኘ ብለን እንደነቃለን፣ ምክንያቱም የጥፋት ውኃን ከመላኩ በፊት ጌታ 120 ዓመታት ታግሦአል (ዘፍጥ. 6:3)፣ ደግሞም በእነርሱ ላይ ከመፍረዱ በፊት ጌታ ለክፉዎቹ ከነዓናውያን ቢያንስ ቢያንስ አራት ክፍለ ዘመናትን ሰጥቶአቸዋል (15:13-16)::

በዓለም ላይ የመጣውን ክፉ እንቆቅልሽ በተመለከተ፣ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የምናገኛቸው ብዙዎች ሰዎች ጻድቃን ብዙ ሲሠቃዩና ገና በለጋነት ዕድሜ ሲሞቱ ሳሉ፣ ክፉዎች ረጅም የሕይወት ዘመንን በደስታ ያሳልፋሉ:: ደግሞም ከችግር ነፃ ናቸው በሚል አሳብ የሚደነቁ ናቸው [መዝ. (37):73፤ ኤር. 12:1-4]:: ሶፋር የሚናገርበትን ነጥብ በማስረጃ ለማስረገጥ ብዙ መረጃዎችን ሆን ብሎ ደብቋቸዋል::

ሶፋር እንዳለው ከሆነ፣ ክፉ ሰው በስኬት ወደ ላይ ከፍ ከፍ እያለ በሄደ መጠን፣ ፍርድ በሚመጣበት ጊዜ ደግሞ አወዳደቁ ከፍተኛ ነው የሚሆነው:: እርሱ በሚወድቅበት ጊዜ፣ ልክ እንደ ገዛ እራሱ ዕዳሪ ወደ ታች ይወድቃል፤ ደግሞም ሰዎች «የት ነው ያለው?» (ኢዮብ 20:6-7) ብለው ይጠይቃሉ:: ልክ እንደ ተረሳ ሕልም ወይም እንደ ምሽት ራእይ ይጠፋል (ቍ. 8)::

የክፉ ሰው ማንነት እና ስም ብቻ የሚጠፉ አይደሉም፣ ነገር ግን ሀብቱም ጭምር ይጠፋል:: ከሞተ በኋላ በሕይወቱ ውስጥ የነበሩ ወንጀሎች መታወቅ ይጀምራሉ:: ደግሞም አባታቸው ለዘረፋቸው ሰዎች ክፍያ ለመመለስ ውርሳቸውን ይጠቀማሉ:: በሞተ ጊዜ አባታቸው «በአፍላ ወጣትነት ላይ» ነበር (ቍ. 11፣ አ.መ.ት)፣ ነገር ግን አሁን ሕይወት-አልባ ሆኖ በመቃብር ውስጥ ተጋድሞአል:: እንደ ሶፋር አነጋገር፣ ክፉዎች ገና ወጣት ሳሉ እና ሳይጠባበቁት ይሞታሉ::

መንፈሳዊውንም ሆነ ዓለማዊውን ሁለቱንም ታሪክ በምትመረምሩበት ጊዜ፣ መቼ ክፉዎች ወይም መቼ ጻድቃን እንደሚሞቱ የምትወስኑበት ግልጽ የሆኑ ሕጎች (መመሪያዎች) የሉም::



በአጠቃላይ አነጋገር፣ የእግዚአብሔርን ሕጎች ችላ የሚሉ ሰዎች ቶሎ ወደ ሞት ለሚመሩ ችግሮች የተጋለጡ ናቸው:: የፍትወተ ሥጋ ንጽሕና መጓደል፣ የአደንዛዥ ዕፅ (አልክሆልና ትንባሆን ጨምሮ)፣ መጠቀም እንዲሁም ግድ-የለሽ አኗኗር የሰውን ሕይወት ለማሳጠር ይረዳሉ፤ ነገር ግን ይህ እንደሚከሰት ዋስትና የለም:: መንፈሳዊ ያልሆኑ (ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌላቸው) ሰዎች እስከ ሽምግልና ዕድሜ ድረስ የሚኖሩ መሆናቸው የሚያስገርም ነው:: ምናልባት ንስሐ የሚገቡበትን ዕድል መስጠቱ ይህ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው::

ሶፋር የክፉ ሰው ሕይወት የሚያመጣውን የሚጠበቅ ውጤት እየተናገር አይደለም፣ ነገር ግን በኃጢአተኞች ላይ የሚደርሰውን የእግዚአብሔርን ፍርድ እየተናገረ ነበር:: ሶፋርና ሁለቱ ጓደኞቹ ኢዮብ ግብዝ እንደ ነበር እርግጠኞች ነበሩ፣ ማለትም የተቀደሰ ሕይወቱ የተደበቀ ኃጢአቱን የሚከድን ነበር:: በሁለተኛው ዙር ንግግሩ፣ ኤልፋዝ ኢዮብ ከሠራቸው ኃጢአቶች አንዳንዶቹን ይጠቅስ ነበር (22:5-9)! ነገር ግን እግዚአብሔር ሁልጊዜ በግብዝነት በሌሎች ኃጢአተኞች ላይ ወዲያውኑ አይፈርድም፣ እንዲሁም የወጣት ሰው መሞት እርሱ ወይም እርሷ ግብዝ ስለ መሆናቸው ማስረጃ አይሆንም::

መንፈሳዊ የሆነው ስኮትላንዳዊው የፕሪስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ፣ ሮቤርት ሙሬይ ምክቼን ገና የሃያ ዘጠኝ ዓመት ወጣት ሳለ እንዲሁም የወንጌል መልእክተኛ የሆነው ዊሊያም ኋይቲንግ ቦርደን («የዬል ቦርደን») በግብፅ ሲሞት ገና የሃያ አምስት ዓመት ወጣት ነበር:: በትውልዳቸው አሜሪካዊ ለሆኑት የወንጌል መልእክተኛ የነበረው ዴቪድ ብሬይነርድ በሚሞትበት ጊዜ ዕድሜው ሃያ ዘጠኝ ነበር:: በሶፋር አነጋገር መሠረት፣ እነዚህ ሰዎች የተደበቀ ኃጢአት ያለባቸው ነበሩ ማለት ነው፣ ስለዚህም ደግሞ እግዚአብሔር ገና በለጋነት ዕድሜያቸው ወሰዳቸው::

**(2) ደስታቸው ጊዜያዊ ነው (ኢዮብ 20:12-19)::** ሶፋር እዚህ ላይ ዋነኛ ተምሳሌታዊ ያደረገው መብላትን ነበር:: ክፉው ሰው፣ ሰዎች ምግብ መመገብ ደስ እንደሚላቸው ዓይነት፣ ኃጢአት መሥራትን ደስ ይለዋል፣ ምግቡን ከመዋጡ በፊት «ጣዕሙ»ን

በአፉ ውስጥ አድርጎ ያጣጥመዋል። በእርግጥ፣ እርሱ ኃጢአትን በጣም ይደሰትበታል፣ እንዲውጠውም አይገደድም! ነገር ግን በአፉ ያለ ያ ምርጥ ምግብ በመጨረሻው ላይ በሰውነቱ ውስጥ መርዝ ይሆናል፣ ደግሞም ይታመምና ሁሉንም ነገር ያስታውከዋል። በኃጢአቱ እየተደሰተ ሳለ፣ መርዘኛ በሆነ እባብ እንደ ተነደፈ ወደ ሞትም እንደሚወስደው ልብ አይለውም። በሌላ አነጋገር፣ ኃጢአት ከእራሱ ጋር ደስታንም ሆነ ቅጣትን ይዞ ይመጣል፤ አንዱን ከፈለግህ፣ ሌላውንም መቀበል ይኖርብሃል። የኃጢአት ደስታ ለጊዜው ብቻ ነው (ዕብ. 11:25)።

ነገር ግን፣ የእግዚአብሔር ፍርድ ከዚህ የበለጠ ነገርንም ያካትታል፦ ክፉ ሰው በኃጢአቱ የሚታመም ብቻ ሳይሆን፣ በሕይወቱ የዕለት ተዕለት በረከቶች (ኢዮብ 20:17) «ማርና ቅቤ በሚያፈስሱ ጅረቶች በወንዞችም አያይም።» የከነዓን ምድር ወተ ትና ማር የምታፈስስ ምድር ናት» (ዘጸአ. 3:8፤ ዘሌዋ. 20:24)። ወተትና ማር መደበኛ ናቸው እንጂ የድሎት ምግቦች አይደሉም፤ ደግሞም «ወተትና ማር የምታፈስስ» ምድር ምርታማ ትሆናለች፣ ሕዝቡንም ልትመግብ ትችላለች። ነገር ግን ክፉ ሰው መሠረታዊ የሆነ የምግብ ጣዕምን ስለሚያጣ፣ ምንም የሚያረካው ነገር የለም። ኃጢአትን የሚያጣጥምበት ሁኔታ ደስታውንም ሆነ የሕይወትን መሠረታዊ በረከቶች አሳጥቶታል።

የመመገብን ሥዕላዊ መግለጫ በመጠቀም፣ ሶፋር ሁለት ነጥቦችን አበጅቶአል፦ ክፉ ሰው የሚውጠው ነገር ያሳምመዋል፣ ደግሞም የሕይወትን መልካም ነገሮች ለማግኘት ያለውን ፍላጎት ይወስድበታል። በኢዮብ 20:18-19 ላይ ሦስተኛ ነጥብን አበጅቶአል፡ - ይህ ክፉ ሰው ከደከመባቸው ነገሮች መካከል አንዳንዶቹን በደስታ ማጣጣም (አላምጦ መዋጥ) አይችልም። ሀብቱን በኃጢአት የሚያገኘው በመሆኑ፣ ሀብት አያረካውም።

ይህ ክርስቶስን ባልተቀበሉና በኃጢአት ለሚገኝ ደስታ እራሳቸውን በሰጡ ብዙ ሰዎች ሕይወት ውስጥ በእርግጠኝነት የሚንጸባረቅ ነው። አብልጠው በወደዱት መጠን፣ እንዲሁም የበለጠ በሚረኩበት ጊዜ፣ ደስታው እየቀነሰ ይሄዳል። ደስታቸው ሲቀንስ አሮጌዎቹን ነገሮች እንደ ገና መልሶ ለመውሰድ ብዙ ኃጢአትን ይሠራሉ፣ በሠሩም መጠን በየትኛውም ነገር ለመደሰት



ያላቸውን ዕድል ከንቱ ያደርጉታል። ምሥሉን ለመለወጥ፣ ሁኔታ ዎችን ሁሉ ይለዋወጧቸዋል፣ እና የሕይወት ሂደት ለአንድ ወቅት እንዳደረገው አሁን ከቶ አይሠራም።

**(3) ሞታቸው የሚያሳምም ነው (ኢዮብ 20:20-29)።** በክፉ ሰው ላይ የሚመጣን ሞት የእርሱ ብልጥግና እንኳ ሊከላከልለት አይችልም (ኢዮብ 20:20፤ ደግሞም መዝ. 49ን ተመልከት)። በብ- ልጥግናው እየተደሰተ ሳለ፣ ክፉ ሰው ጭንቀት፣ ኀዘን እንዲሁም አስፈሪ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቍጣ ይለማመዳል። እግዚአብሔር «በእርሱ ላይ መዓቱን ያወርድበታል» (ኢዮብ 20:23፣ አ.መ.ት)። ክፉ ሰው ሮጦ ለማምለጥ ይሞክራል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር በሰይፍ ይመጣበታል ደግሞም እርሱን የሚወጋውን የነሐስ ጫፍ ያለው ቀስት ይወረውርበታል።

እየተናገረ እዚህ ነጥብ ላይ እንደ ደረሰ፣ ሶፋር የበልዳዶስ ዓይነት ንግግር መናገር ጀመረ (ኢዮብ 18)። ክፉ ሰው ከእግዚአብሔር ፍርድ ለማምለጥ እንደሚጥር ይገልጣል። በጨለማው ውስጥ እየሮጠ ሳለ እና እሳቱ በዙሪያው ሲወድቅ፣ ቀስቱ በእርሱ ላይ ይመጣበታል። ከዚያም ጐርፍ ይመጣበትና ሁሉንም ነገር ጠራርጐ ያጠፋል። ነገር ግን የመጨረሻው አይደለም፦ ክፉው ሰው በመጨረሻ ሰማይና ምድር በእርሱ ላይ ወደሚነሡበትና ኃጢአተኛ ሆኖ ወደሚገኝበት ወደ ፍርድ ቤት ይወሰዳል (20:27)።

## የክፉ ሰው ትክክለኛው ፍጻሜ (21:1-34)

እንዲረዱትና እንዲያዝኑለት ለተጨማሪ አንድ ጊዜ ከለመናቸው በኋላ (ኢዮብ 21:1-6)፣ ኢዮብ ለሶፋር ንግግር ምላሽ ሰጠ እንዲሁም ለእያንዳንዳቸው የሚገባውን ተናገራቸው። ኢዮብ፣ ከእርሱ አመለካከት በመነሣት ክፉዎች ረጅም ዕድሜ እንደሚኖሩ (ቍ. 7-16)፣ ብዙውንም ጊዜ መከራ እንደማይደርስባቸው (ቍ. 17 -21)፣ እንዲሁም የክፉዎች ሞት ከሌሎች ሰዎች የተለየ እንዳልሆነ (ቍ. 22-34) ተናገረ። ኢዮብ የሶፋር ንግግርን በማጤን ነጥብ በነጥብ መልስ ሰጠና ነገሩን ብትንትን አደረገው።

ነገር ግን በመጀመሪያ፣ ምን እንደሚሰማው ይረዱት ዘንድ ኢዮብ ለጓደኞቹ ያቀረበውን አቤቱታ አዳምጡ። «በእውነት እኔን

ለማጽናናት የምትፈልጉ ከሆናችሁ፣ ዝም በሉና አዳምጡ» (ቊ. 2፣ በአጭሩ ሲቀርብ):: ዜኖ የተባለው የግሪክ ፈላስፋ እንዲህ አለ፣ «ሁለት ጆሮዎችና አንድ አፍ ብቻ ሊኖረን የቻለበት ምክንያቱ ብዙ እንድናደምጥና ትንሽ እንድናወራ ነው::» የኢዮብ ጓደኞች ብዙ ቃሎች ኢዮብን ያጽናኑታል ብለው አሰቡ፣ ነገር ግን እርሱ ጸጥታቸው የበለጠ እንደሚያበረታው ተናገረ (13:3)::

ኢዮብ የሚያጉረመርመው በሰው ላይ ሳይሆን፣ በእግዚአብሐር ላይ እንደ ሆነ አመለከተ:: ሰዎች መከራውን አላመጡበትም፣ ስለዚህ መከራዎቹን ሰዎች ሊያስወግዱዋቸው አይችሉም:: ትዕግሥት ያጣ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ስላልመለሰለት ነበር (ቊ. 3):: እግዚአብሔር በቆየ መጠን፣ የኢዮብ ሁኔታ የባሰ እየሆነ ይሄዳል:: «ተመልከቱኝና ተገረሙ፤ አፋችሁን በእጃችሁ ለጉሙ» (21:5፣ አ.መ.ት)::

ኢዮብ ሊናገረው የፈለገውን ነገር እያሰላሰለ ባለ ጊዜ፣ ወደ ጥልቀት ውስጥ ገፋፋው (ቊ. 6):: ይህ ከጭንቅላቱ የመነጨ አሳብ አልነበረም፣ ምክንያቱም ከሕይወትና ሞት መሠረታዊ እውነታዎች ጋር የተያያዘ ነበር:: የኢዮብ ጓደኞች እርሱ በነበረበት ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑ፣ ነገሮችን በተለየ መንገድ ይመለከቷቸውና፣ ነገሮችንም በተለየ መልኩ ይናገሯቸው ነበር::

**የክፉ ሰዎች ዕድሜ ምናልባት ረጅም ሊሆን ይችላል (ኢዮብ 21:7-16)::** የሶፋርን ምንባብ በሚቃረን መልኩ (20:5)፣ ኢዮብ እንዲህ አለ፡- «ኀጢአተኞች ለምን በሕይወት ይኖራሉ? ለምንስ እያየሉ ይሄዳሉ?» (21:7):: በሁሉም አቅጣጫ ዋስትና አላቸው፡- ልጆቻቸውና ቤቶቻቸው በመልካም ሁኔታዎች ላይ ናቸው (ቊ. 8-9፣ 11-12)፣ ንግዳቸው እየደረጀ ይሄዳል (ቊ. 10)፣ ደግሞም ብልፅግናቸውን በደስታ የሚጠቀሙበት ረጅም ዕድሜ ይኖራቸዋል (ቁ. 13):: የቤተሰብ ሀብት የሚካፈሉና የሚደሰቱበት ብዙ ዘሮች አላቸው:: የክፉዎች ሞት ድንገተኛ ነው፤ በስቃይ ውስጥ አያልፉም ደግሞም ነፃ ለመውጣት ረጅም ዘመን አይጠብቁም:: በእርግጥ፣ የኢዮብ ሁኔታ የዚህ ተቃራኒ ነበር፡-ቤተሰቦቹ ተደምስሰዋል፣ ሀብቱ ጠፍቷል፣ ደግሞም የሚመጣበትን ሞት እየተጠባበቀ በታላቅ መከራ እየተሠቃየ ነበር::

ነገር ግን ስለ ክፉዎች ሰዎች አሳዛኙ ነገር ከሕይወታቸው



እግዚአብሔርን ያስወጡበት መንገድና ይህም ሁሉ ሆኖ የሚበለጽጉበት ሁኔታ ነው (ቊ. 14-15):: ከእግዚአብሔር ጋር ምንም ነገር ማድረግ አይፈልጉም፤ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ለእርሱ እንደዚህ ይሉታል፡- «ከእኛ ራቅ! ለብቻችን ተወን!» ወደ እግዚአብሔር መጸለይን እንቢ ብለዋል፣ እርሱን መታዘዝን ወይም ለስኬታቸው እርሱን ማመስገንን ትተዋል:: ይህ ዛሬ የብዙዎቹ ያላመኑ ሰዎች ፍልስፍና ነው፤ ምናልባትም «ተግባራዊ ከሃዲነት» ብላችሁ ትጠሩት ይሆናል (መዝ. 10ን ተመልከቱ):: በዕቅዳቸው ይቅርና እግዚአብሔር በአሳባቸውም ውስጥ የለም (ያዕቆብ 4:13-17):: የሚፈልጉትን ለማድረግ ሲንቀሳቀሱ በእራሳቸው ብቁዎች ናቸው፣ ደግሞም «በገዛ እራሳቸው መንገድ» ያደርጉታል:: እንዲህ ያለውን ሰው በሉቃስ 12:13-21 ኢየሱስ ገልጾታል::

ኢዮብ ይህ የሕይወት ፍልስፍናው እንዳልሆነ ለመናገር ተጣደፈ:: «ከኃጢአተኞችም ምክር እርቃለሁ» (ኢዮብ 21:16):: ክፉዎች ለሀብታቸው ሙገሳውን ይወስዳሉ፣ ነገር ግን ኢዮብ ሁሉም ነገር ከእግዚአብሔር እንደሚመጣ ያስታውቃል (1:21):: እንግዲያውስ ሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች እርሱን እንዴት ከኃጢአተኞች ጋር ይመድቡታል?

የኢዮብን ሁለተኛ ነጥብ ከማየታችን በፊት እጅግ ብዙ የሆኑ ክርስቲያኖች እንደ ሆኑ የሚናገሩ ሰዎች፣ ዘወትር የሀብታሞችን የሕይወት አኪያሄድ የሚያደንቁበትና ስለ እነርሱ የሚቀኑበትን ከንቱ የሆነ እውነታ ልንጠቀመው ያስፈልጋል:: ከመጻሕፍቱ በአንዱ፣ ዶ/ር ኬኔትዝ ቻፊን እየጉበኙ የነበሩና አንድ በከፊል የከተሜ የሆነ ውብ ቤት ሲደርሱ ጉብኝታቸውን ስላቆሙ ስለ አንድ መጋቢና ዲያቆን ይነግረናል:: የግቢው መስክ እንክብካቤ ይደረግለት የነበር ይመስላል፣ ደግሞም ሁለት ውድ የሆኑ መኪኖች በግቢው በር ላይ ቆመዋል:: ከዚህም በላይ መጋቢውና ዲያቆኑ የቤቱ ባለቤት ምቹ በሆነው ስፌ በሆነ ሳሎኑ ቴሌቪዥንን እየተመለከተ እንደ ሆነ ለማየት ችለዋል:: በስፍራው ላይ ያለ ነገር ሁሉ ውብ ነበር:: ዲያቆኑ ወደ መጋቢው ዞሮ ብሎ ጠየቀው፣ «ለዚህ ሰው ምን ዓይነት መልካም ዜና ይኖረናል?»

ከአርባ ዓመታት በላይ በነበረ አገልግሎት፣ ብዙ የጋብቻ ሥነ ሥርዓቶችን አከናውኛለሁ ደግሞም ብዙ ወጣት ጥንዶች በቤ

ታቸው ሲኖሩ ተመልክቼአለሁ:: ጥንዶች ቅድሚያ ሊሰጡዋቸው የሚገቡ ጉዳዮችን አሟልተው ብዙኀኑ ኅብረተሰብ ለቍሳዊ ነገሮች የሚኖርበትን ሁኔታ የመከተል ፈተናን ተቋቁመው መኖራቸው ምን ዓይነት አስደሳች ነገር ነው:: አለመታደል ሆኖ፣ አንዳንዶቹ መንፈሳዊ ራእያቸውን ጥለው በዚህ ምድር ተሳክቶላቸዋል - ይህም ከጌታ እውቀት ውጭ በሆነ መንገድ ነው:: እነርሱ ዋጋቸውን ተቀብለዋል::

**ክፉዎች ዘወትር መከራን አይለማመዱም (ኢዮብ 21:17-21)::** «የክፉዎች መብራት ይጠፋል» በማለት በልዳዶስ ነገሩን አጸናው (18:5)፤ ነገር ግን ኢዮብ እንዲህ ሲል ጠየቀ፣ «ያ ምን ያህል ይከሰታል?» የእግዚአብሔር ቍጣ በዓመፀኞች ሕዝቦች ላይ ሲወርድ በእውነት ምን ያህል አይተሃል? «በነፋስ ፊት እንዳለ ገለባ፣ በዐውሎ ነፋስም እንደ ተወሰደ ዕብቅ የሆኑት ስንት ጊዜ ነው?» (21:18፣ አ.መ.ት):: ጻድቃን ሲሠቃዩ ሳለ ክፉዎች በዚህ ዓለም ዋስትና ያገኙ ይመስላል (ነገር ግን መዝ. 73ን ተመልከት)::

ነገር ግን እግዚአብሔር በክፉዎች ላይ የማይፈርድ ከሆነ፣ በልጆቻቸው ላይ ይፈርዳል (ኢዮብ 21:19):: ሶፋር በዚያ ነጥብ ላይ ተከራክሮአል (20:10)፣ ኤልፋዝም እንደዚሁ አድርጓል (5:4):: በእርግጥ፣ ሁለቱም ያለሙት ልጆቹን ሁሉ ባጣው በኢዮብ ላይ ነበር:: «ነገር ግን ያ ምን ዓይነት ፍርድ ነው?» ሲል ኢዮብ ጠየቀ:: «ሰው በኃጢአት ውስጥ የሚኖር ከሆነ፣ ስለ ኃጢአቱ እንዲሠቃይ ተወው:: ከሞተ በኋላ፣ በቤተሰቦቹ ላይ ስለሚከሰት ነገር ለምን ይጨነቃል? በሲኦል ሳለ በምድር ላይ ስለሚከሰት ነገር የሚያውቀው ምንም ነገር የለም::»

የእግዚአብሔር ቃል አባቶች ስለ ልጆች ኃጢአት ሊቀጡ አይገባም ወይም ልጆች ስለ አባቶች ኃጢአት ሊቀጡ አይገባም የሚለውን ግልጽ አድርጎታል (ኤር. 31:29-30፤ ሕዝ. 18:ከ1 ጀምሮ):: ወላጆች በእርግጠኝነት በልጆቻቸው ኃጢአት በጥልቀት ይጐዳሉ፣ ልጆች ደግሞ በወላጆቻቸው ኃጢአት ውጤት ሊሠቃዩ ይችላሉ፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ፍርድ ሁል ጊዜ ትክክል ነው (ዘዳግ. 24:16):: የኢዮብ ኃጢአት ለልጆቹ ሞትም ምክንያት ሆኖአል ብሎ አሳብ መስጠት የሦስቱን ጓደኞች ጭካኔን ያሳያል::

ሶፋር የክፉ ሰው የሕይወት ዘመን አጭር ነው ብሎአል፣ ነገር



ግን ኢዮብ ክፉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ረጅም ዕድሜ ይኖራሉ በሚል ምላሹ ተቃውሞታል:: ሶፋር የክፉዎች ደስታ ጊዜያዊ ነው ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፍርድ በድንገት ስለ ወረደባቸው ነው ብሏል፣ ነገር ግን ኢዮብ፣ «ይህ ሲከሰት ምን ያህል ተመልክተሃል?» ሲል ጠይቆታል:: አሁን ኢዮብ የክፉዎች ሞት ሥቃይ የበዛበት ነው ለሚለው የሶፋር መከራከሪያ ምላሽ እየሰጠ ነው::

**ክፉዎች ልክ እንደ ሌሎቹ ሰዎች ነው የሚሞቱት (ኢዮብ 21:22-34)::** ሕይወትና ሞት በእግዚአብሔር እጅ ናቸው፣ ስለዚህ እግዚአብሔርን ሊያስተምር የሚችል ወይም የእግዚአብሔርን መንገዶች ለማብራራት እችላለሁ የሚል ሰው ማን ነው? (ቍ. 22) በመጨረሻ በሚገለጥበትና እራሱን እንዲከላከል ረጅም ጊዜን በትዕግሥት ለኢዮብ በሰጠው ጊዜ እግዚአብሔር ኢዮብን ይጠይቀዋል:: ኢዮብ እግዚአብሔርን በመጠየቁ ፈንታ፣ እግዚአብሔር ለኢዮብ ጥያቄዎችን ያቀርብለትና በእነርሱም ኢዮብን ትሑት ያደርገዋል!

ሌሎች ለብዙ ጊዜ ተሠቃይተውና ታመው ሲሞቱ ሳለ አንዳንድ ሰዎች በሕይወት ሙላትና ለጊዜው በጥሩ ጤንነት ላይ ሳሉ እንደሚሞቱ ኢዮብ ተመልክቶአል:: ሌሎች ዘመናቸውን በኀዘን እያጠፉት ሳሉ፣ አንዳንድ ሰዎች ረጅምና የደስታ ሕይወትን በደስታ ያሳልፉታል፤ *ነገር ግን ሞት ለሁላቸውም አንድ ዓይነት ነው::* ጠንከር ባለ አነጋገር ለመጠቀም ያህል፣ እንደ «የጨቅላ ሞት» ወይም «አስቃቂ ሞት» አሊያም «ያልተጠበቀ ሞት» የሚሉት ዓይነት ነገር የለም:: ምክንያቱም *መቼም ሆነ እንዴትም ይምጣ፣ ሞት ሞት ነው::* ሀብታም ሰው ይሞታል፣ ድኻ ሰውም ይሞታል፤ አማኝ ይሞታል፣ የማያምን ሰው ይሞታል፤ «ሁለቱም በዐፈር ውስጥ አንድ ላይ ጐን ለጐን ይጋደማሉ፤ ትሎችም ይወሯቸዋል::» (ቍ. 26) በእርግጥ ኢዮብ ይናገር የነበረው የሞትን *አካላዊ ገጽታ* እንጂ፣ *መንፈሳዊ ገጽታ* አልነበረም:: ሞት በሚመጣበት ጊዜ፣ ሰውዬው በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ መሆኑ ወይም አለመሆኑ *በመጪው ሕይወት ረገድ* በግልጽ ታላቅ ልዩነትን ያመጣል (ዕብ. 9:27)::

ብዙ ሰዎች አንዳንድ አማኝ የሆኑ ክርስቲያኖችን ጨምሮ - ስለ ሞት በአጠቃላይ ወይም የገዛ እራሳቸውን ሞት በተመለከተ ለመናገር በአጠቃላይ ወይም የገዛ እራሳቸውን ሞት በተመለከተ

በተለይ ያመነታሉ። የጤናና የሕይወት ዋስትና አላቸው፣ ነገር ግን ርእሰ ጕዳዩን ማስወገድን ደግሞም ሞት የማይመጣ ይመስል ለየት ያለ እንቅስቃሴ ማድረግን ይመርጣሉ። «የሞት አሳብ፣ የሞት ፍርሃት እንስሳ የሆነውን ሰው ልክ እንደ ማንኛውም ነገር ያድነዋል፣» በማለት የሥነ ኅብረተሰብ አዋቂው ኧርነስት ቤከር ይጽፋል። «የሰው እንቅስቃሴ ዋና ምንጭ ነው፣ ይህም የሞትን ከንቱነት ለማስወገድ ሰፋ ባለ መልኩ የተዘጋጀ እንቅስቃሴ ነው።» *(ዘ ዲናያል ኦፍ ዴዝ፣ ix)።*

ኢዮብ ጓደኞቹን «እነሆ ምክራችሁን፦ በእኔ ላይ ያሤራችሁትን ተረድቻለሁ» (ኢዮብ 21:27) አላቸው። ንግግሩ ልባቸውን እንዳልነካው ሊነግራቸው ሞከረ፣ ደግሞም ንግግሩን በፈጸመ ጊዜ፣ ምን እንደሚናገሩ ያውቃል፣ ይህም ከዚህ በፊት ያሉትን ነው! በቍጥር 28 ላይ ቀድሞውኑ የተቃወማቸውን የተናገሩትን ሁለቱን ንግግሮች ይጠቅሳል (18:13-21 እና 20:20-29) ተመልከት፣ ነገር ግን ተመሳሳይ ዓረፍተ ነገሮችን እንደሚሰማ ይጠባበቃል።

ኢዮብ ጓደኞቹን ከአገራቸው ውጭ ሁኔታውን መርምረውት እንደ ሆነ ይጠይቃቸዋል። ዶርዚ ሴየርስ እንደ ጻፈችው፣ «አመለካከትህ በበቂ ሁኔታ የተወሰነ ከሆነ፣ የምታረጋግጠው ምንም ነገር የለም።» እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፣ «መንገዶችን አልጠየቃችሁምን?» (21:29፣ አ.መ.ት)። የሚጓዙ ሰዎች በአብዛኛው በአመለካከታቸው የጠበቡ አይደሉም። ነገር ግን የዓለም በሆኑ ነገሮች ላይ ሰፋ ያለ ተሞክሮ ያላቸው ናቸው። ካላቸው ጥበብ ሁሉ ጋር፣ ሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች በአመለካከታቸው ገና ጠባቦች ናቸው፣ ምክንያቱም በሌሎች ስፍራዎች ላይ ሕይወት ምን እንደሚመስል ያላዩ ሰዎች ናቸውና። የኢዮብ ጓደኞች ብዙ የተጓዙ ሰዎች ቢጠይቁ በእያንዳንዱ የዓለም ክፍል በጻድቃን ላይ የሚደርሱ መከራዎችን ክፉዎች የሚያመልጡ የሚመስሉበትን ሁኔታን ይማራሉ።

ከዚያም ኢዮብ በጣም ግለኛ በመሆን ጓደኞቹን እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፦ «ክፉዎች ለምድራዊ ሞት የተመደቡ ናቸው ብላችሁ በእውነት የምታምኑ ከሆነ፣ አስጠንቅቃችኋቸው ታውቃላችሁ? በፊታቸው *ስለ ጥፋታቸው ወቅሳችኋቸው ታውቃላችሁ?»* (ቍ. 31



አጠር ብሎ የቀረበ)። ጓደኞቹ፣ አይደለም፣ ስለ ወደፊት ሕይወታቸው ከክፉዎች ጋር ከቶ ተነጋግረን አናውቅም» ብለው ከመለሱ፣ እንግዲያውስ ኢዮብ «ጻድቅ የሆነ ሰውን ስለ ምን ስለ ወደፊት ሕይወት ታስጠነቅቁታላችሁ» ሊላቸው ይችል ነበር። ነገራችሁ ምን ያህል ወጥነት የጐደለው መሆኑ ይታያችኋል?

በ21:34 ላይ የኢዮብ የመደምደሚያ ንግግሩ ሦስቱን ጓደኞቹን በተናገሩት ነገር የማይተማመንበት መሆኑን እንዲያውቁ አደ ረጋቸው። ማጽናናታቸው ከንቱ ነው («ትርጕም-አልባ ነው»፣ አ.መ.ት) መልሶቻቸው ደግሞ ከውሸት በቀር ምንም ናቸው። «ሐሰተኝነት» በሚል የተተረጐመው የዕብራይስጡ ቃል «ሆን ብሎ የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፍ፣ የማጭበርበር ተግባር» ማለት ነው። ዘወትርም «መተላለፍ» በሚል ይተረጐማል። ሦስቱ ጓደኞቹ በኢዮብ ላይ ጥቃት በፈጸሙ ጊዜ፣ እምነትን ጐድተዋል ደግሞም በእግዚአብሔር ላይ የመተላለፍን በደል ፈጽመዋል። ኢዮብን በመርዳት ፈንታ ከመስመር አስወጥተውታል።

«ጌታ ሆይ፣ ዛሬ በማንም ሰው ላይ ሸክምን እንዳልጨምር እርዳኝ፣» በማለት በየዕለቱ የሚጸልይ ጓደኛ አለኝ።

ያንን ጸሎት በልዳዶስ፣ ሶፋርና ኤልፋዝ አለመጸለያቸው እጅግ አስከፊ ነው!

ምናልባት ሁላችንም ይህን ጸሎት መጸለይ ልንጀምር ይገባን ይሆናል!

# ለግል ምልከታና ለቡድን ውይይት
# የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ቁርዝቢ የሶፋር ንግግር ድምር ብለው የጠሩትን ኢዮብ 20:5ን አንብብ፡፡ በዚህ ሥነ አመክንዮ ላይ ከኢዮብ ይወጣል ብሎ ሶፋር የሚጠብቀው ምላሽ ምን ይመስልሃል?

2. ሶፋር፣ «መልካም ሰዎች ገና በወጣትነታቸው ይሞታሉ» ከሚለው አባባል ጋር አልተስማማም ነበር፡፡ በዚህ ላይ የአንተ ምላሽ ምንድን ነው?

3. ብዛቱን እንኳ ባይሆን የዘመናችንን ጥራት ጽድቅ ሊጨምረው የሚችለው በምን መንገዶች ነው?

4. ኢዮብ እንዲያዳምጡት ጓደኞቹን ጠየቃቸው፡፡ በመከራ ውስጥ ያለን ሰው በሚያገለግሉበት ወቅት እርሱን ማድመጥ ምን ያህል ጠቃሚ ነው? ለምን?

5. ክፋዎች በልጥገው ስናይ የሚገጥመንን መሠረታዊ ትግል አብራራ፡፡



6. ዋጋው የተከፈለውን ያየኸውን ክፋት አብራራ፡፡

7. ክፋዎች የክፋታቸውን ውጤት እንዴት ያስወግዳሉ?

8. ክፋት ከትውልድ ወደ ትውልድ በምን መልኩ ነው የሚተላለፈው?

9. አንዳንድ ጊዜ ወንጀል መሥራት ዋጋ ያለው፣ የላቀ ዋጋ የሚያስገኝ በሚመስልበት ጊዜ እንኳ በጽድቅ መንገድ ለመጓዝ እንድንቀጥል የሚያደርገን የቱ አመለካከት ነው?

10. ቀድሞውኑ በነበረበት የሕይወት ሽክም ላይ የኢዮብ ጓደኞች አስቸጋሪ ነገርን የጨመሩበት እንዴት ነበር?

# የዕረፍት ጊዜ

ለተጉዱ ሰዎች መጽናናት መሆን የምትፈልጉ ከሆነ፣ ነገሮችን በእነርሱ ዓይን ለማየት ሞክሩ:: ሌሎች አመለካከቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይህን ለመቀበል ትሑታን ሁኑ:: ሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች ጠባብ የሆነ የሕይወት ተሞክሮ ያላቸው ነበሩ:: ችኮ የሆነ አሳባቸውን አጥብቀው ይዘው መስማትን እንቢ ብለዋል:: ከእርሱ ጋር ለማይስማሙ ሰዎች በጻፈው ደብዳቤ፣ ኦሊቨር ክሮምዌል እንዲህ ብሏል:- «ልትሳሳቱ እንደምትችሉ እንድታስቡ በክርስቶስ ርኅራኄ እለምናችኋለሁ::»

አንድ ሰው አክራሪ ሰዎችን በተመለከተ «አሳባቸውን ሊለውጡ የማይችሉ ሰዎች እንዲሁም የጀመሩትን አንድ ርእሰ ጉዳይን መለወጥ የማይፈልጉ ሰዎች» በሚል በዚህ መልኩ ገለጻቸው:: ሳሙኤል ጆንሰን በአንድ ወቅት ስለ አንድ ሰው እንዲህ ብለው ተናገሩ፣ «ያ ሰው አንድ አሳብ ብቻ ነው ያለው፣ ሊያውም ያ አሳቡ የተሳሳተ አሳብ ነው::»

ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ስለ ሰዎች እና ስለ ሕይወት ሁልጊዜ የምንማረው አንድ አዲስ ነገር ይኖራል:: ጥሩ ተማሪዎች እንዲሁም ጥሩ አድማጮች እንሁን!





# በችሎት ውስጥ ሥነ ሥርዓት ይከበር!

## (ኢዮብ 22-24)

«አዳኙ፣ የእስራኤል አምላክ፣ አንዳንድ ጊዜ እራሱን የሚደብቅ አምላክ ነው፣ ነገር ግን ከቶ እራሱን እንዳይገኝ የሚያደርግ አምላክ አይደለም፤ አንዳንድ ጊዜ በጨለማ ውስጥ ይሆናል፣ ነገር ግን ከቶ እሩቅ አይሆንም::»

- ማቲው ሄንሪ

የሚያጽናና መሆን የሚገባው ውይይት፣ በጓደኞች መካከል ቍጣ የሚያስነሣና ውስጥን የሚያሳምም ክርክር ሲሆን ምን ይባላል? ነገሮችን በማቀዝቀዝ ፈንታ፣ ኤልፋዝ አቃቤ ሕግ ሆኖ ክርክሩን ወደ ችሎት ለወጠው:: ኢዮብ በዐመድ ቁልል ላይ ተቀምጦ ጓደኞቹ በእርሱ ላይ ሲዋሹ ሲያደምጣቸው ሳለ ሙግቱን ሦስት ለአንድ ሆነው ተያይዘውታል:: በአይሁዶች ታልሙድ መሠረት «የሐሰተኛ ምላስ ሦስት ወገኖችን ይገድላል:- እነዚህም ወገኖች የሚዋሹለት ሰው፣ ዋሾው እና ዋሾውን የሚያደምጡ ሰው ናቸው::» በዖፅ ባለ የዐመድ ቁልል፣ በዙሪያው ሁሉ ያለው ሞት ነበር!

### ሦስት የሐሰት ክሶች (22:1-30)

ልክ እንደ ማንኛውም ውጤታማ የሆነ ዐቃቤ ሕግ፣ ኤልፋዝ ሁሉንም ነገር በደንብ አድርጎ አዘጋጅቶታል፤ ደግሞም ሁሉንም ነገር አሳጥሮ አቅርቦታል:: በኢዮብም ላይ ሦስት ከባድ ክሶችን አቀ ረበበት:- እርሱ ኃጢአተኛ ነው (ኢዮብ 22:1-11)፣ እርሱ ኃጢአቶቹን ደብቋቸዋል (ቍ. 12-20)፣ ደግሞም እግዚአብሔር

እርሱን ከመርዳቱ በፊት ኃጢአቶቹን መናዘዝና ንስሐ መግባት አለበት (ቍ. 21-30)::

**(1) ኢዮብ ኃጢአተኛ ነው (ኢዮብ 22:1-11)::** ኤልፋዝ የሰሉ አሽሙሮችን ከመወርወር መቈጠብ አይችልም:: «እርሱ የሚገሥፅህ፣ ፍርድ ቤትም የሚያቀርብህ ስለምትፈራው ነውን?» (ቍ. 4፣ አ.መ.ት):: ፍርድ ቤቶች ስለ ጽድቃቸው ሰዎችን ችሎት ላይ አያቆሙም፣ ስለ ሕግ መተላለፋቸው እንጂ! ስለዚህ፣ እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ አስከፊ ፍርድን በመላኩ፣ እርሱ ኃጢአትን ያደረገ መሆን አለበት:: «ክፋትህ ታላቅ፣ ኀጢአትህም ፍጻሜ የሌለው አይደለምን?» (ቍ. 5) ነገር ግን ኤልፋዝ ኢዮብ የተናገረውን ነጥብ ስጥቶታል፦ «እግዚአብሔር እኔን *ከመያዙ፣ የክሱን ጽሕፈት ከማንበቡ፣ ደግሞም የችሎት ሥርዓቱን ከመምራቱ በፊት* ስለ ምን ቅጣቱን ላከ?» ይህ ሁሉ ተገቢ ያልሆነ ይመስላል::

ኤልፋዝ በመጀመሪያ ኢዮብን ስለ *ትዕቢት (ኵራት)* ኃጢአት ከሰሰው (ቁ. 1-3):: ኢዮብ ባሕርይው እና ጠባዩ ለእግዚአብሔር አስፈላጊ እንደ ሆነ ደግሞም ለእርሱም ቢሆን በሆነ መንገድ እንደማይጠቅመው ነው የሚያስበው:: የኤልፋዝ ሥነ መለኮታዊ መረዳት የሚያተኵረው እግዚአብሔር በዓለም ላይ የሚፈርድ በሩቅ ያለ ዳኛ እንደ ሆነ በመናገር ላይ እንጂ፣ የኃጢአተኞች ወዳጅ እንደ ሆነ በመናገር አይደለም::

ነገር ግን የኢዮብ ባሕርይ ለእግዚአብሔር አስፈላጊ ነበር፣ *ምክንያቱም ዲያብሎስን ጸጥ ለማሰኘት እግዚአብሔር ኢዮብን እየተጠቀመበት ነበር።* ኢዮብም ሆነ ሦስቱ ጓደኞቹ የተደበቀውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ አያውቁም፣ ነገር ግን ኢዮብ እግዚአብሔር በሕይወቱ ውስጥ የሚያከናውነው ዓላማ እንዳለው ደግሞም አንድ ቀን ነፃ እንደሚያወጣው ያምን ነበር:: በተጨማሪም፣ ሕዝቡ ለእርሱ ደስታንም ሆነ ኀዘንን ስለሚያመጡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ባሕርይና ጠባይ ለእርሱ አስፈላጊዎች ናቸው [1ኛ ተሰ. 4:1፤ ዕብ. 11:5፤ ዘፍጥ. 6:5-6፤ መዝ. (37):23]:: እርሱ ለሕዝቡ በቅርብ የማይገኝ በሕዝቡ ጉዳይ የማይገባና በሩቅ ያለ አምላክ አይደለም፣ ነገር ግን እነርሱ በእርሱ ላይ ደስ እንደሚሰኙበት ሁሉ በእነርሱ ደስ የሚሰኝ ነው (መዝ. 18:19፤ ኢሳ. 63:9፤ ዕብ. 4:14-



16)::

እንደ እግዚአብሔር ልጆች «እርሱን የሚያስደስተውን ነገር ዘወትር አደርጋለሁ» ያለውን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሳሌነት ልንከተል ያስፈልጋል (ኢዮብ 8:29) ከዚያም አብ ለኢየሱስ እንደ ተናገረለት ሁሉ እንዲሁ ለእኛ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» በማለት ስለ እኛ መናገር ይችላል (ማቴ. 3:17)::

ከኵራት (ትዕቢት) ጋር በተያያዘ፣ ኤልፋዝ ስለ ምኞት ኢዮብን ይከስሰዋል (ኢዮብ 22:6):: ብዙ ሀብት ለማግኘት ሰዎችን የሚበዘብዝ ስስታም ሰው ነበር:: ኃይሉንና በሰዎች ዘንድ ያለውን ክብር (ቍ. 8)፣ ሰዎችን ዝቅ ለማድረግና ለመዝረፍ ይጠቀምበት ነበር:: በሙሴ ሕግ፣ አበዳሪ ለዋስትና የሚሆን ነገር ከተበዳሪው ይወስድ ነበር:: ነገር ግን ይህ የተበዳሪውን ሥራ፣ ጤና ወይም እንደ ሰውነቱ ያለውን ክብሩን ሊያቃውስበት የሚገባ መሆን የለበትም (ዘጸአ. 22:28-27፤ ዘዳግ. 24:10-13):: ኤልፋዝ ማናቸውም ሳያስፈልጋቸው ከወንድሞቹ ላይ መያዣ እንደ ወሰደ እንዲሁም ዕዳቸውን እስኪመልሱ ድረስ በመያዣ መልክ ልብሳቸውን ገፍፎ እንደ ወሰደ አድርጎ ኢዮብን ከሰሰው!

ኤልፋዝ ኢዮብ በሚኖርበት አካባቢ አልኖረም፣ ስለዚህ ከእነርሱ ጋር ባለው የንግድ ግንኙነት ሰዎችን በዚህ መልክ የሚይዝ መሆኑን እንዴት ሊያውቅ ቻለ? ከእነዚህ ታሪኮች አንዳንዶቹን ከኢዮብ ጠላቶች ጥቂቶቹ ነገሩት ወይ? ነገሩ እንዲህ ከሆነ፣ በገሃድ ጉዳዩን ከማሳወቁ በፊት ክሶቹን መመርመር ነበረበት:: መላው ጉዳይ ብዙ ሰዎችን ይረዳ የነበረውን የእግዚአብሔርን ሰው (ኢዮብ 29:11-17) ዋጋ ለማሳጣት የተደረገ ፍጹም ፈጠራ ነበር::

*ሦስተኛው የኢዮብ ታላቅ ኃጢአት ምሕረትና ርኅራኄን ማጣት ነው* (23:7-9)፣ ይህም ችግረኞችን ዓይቶ ዝም ብሎ የማለፍ ኃጢአት ነው:: እግዚአብሔር የኢዮብን ጸሎት አለመመለሱ አያስደንቅም! «የድሀውን ጩኸት እንዳይሰማ ጆሮውን የሚደፍን ሰው፣ እርሱ እራሱ ይጮኻል አይሰማለትምም» (ምሳሌ 21:13):: ከብዙ የሀብት ክምችቱ በማካፈል ፈንታ ኢዮብ ከደከሙት፣ ከተራቡት፣ ከመበለቶች እና ወላጅ-አልባ ከሆኑ ልጆች ፊቱን ይመልሳል:: እንግዶችን መቀበል ከምሥራቃውያን ሕጎች መካከል

አንዱ ስለሆነ፣ በተለይ የኢዮብ ኃጢአት የተለየ አስቃቂ ነበር።

በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ እግዚአብሔር ለድሆች፣ በተለይም ለመበለቶችና ወላጅ-አልባ ለሆኑት ልጆች ታላቅ የሆነ እንክብካቤን ያሳያል፣ ደግሞም ድሆችን በሚበዘብዙና በሚጨቁኑዋቸው ላይ ቍጣውን ይገልጻል (ዘጸአ. 22:22፤ ዘዳግ. 24:17፣ 26:12)። ችግረኞችን የሚጨቆኑትንና ድሆችን የሚዘርፉትን (ኢሳ. 1:17፤ ኤር. 7:6፤ 22:1-4፤ አሞጽ 4:1፤ 5:11፤ 8:4-10) የፖለቲካም ሆነ የሃይማኖት መሪዎችን ሁሉቱንም ነቢያት ባለመታከት አውግዘዋል። ኢየሱስ ለድሆች ልዩ እንክብካቤ ያሳይ ነበር (ሉቃስ 4:16-19፤ ማቴ. 11:5)፣ ደግሞም የጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን የእርሱን ምሳሌነት ተከትላለች (ገላ. 2:10፤ ያዕ. 1:27፤ 2:1-9፤ የሐዋ. 6:1፤ 1ኛ ጢሞ. 5:1-16)። *ዛሬም* ቤተ ክርስቲያን *ያንን* ምሳሌነት *መከተል* ይኖርባታል።

ኤልፋዝ የመጀመሪያ ነጥቡን ማንም ሊያየው በሚችል ማስረጃ አስቀምጦታል፦ ኢዮብ የብዙ ኃጢአቶቹ ውጤት የሆነውን ታላቅ መከራ እየተቀበለ ነበር (ኢዮብ 22:10-11)። እርሱ ስለ ምን በጨለማ፣ በአደጋ፣ እንዲሁም በመከራው ጥልቀት ውስጥ ይመላለሳል? ይህ ኢዮብ አምላክ-የለሽ መሆኑን የሚሳይ የእግዚአብሔር እጅ ነበር።

በዙሪያው የቆሙና ውይይቱን ያደምጡ የነበሩት ሰዎች እንዲህ ያለውን ክስ በጐረቤታቸው በኢዮብ ላይ ሲሰሙ ደንግጡ። እርስ በርሳቸው እየተያዩ እንዲህ በማለት ሳይጠያየቁ አልቀሩም፦ «ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ስለ ኢዮብ ክፋት እኛ እንዴት ሳናውቅ ቀረን?» ቀጣዩ የኤልፋዝ ነጥብ ይህን ጥያቄ ይመልሳል።

**(2) ኢዮብ ኃጢአቶቹን ሸፍኖአል (ኢዮብ 22:12-20)።** በሌላ አነጋገር፣ ኢዮብ ግብዝ ነበር፣ ይህም ዓረፍተ ነገር ይህ ውይይት ከተጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ከአንድ ጊዜ በላይ ተነግሮአል - አሊያም ተጠቁሞአል። «አምላክ-የለሽ ኑሮ ለሚኖሩ (ለግብዞች) ተስፋቸው ትጠፋለች» አለ በልዳዶስ (8:13)። «የዐመፀኞች ጉባኤ ትመክናለች፤ የጉቦ ሉሰኞችም እንኳን በእሳት ትበላለች» (15:34) አለ ኤልፋዝ። ሶፋር ደግሞ እንዲህ አለ፣ «የክፉዎችም ደስታ ለቅጽበት መሆኑን አታውቅምን?» (20:5)።

ግብዝ መንፈሳዊ ግቦቹን በማሳካት ረገድ ያልተሳካለት ሰው



ማለት አይደለም፣ ምክንያቱም ሁላችንም በአንድም ሆነ በሌላ የወደቅን ነንና፣ ነገር ግን ግብዝ ስንል የቱንም ግብ ለመምታት የማይጥር ሰው ማለት ነው፤ ነገር ግን በተግባር ተገልጦ የማይታይ ሆኖ ሳለ *ሙያ እንዳለው ለሰዎች የሚናገር* ነው። የፒዩሪታን ሰባኪ የሆነው ስቴፈን ቻርኖክ እንዲህ አለ፣ «በእራት ጊዜ ክርስቲያን፣ በሱቆቻችን አረማዊ በቁም ሣጥኖቻችን ደግሞ ዲያብሎስ መሆን አሳዛኝ ነገር ነው።»

ኤልፋዝ ኢዮብን *ወደ ላይ* እንዲመለከት (22:12-14) ደግሞም ማንም ሰው ከእግዚአብሔር የቱንም ነገር መደበቅ እንደማይችል እንዲገነዘብ መከረው። ግብዝ ሰው «እግዚአብሔር አያውቅም ደግሞም ግድም የለውም» በማለት ኃጢአት በመሥራት መቀጠሉን ያደፋፍራል (መዝ. 10ን ተመልከት)። ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ያያል፣ ያውቅማል፤ ደግሞም ግብዝም ሰው ኃጢአቱን ከእግዚአብሔር ሊደብቅ አይችልም። እግዚአብሔር ወዲያውኑ አይፈርድ ይሆናል፣ ነገር ግን በመጨረሻ ፍርድ መምጣቱ አይቀርም።

ከዚያም ኤልፋዝ *ወደ ኋላ* እንዲመለከት (ቊ. 15-18) እና ባለፉት ጊዜያት በኃጢአተኞች ላይ የደረሰውን ነገር እንዲያስታውስ ኢዮብን መከረው። ኢዮብ «ከክፉዎች ምክር» ጋር ምንም ግንኙነት እንዳልነበረው ግልጽ አድርጓል (21:16)፣ ነገር ግን ኤልፋዝ በዚህ ጉዳና ላይ ስለ መሄዱ እርሱን ከስሶታል (22:15)። ግብዞች ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ኃጢአታቸውን መደበቅ እንደሚችሉ፣ ከዚያም ኃጢአታቸው እንደሚገኝ ታሪክ ያሳያል። እግዚአብሔር የሚታገሣቸው ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ለእነርሱ መልካም ነው፣ ቤቶቻቸውንም በመልካም ነገሮች የሚሞላ ነው (ቊ. 18)። ኢዮብ በጣም ሀብታም የመሆኑ እውነታ የኢዮብ ጻድቅነት ማስረጃ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር መልካምነት (ደግነት) ማስረጃ ነበር።

ምስኪኑ ኢዮብ! በየትኛውም ጉዳና ይሄድ ወይም ከከሳሾቹ ጋር ምክንያታዊ የሆነ ንግግር በማድረግ ይወያይ፣ ጊዜውንና ጉልበቱን እያባከነ ነበር። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ጻድቃንን ይባርካል ደግሞም ክፉዎችን ይቀጣል ብለው ነበር፣ አሁን ደግሞ ኤልፋዝ እግዚአብሔር ግብዙን ሰው ይባርካል ደግሞም ቤቱን በመልካም

ነገሮች ይሞላል እያለ ነው፡

የግብዞች መከራ እግዚአብሔር ፍርድን የሚልክ መሆኑ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ግብዞች የገዛ እራሳቸውን ፍርድ የሚያመጡ መሆናቸው ጭምር ነው። ይህም ባሕርይን ያጠፋል፤ ባሕርይ በሚበላሽበት ጊዜ፤ ጨው ጣዕሙን በሚያጣበት ጊዜ (ማቴ. 5:13 ተመልከት) ለሰው የሚቀረው ነገር ምንድን ነው?

ታማኝ ለሆነ ሕይወት እጅግ ታላቅ የሆነ ብድራቱ ስለ እርሱ የምታገኙት ነገር አይደለም፤ ነገር ግን በእርሱ የምትሆኑት ነው የሚለው አባባል ትክክለኛ ነው። ጸጳሱ ብሩክ ዌስትኮት እንዲህ አሉ፤ «ታላላቅ ወቅቶች ጀግናም ሆነ ፈሪ አያደርጉም፤ በሰው ፊት ሰዎች ማን እንደ ሆኑ ብቻ ይገልጣሉ። በጸጥታና ዓይን በማይገባ መልኩ ስንነቃ ወይም ስንተኛ፤ እየበረታን ወይም እየደከምን እንሄዳለን፤ ደግሞም በመጨረሻ ምን እንደ ሆንን ለማሳየት አንዳንድ ችግሮች ይታያሉ።»

**(3) ኢዮብ በኃጢአቱ ንስሐ መግባት ይኖርበታል (ኢዮብ 22:21 -30)።** ኤልፋዝ ልመናውን ለኢዮብ በቅንነት ነበር ያቀረበው፤ ይህም ልክ ሶፋር ኢዮብን ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ በቅንነት እንደ ጠየቀው ሁሉ ማለት ነው (11:13-20)። «ለእግዚአብሔር ተ ገዛ ከእርሱም ጋር ሰላም ይኑርህ፤ በረከትም ታገኛለህ» (22:21፤ አ.መ.ት)። «ብልጥግና» በሚል የተተረጐመው ቃል «በሁሉም ረገድ የሚሆን መልካምነት» ማለት ነው። በእርግጥ፤ ግብዝ ሰው ከችግሮቹ ለመውጣት እና የወደፊት ዕድሉን (ዕድሏን) የተስተካከለ ለማድረግ ሳይሆን፤ ነገር ግን በባሕርይና በአገልግሎት መታደስ ሳቢያ እግዚአብሔርን ለማስደሰትም ሆነ ለማክበር ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለበት።

«ለእግዚአብሔር መገዛት» ማለት ምን ማለት ነው? ከእግዚአብሔር ጋር መዋጋትን ማቆም ደግሞም የእርሱን የሰላም መንገድ መቀበል (ያዕቆብ 4:1-10) ማለት ነው። በተጨማሪም ቃሉን ማድመጥና እግዚአብሔር ለሚናገረው ነገር መታዘዝ ነው (ኢዮብ 22:22)። አንድ ኃጢአተኛ ኃጢአትን መተው አለበት (ቍ. 23) ደግሞም እግዚአብሔርን ታላቁ ሀብቱ ማድረግ (ቍ. 25) ይኖርበታል፤ መጸለይና የእግዚአብሔርን ፊት መሻት አለበት (ቍ. 27)።



ንስሐ ለሚገቡና ወደ እርሱ ለሚመለሱ ሰዎች እግዚአብሔር የገባው ተስፋ ምንድን ነው? እግዚአብሔር ያድሳቸዋል (ቍ. 23) ደግሞም እራሱን ለእነርሱ የተወደደ ነገር ያደርግላቸዋል (ቍ. 25) ስለዚህም ደስታቸው ሁሉ በጌታ (በእግዚአብሔር) ላይ ይሆናል ደግሞም ምድራዊ በሆነ ሀብት ወይም ደስታ ላይ የተመሠረተ አይሆንም (ቍ. 26)። እግዚአብሔር እርሱ አቅጣጫቸውን በሚያሳያቸውና ብርሃን በሚሰጣቸው ጊዜ (ቍ. 28)፤ ጸሎታቸውን ይመልሳል ደግሞም ፈቃዱን እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል (ቍ. 27)። ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ኅብረት በመታደሱ ምክንያት፤ የወደቁትን ሌሎችን ሰዎች መርዳት ይችላሉ (ቍ. 29-30)።

በዚህ ልመናው ኤልፋዝ ጥቂት ግሩም ነገሮችን ይናገራል፤ ነገር ግን ይህን የተናገረው ሊነገረው ለሚገባ ሰው አይደለም። ወደ መጽሐፉ መጨረሻ ስንቃረብ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የሌላቸው ሆነው የተገኙት ኤልፋዝና ሁለቱ ጓደኞቹ እንደ ሆኑ እንደርስበታለን። ኅብረታቸው ይታደስ ዘንድም ኢዮብ ሊማልድላቸው ያስፈልጋል (42:7-10)።

አንተ ኢዮብን ብትሆን ኖሮ፤ ለዚህ ልመና የምትመልሰው መልስ ምንድን ነበር?

## ሦስት መራራነት የሞላባቸው ማጉረምረሞች (23-24)

ከጓደኞቹ ጋር በመከራከር ወይም የኤልፋዝን ልመና እሺ ብሎ በመቀበል በታማኝነቱ ላይ በመደራደር ፈንታ፤ ኢዮብ ሙሉ በሙሉ ችል አላቸው እና ለጌታ መናገሩን ቀጠለ። ቀድሞውኑ ኢዮብ ክርክሩ ከሰዎች ጋር እንዳልሆነ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ሆነ ግልጽ አድርጓል፤ ይህንንም እውነታ በንግግሩ ላይ አጽንዖት ሰጥቶበታል።

ምናልባት ኢዮብ 23:2ን እንደሚከተለው አድርገን ልናቀርብ እንችላለን፤ «የዛሬው ማጉረምረሜ ከምሬት የወጣ ነው፤ ደግሞም ከመጮኽ በቀር ምንም ከማድረግ እንዲጠብቀኝ ከባድ እጅን በላዬ ላይ ማድረግ ይኖርብኛል።» ከእነርሱ ጋር ለመነጋገር ይቻል ዘንድ ብቻ ምን ያህል ሥርዓት መያዝ እንዳለበት ሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች አልተረዱም ነበር። ለሥቃዩ እጁን በመስጠት እና ምንም ባለማድ ረግ ነገር ግን በመጮኽ ፈንታ፤ ኢዮብ ሥቃዩን ለመቋቋም እና

እራሱን ለማጽደቅ ስፍራ ላለመስጠት ፈለገ:: በሚቀጥለው ጊዜ በሥቃይ ውስጥ ያለን ሰው በምትጐበኙበት ጊዜ፣ መከራ የሰውን ኃይል እንደሚያደክም እንዲሁም በጥንካሬው እና በትዕግሥቱ ላይ ታላቅ ፍላጎት እንዲኖር እንደሚያደርግ ልብ በሉ::

ኢዮብ በእግዚአብሔር ላይ የሚያነሣው ሦስት የማይቀበላቸው ነገሮች እንዳሉ ተናገረ::

**(1) «እግዚአብሔር ከእኔ ተሰውሮአል» (ኢዮብ 23:1-12)::** «እርሱን የት እንደማገኘው ባወቅሁ፤ ወደ መኖሪያውም መሄድ በቻልሁ!» (ቍ. 3):: ይህም እግዚአብሔርን በፍርድ ቤት (ችሎት ላይ) ለማግኘት ያቀረበው ሌላ ልመናው ነበር:: ኢዮብ ክርክሩን ለማቅረብ እንዲሁም እግዚአብሔር ፍርዱን እንዲሰጥ ለመፍቀድ ተዘጋጅቶ ነበር:: ኢዮብ፣ እንደ ሕግ ሲጨነቁ እግዚአብሔር ታላቅ ኃይል ያለው ቢሆንም፣ እርሱ ጻድቅ ሰው ነውና፣ ደግሞም በልባቸው ጻድቃን የሆኑትን እግዚአብሔር ሊኰንን አይችልምና፣ እንደሚያሸንፍ ያውቅ ነበር:: «ቅን ሰው ጉዳዩን በእርሱ ፊት ያቀርባል፤ እኔም ከፈራጄ ለዘላለም ነፃ እሆናለሁ» (ቁ.7፣ አ.መ.ት)::

ነገር ግን ሰው እግዚአብሔርን ፈልጎ የሚያገኘው እንዴት ነው? ኢዮብ ወደ ፊትም ሆነ ወደ ኋላ (ምሥራቅ ወይም ምዕራብ)፣ ወደ ግራም ሆነ ወደ ቀኝ (ሰሜን ወይም ደቡብ) ቢሄድ፣ እግዚአብሔ ርን ሊያየው ወይም በፍጥነት እንኳ በከፊል ሊቃኘው አይችልም:: በእርግጥ፣ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ይገኛል (መዝ. 139:7-12)፣ ነገር ግን ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር በግል መገናኘት ፈለገ:: የሚጠይቃቸው ጥያቄዎችና የሚያቀርባቸውም ክርክሮች ነበሩት!

እግዚአብሔር ኢዮብ የት እንደሚገኙ በማቅለጫ (በፈተና) ውስጥ እንዳለ ያውቃል (ኢዮብ 23:10)! ነገር ግን ይህ የእግዚአብሔር ቀጠሮ የሆነ ማቅለጫ (ፈተና) ነበር፣ ይህም በኢዮብ ኃጢአት ምክንያት አይደለም፣ እግዚአብሔር እርሱን ለማንጻት እና የተሻለ ሰው ሊያደርገው መከራዎቹን ተ ጠቅሞበታል:: ይህ «ጻድቃን ለምን ይሠቃያሉ?» ለሚለው ጥያቄ ብቸኛ መልስ አይደለም፣ ነገር ግን ከምርጦቹ መልሶች መካከል አንዱ ነው፣ ደግሞም ለተሠቃየ ሰው ታላቅ መጽናናትን ያመጣለታል::



የእግዚአብሔር ቃል እግዚአብሔር በመከራ ውስጥ ያለውን የመንጻት አገልግሎት ለመግለጽ የወርቅ ማቅለጫን ሥዕላዊ መግለጫነት ዘወትር ይጠቀማል::

«እነሆ እንደ ብር ባይሆንም አንጥሬሃለሁ፤ በመከራ እቶን ፈትኜሃለሁ» (ኢሳ. 48:10፣ አ.መ.ት):: «ልክ ብረት በማቅለጫ እንደሚቀልጥ እስራኤል በግብፅ መከራ ተቀብሏል (ዘዳግ. 4:20)፣ ደግሞም በኋለኛው ዘመን የገጠማት ቀጣት ልክ እንደዚሁ ያለ «የማቅለጫ ተሞክሮ» ነበር:: «አምላክ ሆይ፤ አንተ ፈተንኸን፤ እንደ ብርም አነጠርኸን» [መዝ. (66):10 አ.መ.ት]:: ይህ ሥዕላዊ መግለጫ በ1ኛ ጴጥሮስ 1:6-7 እና 4:12 ላይ በመከራ ውስጥ ስለሚያልፉ ቅዱሳን ትምህርት ለመስጠት ጥቅም ላይ ውሏል::

እግዚአብሔር የገዛ እራሱን ሕዝቦች በማቅለጫ ላይ በሚያስቀምጥበት ጊዜ ዓይኖቹን በሰዓቱ ላይ እጆቹን ደግሞ በሙቀት መለኪያ መሣሪያው ላይ ያኖራል:: እርሱ ለምን ያህል ጊዜ መቆየት እንዳለበትና መጠኑም ምን ያህል ሊሆን እንደሚገባ ያውቃል:: ምናልባት እኛ መጀመሪያውኑ ስለ ምን እንዲህ እንደሚያደርግ ሙቀቱን ለምን አያበርደውም? ወይም አያጠፋውም ብለን እንጠይቅ ይሆናል፣ ነገር ግን ጥያቄዎቻችን ያለማመናችን ማስረጃዎች ብቻ ናቸው:: መልሱ ኢዮብ 23:10 ነው፡- «ግን እኔ የምሄድበትን መንገድ ያውቃል፤ ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ::» *ወርቅ እሳትን አይፈራም::* ማቅለጫው ወርቁን የበለጠ ንጹሕና ብሩህ እንዲሆን ብቻ ነው የሚያደርገው::

*ወደ ማቅለጫው ከመሄዱ በፊት* የኢዮብ ሕይወት እግዚአብሔ ርን የሚያስደስት መሆኑን ልብ ማለቱ ይጠቅማል (ቍ. 11-12):: ኤልፋዝ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲቀበልና እንዲታዘዘውም (22:22) ኢዮብን ያስጠነቅቀዋል፣ ነገር ግን ኢዮብ ያንን ቀድሞውኑ አድርጎታል:: በሕይወት ጉዳና ላይ በሚጓዝበት ጊዜ የእግዚአብሔ ር ቃል መመሪያው ነበር ደግሞም ወደ የትኛውም ጠመዝማዛ መንገድ እንዳይሄድ መጠንቀቅ ነበር:: ነገር ግን ከዚህም ባለፈ፣ የእግዚአብሔር ቃል ከዕለታዊ ምግቡ ይልቅ ለእርሱ ጥንካሬና ብርታት ይሆንለት ነበር:: ልክ እንደ ኤርምያስ (ኤር. 15:16) እና ኢየሱስ (ማቴ. 4:4፤ ዮሐ. 4:31-34)፣ ኢዮብ የእግዚአብሔር ቃል ውስጣዊ ማንነቱን የሚያረካ ብቸኛ ምግብ እንደ ሆነ ደርሶበታል

[*መዝ. 1:2*፤ (119):103፤ 1ኛ ጴጥ. 2:1-3]።

አንዳንድ ሰዎች በመከራ ማቅለጫ ውስጥ ይገባሉ ደግሞም ማቅለጫው እነርሱን ያቃጥላቸዋል፤ ሌሎች በውስጡ ይገባሉ ከዚያም ተሞክሮው ንጹሕ ያደርጋቸዋል። ልዩነቱን ያመጣው ምንድን ነው? *ለእግዚአብሔር ቃልና ለእግዚአብሔር ፈቃድ ያላቸው አመለካከት (ዝንባሌ) ነው።* በቃሉ የረሰረሰን ከሆነ እና ለፈቃዱ የምንገዛ ከሆነ፣ የማቅለጫው ተሞክሮ የቱንም ያህል የሚያሳምም ቢሆንም፣ ያጠራናል ደግሞም የተሻልን እንድንሆን ያደርገናል። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምንጋፋ ከሆንን፣ ደግሞም የእርሱን እውነት በመመገብ ረገድ ከወደቅን፣ የማቅለጫው ተሞክሮ ለእኛ ያለው ፋይዳ እኛን ማቃጠል ብቻ እና ማስመረር ነው።

ኢዮብ ሁለተኛውን የሚያጉረመርምበትን ምክንያት አቀረበ።

**(2) «እግዚአብሔር እያስደነገጠኝ ነው» (ኢዮብ 23:13-17)።** «እርሱ ግን ራሱን ችሎ ብቻውን የሚኖር ነው፤ የሚቋቋመውስ ማን ነው? እርሱ የፈቀደውን ያደርጋል» (ቊ. 13፣ አ.መ.ት)። ኢዮብ ለእርዳታ ወደ እነርሱ ዘወር የሚልባቸው ሌሎች አማልክት አልነበሩትም፣ ደግሞም እግዚአብሔርን ለመቃወም ወይም አሳቡን እንዲቀይር ለማድረግ ምንም መንገድ አልነበረውም። እግዚአብሔር ዓለምን (ህዋን) የሚመራው በጋራ መረዳት ወይም በዲሞክራሲያዊ ምርጫ አይደለም፣ ነገር ግን በትእዛዝ ነው። የእርሱ አሳቦችና መንገዶች ከእኛ አሳቦችና መንገዶች እጅግ የራቁና የመጠቁ ናቸው፣ ነገር ግን የቱ ምርጥ እንደ ሆነ ያውቃል ደግሞም ፈቃዱን መቀበልና በእርሱ መደሰት ይኖርብናል (ኢሳ. 55:8-11)።

የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት የሚገፉት ወይም የሚክዱት ሰ ዎች ከእራሳቸው ላይ ሰላምንና ድፍረትን ሰርቀዋል። «ከመለኮታዊ ሉዓላዊነት አስተምህሮ በላይ የእግዚአብሔርን ልጆች የሚያጽናና የእግዚአብሔር ባሕርይ የለም» አሉ ቻርለስ ሀዶን ስፐረጀን። «በአንድ በኩል በዓለማውያን ዘንድ ከዚህ የበለጠ የሚጠላ አስተ ምህሮ የለም።» ለምን? ምክንያቱም ያ ሰው ልበ ኩሩ (ትዕቢተኛ) ስለሆነ እና ለሁሉን ቻይ አምላክ መገዛት ስለማይፈልግ ነው። ሰ ዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ ደስታን ከማግኘት ይልቅ፣ የገዛ እራሳቸውን ነገር ማድረግ ይፈልጋሉ ደግሞም በገዛ



እራሳቸው መንገድ ያደርጉታል።

ይህ አስተምህሮ እንዲህ ያለ የመጽናናት ምንጭ ከሆነ፣ እንግዲያውስ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት አሳብ በሚመለከት በሚያስብበት ጊዜ፣ ስለ ምን ኢዮብ ደነገጠ? ይህ የሆነው ኢዮብ እጅግ በጣም ብዙ መከራ ስለ ተቀበለና ሁሉን ቻዩ አምላክ በቀጣይ ምን እንደሚያመጣበት ስለሚያውቅ ነበር። በቃሉ ውስጥ ፊቱን በምታዩበትና ድምፁን በምትሰሙበት ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር መገዛት አንድ ነገር ነው። ነገር ግን፣ ልክ እንደ ኢዮብ፣ በጨለማ እና በሥቃይ ውስጥ በምትሆኑበት ጊዜ፣ መውደቅም ሆነ መፍራት ቀላል ነገር ነው። «በእኔ ላይ የወሰነውን ይፈጽማል፤ ይህን የመሰለ ዕቅድም ገና ብዙ አለው» (ኢዮብ 23:14፣ አ.መ.ት)። ቀጥሎም ምን ይከሰታል?

ነገር ግን ኢዮብ 23:14 ከኤርምያስ 29:11 ጋር የሚቃረን መሆን አለበት። «ለእናንተ ያለኝን ዕቅድ እኔ ዐውቃለሁ» ይላል እግዚአብሔር፣ «ዕቅዱም ፍጻሜው ያማረና ተስፋ የሚሰጥ፣ እናንተንም የሚጠቅም እንጂ የሚጐዳ አይደለም» (አ.መ.ት)። *ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታችሁ በሚሆንበት ጊዜ፣ የወደፊቱ ጊዜ ወዳጃችሁ ይሆናል፣ ደግሞም ልትፈሩ አይገባችሁም።* ሮሎ ሜይ የተባለው የሥነ ልቡና ባለሙያ እንዲህ ሲል ጽፎአል፣ «የወደፊቱን ጊዜ ጥቅም ማረጋገጫ እጅግ ውጤታማው መንገድ የአሁኑን ጊዜ በድፍረትና ገንቢ በሆነ መልኩ መቋቋም ነው።» ደግሞም ያንን ለማድረግ ምርጡ መንገድ ለጌታ መገዛት እና እርሱ ሁሉን የሚቆጣጠር መሆኑን መገንዘብ ነው። «ሃሌ ሉያ፣ ሁሉን ቻይ ጌታ አምላካችን ነግሦአልና» (ራእይ 19:6)።

**(3) «እግዚአብሔር ግራ አጋብቶኛል» (ኢዮብ 24:1-25)።** ይህ መላው ምዕራፍ የሚያተኩረው እግዚአብሔር በዚህ ምድር ላይ እንዲሆኑ የሚፈቅዳቸው የሚመስሉ የፍትሕ መጓደሎች ላይ ነው። ኢዮብ ንግግሩን ጥያቄ በመጠየቅ ይጀምራል፣ «እግዚአብሔ ር ስለ ምን ችሎት ለመሰየም አንድ የተለየ ቀንን አይወስንም? ያኔ እኔም እርሱ ዓለምን የሚመራበት መንገድ ምን እንደ ሆነ ልነግ ረው እችል ነበር!»

ኢዮብ *በአገሪቱ ላይ የፍትሕ መጓደል* አለ በሚለው ይጀምራል (ቊ. 1-11)፣ ከዚያም ደግሞ *በከተማ ውዳሴት ወንጀሎች* ይሸጋራል

(ቊ. 12-17):: *በክፉዎች ላይ እርግማን በመጥራት* ንግግሩን ይደመድማል (ቊ. 28-29):: እግዚአብሔር ሊፈርድባቸው ባይፈልግም፣ ኢዮብ ይፈርድባቸዋል!

*በአገሪቱ ውስጥ የፍትሕ መጓደል አለ* (ቊ. 1-11):: አብዛኛውን ጊዜ፣ የትኞቹም ግድግዳዎችና አጥሮች የእርሻ መሬቶችን አይለያዩም፤ እያንዳንዱ ቤተሰብ የገዛ እራሱ የሆነ መሬት አለው፣ ደግሞም ሰዎች የመሬትን ድንበር ያከብራሉ («የወሰን አመልካች ድንጋዮች» አ.መ.ት፤ ዘዳግ. 19:14፤ ምሳሌ 22:28፤ 23:10 ተመልከት):: እግዚአብሔር የመሬት ወሰንን የሚጥሱ እና ንብረትን የሚሰርቁ ሰዎችን ሊረግም ተስፋ ሰጥቷል (ዘዳግ. 27:17)፣ ነገር ግን ክፉ ሰዎች ይህንኑ ያደርጉታል::

ነገር ግን በዚያ አያበቁም:: ምድሪቱ የእኛ ናት የሚሉ ብቻ አይደሉም፣ ነገር ግን በምድሪቱ ላይ ሆነው ሣር የሚግጡትን እንስሳት ሁሉ የእኛ ናቸው የሚሉ ናቸው! ከመበለቶችና አሳዳጊ ከሌላቸው ልጆች መንጋዎችን፣ አህዮችን እንዲሁም በሬዎችን ይወስዱና በድህነት ውስጥ ይጥሉዋቸው ነበር:: ኢዮብ 24:5-11 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ ድሆች መካከል አንዱን ሥዕላዊ መግለጫ ይሰጠናል:: ልክ በበረሃ እንዳሉ የዱር እንስሳት ምግብ ለማግኘት ይቅበዘበዛሉ (ቊ. 5-6)፣ ልብስ ስለሌላቸው ይበርዳቸዋል (ቊ. 7)፣ የሚኖሩበት ቤት ስለሌላቸው በዝናብ ጠል ይበሰብሳሉ (ቊ. 8)፣ ዕዳቸውን እስኪከፍሉ ድረስ ልጆቻቸው ከእጆቻቸው ተነጥቀው ስለ ተወሰዱባቸው ያለቅሳሉ (ቊ. 9)፣ እንዲሁም ለሀብታሞች ሥራ እንዲሠሩ ይገደዱ ነበር፣ ነገር ግን ከሚያመርቱት ምግብ እንዳይበሉ ይከለከሉ (ቊ. 10-11) ነበር:: በሬዎች እንኳ ከሚያበራዩት እህል እንዲበሉ ይፈቀድላቸው ነበር (ዘዳግ. 25:4)!

«አሁን፣» ሲል ኢዮብ ለጓደኞቹ ተናገረ፣ «እግዚአብሔር በክፉዎች ላይ የሚፈርድ ከሆነ፣ ድሆችን ኢፍትሐዊና ሰብዓዊነት በጐደለው መንገድ የሚያንገላቱ ሰዎች ላይ ለምን አይፈርድም?»

*በከተማ ውስጥ ወንጀሎች አሉ* (ቊ. 12-17):: ኢዮብ ስለ *ነፍሰ ገዳዮች* በመናገር ይጀምራል (ቊ. 12-14)፤ የቈሰሉ ሰዎችን ጩኸት ይሰማል ደግሞም የንጹሐንን ሞት ይመለከታል:: በአማካይ፣ ሥልሳ አሜሪካውያን በየቀኑ ይገደላሉ፣ ይህም በዓመት የሚሞቱት ሰዎችን ቊጥር ወደ 22,000 ገደማ ያደርሰዋል:: ይህም እንደ ፊየር ባንክስ፣ አላስካ፣ ወይም ኤል ሴሪቶ፣ ካሊፎርኒያ፣ ወይም አውጉስታ፣ መይን ያሉ ከተሞችን ሰዎች በሙሉ እንደ መግደል ነው:: ከእነዚህ ነፍሰ ገዳዮች አንዳንዶቹ ከቶ አልታወቁም፣ አልተያዙም ወይም አልተከሰሱም፤ ደግሞም ኢዮብ እንዲህ አለ፣ «እግዚአብሔር ግን ተጠያቂዎቹን ዝም ብሎአል» (ቊ. 12፣ አ.መ.ት):: ኢዮብ ማንንም አልገደለም፣ ይሁንና ጓደኞቹ እርሱ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች እንደ ነበረ ተናገሩ!

በቊጥር 15 ላይ ኢዮብ በአንዳንድ የከተሞች ክፍል በእርግጥ ተንሰራፍቶ ያለውን *የፍትወተ ሥጋ ኃጢአት* ጠቅሷል:: ዝሙት ሠሪው እና ድርጊቱ የሚፈጸምባት (አመንዝራዪቱ ሴት) ፍላጎታቸውን ከማርካታቸው በፊት ጨለማን ይጠባበቃሉ:: በተጨማሪም ጨለማን የሚጠባበቅ ሰው፣ ቤት ሰርስሮ የሚገባ *ሌባ* ነው (ቊ. 16-17):: «በከተማ ውስጥ ወንጀል አለ፣» ብሎ ተናገረ ኢዮብ፣ «ደግሞም እግዚአብሔር ስለዚህ ነገር ምንም ሊያደርግ የፈለገ አይመስልም::»

*በክፉዎች ላይ የሚመጣ እርግማን* (ቊ. 18-25):: ይህ አንቀጽ በክፉዎች ላይ ምን እንደሚከሰት እንደሚናገር *ዝርዝር* ሊታይ ይችል ይሆናል፤ ወይም ደግሞ፣ በክፉዎች ላይ እንደ ተናገረ *እርግማን* ተደርጎ እንደ ፍርድ ሊተረጐም ይችላል:: እኔ ፍርድን ያመለጡ የሚመስሉ ክፉ ሰዎች ላይ ኢዮብ ያስተላለፈው የግል እርግማኑ ይመስለኛል::

የኢዮብ እርግማን እንደዚህ አጠር ብሎ ሊቀርብ ይችላል:- «ክፉዎች በውኃ ውስጥ እንዳለ ዐረፋ ወይም በፀሐይ ሙቀት እንደ ቀለጡ በረዶዎች ይጥፉ:: በሁሉ፣ በገዛ እናቶቻቸው እንኳ፣ በመቃብር ውስጥ በሚያርፉበት ጊዜ የተረሱ ይሁኑ:: ሚስቶቻቸው ልጅ-አልባ ይሁኑ ደግሞም ምንም ልጆች አይውለዱ:: በመኸር ላይ እንዳለ ወደ ታች እንደሚወርድ እየቀነሱ ሲመጡ፣ ደኅንነታቸውና ዋስትናቸው ፈጥኖ ይጥፋ» (ቊ. 18-24)::

«እንዲህስ ባይሆን፣» በማለት ኢዮብ ስሜቱን ለሦስቱ ተቺ ጓደኞቹ መናገር ጀመረ:- «ሐሰተኛ የሚያደርገኝ፣ ነገሬንስ እንደ ምናምን የሚያደርገው ማን ነው?» (ቊ. 25):: ነገር ግን ይህን ከቶ ሊያደርጉት አልቻሉም::

ኢዮብ ከገዛ እራሱ በሻገር ሌላ ሰው በችግር ውስጥ ሆኖ በኃጢአትና በፍትሕ መጓደል ላይ ቅዱስ የሆነ ቍጣውን የገለጠበትን ሁኔታ እንዲመለከት ተናገረው:: ዘወትርም፣ የግል መከራ እራስ ወዳድ ያደርገናል፤ ደግሞም የሌሎችን ፍላጎት እንዳናይ ዕውር ያደርገናል፣ ነገር ግን የተጐዱ ሰዎችን እግዚአብሔር እንዲረዳ ኢዮብ ግድ ይለኛል:: ሦስቱ ጓደኞቹ የመከራ እንቆቅልሽን ሳይሆን፣ የተጐዱ ሰዎችን ተመልሰው እንዲመለከቱ ይጥር ነበር:: ኢየሱስም እንደዚሁ «ስለ ባልንጀራ» መወያየት በፈለገው ነገር ግን ባልንጀራው ማን እንደ ሆነ ያላወቀ እና ሊረዳውም ካልሞከረው ሕግ አዋቂ ጋር የገጠመው ችግር ተ መሳሳይ ነው (ሉቃስ 10:25-37)::

በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለ የፍትሕ መጓደል በሰዎች ኑሮ ውስጥ ታላቅ ሥቃይን ያመጣል፤ ስለዚህ ሕጉን ለመጠበቅና ፍትሕን ለማስፈን ማድረግ የምንችለውን ሁሉ ማድረግ ይኖርብናል:: ነገር ግን ሕጉን የሚያወጡት እንዲሁም ሕጉ እንዲተገበር የሚያደርጉት (ሕግ አስፈጻሚዎቹ) ሰዎች ብቻ ናቸው ደግሞም ከሁሉም ነገር ጋር ፍጹም በሆነ መንገድ ሊራመዱ አይችሉም:: ከእነዚህ በአንዱ ቀን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይመለሳል፣ በክፉዎች ላይ ይፈርዳል፣ ደግሞም የጽድቅ መንግሥቱን ይመሠርታል:: እርሱ እስኪመጣ ድረስ በዚህ ዓለም የክፉ መኖር እውነታን መቀበል ይኖርብናል:: ደግሞም «አሜን፣ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ና» ብለን መጸለያችንን መቀጠል ይኖርብናል (ራእይ 22:20)::



# ለግል ምልከታ እና ለቡድን ውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ልክ እንደ ኢዮብ ክፉኛ ብትሠቃዩ፣ ደግሞም እንደ ኢዮብ ብትከሰሱ፣ «ተገቢ አይደለም! እኔ ንጹሕ ነኝ!» ወይም «ይገባኛል» ወይም ከዚህ የተለየ አንድ ነገር የምትሉ ይመስላችኋል? ለምን?

2. ልክ እንደ ማንኛውም ኃጢአተኛ ሰው ሁሉ፣ ኢዮብ ኃጢአተኛ እንደ ነበረ የምናውቅ ስለሆነ፣ ከጓደኞቹ ለቀረበበት ክስ ንጹሕ ነኝ ብሎ መከራከሩን እንዴት እንገመግመዋለን::

3. መልካምነታችን የእግዚአብሔርን ፍቅር የማያስገኝልን ከሆነ፣ ከእርሱ ጋር ባለን ግንኙነት መልካምነታችን የሚፈይደው ነገር ምንድን ነው?

4. በኢዮብ ስፍራ እራሳችሁን ስታስቀምጡ፣ በምትከሰሱበት ክስ መካከል ስላጣችኋቸው ነገሮችና ስለ አካላዊ ሕመም (ሥቃይ) መከራ መቀበል እንዴት ይሰማችኋል?

5. ያለበት ተጨባጭ ሁኔታ ምንም ይሁን ኢዮብ እግዚአብሔርን ለመባረክ ይችል ዘንድ ብርታት የሰጠው ምንድን ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ?

6. የትኛው ከባድ ይመስላችኋል፡- በገዛ እራሳችሁ ያመጣችሁትን ውድቀት መቋቋም ወይስ ሙሉ በሙሉ የማይገባችሁን ውድቀት መቋቋም? ለምን?

7. አስቸጋሪ ጊዜ በሚገጥማችሁ ወቅት፣ የሚገባችሁ መሆኑንና አለመሆኑን ዘወትር ትገመግማላችሁ ወይ? ለምን ትገመግማላችሁ ወይም ለምን አትገመግሙም?

8. ብዙውን ጊዜ፣ መከራ በምትቀበሉበት ወይም በምትታገሉበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ምን እያደረገ ያለ ይመስላችኋል?

9. ኢዮብ እግዚአብሔር አንዳንዴ ግራ እንደሚያጋባው ተናግሮአል:: ስለ እግዚአብሔር ግራ የሚያጋባችሁ ምንድን ነው?

10. እግዚአብሔር ለምን ርምጃ ወስዶ እራሱን ተአምራዊ በሆነ መንገድ አያስታውቅም እንድትሉ የሚያደርጓችሁ በባህላችሁ ያሉ ክስተቶች ምንድን ናቸው?

11. እግዚአብሔር በሕይወቱ ውስጥ ስላለው ጣልቃ ገብነት ለኢዮብ የምትናገሩት ነገር ምንድን ነው?





# እንዴት ያለ ደካማ ሹክሹክታ!

## (ኢዮብ 25-28)

«እያንዳንዱ ዓመት ሰዎች ስለ መንፈሳዊ ነገር እንሥተው በሚነጋገሩበት ቁም ነገር ላይ እንድንቀጠቀጥ ያደርገኛል::»
- ቢሾፕ ብሩክ ኤፍ. ዌስትኮት

በኢዮብ 25 ላይ የበልዳዶስ ንግግር በመጽሐፍ ውስጥ ካሉ ንግግሮች ሁለ አጭሩ ሲሆን፣ በእግዚአብሔር ኃይል (ቍ. 1-3) እንዲሁም ፍትሕ (ቍ. 4-6) ላይ ያተኩራል:: የኢዮብ ጓደኞች ስለ እግዚአብሔር እጅግ በማወቅ ተናግረው ሳለ፣ በመጨረሻ እየተነጋገሩበት ስለ ነበረው ነገር ምንም እንደማያውቁ እግዚአብሔር መግለጡ ለማየት የሚረብሽ ነገር ነው:: ብዙውን ጊዜ፣ ስለ እግዚአብሔር ብዙ የሚናገሩት ሰዎች የሚያውቁት ትንሽ ነው::

*የእግዚአብሔር ኃይል* በባሕርይው ውስጥ (ቍ. 1-3) ይገኛል:: በእርሱ ዘንድ ሁሉን መግዛትና መፈራት አለ ደግሞም በሉዓላዊነት በሰማይ ላይ ግዛቱን አድርጓል:: ሁሉንም ነገር ከቁጥጥሩ በታች አድርጓል ደግሞም በሁሉም ስፍራ የሚከናወነውን ነገር ይመለከታል:: የመላእክት ሠራዊቱ ትእዛዙን በመጠባበቅ ላይ ናቸው ደግሞም ፈቃዱን ለመታዘዝ ዝግጁዎች ናቸው:: ማን ሊቋቋመው ይችላል?

*የእግዚአብሔር ፍትሕ* ቅዱስ የሆነ ባሕርይው ነጸብራቅ ነው (ቍ. 4-6)፣ ምክንያቱም «እግዚአብሔር ብርሃን ነው፣ ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም» (1ኛ ዮሐንስ 1:5):: እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ስለሆነ፣ ሰዎች እንዴት በፊቱ ጻድቅ ነን ይላሉ? (አስታውስ፣ ኢዮብ ታማኝነቱን እንደ ጠበቀ እንዲሁም ኃጢአትን

መናዘዝን ዕንቢ ማለቱ የእግዚአብሔርን ፍርድ አምጥቶበታል።) ሰው ከሴት የሚወለድ በመሆኑ ከኃጢአተኛ ባሕርይ ጋር ነው የሚወለደው (መዝ. 51:5)። በምሥራቅ ጨረቃና ከዋክብት በታላቅ ብሩህነት ያበራሉ፤ ነገር ግን እነርሱም እንኳ በእግዚአብሔር ፊት ንጹሐን አይደሉም። አፈር እና ትል የሆነ ሰው በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ጻድቅ ነኝ ብሎ ሊናገር ይችላል? (ኢዮብ 4:17-18፤ 8:20፤ 9:2 ተመልከት።) አሁን፣ የኢዮብን ምላሽ እንስማለን።

## ኢዮብ ለእግዚአብሔር ኃይል እውቅና ሰጠ (ኢዮብ 26)

በሕዋ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ታላቅ ኃይል ከማጉላቱ በፊት ምንም ስላልረዳው በመጀመሪያ ኢዮብ በልዳዶስን ወቀሰ (ኢዮብ 26:1-4)። ኢዮብ ምንም ኃይል የለውም፣ ነገር ግን በልዳዶስ ጠንካራ አያደርገውም። እንደ ጓደኞቹ አነጋገር፣ ኢዮብ ጥበብ ወይም ማስተዋል ጐድሎታል። «ይህን ቃል እንድትናገር የረዳህ ማን ነው? የማንስ መንፈስ በአንደበትህ ተጠቀመ?» (ቁ. 4፣ አ.መ.ት)። የበልዳዶስ ቃል ከእግዚአብሔር የመጣ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ለኢዮብ መልካምን ባደረገለት ነበር፤ ምክንያቱም ኢዮብ እግዚአብሔር እንዲናገረው ይጮኽ ነበረና። መደምደሚያውም የበልዳዶስ ቃሎች ከበልዳዶስ የመጡ ናቸው፣ ደግሞም ለዚህ ነው ለኢዮብ ምንም ያልፈየደለት።

ከዚያም ኢዮብ የእግዚአብሔርን ታላቅነት አሞገሰ (ቁ. 5-13)። እግዚአብሔር እያንዳንዱን ነገር፣ የሙታንን ዓለም እንኳ፣ ያያል (ቁ. 5-6)። የሙታን መኖሪያ ስፍራን በተመለከተ ኢዮብ ሦስት የተለያዩ ስሞችን ይጠቀማል፦ ውኆች፣ ሲኦል እና «ጥፋት» («አብዶን፣»፣ ራእይ 9:11)። እግዚአብሔር በሙታን ዓለም ላይ የሚሆነውን የሚያይ ከሆነ፣ እንግዲያውስ በሕያዋን ዓለም የሚከናወነውን ነገር በእርግጠኝነት ያውቃል!

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የሚያይ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ሁሉንም ነገር አበጅቶአል፤ ይቆጣጠራልም (ኢዮብ 26:7-13)። ኢዮብ የምስጋና መዝሙሩን በሰማያት ላይ ስላለው የእግዚአብሔር ኃይል በማስመልከት በአንድ ትክክለኛነት ምድርን ይገልጻታል (ቁ. 7)። እግዚአብሔር ደመናትንና ዝናብንም ጭምር ይቈጣጠራል። ከዚያም ኢዮብ ትኩረቱን ወደ ምድር አደረገ (ቁ.



10-11) ደግሞም ዐለይ የምትወጣበትን እና የምትጠልቅበትን አድማስ ስለ መሥራቱ እግዚአብሔርን አመሰገነ። እርሱ ቀንና ምሽትን እንዲሁም ምድርንና ባሕርን የሚቈጣጠር አምላክ ነው። «የሰማይ ምሰሶዎች» ተራሮችን ለመግለጽ የገባ ሥነ ግጥማዊ ሐረግ ነው፤ በምድር ላይ ያርፋሉ፣ ነገር ግን ሰማያትን የተሸከሙ ይመስላሉ። እግዚአብሔር ብቻ ይናገራል፣ ተራሮችም ይንቀጠቀጣሉ (9:6)።

የኢዮብ መዝሙር የመጨረሻው ስንኝ በውኆች ላይ ያለ የእግዚአብሔር ኃይልን ማዕከል ያደረገ ነበር (26:12-13)። እግዚአብሔር እንደ ወደደ ባሕሩን ሊያናውጠውም ሆነ ረጋ እንዲል ሊያደርገው ይችላል፣ ደግሞም በባሕር ውስጥ ባሉ ፍጡራን («ረዓብ») እና በ«ተወርዋሪው እባብ»፣ አ.መ.ት) ላይ ሥልጣን አለው። ደመናትን ሊበትናቸው እና ሰማዩን ከነጕድጓድ ንጹሕ ሊያደርገው ይችላል።

ሦስቱ ጓደኞች ትዕግሥት ባጣ መልኩ ሳያዳምጡት አልቀሩም፣ ምክንያቱም ቀድሞውኑ ኢዮብ ይናገርበት የነበረውን ነገር አውቀው ነበር፣ *ነገር ግን ከንግግሮቹ በመነሣት ትክክለኛ ድምዳሜ ላይ አልደረሱም።* የእግዚአብሔርን እጅ ሥራ ከተፈጥሮ ተመልክተው ነበርና፣ ስለ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንደሚያውቁ አሰቡ፤ ስለዚህ ስለ እግዚአብሔር ለኢዮብ ሊያብራሩለት ቻሉ።

ኢዮብ ደግሞ የዚህ ተቃራኒው ነው ትክክል አለ። «እነዚህ የሥራው ዳር ዳር ናቸው፤ ስለ እርሱ የሰማነው ምንኛ አነስተኛ ነው? የኃይሉንስ ነጐድጓድ ማን ሊያስተውል ይችላል?» (ቁ. 14፣ አ.መ.ት)። በፍጥረት ውስጥ ስለ እግዚአብሔር የምንመለከታቸው ነገሮች የመንገዱ አሻራዎች ብቻ ናቸው፣ እንዲሁም የምንሰማው ነገር የኃይሉ ሹክሹክታ ብቻ ነው! የተፈጥሮን መጽሐፍ በጥንቃቄ ልታነበቡት ትችላላችሁ፣ ይሁንና አሁንም ስለ እግዚአብሔር ገና የምትማሩት ብዙ ነገር ይኖራል። እግዚአብሔር ስለ ፈጠራቸው ነገሮች ጥቂት እውነታዎችን ማወቅ ስለ ፍጥረት ሁሉ አምላክ እውነታን እንደ ማወቅ ያለ ነገር አይደለም።

የአሥራ አራተኛው ምእተ ዓመት ብሪታኒያዊው መንፈሳዊ ጸሐፊ ሪቻርድ ሮል እንዲህ አለ፦ «እግዚአብሔርን በእውነት

ፍጹም በሆነ መንገድ ያወቀ ሰው እርሱ ከመረዳት በላይ እንደ ሆነ እንዲሁም ለመታወቅ የማይቻል እንደ ሆነ ይደርሰበታል፡፡» የበለጠ ስለ እግዚአብሔር እያወቅን ስንሄድ፣ ሊታወቅ የሚገባ እጅግ ብዙ ነገር እንዳለ እናውቃለን! ስለ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እናውቃለን ከሚሉ ሰዎች ተጠበቁ፣ ምክንያቱም እራሳቸውንም ሆነ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ የሚናገሩት ነገር ያስረዳባቸዋልና፡፡

## ኢዮብ በእግዚአብሔር ፍትሐዊነት ላይ ጥያቄ አነሣ (ኢዮብ 27)

እግዚአብሔር ቅዱስ በመሆኑ፣ በእርሱ ፊት ማንም ጻድቅ ሆኖ መቆም እንደማይችል በልዳዶስ ግልጥ አድርጓል (ኢዮብ 28:4-6)፡፡ የዚህ አነጋገር ተፈጥሮአዊ ውጤቱ ስለ ኃጢአታቸው ሰዎችን ለመቅጣት እግዚአብሔር ይገደዳል፤ አለበለዚያ፣ እርሱ ጻድቅ አምላክ አይሆንም፡፡ ኢዮብ እየተሠቃየ ከሆነ፣ አንዳች ኃጢአት ሠርቶ መሆን አለበት፡፡

**ኢዮብ መሐላ አደረገ (ኢዮብ 27:1-6)**፡፡ ኢዮብ እንደ ገና ታማኝነቱን በማጽናት ቆመ (10:1-7፤ 13:13-19፤ 23-27፤ 23:2-7)፤ ነገር ግን በዚህ ጊዜ መሐላ አደረገ፡- ይህም «ሕያው እግዚአብሔርን» የሚል ነበር (27:2)፡፡ በዚያ ዘመን በነበሩት የምሥራቅ ሰዎች መካከል፣ መሐላ ማድረግ ከባድ ነገር ነበር፡፡ የምትናገሩት ነገር እውነት ባይሆን እንዲገድላችሁ እግዚአብሔርን እንደ መጋበዝ ነበር፡፡ ኢዮብ ስለ እራሱ ያንን ውሳኔ ለማሳለፍ እርግጠኛ ነበር፡፡

በተጨማሪም ኢዮብ እግዚአብሔር ፍትሕን እንዳላሰፈነበት («ፍትሕ የነሣኝ» ቊ. 2፣ አ.መ.ት) የሚል ክሱን በተደጋጋሚ አቅርቦአል፡፡ በእርሱ ላይ የቀረቡ ክሶችን እንዲያሳውቅ ኢዮብ እግዚአብሔርን ጠይቋል፣ ነገር ግን ለማያት ጸጥ ብለዋል፡፡ ኢዮብ ችሎት እንዲሰየምና እርሱንና እግዚአብሔር በአንድ ላይ እንዲገናኙ ተናግሯል፣ ነገር ግን የተዘጋጀ ችሎት አልነበረም፡፡

ስለዚህ እርሱ በሕይወት እስካለ ድረስ፣ እራሱን መከላከልና ታማኝነቱን መጠበቅ ይችላል፡፡ ጓደኞቹን ለማስደሰት ሲል ወይም እግዚአብሔር የወደፊት ዕጣ ፈንታውን የተቃና እንዲያደርግለት



ሲል ብቻ መዋሸት አይኖርበትም፡፡ (በዚያ ሰይጣን ይደሰታል!) ጓደኞቹ ምንም ይበሉ ወይም አምላኩ በእርሱ ላይ ምንም ያድርግ፣ ኢዮብ ኅሊናውን («ልብ»፣ ቊ. 6) በመጠበቅ መኖር ነበረበት፡፡

**ኢዮብ እርግማንን ተናገረ (ኢዮብ 27:7-10)**፡፡ በምሥራቅ፣ የተከሰሱ ሰዎች ንጽሕናቸውን ማጽናታቸው ብቻ በቂ አይደለም፣ በተጨማሪም እነርሱ በደለኞች እንደ ሆኑ በተናገሩ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔርን ቊጣ እንዲጠሩ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የኢዮብ ቃሎች «ኢምፕሪካቶሪ»-እርግማንን በጠላት ላይ የሚያውጁ መዝሙሮችን ያስታውሱናል (መዝ. 58፣69፣ 137፣ ወዘተ. . .) ይህም በጠላቶቹ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እንዲመጣ መዝሙረኛው ያቀረባቸው ጸሎቶች ናቸው፡፡

የኢዮብ ጠላቶች እነማን ነበሩ? እርሱ በደለኛ ነው ደግሞም በእግዚአብሔር ሊቀጣ ይገባዋል ከሚሉት ከሦስቱ ጓደኞቹ ጋር የሚስማማ የቱም ሰው ጠላቱ ነበር፡፡ ይህ ውይይት እየተደረገ ሳለ፣ ብዙ ሰዎች በዐመድ ቁልሉ ዘንድ የተሰበሰቡ ደግሞም ክርክሩን እየሰሙ እንዲሁም ብዙዎቹ ምናልባት ከበልዳዶስ፣ ከሶፋርና ከኤልፋዝ ጋር እየወገኑ ያሉ ይመስላል፡፡ ኢዮብ በዚያ ያሉ የሚነገረውን የሚያደምጡ ሰዎች ከኢዮብ ጓደኞች ጋር በመስማማት ራሳቸውን ሲነቀንቁ ተመለከተ፣ ደግሞም እርሱ በቊጥር እንደ ተበለጠ አወቀ፡፡

የኢዮብ ቃሎች ለእኛ፣ በተለይ በኢየሱስ (ማቴ. 5:38-48) እና በጳውሎስ (ሮሜ 12:17-21)፣ በሁለቱም ከተነገሩት ጠላቶቻችንን ይቅር ማለት እንደሚገባ ከተማርነው ትምህርት ጋር አዛምደን ስንመለከታቸው፣ የጭካኔ ንግግሮች ሊመስሉን ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ኢዮብ የተራራው ስብከት ይቅርና የሙሴ ሕግ ከመሰጠቱ በፊት እንኳ የኖረ ሰው ነበር፤ ደግሞም በኢየሱስ (ሉቃስ 23:34) እና በእስጢፋኖስ (የሐዋ. 7:60) ውስጥ የታየው መንፈስ በእርሱ ውስጥ እንዲኖር መጠበቅም አይኖርብንም፡፡

ይሁን እንጂ፣ በእግዚአብሔር እይታ፣ ኢዮብ *ትክክል* ነበር፡፡ እግዚአብሔር በሰማይ ሠራዊት ፊት ኢዮብ «እንከን አልባና፣ ጻድቅ እግዚአብሔርን የሚፈራና ከክፋት የራቀ ሰው መሆኑን» ሁለት ጊዜ፣ መስክሮአል (ኢዮብ 1:8፣ 2:3)፡፡ ስለዚህ፣ የኢዮብ

ጠላቶች ተሳስተዋል፤ ደግሞም ኢዮብ ነፃ እንዲያወጣው እግዚአብሔርን የመጠየቅ መብት ነበረው:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ኢዮብ ጻድቅ እንደ ሆነ ጠላቶቹ ደግሞ እንደ ተሳሳቱ ማረጋገጥ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነበር:: ታዲያ፣ ኢዮብ ከእግዚአብሔር ሌላ የት ሄዶ እርዳታን ይጠይቅ?

ሦስቱ ጓደኞቹ በተደጋጋሚ የክፉዎች ፍጻሜ ምን ዓይነት አስከፊ እንደ ሆነ በመንገር አስጠንቅቀውታል፣ ስለዚህ ኢዮብ ቃሎቻቸውን መልሶ ወረወረላቸው:: «ጠላቴ እንደ በደለኛ፣ ባላንጣዬም እንደ ክፉ ይሁን» (27:7፣ አ.መ.ት):: ኢዮብ ጠላቶቹ በታላቅ ኀዘን ውስጥ ሆነው ለእርዳታ ወደ እግዚአብሔር ሲጮኹ ነገር ግን ምንም መልስ ሳያገኙ ተመልክቷል፣ ደግሞም በድንገት በሞት ሲወገዱ አይቷል:: ነገር ግን የኢዮብ ጓደኞች በእርሱ ላይ እየተነበዩት ያሉትና ምናልባትም ይመጣል ብለው የሚጠብቁት ይህን አይደለምን?

በልዳዶስ እግዚአብሔር ጻድቅ እንደ ሆነና እርሱን የማይታዘዙትን ሰዎች እንደሚቀጣ አስረግጦ ተናግሮአል:: ነገር ግን ይህ ማለት እያንዳንዱ መከራ የሚቀበል ሰው ስለ ሠራው ኃጢአት የሚቀጣ ነው ማለት አይደለም:: አንዳንድ ጊዜ በሌሎች ሰዎች ኃጢአት ምክንያት መከራ እንቀበላለን (ለምሳሌ፣ ዮሴፍ) ወይም እግዚአብሔር ከኃጢአት ስለ ጠበቀን እንሠቃያለን (ለምሳሌ፣ ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮ. 12):: ኢየሱስ የተሠቃየው ስለ እራሱ ኃጢአት አልነበረም፣ እርሱ ምንም ኃጢአት አልነበረበትምና:: ነገር ግን ለዓለም ኃጢአት ነበር የተሠቃየው (1ኛ ጴጥሮስ 2:22-24፣ 3:18)፤ ደግሞም በሥቃዩና በሞቱ ምክንያት ኃጢአተኞች ለማመንና ዘላለማዊ ሕይወትን ለመቀበል ይችላሉ::

**ኢዮብ አንድ ትምህርት ያስተምረናል (ኢዮብ 27:11-23)::** «ስለ እግዚአብሔር ክንድ አስተምራችኋለሁ» (27:11፣ አ.መ.ት) አለ ኢዮብ፤ ደግሞም በክፉዎች ላይ የሚመጣ የእግዚአብሔርን ፍርድ ዘረዘረ:: እግዚአብሔር ኢዮብን ነፃ በሚያደርግበት ቀን፣ በጠላቶቹ ላይ የሚከሰተው ነገር ይህ ነው::

ይሞታሉ፣ ደግሞም መበለቶቻቸው አያለቅሱላቸውም፣ ይህ በምሥራቃዊ ዓለም ባህል አስከፊ ስድብ ነበረ:: ልጆቻቸው በሰይፍ



ይታረዳሉ ወይም በወረርሺኝ ይሞታሉ፤ ከዚህ ያመለጡ ካሉ የሚመገቡትን ለማግኘት ሲሉ በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ለማኞች ይሆናሉ:: ክፉዎች ሀብታም ሆነው ይጋደማሉ፣ ድሃ ሆነውም ይነቃሉ:: የብር ጌጣቸውና ውድ የሆኑ ልብሳቸው ይጠፋሉ:: ቤቶቻቸው ልክ እንደ ኩቦች (ወይም የሸረሪት ድር)፣ ወይም በሜዳ ላይ እንዳለ የጉበኛ ጎጆ ይጠፋሉ:: የክፉዎች ሞት ሰላማዊ አይሆንም:: ፍርሃት፣ ልክ እንደ ጐርፍ፣ በማታ ይመጣል ጠርጎም ይወስዳቸዋል:: ክፉዎች ለማምለጥ ቢሞክሩ እንኳ፣ ነጐድጓድ ይከተላቸውና ያጠፋቸዋል::

በዚህ መግለጫ ውስጥ የኢዮብ ጓደኞች የተናገሩዋቸው ብዙዎቹ በጓደኞቹ «በፍርድ» ሥዕላዊ መግለጫዎች እርሱን ለመቃወም የተናገሯቸው መሆናቸውን ልትገነዘቡ ትችላላችሁ:: የሚናገሩዋቸው ነገሮች የእራሳቸውን ቅጣቶች የሚያውጁ መሆናቸውን ተመልክተው ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ሊያስታውሳቸው ኢዮብ ይህን ሆን ብሎ ነበር ያደረገው:: «እንዳይፈረድባችሁ በማንም ሰው ላይ አትፍረዱ፤ በምትፈርዱበትም ዓይነት ይፈረድባችኋል፤ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል» (ማቴ. 7:1-2)::

የእግዚአብሔር ቃል በጠላት የታሰበ ፍርድ በጠላት በእራሱ ቤት ላይ እግዚአብሔር እንደ መለሰው ብዙ ጊዜ ይናገራል:: ፈርዖን ግና የሚወለዱ የዕብራውያን ሕፃናት በወንዝ ውስጥ እንዲሰጥሙ አዘዘና፣ በኋላ የገዛ እራሱ ጦር በቀይ ባሕር ውስጥ ሰጠመ (ዘጸአ. 1:15-22፤ 14:23-31):: ሐማ መርዶክዮስን ለመስቀል መስቀያ አዘጋጀ፣ ነገር ግን በዚህ ፈንታ ሐማና ወንዶች ልጆቹ ተሰቀሉበት (አስ. 7:10፤ 9:25):: የዳንኤል ጠላቶች ሊያጠፉት ሞክረው ነበር፣ ነገር ግን በዳንኤል ፈንታ እነርሱና ቤተሰቦቻቸው በአንበሳ ጕድጓድ ውስጥ በመጣል መጨረሻቸው ሆነ (ዳን. 6:24፤ ምሳሌ 11:8ን ተመልከት)::

በኢዮብ 27:23 አተረጓጐም ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች አይስማሙበትም:: ኒው አሜሪካን ስታንዳርድ ባይብል፣ «ሰዎች በእርሱ ላይ እጃቸውን ያጨበጭባሉ፣ ደግሞም ከስፍራው ላይ ያስወግዱታል» በሚል ይነበባል፣ ደግሞም ከዚህ ጋር ብዙዎቹ ትርጉሞች ይስማማሉ፣ ነገር ግን ሰዎች የሚለው ቃል የመጀመሪ

ያ በሆነው ጽሑፍ (በዕብራይስጡ) ውስጥ የለም:: በቀጥታ «እርሱም በእርሱ ላይ እጆቹን ያጨበጭባል» ብቻ ነው የሚለው:: «እርሱ ማን ነው?» ኤልመር ቢ. ስሚክ *በኤክስፖዚተሪ ባይብል ኮመንተሪ*፣ እግዚአብሔር ሊሆን ይችላል ሲል አሳብ ይሰጣል፣ ደግሞም ቍጥር 23 የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት እግዚአብሔር ከሆነበት ከቍጥር 13 ጋር ሊያያዝ ይገባል (ጥራዝ 4፣ 972):: ቍጥር 23ን «በእነርሱ ላይ እጆቹን ያጨበጭብባቸዋል ደግሞም ከመኖሪያው [ከሰማይ] ያሳድዳቸዋል::» ብሎ ተርጕሞታል:: እግዚአብሔርም ሆነ ሰው፣ ክፉዎች በሚጠፉበት ጊዜ ይደሰታሉ::

## ኢዮብ የእግዚአብሔርን ጥበብ ፈለገ (ኢዮብ 28)

«ነገር ግን ጥበብ ከየት ይገኛል?» (ኢዮብ 28:12):: «ታዲያ ጥበብ ከወዴት ትመጣለች? ማስተዋልስ የት ትገኛለች?» (ቍ. 20፣ አ.መ.ት):: ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የጠየቀበት ምክንያት «በጥበብ» ስም ሦስቱ ጓደኞቹ ይናገሩዋቸው የነበሩ «ለዛ ቢስ አባባሎች» እና «የታወቁ እውነታዎችን» መስማት ታክቶት ነበር:: ጓደኞቹ ቃሎቻቸው ንጹሕ «ወርቅ» እንደ ሆኑ እርግጠኞች ነበሩ፣ ነገር ግን የወረቀት ማስጌጫ እና የማይረቡ ቆሻሾች እንደ ሆኑ ኢዮብ ድምዳሜ ላይ ደረሰ:: ሦስቱ ሰዎች *እውቀት* ነበራቸው፣ *ጥበብ* ግን ይጐድላቸው ነበር::

«ጥበብ የእውቀት ትክክለኛ አጠቃቀም ነው፣» በማለት ቻርለስ ስፐርጀን ተናገሩ:: «ማወቅ ማለት ጥበበኛ መሆን ማለት አይደለም:: ብዙ ሰዎች (ወንዶች) ብዙ ነገር ያውቃሉ፣ ደግሞ ከሁሉም የላቁ ቂሎች ናቸው:: ቂል መሆኑ ከሚታወቅበት የሚበልጥ ቂል ከቶ የለም:: ነገር ግን እውቀትን በሥራ ላይ ማዋል ጥበብ ነው::

በዚህ ስለ ጥበብ በሚናገረው ግጥም ውስጥ፣ «ጥበብ የሚገኘው የት ነው?» ለሚለው ጥያቄው ኢዮብ ሦስት ምላሾችን ይሰጣል::

**(1) ጥበብን በማዕድን ፍለጋ ቍፋሮ ማግኘት አትችሉም (ኢዮብ 28:1-11)::** ኢዮብ ጀግና የሆኑ ሰዎች ወርቅን፣ ብረትን፣ መዳብን፣ እና የከበሩ ድንጋዮችን ቈፍረው ወደሚያወጡበት ወደ መሬት ጥልቀት ይወስደናል:: የከበሩ ብረቶችና የከበሩ ድንጋዮች በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የጥበብ ምልክቶች በመሆን ጥቅም



ላይ ውለዋል (ምሳሌ 2:1-10፤ 3:13-15፤ 8:10-21፤ 1ኛ ቆሮ. 3:12-23):: አንድ ጊዜ ካገኛችሁት በኋላ፣ በማቅለጫው ውስጥ ታጠሩታላችሁ ደግሞም ተግባራዊ ጥቅም እንዲሰጥ ታበጁታላችሁ:: ጳውሎስ የእግዚአብሔር ጥበብ ተቃራኒ የሰው ጥበብ፣ እርሱም «እንጨት፣ አገዳ እና ገለባ» ማለትም ውብ ያልሆኑ ዕድሜ የሌላቸው እና ጥቅም-አልባ የሆኑ ቍሳቍሶች ናቸው ብሏል (1ኛ ቆሮ. 3:12):: በምድር ገጽ ላይ እንጨትን፣ አገዳንና ገለባን ታገኛላችሁ፤ ነገር ግን እውነተኛ ሀብቶችን ለማግኘት የምትፈልጉ ከሆናችሁ፣ በጥልቀት መቆፈር ይኖርባችኋል::

ሰዎች እንዴት ጠንክረው እንደሚሠሩ እንዲሁም ቍሳዊ ሀብትን ለማግኘት ታላቅ አደጋን እንደሚጋፈጡ ኢዮብ ያብራራል:: በጠንካራ ዐለቶች ውስጥ ፈልፍለው ይገባሉ፣ ሀብትንም ለማግኘት ሕይወታቸውን አደጋ ላይ ይጥላሉ:: *ወንዶችና ሴቶች የእግዚአብሔር ጥበብን ለማግኘት ጥረት ለምን አያደርጉም?* የእግዚአብሔር ቃል በከበሩ ሀብቶች እንደ ተሞላ ጥልቀት ያለው የማዕድን ማውጫ ጕድጓድ ነው፣ ነገር ግን አማኙ ሀብቱን ለማግኘት ጥረት ማድረግ ይኖርበታል:: ጥንቃቄ የተሞላበት ንባብ፣ እና ጥናት፣ ጸሎት፣ ማሰላሰል፣ እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል ሀብቶችን ቆፍሮ ለማውጣት መታዘዝን ያስፈልጋል፣ ደግሞም መንፈስ ቅዱስ በዚህ ረገድ ሊረዳን ፈቃደኛ ነው:: ይህ ታላቅ ሀብት በአቅራቢያችን ላይ ሳለ ስለ ምን እኛ ቸልተኞች ሆንን?

ምንም እንኳ ሰው ምድርን በጥልቀት ሊቆፍር ደግሞም ታላቅ ሀብትን ለማገኘት ቢችልም፣ ደግሞም ወፎች እና አውሬዎች ሊሄዱበት ወዳልደፈሩባቸው ስፍራዎች ቢሄድም፣ ምንም እንኳ የተደበቁ የታላላቅ ወንዞች መነሻ ምንጫቸውን ለማገኘት ቢችልም፣ *ሰው የእግዚአብሔርን ጥበብ ሰብዓዊ በሆነ ጥረት ብቻ ሊያገኘው አይችልም::* ከድፍረት እና ከተጨበጠ እውቀት ያለፈ ነገርን ይሻል፤ ትሕትና እና መንፈሳዊ እይታን ይጠይቃል::

አንድ ሰው በአንድ የሕይወት አቅጣጫ ላይ በሚደነቅ መልኩ የተሳካለት የመሆኑ እውነታ እርሱ ወይም እርሷ የሕይወት ገጽታ ላይ እንዲናገሩ ብቃትን ይሰጣቸዋል ማለት አይደለም:: የማስታወቂያ ባለሙያዎች ምላጭን ወይም መኪናን ለመሸጥ ፖሮጮችን፣ ወይም መድኃኒትን ለመሸጥ ወንድ እና ሴት ተ

ዋናዎችን ይጠቀማሉ። ታዋቂ የሆኑ ሳይንቲስቶች (መጽሐፍ ቅዱስን አጥንተው የማያውቁት) ስለ መንፈሳዊ ነገሮች በሥልጣን በሚናገሩበት ጊዜ፣ ልክ ያልሠለጠነ አማተር የሥነ መለኮት ሰው እንደሚናገረው ሁሉ አሳባቸው ተቀባይነትን ያገኛል።

**(2) ጥበብን ልትገዛት አትችልም (ኢዮብ 28:12-19)።** የቱም ነገር ሊገኝም ሆነ ሊከናወን የሚችለው በቂ ገንዘብ ያላችሁ ከሆነ ብቻ ነው ሲል ዘመናዊው ኅብረተሰብ ያስባል። ወንጀልን በመከላከል ረገድ ብክለትን ለማስቆም፣ የሥራ በሮችን ለመክፈት እና የተሻለ የአየር ንብረት ለመፍጠር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተለቅ ያለ የዓመታዊ በጀት ድልድልን ይጠይቃሉ። በዘመናዊው ማኅበረሰብ ውስጥ ለመኖር የተወሰነ የገንዘብ መጠን የሚያስፈልግ ሲሆን፣ ዓለም እንደምትናገርለት ገንዘብ ሁሉንም ነገር የሚሠራ አይደለም። *ገንዘብ ሊገዛቸው የማይችሉ ነገሮችን የማትጥሉ ከሆነ፣* ገንዘብ ሊገዛቸው በሚችሉ ነገሮች መደሰት መልካም ነው (1ኛ ጢሞ. 6:17)።

በእነዚህ ቍጥሮች ውስጥ ኢዮብ ወርቅን አምስት ጊዜ፣ ብርን አንድ ጊዜ ይጠቅሳል፣ እንዲሁም ሰባት ልዩ ልዩ የከበሩ ድንጋዮችን በስም ይጠራል፤ ይሁንና ከእነዚህ ሀብቶች የትኛውም ቢሆን በግል ወይም ደግሞ ሁሉም በአጠቃላይ፣ የእግዚአብሔርን ጥበብ ሊገዙ አይችሉም። እውነተኛው ችግር *ሰው የጥበብን ዋጋ በአእምሮው ሊገምተውም የማይችል ሆኖ ሳለ፣ በእርካሽ ዋጋ ሊያገኘው እንደሚችል ማሰቡ ነው* (ኢዮብ 28:13)። «(ጥበብ) ከቀይ ዕንቍ ይልቅ ውድ ናት፤ አንተ ከምትመኘውም ሁሉ የሚስተካከላት የለም» (ምሳሌ 3:15)። እውነተኛ ጥበብ ውድ ናት። አንድ የተቀዳ ነገርን በመስማትህ፣ ዐውደ ጥናት በመካፈልህ ወይም ኃይለኛ ሰባኪን በማዳመጥህ ብቻ ወዲያውኑ የምትቀበላት አይደለችም።

**(3) ጥበብ ከእግዚአብሔር ብቻ ትመጣለች (ኢዮብ 28:20-28)።** ወፎች ሊበሩበት ወደሚችሉት ከፍታ ሂድ፣ በዚያ ጥበብን አታገኛትም። እንደ አባዶን እና ሞት ጠልቀህ ሂድ፣ በዚያም ጥበብን አታገኛትም። ጥበብ የት እንደምትገኝ የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉን ማየት ይችላልና። (በዚያ ምን እንዳለ ለማየት መሬትን ጠልቆ መቈፈር



አያስፈልገውም!) እግዚአብሔር የንፋስን ግፊት ለማስተካከል እንዲሁም በከባቢ አየር ላይ ያለውን የውኃ መጠን ለመለካት የሚያስፈልገው ጥበብ አለው። እነዚህ መጠኖች ከተቀየሩ፣ በተፈጥሮ ላይ ምን ዓይነት መዛባትን ያመጡ ይሆን! እግዚአብሔር ዝናብን እንዴት እንደሚቈጣጠር ደግሞም በምድር ላይ በሚወርድበት ጊዜ ነጐድጓዱን እንዴት እንደሚመራው ያውቃል። የመብረቅ ብልጭታ እና የነጐድጓድ ድምፅ ለእኛ በዘፈቀደ የሚመጡ ሊመስሉን ይችላል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር መብረቅንና ነጐድጓድን እንኳ ይቈጣጠራል።

ኢዮብ «ጥበብ የት ትገኛለች?» የሚለውን ጥያቄውን በኢዮብ 28:28 ላይ ይመልሳል፡- «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፣ ቅዱስንም ማወቅ ማስተዋል ነው» (መዝ. 111:10፤ ምሳሌ 1:7፤ 9:10 ተመልከት)። ይህ እግዚአብሔር ስለ ኢዮብ የተናገረለት ነበር (ኢዮብ 1:8፤ 2:3)፤ ስለዚህ፣ ጓደኞቹ ስለ እርሱ ምንም ቢናገሩም፣ *ኢዮብ የጥበብ ሰው ነበር።*

«እግዚአብሔርን መፍራት» ምንድን ነው? እግዚአብሔርን መፍራት ለእርሱ ያለ ስለ ማንነቱ፣ ስለ ተናገረው ነገር፣ እንዲሁም ስለሚያደርገው ነገር አክብሮታዊ ፍቅር ነው (ሚል. 2:5-6)። ሽባ የሚያደርግ ሳይሆን፣ ጕልበታማ የሚያደርገው ነው የእግዚአብሔር ፍርሃት (ፈሪሃ እግዚአብሔር) የሚባለው። እግዚአብሔርን በምትፈራበት ጊዜ፣ ትእዛዛቱን ትጠብቃለህ (መክ. 12:13)፣ በመንገዱ ትሄዳለህ (ዘዳግ. 8:6)፣ ደግሞም ታገለግለዋለህ (ኢያሱ 24:14)። አንተ ለእርሱ ታማኝ ትሆናለህ ደግሞም የሙሉ ልብ አገልግሎት ትሰጠዋለህ (2ኛ ዜና 19:9)። ልክ እንደ ኢዮብ፣ እግዚአብሔርን በምትፈራበት ጊዜ፣ ከክፉ ትርቃለህ (ምሳሌ 3:7-8)። «እግዚአብሔርን መፍራት» ፍርሃትን ማሸነፊያ ፍርሃት ነው (መዝ. 112)፤ ምክንያቱም እግዚአብሔርን የምትፈራ ከሆነ፣ ሌላ ማንንም መፍራት አያስፈልግህም (ማቴ. 10:26-31)።

ስለዚህ፣ ወደ እውነተኛ ጥበብ እንድናመራ የሚያደርገን የመጀመሪያው ደረጃ እራሳችንን በተመለከተ ትሑት የሆነ አመለካከትን (ዝንባሌን) ያካተተ ለእግዚአብሔር የሚኖረን የአክብሮት ዝንባሌ ነው። *ግለሰባዊ የሆነ ኩራታችን ለመንፈሳዊ ጥበብ ትልቁ ዕንቅፋት ነው።* «ትዕቢት ስትመጣ ውርደትም ትከተ

ላለች፣ በትሑት ዘንድ ግን ጥበብ ትገኛለች» (ምሳሌ 11:2)::

ቀጣዩ ደረጃ ጥበብን እንዲሰጥ እግዚአብሔርን መለመን (ያዕ. 1:5) ደግሞም ጥበቡን በደኅና ሁኔታ እንድንይዝ፣ በተለይም የእግዚአብሔርን ቃል በማወቅና በማድረግ ረገድ እርሱ የሰጠንን በአግባቡ መጠቀም (ማቴ. 7:21-29) ነው:: ማጥናት ብቻውን ዋጋ የለውም፤ እግዚአብሔር እንድናደርገው የተናገረውን ነገር ማድ ረግም (መታዘዝም ጭምር) ይኖርብናል (ዮሐ. 7:17):: በእምነት በምንመላለስበት ጊዜ በየዕለት ተዕለት የሕይወት ጉዳዮች ውስጥ የእግዚአብሔርን ጥበብ እናገኛለን:: መንፈሳዊ ጥበብ የተሰወ ረ ምሥጢር አይደለም፤ መንፈሳዊ ጥበብ ግላዊም ተግባራዊም ነው::

በቤተ ክርስቲያን ካሉ ሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት በምናደርግበት ጊዜ እንዲሁም አንዳችን ከሌላው ጋር መልካም ነገሮችን በምንካፈልበት ወቅት ጥበብን ልንማር እንችላለን:: እንዲሁም ምርጥ መጻሕፍትን ማንበብ በጥበብና በመረዳት ባለጠግነት ለማደግ ይረዳናል:: አስፈላጊው ነገር በክርስቶስ ላይ ማተኮራችን ነው፣ ምክንያቱም እርሱ ጥበባችን ነውና (1ኛ ቆሮ. 1:24)፣ በእርሱ ውስጥ «የተሰወረ የእውቀት መዝገብ» ተ ጠብቆአልና (ቈላ. 2:3):: ክርስቶስን የበለጠ ባወቅነው መጠን እና እርሱን እየመሰልን በሄድን ቍጥር፣ የበለጠ በጥበብ እየተመላለስን እንዲሁም በተሻለ መንገድ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየተረዳን እንሄዳለን:: እግዚአብሔርን በቃሉ ውስጥ እንድናይ እንዲሁም በክርስቶስ ያለውን ሀብት (ባለጠግነት) መረዳት እንድንችል የልቡናችንን ዓይኖች እንዲከፍትልን ለመንፈስ ቅዱስ እራሳችንን መስጠት ይኖርብናል (ኤፌ. 1:15-23)::

የኢዮብ ንግግር ገና አልተፈጸመም በሚቀጥሉት ሦስት ምዕ ራፎች ውስጥ፣ ኢዮብ የሕይወት መንገዱን ይከልሳል ከዚያም ወይ ነፃ እንዲያወጣው አሊያም እንዲፈርድበት እግዚአብሔርን አበክሮ ይጠይቃል:: ያም የክርክሩ ፍጻሜ ይሆንና አዲስ ተሳታፊ ኤሊሁ እና እግዚአብሔር ንግግር እንዲያደርጉ በሩን ይከፍትላቸዋል::



# ለግል ምልከታና ለቡድን ውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ስለ እርሱ ምንም ነገር የማያውቅ የሚመስል አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ስም በሳምንት ስንት ጊዜ ሲጠቅስ ሰምተሃል?

2. ኢዮብ ከመረዳት ይልቅ ለጉዱት ጓደኞቹ ምላሽ የሚሰጥበትን ዕ ድል አግኝቷል:: ዕድሉ ቢኖርህ፣ እየደከምህ በምትሄድበት ጊዜ አንተን ለጕነተለህ ሰው ምን ትለው ነበር?

3. ኢዮብ የእግዚአብሔርን ኃይል ከሰማይ እና ከደመናት እንዲሁም ከዝናብ ጋር በማስተያየት ይናገራል:: ከእግዚአብሔ ር ፍጥረት ስለ ታላቅነቱ አንተን የሚናገርህ ምንድን ነው?

4. የኢዮብ ጓደኞች የእነርሱ ግንዛቤ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚገባውን ሁሉ የሚወክል ይመስላቸዋል:: የአንተ መረዳት ስለ እግዚአብሔር ሊነገር ከሚገባው እውነት ውስጥ ምን ያህሉን በመቶኛ ይወክላል?

5. ኢዮብ እግዚአብሔር በቅንነት እንዳልተመለከተው ተናግሯል። ኢዮብ ኃጢአተኛ ስለ መሆኑ እንዲሁም እግዚአብሔርን የማያከብር ስለ መሆኑ የተናገረበትን ልታብራራ ትችላለህን?

6. ወርቅን ቆፍረን እንደምናገኘው ጥበብን ቆፍረን የማናገኝ ከሆነ፣ ጥበብን የምናገኝባቸው አንዳንድ መንገዶች ምን እና ምን ናቸው?

7. ጥበብን አንድ ጊዜ ካገኛችኋት በኋላ ማጣት ይቻላል? የሚቻል ከሆነ፣ እንዴት ሊከሰት ይችላል?

8. ኢዮብ «ጓደኞቹን» በሚያዳምጥበት ጊዜ ያሳየው ምን ዓይነት ጥበብን ነበር?

9. ዌርዝቢ እንዲህ ብለዋል፣ «ለመንፈሳዊ ጥበብ ትልቁ ዕንቅፋት በግል ሕይወት ውስጥ ያለ ኵራት (ትዕቢት) ነው።» ሌሎቹ ዕንቅፋቶችስ ምንድን ናቸው?





# ነገሬን አቅርቤአለሁ!

## (ኢዮብ 29-31)

«እግዚአብሔር በአንድ ወቅት እንድንሆንለት የሚሻውን ከመሆን መለየት እስከ ፈለግን ድረስ፣ ዓላማ ለሌለው ነገር እራሳችንን እናሠቃያለን።»

- ጌርሃርት ቴርስቲጄን

ኢዮብና ሦስቱ ጓደኞቹ በሦስት ዙር ንግግር አደረጉ፣ ደግሞም የመከላከያ ንግግሩን ለመጠቅለል አሁን ጊዜው መሆኑ ለኢዮብ ተሰምቶታል። «ኢዮብም እንዲህ ሲል ንግግሩን ቀጠለ» የሚለው አባባል (ኢዮብ 29:1) ኢዮብ ተራውን እንዲናገር ሶፋርን እየጠበቀው እንደ ነበረ ያሳየናል፣ ነገር ግን ሶፋር ጸጥ ብሎ ነበር። ምናልባት ሶፋር ከዚህ በኋላ ከኢዮብ ጋር መነጋገር (መከራከር) ጊዜ ማባከን እንደ ሆነ ተሰምቶት ይሆናል።

በእነዚህ ሦስት ምዕራፎች፣ *ኢዮብ የጥንቱን በረከቶች አስታወሰ* (ኢዮብ 29)፣ *ስለ አሁኑ መከራ ሰቆቃውን አሰማ* (ኢዮብ 30)፣ *ደግሞም ወደ ፊት ነፃ እንዲያወጣው እግዚአብሔርን በብርቱ ጠየቀ* (ኢዮብ 31)። የንግግሩንም መጨረሻ «. . . ባገኝ ኖሮ» በሚሉ በአሥራ ስድስት ዓረፍተ ነገሮች ቋጨ ደግሞም እንዲፈርድበት ወይም ነፃ እንዲያወጣው እግዚአብሔርን አበክሮ እየጠየቀ መጋላ አደረገ። ይህም ኢዮብ፣ «ብዙ ተነጋግረናል! እናንተ ሦስት ሰዎች ምን እንደምታስቡ ግድ የለኝም፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ዳኛዬ ነው፤ ደግሞም ነገሬን ወደ እርሱ አቅርቤአለሁ። አሁን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ፣ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ለጉዳዩ እልባትን እርሱ ይስጥ» የሚል ይመስላል።

## ኢዮብ በሕይወቱ የነበረውን ደስታ ወደ ኋላ ተመልሰ ተመለከተ (ኢዮብ 29)

እርሱ ከቶ አለመወለድን እንደሚመኝ በመናገር የመከላከያ ንግግሩን ከፈተ (ኢዮብ 3)። አሁን ደግሞ የመከላከያ ንግግሩን እርሱ እና ቤተሰቡ የነበሩዋቸውን በረከቶች እንዲሁም ችግር ውስጥ ከመውደቁ በፊት የነበሩትን ደስታዎች በማስታወስ ይዘጋል። ይህም ሕይወትን ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ማየት የሚገባን ስለ መሆኑ መልካም አስታዋሻችን ነው። አዎን፣ እግዚአብሔር አስቸጋሪ ሁኔታዎችንና ኀዘኖችን እንድንለማመድ ይፈቅዳል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲሁ ድሎችንና ደስታን ይልካል። «መልካሙን ነገር ከእግዚአብሔር ተቀበልን፣ ክፉውንስ አንቀበልምን?» (2:10)። ሲ. ኤች. ስፐርጀን እጅግ ብዙ ሰዎች በረከቶቻቸውን በአሸዋ ላይ ይደፋሉ ነገር ግን ኀዘናቸውን በዕምነ በረድ ላይ ያስፍራሉ አለ።

«በእግዚአብሔር የተጠቀምሁበት ዘመን፣ ያለውንም ወራት ምንኛ ተመኘሁ!» (29:2)። በፈተናዎች ውስጥ በምናልፍበት ጊዜ፣ «ያለፉት መልካም ዘመናትን መመኘት» ለእኛ የተለመደ ነገር ነው፤ ነገር ግን ምኞታችን ሁኔታዎችን አይለውጥም። አንድ ሰው «ያለፉት መልካም ዘመናትን» እንደ «የመጥፎ ትዝታ እና የመልካም ምናባዊ አሳብ ድብልቅ» አድርጎ ይገልጸዋል። ወደ ኢዮብ ጉዳይ ስንመለስ ግን፣ ምንም እንኳ ትውስታው ትክክል ቢሆንም፣ «ያለፉት መልካም ዘመናት» በእውነት መልካም ነበሩ።

በተገቢው መንገድ ከተጠቀምንበት፣ በትውስታ ውስጥ አገልግሎት አለ። ሙሴ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የመራበት መንገድ እንዲሁም ለእነርሱ ያደረገውን ጥበቃ እንዲያስታውሱ መክሮአቸዋል (ዘዳግ. 8:2)። እንዲያውም፣ *አስታውስ* የሚለው ቃል በዘዳግም ውስጥ አሥራ አራት ጊዜ ደግሞም *መርሳት* የሚለው ቃል ዘጠኝ ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል። በተስፋ መቁረጥ ጊዜ ያት፣ «የልዑልን ቀኝ እጅ ማስታወስ» መልካም ነው [መዝ. (77):10-11፤ ደግሞም (42):6ን ተመልከት]። ነገር ግን፣ መጪው ጊዜ የሚመራን ራዳር መሆን አለበት እንጂ፣ የሚይዘን መልሕቅ መሆን የለበትም። ትላንትና የተማርነውን ነገር ዛሬ ለማባዛት ከሞከርን፣ እራሳችንን ብስለትን በሚሰርቅ ግትርነት ውስጥ እናገኘ



ዋለን።

ኢዮብ *በቤቱ ውስጥ ያለን የእግዚአብሔርን ህልዎት (መገኘት)* እንደ ቊጥር አንድ ደስታ መቊጠሩ ጉልህ የሆነ ነገር ነው (ኢዮብ 29:2-6)። እግዚአብሔር ይመለከተዋል እንዲሁም ከእርሱ ጋር «ወዳጅነትን» ያደረጋል (ቊ. 4፣ አ.መ.ት)። የእግዚአብሔር ብርሃን በኢዮብ ላይ ነበር ደግሞም የእግዚአብሔር ህልዎት ከእርሱና ከልጆቹ ጋር ነበር። የኢዮብ ሀብትና ስኬት ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር ነበር፣ ይህም «መንገዱ በቅቤ የራሰ፣ ዐለቱም የወይራ ዘይት *ያመነጭ* በነበረበት» ጊዜ ነበር።» (ቊ. 6፣ አ.መ.ት)። (ሶፋር፣ ንስሐ ቢገባ፣ ማርና ወተት እንደሚሆንለት ለኢዮብ ቃል ገብቶለታል።)

በዚህ የመክፈቻ ንግግር ውስጥ አንድ የተለየ አሳዛኝ ማስታወሻ አለ፦ በሕይወት የመጀመሪያ ወቅት ላይ ለመገኘት ኢዮብ ተመኘ (ኢዮብ 29:4)። ይህ የሚጠበቅ (ተአምራዊ) የሆነ ፍላጎት ሲሆን፣ አደገኛም ጭምር ነው። *የአሁን ዘመኑን ዕድሎች ችል እስከምንል ድረስ ባለፉት ዘመናት በነበሩ ክብሮች ላይ እጅግ የምናተኵር ከሆነ፣ ከወደፊቱ ጊዜ ጋር ለመገናኘት ዝግጁ ያልሆንን ሆነን እንገኛለን።* ወደድንም ጠላንም፣ የወደፊቱ ጊዜ ይመጣል። ጥቂት ሰዎች እርጅና እና ይዞት ያመጣውን ልዩ ችግር በአንክሮት ይጠባበቁታል፣ ነገር ግን ይዞት የሚመጣውን ነገር ልናስወግደው አንችልም። ብዙ የልደት በዓላቸውን ያከበሩ ሰዎች ረጅም ዕድሜ መኖራቸው የተረጋገጠ እውነታ ነው፣ ደግሞም ረጅም ዕድሜ የኖሩ ሰዎች ሽማግሌዎችና አሮጊቶች ይሆናሉ፤ እንዲሁም ያረጁ ሰዎች ደግሞ ውሎው አድረው ይሞታሉ።

«ከቶ አልሞትም» የሚሉትን ቀልዶች ታስታውሳለህን? በበረዶ ላይ ተንሸራታቾች ፍጹም አይሞቱም፦ ወደ ታች ይወርዳሉ እንጂ። የሸመገሉ ጋጋሪዎች ከቶ አይሞቱም፦ ለመነሣት ያቅታቸዋል እንጂ። የቀድሞ የእግር ኳስ ተጫዋቾች ከቶ አይሞቱም፦ የሚወገዱ ብቻ ይሆናሉ እንጂ። የጥንት የገና ጨዋታ ተጫዋቾች ከቶ አይሞቱም፦ እሩሩን መቅላት ብቻ ይሳናቸዋል እንጂ። እኛ ከቶ አንሞትም ብለን እናስብ ይሆናል፣ ነገር ግን ጌታ ሊወስደን ካልተመለሰ በቀር እንሞታለን፤ ይህም ለእርጅና እና ለሞት ዝግጁ መሆን አለብን ማለት ነው። በኀዘኔታ

ወደ ኋላ ማየቱ ከንቱ ነው፤ በደስታ ወደ ፊት ማየቱ እምነት ነው::

«እንዴት እንደሚያረጁ ማወቁ የጥበብ ዋናው ሥራ ነው፤ እንዲሁም በታላቁ የኑሮ ኪነ ጥበብ ውስጥ እጅግ አስቸጋሪዎቹ ምዕራፎች ናቸው» ሲሉ ሄነሪ አሚይል ጻፉ::

ቀጥሎም ኢዮብ *ለሌሎች ዘንድ የሚሰጥ አክብሮትን* ደስታ ዘረዘረ (ቍ. 7-11):: በከተማው ውስጥ በሚጓዝበት ጊዜ፣ እርሱን ለማሳለፍ ወጣቶች ስፍራ ይለቅቁለት ነበር:: ከከተማዋ መሪዎች ጋር በከተማዪቱ በር አብሮ ይቀመጥ ነበር፣ ደግሞም እርሱ በደረሰ ጊዜ ንግግራቸውን እንኳ ያቆሙ ነበር:: የትም ቢሄድ፣ በአክብሮት ይስተናገድ ነበር:: «የሰሙኝ ሁሉ ያሞጋግሱኝ፣ ያዩኝም ያመሰግኑኝ ነበር» (ቍ. 11፣ አ.መ.ት)::

ሦስተኛ የደስታ ምንጩ *ሌሎችን ማገልገል* ነበር (ቍ. 12-17):: እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠውን ነገር ኢዮብ ለሌሎች ያካፍለው ነበር:: ኤልፋዝ ድሆችንና ችግረኞችን ስለ መበዝበዙ ኢዮብን ከሰሰው (22:5-9)፣ ነገር ግን ኢዮብ ይህን አስተባበለ:: እነዚህ ቍጥሮች ለብዙዎች ርዳታንና ደስታን ስላመጣ ርኅሩኅ ስለ ነበር ሰው አገልግሎት ይገልጻሉ:: የአካል ጕዳተኞችን ሲረዳ፣ ለችግረኛ የሚያስፈልገውን ሲሰጥ ደግሞም ለመጻተኞች ጥብቅና ሲቆም እንኳ በከተማው ውስጥ ጽድቅንና ፍትሕን ያጠነክር ነበር (29:14፤ ኢሳ. 59:17):: ነገር ግን ኢዮብ ችግረኞችን መርዳቱን አላቆመም ነበር፤ በተጨማሪም ክፉዎችን በመጋፈጥ ኃይላቸውን ይሰብር ነበር (ኢዮብ 29:17):: ኢዮብ ክፉዎችን ደካሞችን ለመንጠቅ ዝግጁ ከሆኑ ጨካኝ አውሬዎች ጋር አወዳደራቸው፣ ነገር ግን እርሱ መጣና ለዚህ የተዳረጉትን ሰዎች ከገዛ መዳፋቸው ነጥቆ አወጣቸው::

*በወደፊቱ ጊዜ ላይ መተማመን* (ቍ. 18-20) የሚሠጋቸው ነገሮች በእርሱ ላይ ከመምጣታቸው በፊት ለኢዮብ ሌላው ምንጭ ነበረ:: እግዚአብሔር ኢዮብን እየባረከው ነበር፣ ደግሞም እነዚያን በረከቶች ኢዮብ ለሌሎች ያካፍላቸው ነበር፤ ስለዚህም ሕይወት ለብዙ ዓመታት በዚያ መንገድ እንዲቀጥል ለማመን በቂ ምክንያት ነበረው:: አፍላ ጕልበት ያለው እና ብርቱ ሆኖ እንደሚቆይ፣ እስከ ሽምግልና ዕድሜ እንደሚኖር እንዲሁም በሰላምና በክብር



እንደሚሞት ይተማመን ነበር:: እራሱን ፍሬ እያፈራ እንደሚኖር በጥልቀት ሥር እንደ ሰደደ ዛፍ ይመለከት ነበር [ቍ. 19፤ መዝ. (92):12-14]:: ልጆች አንዳንድ ጊዜ እንደ ቀስት ተደርገው የሚታዩ በመሆናቸው [መዝ. (127):3-5]፣ ኢዮብ 29:20 ኢዮብ አካላዊ የሆነውን ብርታቱን መጠበቅ የሚፈለግበት እንደ ሆነና ብዙ ልጆችም እንደሚወልድ ያመለክታል::

የመጨረሻው የደስታው ምንጭ *የማበረታቻና የእርዳታ ቃሎችን የመናገር ዕድል* ነበር (ቍ. 21-25):: እርሱ በእርግጥም «በርናባስ» የመጽናናት ልጅ ነበር (የሐዋ. 4:36):: እርሱ በሚናገርበት ጊዜ፣ ልክ እንደ ዝናብ በዝግታ የሚወርድና የሚያረሰርስ ነበር:: ፈገግ በሚልበት ጊዜ፣ መላው ሁኔታውን ብሩህ ያደረገው ደግሞም ለሰዎች ተስፋን የሰጠ ነበር:: የኢዮብ ይሁንታ ልክ እንደ አዲስ ቀን መምጣት ነበር! ግራ የተጋቡ ሰዎች ብልሃት ያለበትን ውሳኔ ያደርጉ ዘንድ የሚረዳ እንዲሁም ለኀዘንተኞች መልካም የሆነ መጽናናትን እና ተስፋን የሚሰጥ መሪ ነበር::

አዎን፣ ኢዮብ ብልጥግናን እና ብድራትን የሚከፍል ሕይወትን ኑሮአል፣ ነገር ግን ያ ሁሉ ነገር ተወስዷል::

## ኢዮብ በእግዚአብሔር ፍርድ ዙሪያ ይመለከት ነበር (ኢዮብ 30)

ካለፈው የደስታ ዘመን፣ ኢዮብ በቅጽበት የቅሬታ እና የተስፋ መቍረጥ ወደ ሆነው የአሁኑ ሁኔታ ተመልሶአል:: ገና በንግግሩ መጀመሪያ «አሁን ግን» በሚል ቃል ሲያጐረመርም ልትሰሙት ትችላላችሁ (ኢዮብ 30:1፤ ቍ. 9፣ ደግሞ 16ን ተመልከት):: ኢዮብ ወዳለፈው ዘመን ትውስታ በመሄድ ማምለጥ እንደሌለበት፣ በአሁኑ ዘመን ያለበትን እውነታ መቀበል እንዳለበት በበቂ ሁኔታ ተረድቶአል:: የሕይወትን ምዕላተ ሁኔታ ለመያዝ ዕንቢ የሚሉ ሰዎች እውነታን በመጣል አደጋ ውስጥ ናቸው፣ እናም ብዙም ሳይቆዩ እራሳቸውን ማወቁ ያዳግታቸዋል::

«ፍላጎታቸውን ለማላላት ባደረጉት ጥረት ስኬት-አልባ በመሆናቸው፣ የቱንም ባሕርይ ይምረጡ፣ ሁሉም ሕመማን ተመሳሳይ ጠባይ አላቸው፡- *ሁሉም በዙሪያቸው ያለውን ዓለም እውነታ ይክዳሉ*» (*ሪየሊቲ ቴራፒ*፣ 6) በማለት የሥነ ልቡና

ባለሙያው ዊሊያም ግላሴር ጽፎአል፡፡ ባለፈው ዘመን ትዝታ መኖርን በማስወገድ እንዲሁም በታማኝነት እውነታዎችን በመጋፈጥ፣ ብስለትንና ታማኝነትን በመለማመድ ረገድ ኢዮብ ታላቅ እርምጃን ተራመደ፡፡ ባቀረበው የሰቆቃ ዜማ፣ ኢዮብ፣ አሁን ያለበትን ሁኔታ ካለፈው ሁኔታው ጋር ያነጻጽራል፡፡ ደግሞም እያንዳንዱ ነገር በእግዚአብሔር ፍርድ እንዴት እንደ ተለወጠ አሳይቷል፡፡ አምስቱ «ማጕረምረሞቹ» በምዕራፍ 29 ላይ ከዘረዘራቸው ደስታዎች ጋር በትይዩ መልኩ ተቀምጠዋል፡-

1. «ክብር የለኝም» (30:1-15፣ ደግሞ 29:7-11ን ተመልከት)፡፡
2. «በረከት የለኝም» (30:16-23፣ ደግሞ 29:2-6 ተመልከት)፡፡
3. «እርዳታ የለኝም» (30:24-25፣ ደግሞ 29:12-17 ተመልከት)፡፡
4. «የወደፊት መልካም ጊዜ የለኝም» (30:26-28፣ ደግሞ 29:18-20 ተመልከት)፡፡
5. «አገልግሎት የለኝም» (30:29-31፤ ደግሞ 29:21-25 ተመልከት)

**(1) «ክብር የለኝም» (ኢዮብ 30:1-15)፡፡** በአንድ ወቅት ኢዮብ ሲመጣ ስፍራ ይለቅቁ የነበሩ ወጣቶች (ኢዮብ 29:8) አሁን ይሳለቁበታል ደግሞም በፊቱ ላይ ይተፉበታል (30:1፣ 9-10)፡፡ ነገር ግን የዚህ ተሞክሮ አስከፊው ገጽታ እነዚህ ልጆች ኢዮብ አባቶቻቸውን በምድረ በዳ ከሚቅበዘበዙ አህዮች ጋር ያነጻጸራቸው እጅግ የሚናቁ መሆናቸው ነበር፡፡ እነርሱ «የሰነፎችና የነውረኞች ልጆች ናቸው፤» ይላቸዋል (ቍ. 8)፡፡ ምግብንና ለእሳት ማቀጣጠያ ማገዶን ፍለጋ በምድረ በዳ የሚቅበዘበዙ ከማኅበረሰቡ የተገለሉ ሰዎች ነበሩ፡፡ በአንድ ወቅት፣ ኢዮብ በምሥራቅ ካሉ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ታላቁ ሰው ነበር፤ አሁን ደግሞ የእነዚህ ከርታታ ሰዎች ዘፈን ሆኖአል (ቍ. 9)፡፡

እነዚህ ሰዎች የኢዮብን ጫማ ለመሸከም የሚበቁ አልነበሩም፣ አሁን ደግሞ በግልጽ በእርሱ ላይ ይሳለቃሉ፡፡ ልዩነቱን ያመጣው ምንድን ነበር? *አሁን ኢዮብ ልክ እንደ እነርሱ የተጣለ ነበር፡፡*



የኢዮብ ቀስት በእጁ ላይ በሚበረታበት ጊዜ (በሚታደስበት ጊዜ)-ይህ የብርታትና የስኬት ምልክት ነበረ (29:20)-እነዚህ ሰዎች ያከብሩታል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር የቀስቱን አውታር ስላላላውና በመከራም ስለ መታው፣ እነዚህ ዓመፀኞች (ወሮበሎች) ገደባቸውን ገለል በማድረግ እርሱን ሰደቡት (30:11)፡፡ ቀድሞ ኢዮብን በሚያከብሩት ጊዜ፣ ይህን ያደርጉ የነበሩት በጠባዩ እና በታማኝነቱ (ቅንነቱ) ምክንያቱ አልነበረም፡፡ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን ስፍራም ሆነ ሀብቱን ያከብሩ የነበሩት እንደሚረዳቸው ተስፋ በማድረጋቸው ምክንያት ነበር፡፡ ወዳጅነታቸው የከዳተኝነት ነበር፣ ደግሞም አክብሮታቸው የማስመሰል ነበር፡፡

እነዚህ ጎዳና ተዳዳሪዎች «መቈጠብን ስለ ተዉ» (ቍ. 11፣ አ.መ.ት)፣ ሕይወትን ለኢዮብ አሳዛኝ አድርገውበታል፡፡ ኢዮብ ምሽግ እንደሚሠሩ፣ በመንገዱ ላይ ወጥመድን እንደሚዘረጉ፣ ቅጥሮቹን እንደሚያፈርሱ፣ ደግሞም እንደሚያጠቁት ጨካኝ ጠላቶቹ አድርጐ ይሥላቸዋል (ቍ. 12-14)፡፡ በተጨማሪም ልክ ኢዮብን እንደሚያስፈራሩ ክብሩንም ሁሉ ጠራርገው እንደሚወስዱ ደግሞም አላፊ የሆነውን ደመና እንደሚወስደው ንፋስ (ቍ. 15) ምቾቱን የሚያጠፉ ማዕበሎች ነበሩ፡፡

ኢዮብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተቀበላቸው መከራዎች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መከራዎችን ተለማምዶአል፡፡ ሰዎች በሐሰት ከሰውታል (ማቴ. 26:59-64)፣ በላዩ ላይ ተተፍቶበታል (ቍ. 67)፣ እንዲሁም መከራ በሚቀበልበት ጊዜ ተሳልቀውበታል (ሉቃስ 23:35-39)፤ ደግሞም «የሰካራሞች ዘፈን» ሆኖአል [መዝ. (69):12]፡፡ ኢዮብ ስለዚህ የሚያውቀው ነገር የለም፣ ነገር ግን «በክርስቶስ መከራ ተካፋይ እንዲሆን» (ፊልጵ. 3:10) እግዚአብሔር አክብሮታል፡፡ ምንም እንኳ በዐመድ ቁልል ላይ የተቀመጠ ቢሆንም፣ ኢዮብ እጅግ በላቀ መንገድ ከፍ ከፍ ብሎ ነበር!

**(2) «በረከት የለኝም» (ኢዮብ 30:16-23)፡፡** «የመከራ ዘመንም ይዞኛል» ሲል ኢዮብ አጕረመረመ (ቍ. 16)፡፡ ይህ ከቅቤና ከዘይት ዘመን ጋር ምንኛ የሚቃረን ነው (29:6)! እርሱን በበረከት በማጥለቅለቅ ፈንታ፣ እግዚአብሔር መሠረታውያን የሆኑ የሕይወት ደስታዎችን እንኳ ወሰደበት፡፡ በቀን ኢዮብ ሊሸከሙት የማይቻል መከራ ይሸከማል፤ በምሽት ደግሞ እግዚአብሔር

ከእርሱ ጋር ይታገላል፣ አልባሳቱን ልክ መደረቢያ ያደርግበታል፣ እንዲሁም በጭቃ ላይ ይጥለዋል (30:16-19፣ አ.መ.ት)፡፡ በየምሽቱ፣ እግዚአብሔር ከኢዮብ ጋር ይታገላል፤ በዚህም ኢዮብ ይደክማል፡፡

ኢዮብ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፡፡ ነፃ እንዲያደርገው ከተቀመጠበት ተነሥቶአል ደግሞም ጮኋል፣ ነገር ግን ጸሎቱ አልተመለሰም (ቍ. 20)፡፡ የእግዚአብሔር እጅ ርዳታ በማምጣት ፈንታ፣ በጭካኔ ኢዮብን ታጠቃለች፤ ደግሞም በማዕበል ውስጥ እንዳለ ላባ ታንገላታዋለች (ቍ. 21-22)፡፡ ኢዮብ ስለ ሕይወቱ ጸለየ፣ ነገር ግን ሞት የማይቀር ጉዳይ መሰለ (1:23)፡፡

**(3) «እርዳታ የለም» (ኢዮብ 30:21-25)፡፡** ኢዮብ ሌሎችን በመርዳት ረገድ ታማኝ ነበር (29:12-17)፣ ነገር ግን አሁን እርሱን ማንም አይረዳውም፡፡ ከእርሱ ጋር አያለቅሱም ወይም እርሱን አይነኩትም፡፡ እርሱ ምናልባትም ሊያረክሳቸው እንደሚችል ለምጻም ሰው ነበር የሚታየው፣ ወይም እግዚአብሔር በየትኛውም ጊዜ ሊያጠፋው እንደሚችል የተፈረደበት ሰው ነበር፡፡ እርሱን በጣም መቅረብ ብልሃት አልነበረም፡፡

ኢዮብ ረድቶአቸው የነበሩ ሰዎች የት ነበሩ? በእርግጠኝነት አንዳንዶቹ ወዳጃቸውን (ባለውለታቸውን) በማበረታታት ለእርሱ ያላቸውን አድናቆት ማሳየት ነበረባቸው፡፡ ነገር ግን ማንም ሰው ሊረዳው አልመጣም፡፡ ማርክ ትዌይን እንዲህ ሲል ጽፎአል፣ «የተራበን ውሻ ወስዳችሁ ባለጠጋ ብታደርጉት፣ አይነክሳችሁም፡፡ ይህ በሰውና በውሻ መካከል ያለ ዋና ልዩነት ነው፡፡»

ሌሎችን የምናገለግልበት የልባችን አሳብ እኛን እንዲያገለግሉ ለማስገደድ አይደለም (ሉቃስ 14:12-14)፡፡ ክርስቶስን የምንወድ እና እርሱን ለማክበር የምንሻ ስለሆነ (ማቴ. 5:16) እንዲሁም ለችግራቸው ስለምንራራ እና ልንረዳቸው ስለምንፈልግ (ሮሜ 12:15፤ ሉቃስ 10:25-37)፣ ሌሎችን እንረዳለን፡፡ የወንጌል መልእክተኛ የሆኑት ዶ/ር ዊልፍሬድ ግሬንፌል እንዲህ አሉ፣ «እኛ ለሌሎች የምንሰጠው አገልግሎት በዚህ ምድር ላይ ስንኖር የምንከፍለው የቤት ኪራይ ነው፡፡»

**(4) «መልካም የሆነ የወደፊት ጊዜ የለኝም» (ኢዮብ 30:26-28)፡፡** በብልጥግናው ወራት (ዘመናት)፣ ኢዮብ ረጅምና ምቹ



ሕይወትን (ኑሮን) እንዲሁም ሰላማዊ ሞትን ይጠባበቅ ነበር (29:18-20)፣ ነገር ግን አሁን ሁሉም ነገር ተለውጧል፡፡ መልካምን ሁሉ ይጠባበቅ ነበር፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ክፉን ላከበት፤ ብርሃንን ይጠባበቅ ነበር፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ጨለማን ላከበት፡፡ በምቾትና ሰላም ፈንታ፣ በውስጡ ቋሚ የሆነ ግር ግር ይለማመዳል፡፡ «በውስጤ ያለው ነውጥ አላቋረጠም፤ የመከራ ዘመንም መጣብኝ» ይላል (30:27፣ አ.መ.ት)፡፡

እንግሊዛዊው ጸሐፊ ዊሊያም ሀዝሊት እንዲህ ሲል ጽፎአል፣ «ተስፋ ምርጥ ይዞታ ነው፡፡ ከተስፋ ውጭ ያሉት ካልሆኑ በቀር ሙሉ በሙሉ የሚያሳዝን የለም፣ ደግሞም በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ዝቅ እያሉ የሚሄዱት ጥቂቶች ናቸው፡፡» ኢዮብ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ነበር፣ ጌታም እንኳ ለዚህ ግድ የሚሰኝ አይመስልም ነበር፡፡ የኢዮብ ሰውነት ደካማና ትኩሳታማ ነበር፣ ደግሞም ቆዳው ከበሽታ የተነሣ ጥቁር ነበር፡፡

**(5) «አገልግሎት የለኝም» (ኢዮብ 30:29-31)፡፡** ባለፈው ጊዜ፣ የኢዮብ ቃሎች ለብዙዎች መጽናናትንና ተስፋን አምጥቶላቸው ነበር (29:21-25)፤ ነገር ግን አሁን ቃሎቹ ልክ እንደ ቀበሮ ማላዘን እንዲሁም እንደ ጉጉት እና ሰጎን ማቃሰት (ሚክ. 1:8) ያሉ ነበሩ፡፡ ተስፋው የሞተ ስለ ነበር፣ የኢዮብ ዝማሬ የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ እንደ ሙሾ ነበር፡፡ በገናውና ዋሽንቱ ወደ ተራ ድምፅነት ተቀይረዋል፡፡ እርሱ እራሱ በተስፋ መቁረጥ ጉድጓድ ውስጥ ሳለ ለሌሎች የመጽናናትን ቃል እንዴት ሊያመጣ ይችላል? «አሁን ተስፋዬ ወዴት ነው?» ሲል ቀደም ብሎ በክርክሩ ላይ ተናግሮአል፡፡ «ታዲያ የእኔ ተስፋ ወዴት ነው? ተስፋዬን የሚያይልኝ ማን ነው?» (ኢዮብ 17:15)፡፡

## ኢዮብ የእግዚአብሔርን ፍትሕ ለማግኘት ወደፊት ይመለከታል (ኢዮብ 31)

ይህ ምዕራፍ ኢዮብ ያቀረበውን የመጨረሻውን መከላከያውን ይዘግባል፡፡ ኢዮብ እራሱን በእግዚአብሔር መሐላ ሥር ያስገባበት እና እርሱ መሳሳቱን እግዚአብሔር ካረጋገጠለት (31:35-37) የእግዚአብሔር ፍርድ እንዲወርድበት የጠየቀበት ሕጋዊ ሰነድ ይመስላል፡፡ የኢዮብ ብቸኛው ተስፋ እግዚአብሔር ጩኸቱን ሰምቶ

ስሙን ነፃ ማውጣቱ ነበር:: ጠላቶቹ አፋቸውን ከዘጉ እና ክብሩ መመለሱን ካወቀ በሰላም ሊሞት ይችላል:: በቁጥር 16 ላይ «. . . ቢኖረኝ» በሚሉ ዓረፍተ ነገሮች፣ ኢዮብ ሕይወቱን በክሰሳ መልክ ይቃኛል ደግሞም ግንኙነቶቹን ይመለከትና ፍርድን እንዲያደርግ እግዚአብሔርን ይጠይቃል:: «የመከላከያ ፊርማዬ እነሆ፣» (ቊ. 35፣ አ.መ.ት) አለ ኢዮብ መሐላውን ገዛዳዊ ባደረገና በሰነዱ ላይ እየፈረመ ሳለ:: «ነገሬን አቅርቤያለሁ!»

በቊጥር 33-37 ውስጥ ኢዮብ ሦስት ነገሮችን:- ማለትም እንዲሰማው፣ ለክሱ መልስ እንዲሰጥለት፣ ደግሞም ንጹሕ መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ እንዲሰጠው እግዚአብሔርን («ከሳሼ» = ዳኛ) ጠየቀ:: እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ማድረግ የማይችል ከሆነ፣ እንግዲያውስ በኢዮብ መኸላዎች ውስጥ የተካተቱትን እርግማኖች እግዚአብሔር እንዲልክበት ኢዮብ ፈቃደኛ ነበር:: ኢዮብ እነዚህ ነገሮችን ወደ ፍጻሜ ለማምጣት የሚያስፈልግ ከሆነ፣ ለእግዚአብሔር የሄደበትን እያንዳንዱን ደረጃ ለማቅረብ ዝግጁ ነበር:: ኢዮብ የሚደብቀው ምንም ነገር አልነበረውም፤ እርሱ ሰዎችን በመፍራት በይሉኝታ የሚታሰር ግብዝ አልነበረም (ቊ. 33-34)::

**ኢዮብ የተባለው ሰውዬ (ኢዮብ 31:1-12)::** ኢዮብ የትኛውም ሰው የሚያዝባቸውን ሦስት ኃጢአቶችን ይጠቅሳል:: እነርሱም *ሥጋዊ ምኞት* (ቊ. 1-4)፣ *ማታለል* (ቊ. 5-8)፣ እና *ዝሙት* (ቊ. 9-12) ናቸው::

1. *ሥጋዊ ምኞት* ወደ ኃጢአት የሚወስድ የመጀመሪያው ርምጃ ነው፣ ኃጢአት ደግሞ ወደ ሞት የሚወስደው የመጀመሪያው ርምጃ ነው (ያዕ. 1:13-16):: የሚስብ ሰውን ማየት እና ማድነቅ አንድ ነገር ነው፣ ነገር ግን በልብ ውስጥ ለሚደረግ ምኞት ሲባል መመልከት ደግሞ የተለየ ነገር ነው:: ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ «ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል» (ማቴ. 5:28):: በልብ ውስጥ የሚፈጸም ኃጢአት በተግባር እንደሚፈጸም ኃጢአት አጥፊ ባይሆንም፣ ወደ ተግባሩ የሚመራ የመጀመሪያ ደረጃ ነው፤ ደግሞም የተበከለ አስተሳሰብ የት እንደሚወስዳችሁ ከቶ አታውቁም:: ከዚህም በላይ፣ እግዚአብሔር ከላይ ሆኖ ተ



ግባራችንንም ሆነ «የልባችንን አሳብና ዝንባሌ» ሁለቱንም (ዕብ. 4:12-13) ይመለከታል፤ እርሱ በሁለቱም ላይ ይፈርዳል:: «ለኃጢአተኞች ጥፋት፣ ክፉ ለሚያደርጉም መቅሠፍት አይደለምን?» (ኢዮብ 31:3፣ አ.መ.ት)::

2. *ማታለል* ኢዮብ የካደው ሁለተኛው ኃጢአት ነው (ቊ. 5-8):: በንግድ ልውውጡ ውስጥ ማታለልን ከቶ አልተጠቀመም:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እንደዚህ ያለ ነገርን ከሚያደርጉ ሰዎች ጋር አልተጓዘም:: ሚዛኖቹ የታመኑ ነበሩ (ዘሌዋ. 19:35-37፤ ምሳሌ 11:1)፣ ደግሞም እግዚአብሔር እርሱን የሚመዝንበትን ሁኔታ አይፈራም (ዳን. 5:27)! ልቡ በምንዝርና ምኞት የተያዘ አልነበረም፣ እጆቹም የረከሱ አይደሉም፣ ምክንያቱም የእርሱ ያልሆነውን ነገር አልወሰደም:: በፍትወት ምኞትና በማታለል የሚከሰስ ጥፋተኛ ቢሆን ኖሮ፣ በቀጣዩ የሰብል ወቅት ምርቱ በሌሎች እንዲወሰድበት ኢዮብ ፈቃደኛ ነበረ::

3. *ዝሙት* (ኢዮብ 31:9-12) በልብ ውስጥ ባለ ምኞት ይጀምራል (ቊ. 1)፣ ይህም ድብቅ ጥረትን ኃጢአተኛ ባሕርይን ለማርካት ወደሚሆን ፍላጎት ይመራል:: ኢዮብ የጎረቤቱ ሚስት ብቻዋን የምትሆንበት ጊዜን ከቶ አድብቶ አይጠባበቅም ነበር:: ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ ኖሮ፣ እንግዲያውስ የእርሱ ሚስት ለሌላ ሰው እህል አስፈጪ ባሪያ እንድትሆን ይፈቅዳል! ዝሙት በዚህ ሕይወት አሳፋሪና ሥቃያማ ውጤቶችን የሚያስከትል እንዲሁም በሚቀጥለው ዓለም ደግሞ ፍርድን የሚያመጣ አስቃቂ ወንጀል ነው (ምሳሌ 6:27-29፤ ኤፌ. 5:3-7፤ ዕብ. 13:4)::

**ቀጣሪው ኢዮብ (ኢዮብ 31:13-15)::** ኢዮብ አገልጋዮቹን በሚይዝበት አያያዝ ረገድ እራሱን እጅግ በጥንቃቄ ይመረምራል:: በዚያ ዘመን ብዙዎቹ አሠሪዎች (ጌቶች) ያንን የሕይወት ገጽታ ችል ብለውት ነበር:: ኢዮብ ሠራተኞቹን በቸርነት ይይዛቸው ነበር:: ደግሞም ኀዘን በሚገጥማቸው ጊዜ በጐ በሆነ መልኩ ለችግራቸው መፍትሔ ይሰጣቸው ነበር:: ምክንያቱም አንድ ቀን እርሱ ለእግዚአብሔር ምላሽ ይሰጥበታል (ቊ. 14፤ ኤፌ. 6:9):: በተጨማሪም እርሱ እነርሱን በፈጠረው በዚያው አምላክ የተፈጠረ መሆኑን እንዲሁም እነርሱ በተፈጠሩበት በዚያው መንገድ የተፈጠረ መሆኑን ያውቅ ነበር::

**የሌሎች ጎረቤት የነበረው ኢዮብ** (ኢዮብ 31:16-23፣ 29-32):: ኤልፋዝ ለቀረበበት የሐሰት ክስ ምላሽ ሲሰጥ (22:6-9)፣ ኢዮብ ለድሆችና ለችግረኞች ቀድሞውኑ እንዴት እንክብካቤ ያደርግ እንደ ነበረ ተናግሯል (29:12-17)፤ ነገር ግን አሁን ይህን የመሐላው ክፍል አድርጎ ደግሞ ያቀርበዋል:: በትምክህት እየደነፋ አልነበ ረም፤ በሰዎች ፊት እራሱን ከተቃጣበት ጥቃት (ክስ) እየተከላከለ እንዲሁም ነፃ እንዲያወጣው እግዚአብሔርን እየተማጠነ ነበረ:: በየትኛውም ሰው ላይ በችሎት ፊት እጆቹን ቢያነሣ ኢዮብ እግዚአብሔር እጆቹን ከመገጣጠሚያዎቻቸው ላይ ነቅሎ እንደሚያነሣ ተስፋ ያደርግ ነበር::

ኢዮብ ለመበለቶች፣ አሳዳጊ ለሌላቸው ልጆች፣ እንዲሁም ለድሆች አሳቢና ርኅሩኅ ነበር:: ስለዚህ ምግብና አልባሳትን ይሰጣቸውና በችሎትም ከሚሰነዝርባቸው ክስ ይከላከልላቸው/ ይሟገትላቸው ነበር:: ልክ እንደ ቤተሰቡ አባላት አድርጎ ይቈጥራቸው ነበር፣ ደግሞም እራሳቸውን እስኪችሉ ድረስ ይንከባከባቸው ነበር:: እግዚአብሔር ለኢዮብ ሀብቱን ሰጠው፣ ደግሞም ለሌሎች የማያካፍለው ከሆነ፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ሊወስድበት ይችላል (31:23):: ነገር ግን ኢዮብ ለጠላቶቹም ጭምር መልካም ወዳጅ ነበር (ቊ. 29-31) ደግሞም በከተማው በኩል ለሚያልፉ እንግዶችም መልካም ወዳጅ ነበር (ቊ. 32):: ኢዮብ ባለ ጠጋና ኃይለኛ የአካባቢው ገዢ ስለ ነበረ፣ የሚቀኑበትም ሆነ የሚጠሉት ብዙ ሰዎች መኖራቸው ጥርጥር የሌለው ነገር ነው፤ ይሁንና ኢዮብ ለሁላቸውም ደግ ነበር:: ዕድል ባልገጠማቸው ጉዳይ ላይ አልፈነደቀም (ዘጸአ. 23:4-5፤ ምሳሌ 24:17-18፤ ማቴ. 5:43-47) ወይም እነርሱን እንዲረግምለት እግዚአብሔርን አልለመነውም (ሮሜ 12:17-21)::

ኢዮብ ለመጻተኞች ደግ ነበር፣ የሚመገቡት ምግብ እንዲሁም ምሽቱን የሚያርፉበት ስፍራ ይሰጣቸዋል:: ስለ ስግብግብነቱ የትኞቹም የኢዮብ አገልጋዮች ሊከስሱት አይችሉም (ኢዮብ 31:31፣ አ.መ.ት):: ቤቱ ለሁሉም ክፍት ነበር፣ ደግሞም በልግሥና የሚሰጥ ሰው ነበር::

**አምላኪው ኢዮብ (ኢዮብ 31:24-28)::** ኢዮብ በቀን ልብ



እግዚአብሔርን ያመልክ ነበር:: ሀብቱን አያመልክም፣ ለደኅንነቱ ዋስትናነትም አይታመንበትም፣ አሊያም እርሱን ለማግኘቱ ምስጋናውን አይወስድም (ዘዳግም 8:17-18):: ኤልፋዝ ወርቅን አምላኩ ስለ ማድረጉ ኢዮብን ይከስሰዋል (ኢዮብ 22:24-25)፣ ነገር ግን ኢዮብ ይህንን ካደ:: ወርቅን ወይም ሰማያዊ አካላትን አላመለከም ደግሞም በድብቅ «ስለ ክብራቸው አፉ እጁን አልሳመም» ነበር (31:27፣ አ.መ.ት):: ኢዮብ እንዲህ ያለውን ኃጢአት አድርጎ ቢሆን፣ ሰዎች አያዩት ይሆናል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ይመለከተዋል:: ደግሞም ለእርሱ ታማኝ ባለመሆኑ እግዚአብሔር ይፈርድበታል::

***መጋቢው ኢዮብ*** **(ኢዮብ 31:38-40)::** በቊጥር 35-37 ኢዮብ እንዲሰማ «ገሃዳዊ ጥያቄውን» አቅርቧል:: ደግሞም በሰነዱ ላይ ፈርሞአል:: ከዚያም ሊሸፈን የሚገባ አንድ ተጨማሪ ስፍራ እንዳለ አስታወሰ:- ይህም እግዚአብሔር በሰጠው መሬት ላይ ያለው መጋቢነት ነበር:: ኢዮብ መሬቱን ይመለከተው የነበረው ልክ ሰው የሆነ ያህል ነበር:: መሬቱን በተሳሳተ መንገድ ተ ጠቅሞበት ቢሆን፣ መሬቱ በእርሱ ላይ በጮኸበት እና በሥቃይ ባለቀሰ ነበር (ቊ. 38):: የኢዮብ እርሻ እጆች ብዙ ተሠርተ ውባቸውና ጥቂት ተከፍሏቸው ቢሆኑ ኖሮ፣ እግዚአብሔር የስንዴንና የገብስን መከር በመስጠት ፈንታ የአረምን መከር ሊሰጠው አስፈላጊ ምክንያት በኖረው ነበር::

የኢዮብን መሐላ ከልሱ፣ ደግሞም በእነዚህ ኃጢአቶች በድሎ ከተገኘ አስቸጋሪ ፍርድን እንዲልክ እግዚአብሔርን ሲጠይቅ ታገኙታላችሁ፤ ሌሎች መከሩን ይብሉት ደግሞም ተክሉን ይንቀሉት (ቊ. 8)፣ ሚስቱ የሌላ ሰው አገልጋይ እና ፈጪ ትሁን (ቊ. 10)፤ ክንዶቹ ከትከሻው ላይ ይውደቁ (ቊ. 22)፤ መከሩ አረምና እሾህ ይሁን (ቊ. 40):: እርሱ ከእነዚህ ሌሎች ፍርዶች ጋር ጻድቅ የሆነ የእግዚአብሔርን ፍርድ ለመቋቋም ፈቃደኛ መሆኑን ግልጥ አድርጓል (ቊ. 14፣ 23፣ 28)::

የኢዮብ ንግግሮች በተፈጸሙ ጊዜ፣ ቀጥሎ ምን ይሆን በማለት እየተገረሙ እያንዳንዳቸው በጸጥታ ተቀመጡ:: እግዚአብሔር ወዲያውኑ ፍርድን በመላክ ኢዮብ በደለኛ መሆኑን ያረጋግጥ ይሆን? ወይስ ኢዮብ አበክሮ ያቀረበውን ጥያቄ ተቀብሎ፣

ለእርሱ ተገልጦ፣ እራሱን እንዲከላከል ለኢዮብ ዕድል ይሰጠው ይሆን? ምናልባት እግዚአብሔር ከሰማይ ይናገር እና የኢዮብን ጥያቄዎች ይመልስ ይሆናል።

እግዚአብሔር ነፃ እንደሚያወጣው ያውቅ ነበርና ኢዮብ እግዚአብሔርን አበክሮ ጠየቀ። ሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች እግዚአብሔር እንደሚፈርድበት እርግጠኞች ነበሩ።

እግዚአብሔር ምን ያደርግ ይሆን? መልሱ ያስደንቃችሁ ይሆናል!



## ለግል ምልከታ እና ለቡድን ውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ኢዮብ ካለፉት ጊዜያት በመጀመር በረከቶቹን ቈጠረ። ያለፉት ዘመናት በረከቶችህ ከሆኑት አንዳንዶቹ ምንድን ናቸው?

2. በትግል መካከል በምንሆንበት ጊዜ ያለፉት ዘመናት በረከቶች መጽናናትን የሚያመጡልን እንዴት ነው?

3. ኢዮብ ከቤተሰብ ጀምሮ እስከ ንብረቶቹ እንዲሁም መልካም የሆነውን ስሙንና ክብሩን ሁሉ አጣ። ንብረትንና ክብርን በማጣት መካከል ያሉ አጠቃላይ ልዩነቶችን ዘርዝር።

4. ኢዮብ ሦስት ታላላቅ የኃጢአት ምድቦችን አብራርቶአል፦ እነዚህም የዓይን አምሮት (የሥጋ ምኞት)፣ ማታለልና ዝሙት ናቸው። ሌሎች ኃጢአቶች በእነርሱ ውስጥ የሚካተቱበትን ተመሳሳይ የኃጢአት ዝርዝሮችን የምታዘጋጅ ከሆነ፣ በዝርዝርህ ውስጥ የሚገኙ ምን ምን ይሆናሉ?

5. ኢዮብ ቀጣሪነቱንና ጉርብትናውን ጨምሮ በእያንዳንዱ ሚናው ውስጥ እራሱን ገምግሞአል። እራስህን በምትመረምርበት ጊዜ፣

እራስህን የምትተችበት ዋነኞቹ ሚናዎች ምንድን ናቸው?

6. ኢዮብ የማይገባውን ምስጋናም ሆነ ወቀሳ ለመቀበል ፈቃደኛ አይደለም:: ይህን ዓይነት አቋም በመውሰዱ ኢዮብ ሕይወቱ የበለጠ አስቸጋሪ እንዲሆን ያደረገበት ጥቂት መንገዶችን ዘርዝር::

7. መከራ ወደፊት የሚኖረንን አመለካከት የሚነካው እንዴት ነው?

8. ልክ እንደ ኢዮብ በእራስህ ላይ እንኳ የእግዚአብሔር ፍርድ እንዲመጣ ተመኝተህ ታውቃለህን? ከሆነ፣ ይህ መቼ ነበር የሆነው?

9. ኢዮብ ዘግበ ካጣቸው ነገሮች መካከል:- ክብር፣ በረከት፣ እርዳታ፣ የወደፊት ተስፋ፣ አገልግሎት እጅግ አስቸጋሪ የሆኑት የትኞቹ ናቸው? ለምን?





# ኤሊሁ መልሶቹ አሉት

## (ኢዮብ 32-33)

«ከንቱ ሰው ሊኮራና እርሱ በገሃዱ እውነት ዓለም አቀፍ ጠንቅ ሆኖ ሳለ ሁሉን የሚያስደስት እንደ ሆነ ሊያስብ ይችላል::»

- ቤኔዲክት ስፒኖዛ

ኢዮብ ጸጥ ብሎ ነበር:: የመከላከያ ንግግሩን ጨርሶአል ደግሞም በጓደኞቹ የተከሰሰባቸውን ኃጢአቶች አለመፈጸሙን በመናገር መኀላ ፈጽሞአል:: ኢዮብ ወይ ነፃ እንዲያወጣው አሊያም በእርሱ ላይ እንዲፈርድ እግዚአብሔርን አበክሮ ጠይቋል:: መከራው ለረጅም ጊዜ ቀጥሎበታል፣ ደግሞም እርምጃ የሚወስድበት ሰዓኛው ጊዜው ነበር::

ሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች ኢዮብ እጅግ በድፍረት *ለእግዚአብሔር* እና *ስለ እግዚአብሔር* እየተናገረ ስለ ነበር ጸጥ ብለው ነበር:: በኢዮብ ላይ የሚመጣው ፍርድ ቀጣዩ የመነጋገሪያ አጀንዳቸው እንደሚሆን እርግጠኞች ነበሩ::

*ነገር ግን እግዚአብሔር ጸጥ ብሎ ነበር::* ከሰማይ የመጣ እሳት የለም፣ ደግሞም በመለኮታዊ ቍጣ የተናገረ ድምፅ አልነበረም:: ጸጥታው ሦስቱ ጓደኞቹ ስለ ኢዮብም ሆነ ስለ እግዚአብሔር የተናገሩት ነገር ስሕተት መሆኑን የሚያመለክት የእግዚአብሔር ጥበባዊ ምስክርነት ነበር:: በተጨማሪም፣ የፍጥረተ አጽናፉ አምላክ ከፍጥረቱ ጥረ የራቀ እንዳልሆነ ለኢዮብ የተሰጠ የእግዚአብሔር ምስክርነት ነበር:: አንድ ሰው አሁን መታየ ጊዜው

ነው ስላለ ብቻ እግዚአብሔር አይገለጥም።

ታዋቂ በሆነው በለንደን በሚገኘው ሰዎች ንግግር በሚለማመዱበት ሀይድ ፓርክ በሚባል መናፈሻ ክርስትናን የሚያጣጥል ሰው እንዲህ ያለ ብርቱ የተግዳሮት ጥሪ አቀረበ፡- «እግዚአብሔር ካለ፣ እንዲገድለኝ አምስት ደቂቃዎችን እሰጠዋለሁ?» ሰዓቱን አውጥቶ ተጠባበቀ። ከአምስት ደቂቃዎች በኋላ፣ ፈገግ አለና እንዲህ አለ፡- «ወዳጆቼ፣ ይህ እግዚአብሔር አለመኖሩን ያረጋግጣል!»

በተሰበሰበው ሕዝብ መካከል የነበረ አንድ አማኝ የሆነ ክርስቲያን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ «የሁሉን ቻይ አምላክን ትዕግሥት በአምስት ደቂቃ ውስጥ ማስጨረስ የምትችል ይመስልሃልን?»

ይሁን እንጂ፣ በዐመድ ቁልሉ ዙሪያ ከተሰበሰበው ሕዝብ መካከል የነበረ አንድ ሰው ጸጥ አላለም። እርሱ ኤሊሁ ሲሆን፣ እርሱም የማይታወቅ ሰው በመሆኑ፣ ሰዎች ማንነቱን ይለዩት ዘንድ ሙሉ ታሪኩ መናገር ተገቢ ነበር (ኢዮብ 32:21)። ኢዮብም (1:1) ሆነ ሦስቱ ጓደኞቹን (2:11) ሰዎች ይለዩአቸው ዘንድ እንዲህ ያለ የማንነት መግለጫ መስጠትር አላስፈለገም።

ኤሊሁ ረጅም ንግግር-በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ስድስት ምዕ ራፎችን-ተናገረ፣ በእነዚህም ምዕራፎች የእግዚአብሔርን ባሕርያት አብራራ ደግሞም ይህን እውነታ ከኢዮብ የሕይወት ሁኔታ ጋር አዛምደው። የእርሱን ንግግር በአስተዋፅኦ የምናስቀምጥበት አንዱ መንገድ የሚከተለው ነው፡-

1. እግዚአብሔር በእኔ በኩል እየተናገረ ነው (ኢዮብ 32፤ ቊ. 8ን ልብ በሉ)።
2. እግዚአብሔር ቸር ነው (ኢዮብ 33፤ ቊ. 24ን ልብ በሉ)።
3. እግዚአብሔር ትክክል ነው (ኢዮብ 34-35፤ ቊ. 34:10-12ን ልብ በሉ)።
4. እግዚአብሔር ታላቅ ነው (ኢዮብ 36-37፤ ቊ. 36:5፣ 26ን ልብ በሉ)።



ኤሊሁ እንደ ሌሎቹ ተናጋሪዎች ጥቂት ተመሳሳይ ነገሮችን የተናገረ ቢሆንም፣ የእርሱ ዓላማ ከሌሎቹ የተለየ ነበር። ኢዮብ ኃጢአተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ አልጣረም፣ ነገር ግን ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር የነበረው አመለካከት ስሕተት መሆኑን ነበር ያ ረጋገጠው። ኤሊሁ አዲስ እውነታን ወደ ክርክሩ አመጣ፡- ይህም እግዚአብሔር መከራ የሚልከው የግድ ኃጢአታችንን ለመቅጣት ሳይሆን፣ ነገር ግን ኃጢአትን ከመሥራት ሊጠብቀን (33:18-24)፣ እንዲሁም የተሻልን ሰዎች ሊያደርገን (36:1-15) ነው። ጳውሎስ ከመጀመሪያው ነጥብ ጋር ይስማማል (2ኛ ቆሮ. 12:7-10) ደግሞም የዕብራውያን ጸሐፊ ከሁለተኛው ነጥብ ጋር ይስማማል (ዕብ. 12:1 -11)።

ኤሊሁ ስለ እግዚአብሔር አስረግጦ የተናገራቸውን ሁለቱን የመጀመሪያዎቹን ዓረፍተ ነገሮች ልብ እንበል።

## 1. እግዚአብሔር በእኔ በኩል እየተናገረ ነው (ኢዮብ 32)

ኤሊሁ ከመናገሩ በፊት በትዕግሥት መጠበቁ ላይ አጽንዖት ሰጥቷ ል፣ ደግሞም ሁለት ምክንያቶችን አቅርቦአል። አንደኛው ምክንያት፣ እርሱ ከኢዮብም ሆነ ከሦስቱ ጓደኞቹ በዕድሜ ትንሽ ነበር፣ ደግሞም ወጣቶች ዕድሜንና ተሞክሮን ማክበር ነበረባቸው (ኢዮብ 32:4፣ 6-7)። እነዚህን ሽማግሌዎች አቋርጦ መናገሩ በባህሉ ነውር ነበር።

ሁለተኛው ምክንያቱ ሙሉ የሆነውን ክርክር በማዳመጥ የክርክራቸው መሠረት የሆነውን ምልልሳቸውን በሙሉ ማግኘት ስለ ነበረበት ነበር (ቊ. 11፣ ምሳሌ 18:13)። ኤሊሁ ከንግግራቸው የመጥቀሱ እውነታ በጥሞና ማድመጡንና እያንዳንዱ ሰው የተናገ ረውን ነገር ማስታወሱን ያመለክታል (ኢዮብ 32:12)። ልክ እንደ ብዙዎቹ «ወጣት የሥን መለኮት ምሁራን፣» ኤሊሁ በንግግሩ ውስጥ የወጣትነት ስሜቱ ይንጸባረቃል («እኔ የማውቀውን አድምጡ!» ቊ. 6፣ 10፣ 17፣ 33:1-3)፤ ነገር ግን በአብዛኛው፣ እርሱ ለጥያቄዎቹ መልስ በማግኘት ኢዮብን ሊረዳው እንደሚችል የሚያስብ ቅን የሆነ ወጣት ነበር።

ወደ ውይይት ለመግባት እራሱን ካስተዋወቀ በኋላ፣ ኤሊሁ

መናገሩ ለእርሱ እንዲሁም ማድመጡ ለእነርሱ አስፈላጊ የሚሆንበትን አራት ምክንያቶችን ይሰጣል:: ለነገሩ እርሱ «ምንም» አይደለም፤ ደግሞም እርሱ ሊናገረው ያለውን ነገር ሊሰሙት የሚገባ እንደ ሆነ ሊያሳምናቸው ይገባው ነበር::

**(1) እርሱ ብስጩ ነበር (ኢዮብ 32:1-3፣5)::** በዚህ ቍጥር ውስጥ ኤሊሁ የተቈጣ ስለ መሆኑ አራት ጊዜ ተነግሮናል:: ኢዮብን በአግባቡ ስላልገጠሙት በሦስቱ ጓደኞቹ ላይ ተቈጥቷል፣ ደግሞም ከእግዚአብሔር ይልቅ እራሱን ትክክለኛ በማድረጉ በኢዮብ ላይ ተቈጥቷል:: ኢዮብ እግዚአብሔር መሳሳቱን ተናግሮአል፣ ደግሞ ሦስቱ ጓደኞቹ ኢዮብ የተሳሳተ መሆኑን ማረጋገጥ አልቻሉም! በልዳዶስ፣ ሶፋር እና ኤልፋዝ ምክንያታቸውን ሰጥተዋል (ቍ. 15) ደግሞም እንዲመጣ እና በግል ከኢዮብ ጋር እንዲገናኝ እግዚአብሔርን እየተጠባበቁ ነበር (ቍ. 12-13):: ኤሊሁ ውድቀታቸው አስጠላው::

«በስሜት መክነፍ ቀላል ነው፣ ያንን ማንም ሊያደርግ ይችላል፣ ነገር ግን በትክክለኛው ሰው ላይ በተገቢው መጠን እና በትክክለኛው ሰዓት እንዲሁም አግባብነት ላለው ነገር በትክክለኛው መንገድ መቈጣት - ቀላል ነገር አይደለም፣ ደግሞም እያንዳንዱ ሰው ሊያደርገው የሚችል አይደለም::» በማለት አርስቶትል ጽፎአል::

**(2) እርሱ እስትንፋሰ-እግዚአብሔርን ተቀብሏል (ኢዮብ 32:8-10)::** ዕድሜ ጥበብን ሊያመጣ ይገባል፣ ነገር ግን ይህን ስለ ማድረጉ ዋስትና የሚሆን ነገር የለም (ምሳሌ 16:31):: ሰነፍ ወጣቶች እንዳሉ ሁሉ ሰነፍ ሽማግሌዎችም አሉ! እንደ ወጣት፣ ኤሊሁ በእግዚአብሔርም ሆነ በሰዎች የአሠራር መንገድ ላይ ሰፊ የሆነ ተሞክሮ እንዳለው ሊናገር አይችልም፣ ነገር ግን አንድ የተሻለ መልካም ነገር እንዳለው ተናገረ:- ይህም የመንፈስ ቅዱስ አብሪነት (ገላጭነት) ነው:: መንፈስ ቅዱስ የኤሊሁ ቃሎችን ይመራ ነበር (1ኛ ቆሮ. 2:11) ደግሞም የእግዚአብሔር እውነት ለእርሱ ይገለጥለት ነበር:: ኤሊሁ በእግዚአብሔር የተማረ ነበርና በተሞክሮ የሚመጣ ጥበብ አላስፈለገውም [መዝ. (119):97-100]::

ይህም ኤሊሁ በተደጋጋሚ ኢዮብንና ጓደኞቹን ለምን እንደ መከራቸው ያብራራል (ኢዮብ 32:10፣ 33:1፣ 31፣ 33፤ 34:2፣ 10፣ 16፤ 37:14):: በተጨማሪም «የእኔ አሳብ» የሚለውን ሐ



ረግ ለምን አጽንዖት እንደ ሰጠው ያብራራል (32:6፣ 10፣ 17፤ «እኔ የማውቀውን» ያላል በአዲሱ መደበኛ ትርጉም) እንዲሁም «ቃሎቼ» ይላል (33:1-3):: አንድ ሰው በየዕለቱ እስትንፋሰ-እግዚአብሔርን ተቀብያለሁ ስለማይል፣ ብታዳምጠው ይሻልሃል!

**(3) እርሱ ከአድሎ የጸዳ ነበር (ኢዮብ 32:14፣ 21-22)::** «እርሱ ግን ቃሉን በእኔ ላይ አልተናገረም፤ እኔም በንግግራችሁ አልመልስለትም» (ቍ. 14):: ኢዮብም ሆነ ሦስቱ ጓደኞቹ እርሱን በግሉ ስላላጠቁት የሚወግንበት ምንም ምክንያት እንደሌለ ግልጥ አድርጓል:: በተጨማሪም ኤሊሁ ምንም እንኳ ያንን የሰጠውን ተስፋ ሙሉ በሙሉ ባይፈጽመውም፣ እነርሱ ቀድሞውኑ ያቀረቧቸውን መከራከሪያ አሳቦች እንደ ገና አድሶ እንደማይጠቀምባቸው ይናገራል::

ምናልባት ኤሊሁ ከአድሎ የጸዳ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን በምንም መንገድ ገለልተኛ ሊሆን አይችልም:: በዚያ ጉዳይ ላይ እጅግ ተቈጥቶአልና! በጉዳዮች ላይ ብቻ ለመናገር ቃል ገብቶ ነበር፣ ነገር ግን በቍጣ ውስጥ ሆኖ ከተናገራቸው ነገሮች አንዳንዶቹ ከፍልስፍናዊነት ይልቅ ግለኝነት የተጠናወታቸው ነበሩ:: ነገር ግን ተስፋውን ጠብቋል ደግሞም ማንንም በሽንገላ አላሞገሰም (ቍ. 21-22):: ንግግሩን በምታነብበት ጊዜ፣ ስድስት ጊዜ ኢዮብን በስሙ እየጠራ ሲያነጋግረው ልብ ትላለህ (33:1፤ 34:5፣ 7፣ 35፣ 36፤ 35:16)፣ ይህም ሦስቱ የኢዮብ የቅርብ ጓደኞች እንኳ በብዙው ንግግራቸው ውስጥ ያላደረጉት ነበር:: በምሥራቅ፣ ለአንድ ወጣት ሽማግሌዎቹን እንዲህ ባለ መልኩ መጥራት በአብዛኛው ያልተለመደ ነገር ነበር::

**(4) ተገዶ ነበር (ኢዮብ 32:16-20)::** ኤሊሁ ለመናገር ዕድል ያገኝ ዘንድ ለረጅም ጊዜ ጠብቋል፣ በውስጡ ያለ ውጥረት ወደሚፈነዳበት ደረጃ ደርሷል:: የወይን አቁማዳ በወይን ጠጅ እንደሚሞላ ሁሉ፣ እርሱ በቃል ተሞልቶ ነበር:: አዲስ የወይን ጠጅ በሚፈላበት ጊዜ፣ የወይን አቁመዳው እንዲወጠር የሚያደርግ ጋዝን ያመነጫል፤ ደግሞም የወይን አቁማዳው አሮጌ እና ደረቅ ከሆነ፣ ይቀደዳል (ይፈነዳል) (ማቴ. 9:17):: ኤሊሁ «በጋዝ ተሞልቷል» ብሎ አሳብ ቢሰጥ እርሱ ይቀየማል፣ ምክንያቱም ለእርሱ የሚሰማው እየስገደደው ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ

እንደ ሆነ ነበር:: ኤሊሁ ለእያንዳንዱ ሰው የሚያውቀውን ነገር ለመናገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ፈቃድ (ይሁንታ) አለው:: የሚያውቀው ኢምንት በመሆኑ፣ በመጨረሻ እግዚአብሔር በዚያ ስፍራ በተገለጠ ጊዜ ኤሊሁንም ሆነ የተናገረውን ነገር ሁሉ ቸል አለው::

## 2. እግዚአብሔር ቸር ነው (ኢዮብ 33)

ይህ ሊሠመርበት የሚገባ ንግግር ነው፣ ምክንያቱም የመከራን ዓላማ በተመለከተ ወደ ክርክሩ አዲስ አሳብን ያመጣ ነው:: የኢዮብ ጓደኞች የሚቀበለው መከራ እግዚአብሔር እርሱን እየቀጣው እንደ ሆነ የሚያሳይ ማስረጃ ነው ብለው ይከራከሩ ነበር፣ ነገር ግን ኤሊሁ አሁን አንዳንድ ጊዜ *ኃጢአት ከመሥራት ሊጠብቀን እግዚአብሔር እንድንሠቃይ ይፈቅዳል* እያለ ይከራከራል:: በሌላ አነጋገር፣ መከራ መከላከያ እንጂ *መቅጫ* ላይሆንም የሚችልበት ሁኔታ አለ:: (በ2ኛ ቆሮ. 12:7-10 የተ ዘገበውን የጳውሎስን ተሞክሮ ተመልከቱ::) ከኃጢአት እንዲሁም ወደ ሞት ጉድጓድ ከመሄድ ሊጠብቀን እግዚአብሔር የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል፣ ይህም ደግሞ የጸጋው ማስረጃ ነው (ኢዮብ 33:24)::

ወደ ክርክሩ ከመዝለቁ በፊት፣ ኤሊሁ ቃሎቹ ከቅንነት የወጡ እና በእግዚአብሔር መንፈስ የተሰጡ እንደ ሆኑ ለኢዮብ አረጋግጦለታል፣ ስለዚህም ኢዮብ የሚፈራበት ምንም ምክንያት አልነበረም (ቊ. 1-7):: ኤሊሁ ከእግዚአብሔር ጋር «ውስጣዊ የሆነ ግንኙነት» እንዳለው አልተናገረም፤ ልክ እንደ ኢዮብ ሁሉ ከአፈር የተሠራ ነበር:: በንግግሩ እጁን የሚያከብድ እንዳልሆነ አስቀድሞ ቃል ገብቶአል፣ ደግሞም ምላሽ ለመስጠት ነፃነት እንዲሰማው በመንገር ኢዮብን ጋብዞታል:: ኤሊሁ ይህ የአንድ ወገን ንግግር እንዲሆን አይፈልግም፣ ነገር ግን የሆነው ነገር ይኸው ነው:: ወይ በኤሊሁ ንግግር ኢዮብ ጸጥ ብሏል፣ አሊያም ደግሞ ኢዮብ የሚናገርበትን ዕድል ሳይሰጥ ኤሊሁ ባለማቋረጥ ተናግሮአል (ቊ. 31፣ 33 ተመልከት)፣ ወይም ኢዮብ ምላሽ መስጠቱ ጥቅም የሌለው ሆኖ አግኝቶታል::

ቃሎቹ የሚረዱ እንጂ የሚጐዱ እንዳይደሉ ለኢዮብ



ካረጋገጠለት በኋላ፣ ኤሊሁ ኢዮብ ስለ እርሱ የተናገረውን ወደ መጥቀሱ አመራ (ቊ. 8-11):: ኤሊሁ ላቀረበው መከራከሪያ መነሻው የኢዮብ ቃሎች ነበሩ::

በመጀመሪያ፣ ኢዮብ ኃጢአት የሌለብኝ ነኝ ሲል ተናግሮአል አለ ኤሊሁ (ቊ. 9)፣ *ይህም ኢዮብ የተናገረው ነገር አይደለም*:: ኢዮብ ኃጢአት-አልባ እንደ ሆነ ተናግሮአል የሚለው የሶፋር ትርጓሜ እንጂ፣ ኢዮብ ያወጀው ነገር አልነበረም (11:4):: ኢዮብ አልዋሸሁም አለ (6:30)፣ ክፉ እንዳልሆነ (10:7) ተናገረ፣ ትክክልና ቅን እንደ ሆነ (12:4)፣ ደግሞም ለእግዚአብሔር ሳይታዘዝ እንዳልቀረ (23:11-12) ተናገረ፤ ነገር ግን እርሱ ኃጢአት-አልባ እንደ ሆነ ብቻ አልተናገረም:: በቋሚነት ታማኝነቱን ጠብቋል (2:3፤ 27:4-5)፣ ነገር ግን ከቶ ፍጹም እንደ ሆነ አልተናገረም:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ፍጹም መሆን ይቻላል የሚለውን ክዶአል (9:20-21):: የኤሊሁ መሠረታዊ የክርክር መነሻው ደካማ ነበር፣ ምክንያቱም የሶፋርን ቃሎች ከኢዮብ ቃል ጋር አሳክሮታል:: ምናልባት ኢዮብ ኃጢአት-አልባ እንደ ሆነ የተናገረ ይመስል ይሆናል፣ ነገር ግን እርሱ እንከን-አልባ ነኝ ማለቱ ከኃጢአት-አልባነት ፍጹም የተለየ መሆኑን ነበር የተናገረው::

ሁለተኛ፣ ኤሊሁ ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር እርሱ ትክክል አለመሆኑንና በጠላትነትም እንደ ተመለከተው የተናገረውን ጠቀሰ (33:10-11):: ይህ ጥቅስ በትክክል የተባለ ነበር (13:24፣ 27፤ 16:9፤ 19:7፣ 11):: በንግግሩ ፣ ስለ ምን እርሱን እንደሚያጠቃው እንዲሁም ተገቢ የሆነ ፈተናስ ስለ ምን እንደማይሰጠው ኢዮብ በተደጋጋሚ እግዚአብሔርን ይጠይቅ ነበር:: የኤሊሁ ታላቁ ትኩረት እግዚአብሔር ስለ እራሱ የተናገረውን በመደገፍ መከራከር አልነበረም፣ ነገር ግን ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር የተናገረውን መቃወም ነበር::

ኢዮብ 33 በናሙናነት የተቀመጠ በመሆኑ፣ ይህ «ወጣት የሥነ መለኮት አዋቂ» በሕዝብ ዘንድ ስለሚነገረው ነገር ያውቃል፡ በመጀመሪያ፣ አስረግጦ ስለሚጽፈው ነገር ፍሬ ጉዳዩን በቊጥር 12-14 ጠቀሰው:- እግዚአብሔር ከሰው ይበልጣል:: ደግሞም ሁልጊዜ ልብ ሊባል በማይቻል መንገድ ለእርሱ ይናገረዋል:: ከዚያም እርሱ እግዚአብሔር ለሰዎች የሚናገርበትን ሦስት የተ

*ለያዩ መንገዶችን ይገልጻል፡- ሕልሞችና ራእዮች* (ቁ. 15-18)፣ *መከራ* (ቁ. 19-22) *እንዲሁም መካከለኛ የሚሆን መልአክ አገልግሎት* ናቸው (ቁ. 23-33)።

ከቁጥር 14-33 ባለው ላይ *ጉድጓድ* የሚለው ቃል አምስት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል። በመቅጣት በኩል የእግዚአብሔር ዓላማ ትምክሕትን በመሰባበር እና መልሶ ወደ መታዘዝ በማምጣት (ኢዮብ 33:17-18) ሰዎችን ከሞት ማዳን ነው (ያዕ. 5:19-20)። እግዚአብሔር ከጉድጓዱ ሊያድናቸው ይሻል (ቁ. 18)፣ ነገር ግን ዓመፀኞች የሆኑ ኃጢአተኞች ወደ ጉድጓዱ ቀርበዋል (ቁ. 22)፣ ከዚያም ወደ ጉድጓዱ ይወርዳሉ (ቁ. 24)፣ ከዚያም ወደ ጉድጓዱ ይገባሉ (ቁ. 30)፣ በዚህም ደግሞ ይድናሉ። «እግዚአብሔር ይህን ሁሉ፣ ሁለት ሦስት ጊዜ ለሰው ያደርጋል። ይኸውም የሕይወት ብርሃን ይበራለት ዘንድ፣ ነፍሱን ከጉድጓድ ለመመለስ ነው» (ቁ. 29-30፣ አ.መ.ት)። እግዚአብሔር «ማንም እንዲጠፋ አይፈልግም» (2ኛ ጴጥ. 3:9)።

**(1) ሕልሞችና ራእዮች (ኢዮብ 33:15-18)።** በመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ፣ እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ በሕልሞችና በራእዮች በኩል ይናገራቸው ነበር፤ ዛሬ መንፈሱ በቀዳሚነት በቃሉ በኩል ይመራናል (ዕብ. 1:1-2)። ኃጢአተኞች የሚያስፈሩ ራእዮችንና ሕልሞችን የሚያዩ ከሆኑ፣ ምናልባት ያቀዱዋቸውን ኃጢአቶች እንዳይፈጽሙ ያስደነግጡዋቸዋል። ኢዮብ እራሱ አስፈሪ ሕልሞችን ያልም ነበር (ኢዮብ 7:13-14)፤ ደግሞም ኤልፋዝ ያየው የማይረሳ የምሽት ራእይ አለ (4:12-21)። እግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያደምጡ እና እንዲታዘዙ የሚደርገውን «የሰዎችን ጆሮ ለመክፈት» ሕልሞችንና ራእዮችን ይሰጣል። እራሳቸውን የማያዋርዱ ከሆኑ፣ ወደ ሞት ጉድጓድ ይወርዳሉ።

አንድ ሰው በኒው ዮርክ ከተማ መንገድ ላይ አንድ እንግዳ የሆነ ሰውዬን ያስቆመውና እንዲህ ይለዋል፣ «ሕልምህን ልትነግረኝ ትችላለህ? እኔ ወደ ሥነ አእምሮ ባለሙያ እየሄድሁ ነኝ፣ ደግሞም ለአንድ ሳምንት ያህል እንቅልፍ አልተኛሁም። ለእርሱ እምነግረው አንድ ሕልምን ክፉኛ እፈልጋለሁ!»

ሁሉም ሕልሞች የተሰወሩ ትርጓሜዎች ያሏቸው አይደሉም፣ ደግሞም ሁሉም ሕልሞች ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰየ መልእክት



ይዘው የሚመጡ አይደሉም። ተገቢ ባልሆነ የምግብ አወሳሰድ ምክንያትነት ከአንድ በላይ የሆኑ ቅገርቶች ይከሰታሉ! «ከሕልም መጻሕፍት» በተማሩት ነገር ዙሪያ ሕይወታቸውን መምራት የሚፈልጉ ሰዎች ከምሪት ይልቅ ግራ መጋባትን የሚጠይቁ ናቸው። እግዚአብሔር የኩሩ ኃጢአተኞችን መተማመን ለማንቀጥቀጥ/ለማናጋት ሕልሞችን ሊጠቀም ይችላል፣ ነገር ግን ዛሬ ይህ ዘወትር የሚሠራበት መንገድ አይደለም።

**(2) *መሠቃየት* (ኢዮብ 33:19-22):-** *«ዘ ፕሮብሊም ኦፍ ፔይን»* በሚለው መጽሐፋቸው፣ ሲ. ኤል. ሌዊስ እንዲህ ይላሉ፣ «እግዚአብሔር በደስታችን ውስጥ በሹክሹክታ ይናገራል፣ በኅሊናችን ውስጥ ይናገራል፣ ነገር ግን በሥቃያችን ውስጥ ጮክ ብሎ ይናገራል፡- ይህም ደንቆሮ የሆነችውን ዓለም የሚያሰማበት የድምፅ ማጉሊያ መሣሪያው ነው።» እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ፣ ሊያስጠነቅቀን፣ ትሑት ሊያደርገን፣ ደግሞም ወደ መሰጠት ስፍራ ሊያመጣን የሚያሳምሙ ነገሮችን (ሥቃይን) ይጠቀማል (ዕብ. 12:1-11)። ኤሊሁ በመኝታው ላይ ሆኖ የሚሠቃይን፣ የምግብ ፍላጎት ስለሌለው እየመነመነ የሄደን በሽተኛ ሰው ይገልጻል (ይህ የኢዮብ ሥዕላዊ መግለጫ ነውን? 6:7፤ 7:3-6፤ 16:8፤ 17:7፤ 19:20 ተመልከት)። ነገር ግን ይህ ሰው እየተሠቃየ ነው፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ትኩረቱን እንዲያገኝ ይፈልጋል ደግሞም ሕግን ከመጣስ ሊከለክለው ይፈልጋል።

ሁሉም ሥቃይ ከእግዚአብሔር ይመጣል ማለት ስሕተት ነው፤ ምክንያቱም እኛ እራሳችን ለአንዳንድ መከራዎች ሥቃዮች ምክንያት ነን። ጥንቃቄ የጐደለው አሽከርካሪ አደጋ ሊያመጣ በዚህም ብዙዎች ሊሠቃዩ ይችላሉ። ተገቢ ያልሆነ አመጋገብ የሰውነት ጤናን ሊያዛባ ደግሞም የተጐዱ የሰውነት ክፍሎች ሕመም እንዲያመጡ ሊያደርግ ይችላል። በኃጢአት ውስጥ ደስታ አለ (ዕብ. 11:25)፣ ነገር ግን ኃጢአት ሥቃይ ሊያመጣ ይችላል። «የወስላቶች መንገድ ግን ሻካራ ናት» (ምሳሌ 13:15)። ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕግ የሚያረክሱ ከሆነ፣ ሊከፈል ያለ ዋጋ ይኖራል።

ደግሞም ሁሉም ሥቃዮች ስለ ኃጢአት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጡ ቅጣቶች ናቸው ማለት አይኖርብንም። ኢሊሁ ሰዎች

*ኃጢአትን ከመሥራት እና ወደ ጕድጓድ ከመሄድ እንዲታቀቡ* እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ እንዲሠቃዩ ይፈቅዳል በማለት ይከራከራል። ከመታበይ ይጠብቀው ዘንድ እግዚአብሔር «ለሥጋው መውጊያን» ሰጠው ደግሞም ጳውሎስ ስለዚያ እግዚአብሔርን ማመስገንን ተማረ (2ኛ ቆሮ. 12:7-10)። ኤሊሁ፣ ኢዮብ ለእግዚአብሔር ይገዛል፣ ያለበትን ሥቃያማ ሁኔታ ይቀበላል፣ ደግሞም ከዚህ እግዚአብሔር ለእርሱ ያዘጋጀውን በረከት ያገኛል ብሎ ተስፋ አድርጎ ነበር።

*ማንም መታመም አይፈልግም*፤ እያንዳንዱ ሰው ስለ ፈውስ ይጸልያል። ነገር ግን ብሪታኒያዊው የማኅበረ ምእመናንን የበላይ ባለ ሥልጣንነት የምትቀበል ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆነ የሥነ መለኮት አዋቂ፣ ፒ. ቲ. ፎርሲዝ እንዲህ አለ፡- «ከመወገዱ ይልቅ ስለ ሥቃይ መለወጥ መጸለይ ታላቅ ነገር ነው።» ይህም ጳውሎስ በሥጋው መውጊያ እንዲያደርግ የተማረው ነገር ነው። እርሱን ሊጥለው የመጣ መሣሪያ፣ በእግዚአብሔር ጸጋ፣ እርሱን የሚገባው መሣሪያ ሆነ! ያን የሥቃይ መልእክተኛ አጥቶ ቢሆን ኖሮ፣ ምናልባት ጳውሎስ በመንፈሳዊ ክንዋኔዎቹ ሊኩራ ይችል ነበር፤ ደግሞም ያ ወደ ኃጢአት በወሰደው ነበር።

ኤሊሁ፣ እግዚአብሔር ሰዎችን ከጕድጓድ ይጠብቃቸው ዘንድ ለሰዎች የሚነገርበትን ሁለት መንገዶች፡- ማለትም ራእዮችና ሕልሞች፣ እንዲሁም በሽታ እና ሥቃይን፣ አቅርቧል። አሁን ሦስተኛውን ያቀርባል።

**(3) የአማላጁ መልአክ አገልግሎት (ኢዮብ 33:23-33)**። የኢዮብ መጽሐፍ መላእክት (የእግዚአብሔር ልጆች) ስለ ተግባራቸው ሪፖርት የሚያቀርቡበትን ሰማያዊ ችሎት በመዘርዘር ይጀምራል (ኢዮብ 33፤ 1:6 ጀምሮ፤ 2:1 ጀምሮ)። ኤልፋዝ በ4:18 እና ምናልባትም ደግሞ በ5:1 ላይ («ቅዱሳኑ») በማለት ጠቅሷቸዋል፣ በተጨማሪም ደግሞ መላእክት በ38:7 ላይ በዓለም መፈጠር እንደሚደሰቱ ሆነው ተጠቅሰዋል። ከዚህ ከአሁኑ አንቀጽ በቀር፣ መላእክትን በተመለከተ በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱ ምንባቦች እነዚህ ብቻ ናቸው።

ኤሊሁ አስፈሪ ሥዕልን ይሥላል። ኃጢአተኞች በሕልምና በራእይ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል ደግሞም በበሽታና በሥቃይ



ይቀጣሉ። እርሱ ወደ መቃብር ቀርቦአል ደግሞም «አጥፊዎቹ» («የሞት መልእክተኞች») ሊይዙት ቀርበዋል (33:22)። ከዚያም ልዩ መልእክተኛ በድንገት ተነሣ («ከሺህ መካከል አንድ») እና በጕዳዩ ላይ ልመና ይቀርባል። ይህ መልእክተኛ ሁለቱ እጥፍ አገልግሎት አለው፡- ምን ሊያደርግ እንደሚገባው ለተሠቃየው ሰው ይነግረዋል (ቍ. 23) ደግሞም ሰውዬው እንዲታደስ ወደ እግዚአብሔር ይማልዳል።

ይህም የሚማልደው መልአክ የጌታ መልአክ፣ ሕይወቱን ለኃጢአተኞች እንደ ቤዛ አድርጎ የሰጠው (1ኛ ጢሞ. 2:5፤ ማር. 10:45) እንደ እግዚአብሔር መልአክ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ይመስላል። እንዲሁም ልዩ ተግባራትን ለማከናወን የእግዚአብሔር ልጅ በብሉይ ኪዳን ዘመን ምድርን ይጐበኝ ነበር (ዘፍ. 16:9፤ 22:11፤ ዘጸአ. 3:2፤ መሳ. 6:11)። ነገር ግን ኤሊሁ ይህን መልአክ የተመለከተው በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለ መካከለኛ ብቻ ሆኖ ሳይሆን፣ ነገር ግን ለኃጢአተኞች ቤዛን አዘጋጅም ጭምር ሆኖ ነበር።

*ይህም በመላው ክርክሩ ሁሉ ውስጥ ኢዮብ እየጠየቀ የነበረው ሰማያዊ «አማላጅ» (መካከለኛ) ነው!* ኢዮብ እርሱንና እግዚአብሔርን በአንድ ላይ ወደ ችሎት የሚያመጣ ዳኛ ፈለገ (ኢዮብ 9:33)፣ ይህም በእግዚአብሔር ፊት ክርክሩን የሚያቀርብለት ሰማያዊ «ምስክር» ነው (16:19)፤ ይህም ከሞቱ በኋላ እንኳ ነፃ የሚያወጣው «ተቤዢ» ነው (19:25)። የዚህ መልአክ አገልግሎት ግልጽ በሆነ መልኩ የእግዚአብሔር ጸጋ ተግባር ነው (33:24)። «ለሰውዬውም በመራራት፣ ቤዛ አግኝቼለታለሁና፣ ወደ ጕድጓድ እንዳይወርድ አድነው» (ቍ. 24፣ አ.መ.ት) ይላል። ያም ሁለቱንም፣ መካከለኛችንም ሆነ ቤዛችንን ኢየሱስ ክርስቶስን አስመልክቶ የሚናገር ይመስላል (1ኛ ጢሞ. 2:5-6)።

«የመቤዠት» ፅንሰ አሳብ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ መለኮት ትምህርት ጋር ተቆራኝቷል። የዕብራይስጡ ቃል «መሥዋዕት በማቅረብ ኃጢአትን ማስተሰረይ» በሚል ይተረጐማል። የተኰነነ ኃጢአተኛ እንደ ገንዘብ [መዝ. (49):7-9]፣ መልካም ሥራዎች፣ ወይም መልካም ውስጣዊ ዝንባሌ ባሉ ክፍያዎች ነፃ መውጣት አይችልም። ክፍያው እግዚአብሔር የሚቀበለው መሆን አለበት፣

ደግሞም እግዚአብሔር የደም መፍሰስን ጠይቋል (ዘሌዋ. 16-17)፡፡ ኢዮብ እንዲቤገዩት ሦስት ጓደኞቹን አልጠየቀም ምክንያቱም እንደማይችሉ ያውቅ ነበር (ኢዮብ 6:21-223)፡፡ እግዚአብሔር ብቻ ይህን ማዘጋጀት ይችላል፣ ደግሞም እርሱ ይህን አድርጎታል፡፡ እግዚአብሔር ወደ ጉድጓድ ሊወርዱ ለተዘጋጁ፣ *ለጠፉ ኃጢአተኞች፣ መቤዠት ሲያዘጋጅ አለመቀበላቸው ምንኛ ቂሎች ናቸው!*

እርሱ እራሱን ትሑት የሚያደርግ ከሆነ ብቻ እግዚአብሔር ያለበትን ሁኔታ በቅጽበት እንደሚለውጠው ኤሊሁ ለኢዮብ ቃል ገብቶለታል፡፡ ይህ ልክ እንደ አዲስ ልደት ነበር የሚሆነው (33:25፣ ደግሞ ዮሐንስ 3ን ተመልከት)! እንደ ገና በድጋሚ ጸሎትን እና ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ኅብረትን በደስታ ያጣጥማል (ኢዮብ 33:26)፡፡ ኃጢአቱን ይናዘዛል ደግሞም እርሱ ከሚገባው እጅግ ባነሰ ሁኔታ እግዚአብሔር እንደ ቀጣው ያምናል (ቁ. 27)፡፡ ኢዮብ ከጨለማ ወደ ብርሃን ይወጣል ደግሞም የእግዚአብሔርን መቤዠት ምስክርነት በደስታ ይሸከማል (ቁ. 28)፡፡

ኢዮብ 33:31-33 ኤሊሁ የኢዮብን ምላሽ የሚፈልግ መሆኑን ይጠቁማል፣ ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ ኤሊሁ ኢዮብ ጸጥ እንዲል ይፈልጋል! ኤሊሁ በሚናገረው ርእሰ ጉዳይ ላይ ጢም ብሎ በመሞላቱ መቀጠሉን ፈልጓል፣ ስለዚህ ንግግሩን ማቆምን አልፈለገም፡፡ ነገር ግን ኢዮብ ምላሽ አልሰጠም *ምክንያቱም እንዲናገር እግዚአብሔርን እየጠበቀ ነበር፡፡* ኢዮብ ቀድሞውኑ ነገሩን ዘርዝሮ አቅርቧል ደግሞም ጓንቱን ጥሏል፡፡ ኤሊሁ ስለ እርሱ የማያስበውም ሆነ የሚናገረው ነገር ለእርሱ ኢምንት ልዩነትን ነበር ሊያመጣለት የሚችለው፡፡

ኢዮብ ጉዳዩን እጅግ በጣም ወደ ላቀ ችሎት ወስዶታል፣ ደግሞም ኤሊሁ መናገሩን በፈጸመ ጊዜ፣ ዳኛው ይገለጣል፡፡



# ለግል ምልከታና ለቡድን ውይይት የተሰጡ ጥያቄዎች

1. በምዕራፍ አሥራ አንድ መክፈቻ (በዚህ መጽሐፍ) ላይ፣ ኢዮብ ከሁሉ ወደ መበሳጨት ነጥብ ላይ ደርሶ ነበር፡፡ በትግል ውስጥ ሆነህ ከሰው ሁሉ ጋር የተበሳጨህበትን ጊዜ እና እልባት ለመስጠት የተከሰተውን ነገር ዘርዝር፡፡

2. ልክ እንደ ኢዮብ እና ሦስቱ ጓደኞቹ፣ እግዚአብሔር ዝም ባለበት ጊዜ ተቀምጠን ሳለን የሚሰማን ስሜት ምን ዓይነት ነው?

3. ኤሊሁ በኢዮብ እና በሦስቱ «ጓደኞቹ» ስለ እግዚአብሔር ሲቀርብ የሰማውን የተሳሳተ አመለካከት ለመቃወም ተናገረ፡፡ ከትውስታህ ውስጥ፣ ስለ እግዚአብሔር የነበሩቸው የተሳሳተ አመለካከት ምን ነበር?

4. እግዚአብሔር ቅድስናውን፣ ፍትሑን እንዲሁም ይቅርታውን እንዴት ነው በሚዛን የሚይዘው በሚለው ላይ እግዚአብሔርን እንዴት ትመለከተዋለህ?

5. ኤሊሁ ኢዮብ እና ጓደኞቹ ሲናገሩ በንዛድ አደመጠ:: የምትናገረው ብዙ ነገር እያለህ፣ ነገር ግን ሁሉም ተናግረው እስኪያበቁ ለመጠበቅ ስትገደድ ምን ይሰማሃል?

6. ኤሊሁ እንዳቀረበው፣ መከራ አንዳንድ ጊዜ ከኃጢአት የሚጠብቀን እንዴት ነው?

7. «ኃጢአት-አልባ» በመሆን (ልክ ኤሊሁ እንዲህ ስለ ማለቱ ኢዮብን እንደ ከሰሰው ያለ) እና «እንከን-አልባ» በመሆን (ኢዮብ እራሱን እንደ ገለጸው) በዚህ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

8. በኤሊሁ ንግግር ውስጥ ያለው «የአማላጅ መልአክ» ሚናን በ1ኛ ጢሞቴዎስ 2:5-6 ከተገለጠው ከኢየሱስ ሚና ጋር አመሳክር::

9. ከመጀመሪያው የኤሊሁ ንግግር ክፍል በኋላ ኢዮብ ጸጥ ያለው ለምን ይመስልሃል?





# ኤሊሁ ስለ እግዚአብሔር አብራራ እንዲሁም ጥብቅና ቆመ

## (ኢዮብ 34-37)

«እንግዲያውስ፣ እኔ የማመልከው አምላክ ምንድን ነው? አንተ ከእኛ እጅግ የተሰወርህ ነህ፣ ግን ደግሞ ካጠገባችን ያለህ፣ እጅግ ውብና እጅግ ኃያል ደግሞም ጸንተህ የምትኖር ነህ፤ ይሁንና በሙላት ልናውቅህ አንችልም::»

- ቅዱስ አውግስጢኖስ

ሥነ መለኮት («ስለ እግዚአብሔር የሚደረግ ጥናት») «የሳይንሳዊ ጥናቶች ሁሉ ንጉሥ» በመባል ይጠራል፣ ምክንያቱም አለን ከምንላቸው እውቀቶች እጅግ አስፈላጊ የሆነውን እውቀት፣ ስለ እግዚአብሔር ማወቅን የሚይዝ በመሆኑ ነው:: ሥነ መለኮት አስፈላጊ የሆነ ሳይንስ ነው፣ ነገር ግን አስቸጋሪ የሆነ ሳይንስ ነው፣ ምክንያቱም የማይታወቀውን ማወቅ የእኛ ጥረት ነውና (ሮሜ 11:33-36):: እግዚአብሔር እራሱን በፍጥረት ውስጥ ገልጦአል፣ ነገሮችን በሚያዘጋጅበት ሁኔታ፣ በቃሉ፣ እንዲሁም ከሁሉ በላቀ መልኩ በልጁ ገልጦአል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በገለጠው ነገር ላይ ያለን መረዳታችን ሁል ጊዜ ግልጥ ላይሆን ይችላል::

«የጣዖት አምልኮ ፍሬ ነገር፣» ኤ. ደብሊው. ቶዘር ሲጽፉ፣ «ለእግዚአብሔር ያልተገቡ የመዝናኛ አሳቦችን ማሰብ ነው» ብለዋል:: *(ዘ ኖውሌጅ ኦፍ ዘ ሆሊ፣ 1)*:: ስለዚህ፣ ሁሉን ቻዩን ለመግለጽም ሆነ ለእርሱ ጥብቅና ለመቆም የሚሞክር ማንኛውም ሰው የአምላኪ ሰው ትሑት ልብ ያስፈልገዋል፣ ምክንያቱም «ሰ

ውቀት ያስታብያል፣ ፍቅር ግን ያንጻል» (1ኛ ቆሮ. 8:1፣ አ.መ.ት)

የኤሊሁን ንግግር ስታነብቡ ሳላችሁ፣ እርሱ ገና ያላደገ መሆኑ ይታያችኋል፤ እርሱ አብጦ ነበር:: በተጨማሪም የአድማጮቹ አእምሮ እየባዘነ መሆኑንም ትደርሱበታላችሁ፣ ምክንያቱም በጥንቃቄ እንዲሰሙ በተደጋጋሚ ከመምከር አልቦዘነምና (ኢዮብ 33:1፣ 31፣ 33፤ 34:2፣ 10፣ 16):: በመጨረሻዎቹ ሁለት ሦስተኛ ንግግሩ፣ ኤሊሁ የእግዚአብሔርን ፍትሕ በተመለከተ ጥብቅና ቆመ ደግሞም የእግዚአብሔርን ታላቅነት አብራራ (ኢዮብ 36-37)::

## እግዚአብሔር ልክ ነው (ኢዮብ 34-35)

ኤሊሁ በማቆላመጥ/በሽርደዳ እንደማይናገር ቃል ገብቶአል (ኢዮብ 32:21)፣ ነገር ግን በ34:2 ላይ አድማጮቹን «ጠቢባን» እና «ዐዋቂ ዎች» (አ.መ.ት) በሚል በሚጠራበት ጊዜ፣ ወደዚሁ ቀርቦ ነበር:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እየሸነገለ የነበረው እራሱን ነው፣ ምክንያቱም እነዚህ «ዐዋቂ ጠቢባን ሰዎች» እርሱን ለማድመጥ ፈቃደኞች ከሆኑ፣ እርሱ ከእነርሱ ይበልጥ የተማረ እና ጠቢብ መሆኑን ማሰብ ይኖርባቸዋልና! የኢዮብን ቃሎች በመጥቀስ (ቍ. 3፤ 12:11)፣ ኤሊሁ ቃሎቹን በሚያቀነባብርበት ጊዜ፣ የመለየት ጥበብን እንዲጠቀሙ ይለምናቸዋል፣ ስለዚህም ደግሞ በዚህ እርሱ ከእነርሱ ጋር «መልካሙን አብረው ያውቃሉ» (34:4፣ አ.መ.ት):: ኤሊሁ ንግግሩን ጣዕም ያለው ገንቢ ምግብን በደስታ ከማጣጣም ጋር ያወዳድራል::

ኤሊሁ ውይይት እንዲደረግባቸው ሁለቱን ኢዮብ ተቃውሞ ያነሣባቸውን ነገሮች ይዘረዝራል:- እነርሱም «እግዚአብሔር ፍትሐዊ አይደለም» (ቍ. 5-6) እና «እግዚአብሔርን በማገልገል ውስጥ ምንም ትርፍ የለም» (ቍ. 7-9) የሚሉ ናቸው:: ለመጀመሪያው ተቃውሞ በቍጥር 10-37 እንዲሁም ለሁለተኛው ተቃውሞ በኢዮብ 35 ውስጥ መልስ ሰጠ::

**(1) እግዚአብሔር ፍትሐዊ አይደለም (ኢዮብ 34:5-6፣ 10-37)::** እግዚአብሔር ፍትሐዊ አለመሆኑ በኢዮብ ንግግር ውስጥ አንዱ ዋና አሳብ ነበር:: እርሱ ልክ ኃጢአተኛ በሚያዝበት መንገድ መያዝ ይሰማዋል፣ ደግሞም እግዚአብሔር ወደ ችሎት መጥቶ ለኢዮብ ያደረገውን ስሕተት አልነገረውም (9:2፣ 17-20፤ 19:6-7፤



27:2):: ኤሊሁ ኢዮብ ከበደል የነጻ ነው ይሁንና ፍትሕን ተነፍጓል ማለቱን (34:5፤ 10:7፤ 6:29)፣ ደግሞም እግዚአብሔር ቀስቶችን ወርውሯል ማለቱን አስታወሰ (34:6፤ 6:4)::

በእግዚአብሔር ዘንድ የፍትሕ መጓደል አለመኖሩን ለማረጋገጥ ኤሊሁ ሦስት የመከራከሪያ ነጥቦችን አቀረበ:: የመጀመሪያው፣ *እግዚአብሔር ፍትሕን የሚያጉድል ከሆነ፣ እንግዲያውስ እግዚአብሔር አይደለም* (34:10-15):: «ክፋትን ያደርግ ዘንድ ከእግዚአብሔር፣ በደልንም ይሠራ ዘንድ ሁሉን ከሚችል አምላክ ይራቅ» (ቍ. 10):: «በእውነት እግዚአብሔር ክፋትን አይሠራም፣ ሁሉን የሚችል አምላክ ፍትሕን አያጣምምም» (ቍ. 12፣ አ.መ.ት):: አብርሃም እንዲህ ሲል ጠየቀ:- «የምድር ሁሉ ፈራጅ በጽድቅ አይፈርድምን?» (ዘፍጥ. 18:25)፣ ግልጽ የሆነው መልስ ደግሞ ይፈርዳል የሚል ነው!

እግዚአብሔር በእውነት አምላክ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ፍጹም መሆን አለበት፣ ፍጹም ከሆነ ደግሞ፣ እንግዲያውስ ስሕተት ሊሠራ አይችልም:: ልክ ባለ አራት ማዕዘን ክብ ወይም ባለ ሦስት ማዕዘን ድቡልቡል እንደ ሌለ ሁሉ፣ ፍትሐዊ ያልሆነ አምላክም እንዳለ የሚታሰብ አይደለም:: እንደ ኤሊሁ ከሆነ፣ ለእኛ ፍትሐዊ የማይመስለን ነገር በእውነት ለእርሱ ፍትሐዊ ነው:- ስላደረጉት ነገር እግዚአብሔር መልሶ ለኃጢአቶች ክፍያቸውን እየከፈላቸው ነው (ኢዮብ 34:11):: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እግዚአብሔር እጅግ ፍትሐዊ ከመሆኑ የተነሣ *ኃጢአት እራሱ ክፉ አድራጊውን እንዲቀጣ ሥርዓትን* አበጅቶአል (መዝ. 7:15፤ 9:15-16፤ 35:8 ተ መልከቱ):: የእግዚአብሔርን ፍትሕ ማምለጫ መንገድ የለውም::

እግዚአብሔር ሉዓላዊ መሆኑን እንዲሁም ሉዓላዊ የሆነ አምላክ በየትኛውም ሕግ ሊጠየቅ እና በየትኛውም ፍርድ ቤት ሊዳኝ አይችልም:: ንጉሥ ስሕተት ሊሠራ ይችላል:: እግዚአብሔር *ወደ ዙፋኑ እንዲመጣ አልተደረገም*፣ ስለዚህም ደግሞ ከዙፋኑ እንዲወገድ አይደረግም (ኢዮብ 34:13):: እግዚአብሔር ጻድቅ አይደለም ማለት እርሱ እግዚአብሔር አይደለም በዙፋኑ ላይ እንዲቀመጥም መብት የለውም እንደ ማለት ነው:: ነገር ግን እግዚአብሔር እስትንፋሳችንን ይቈጣጠራል ደግሞም ሕይወታችንን ፈጥኖ ሊወስድ ይችላል (ቍ. 14-15፤ የሐዋ.

17:25፣ 28)። «ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው፤ ርኅራኄው አያልቅምና» (ሰቆ. 3:22)።

የኢዮብ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ያጕላል። ገና ከመጀመሪያው ምዕራፍ ጀምሮ፣ እግዚአብሔር ሁሉን በመቈጣጠር ላይ መሆኑ ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም ሰይጣን እንኳ ሊያደርገውና ሊያደርገው የማይችለው ነገር ተነግሮታል። በክርክሩ ወቅት፣ እግዚአብሔር የሌለ ሆኖ ይታያል፣ ነገር ግን ኢዮብ የሚሰማውን ነገር እንዲሁም ጓደኞቹ የሚሉትን ነገር ያውቃል። በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ ሠላሳ አንድ ጊዜ እግዚአብሔር «ሁሉን ቻይ» ተብሏል። ኤሊሁ ግቡ ላይ በማተኮር ረገድ ትክክል ነበር:- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው ደግሞም ስሕተትን አይሠራም።

ሁለተኛ መከራከሪያ ነጥቡ፣ *እግዚአብሔር ፍትሐዊ ካልሆነ፣ በምድር ላይ ፍትሐዊ የሆነ መንግሥት አይኖርም* (ኢዮብ 34:16-26)። ልክ እንደ ተከበረ ሽማግሌ፣ ኢዮብ በአካባቢው መንግሥት ሥራ ላይ ተሳትፎአል ደግሞም ለተጠቁ ሰዎች ፍትሕን ለማስፈን እገዛ አድርጓል (29:7-17)። ነገር ግን ሁሉም የሰዎች መንግሥት በእግዚአብሔር የተመሠረተ ነበር (ዘፍጥ. 9:1-7፤ ሮሜ 13:1-7)፤ ስለዚህ ሟች የሆኑ የሰው ልጆች በምድር ላይ ፍትሕን የሚያሰፍኑ ከሆኑ፣ ቅዱስ እና ሉዓላዊ የሆነ እግዚአብሔር ከሰማይ ፍትሕን አያሰፍንም? እርሱ ነገሥታትን ከዙፋናቸው ለማውረድ እንዲሁም ልዑላንን ማስወገድ ይችላል ደግሞም አያደላም (ዳን. 4:25፣ 32፣ 35)። ዓለምን የሚገዛ እግዚአብሔር ፍትሕ-አልባ ከሆነ፣ ምንም ዓይነት ሥርዓትና ቅንጅት የለም፣ ደግሞም ሁሉም ነገር ተለያይቶ ይወድቃል።

ይሁን እንጂ፣ ኤሊሁ አንዱን የመለኮት ባሕርይ:- የእግዚአብሔርን ፍትሐዊነት ነቅሶ ብቻ በማውጣቱና በማጕላቱ አንድ ትልቅ ስሕተትን ሠራ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር አፍቃሪና ቸር ጭምር ነውና። (በልዳዶስም እንደዚሁ በንግግሩ ተመሳሳይ ስሕተት ሠርቷል።) እግዚአብሔር በጥበቡ፣ ፍትሑንም ሆነ ፍቅሩን አርኪ በሆነ መልክ የሚያስተናግድበት የመቤዠት ዕቅድ አለው (ሮሜ 3:21-31)። በመስቀሉ ምክንያት፣ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ሊቤዥ እና አሁንም ጽድቁን ሊያጕላ ደግሞም ቅዱስ የሆነ ሕጉን የተጠበቀ እንደ ሆነ ሊያደርገው ይችላል።



የኤሊሁ ሦስተኛ የመከራከሪያ ነጥብ *እግዚአብሔር ፍትሐዊ ካልሆነ፣ እንግዲያውስ በዓለም ላይ የሚከናወነውን ነገር ማየት አይገባውም* የሚል ነው (ኢዮብ 34:21-30)። ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው ደግሞም ሁሉንም ነገር ማየት ይችላል! ሰብዓዊ የሆነ ዳኛ፣ ካሉበት ውስንነቶች ጋር፣ የተለያዩ ጕዳዮችን አዳምጦ የሚችለውን ምርጥ ውሳኔ ያስተላልፋል፣ ደግሞም አንዳንድ ጊዜ ስሕተትን ይሠራል። ነገር ግን እግዚአብሔር እያንዳንዷን ርምጃችንን ይመለከታል፣ እንዲሁም ከእርሱ የምንደበቅበት ምንም ስፍራ የለም [መዝ. (139):7-12]። ኢዮብ እግዚአብሔርን በፍርድ ችሎት ላይ ሊያገኘው ፈለገ፣ ይህም ጕዳዩን ማቅረብ እንዲቻለው ነበር፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ቀድሞውኑ የማያውቀው የቱን ነገር ኢዮብ ሊያቀርብ ይችላል? «ሰው ለፍርድ ፊቱ ይቀርብ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ቀጠሮ አይዝለትም» (ኢዮብ 34:23)። እንደ ሰብዓዊ ባለ ሥልጣናት፣ እግዚአብሔር መርማሪ ቡድን ማሰማራትና መረጃዎችን መሰብሰብ አያስፈልገውም፤ ሁሉንም ነገር ያውቃል ደግሞም ፍጹም በሆነ መንገድ መፍረድ ይችላል።

ከቀረቡት ተቃውሞዎች አንዱ እግዚአብሔር ጸጥ ማለቱና ከእርሱ መሰወሩ ነበር (9:11፤ 23:1-9)፤ ነገር ግን ኤሊሁ ለዚያ መልስ ነበረው:- «እርሱ ዝም ቢል፣ ማን ሊወቅሰው ይችላል? ፊቱንስ ቢሰውር፣ ማን ሊያየው ይችላል?» (34:29፣ አ.መ.ት)። በኢዮብ 24 ላይ፣ ኢዮብ የሰዎችን ኃጢአት ቸል ስለ ማለቱ እግዚአብሔርን ይወቅሳል፣ ነገር ግን በፈራጁ ላይ ለመፍረድ እርሱ ምን መብት አለው? በከነዓን ያሉ ክፉ ሕዝቦች ላይ ለመፍረድ እግዚአብሔር አራት ምእተ ዓመታት ጠብቆአል (ዘፍጥ. 15:13-16) እንዲሁም የጥፋት ውኃን ከመላኩ በፊት ለ120 ዓመታት ታግሦአል (6:3)። እግዚአብሔር ንስሐ እንዲገቡ ጊዜን በመስጠቱ ኃጢአተኞች የታደሉ ናቸው (2ኛ ጴጥ. 3:9)።

እግዚአብሔር በሕዝቦችና በግለሰቦች ላይ ይገዛል (ኢዮብ 34:29)፣ ነገር ግን ለሚሠሩት ኃጢአት እርሱ ተጠያቂ አይደለም፤ ምክንያቱም እርሱ ነፃነትንና ውሳኔ የማድረግን ፈቃድ ሰጥቷቸዋል። በተጨማሪም ከኃጢአት የመመለስና በእግዚአብሔር የመታመንን ነፃነት ሰጥቷቸዋል። በዚህ ምክንያት፣ ኤሊሁ

ኃጢአቱን እንዲናዘዝና ንስሐ እንዲገባ ለኢዮብ ልመናን በማቅረብ የዚህ ክፍል ንግግሩን ይቋጫል (ቊ. 31-33)። «የማታውቀውን እንዲያስተምርህ እግዚአብሔርን ጠይቀው፣ ደግመህም እንዲህ ያለ ኃጢአት እንደማትሠራ ቃል ግባ» ብሎ መከረው (ቊ. 32 ተ መልከት)። እግዚአብሔር በእርሱ መንገድ ብድራታችንን ይከፍለናል እንጂ፣ በእኛ መንገድ አይደለም፤ ደግሞም እርሱ ከሚጠይቃቸው ነገሮች መካከል አንዱ ንስሐ መግባትና ከኃጢአት መመለስ ነው።

ኤሊሁ ንግግሩን አቆመ እና የሚናገርበትን ዕድል ለኢዮብ ሰጠው (ቊ. 33)፣ ነገር ግን ኢዮብ ምንም አልተናገረም። ምናልባት ይህ ኤሊሁን የበለጠ እንኳ ሳያስቈጣው አልቀረም፤ ምክንያቱም ይህን የንግግሩን ክፍል በኢዮብ ላይ አሳዛኝ የሆነ ክስ በማቅረብ ነበር የደመደመው። ኢዮብ እውቀትና ማስተዋል እንደሚያንሰው ተናግሮአል፣ ደግሞም ኢዮብ ዓመፀኛና በትዕቢት በእግዚአብሔር ላይ ተናግሮአል ብሏል። ዛሬ እጅን ማጨብጨብ መስማማትን መግለጫ ምልክት ነበር ነገር ግን በዚያ ዘመን፣ የማሾፍና የንቀት መግለጫ የሆነ አካላዊ ምልክት ነበር፣ (27:23፤ ሰቆ. 2:15)። ኤሊሁ ኢዮብ ተጨማሪ የሆነ ፈተና እንኳ እንደሚያስፈልገው አድርጎ ደመደመ (ኢዮብ 34:36)! ምናልባት ያ ወደ መረዳቱ ያመጣው ይሆናል።

የኢዮብን የመጀመሪያ ተቃውሞ ካለፈ በኋላ፣ ኤሊሁ ወደ ሁለተኛው ጥያቄ ተመለሰ።

**(2) «እግዚአብሔርን በመታዘዝ ውስጥ ትርፍ የለም» (ኢዮብ 34:7-9፤ 35:1-16)።** እንደ ገና ኤሊሁ የኢዮብን ቃሎች መልሶ በፊቱ ላይ ሊጥልበት ይሞክር ነበር፡- እነርሱም «እኔ በደለኛ አይደለሁም» (10:7፤ 12:4፤ 27:6)፣ ደግሞም «እግዚአብሔርን በመታዘዝ ምን አገኘሁ?» (9:29-31፤ 21:15) የሚሉ ናቸው። ኢዮብ የመጀመሪያውን ዓረፍተ ነገር ተናግሮአል፣ ነገር ግን ሁለተኛው ንግግሩ በትክክል ያልተጠቀሰበት ሁኔታ ነበር ያለው። ሰይጣን እርሱ ሊያደርገው እንደሚፈልግ ዓይነቱን ድርድር ኢዮብ ከቶ አላደረገም (1:9፣ 21፤ 2:9-10)። ኤልፋዝ በዚህ ርእስ ውይይትን ከፍቶ ነበር (ኢዮብ 22) ደግሞም በእግዚአብሔር ባሕርይ ላይ የሰው መቀደስም ሆነ በደሉ ምንም ልዩነትን



አያመጣም ወደሚል መደምደሚያ መጣ። ነገር ግን ኤሊሁ ከዚህ ፍሬ ነገር ጋር እንደ ገና ጊዜ ማጥፋት አስፈላጊ እንደ ሆነ ተ ሰምቶታል።

ኤሊሁ አድማጮቹን ወደ ሰማይ እንዲመለከቱ እንዲሁም ደመናት ምን ያህል ሩቅ እንደ ሆኑ እንዲያዩ ጠይቋቸዋል፣ ከዚያም ደግሞ የእግዚአብሔር ዙፋን ከሞት ምን ያህል ሩቅ እንደ ሆነ ተናግሯል (33:5-7)። በምድር ላይ ያለ የሰው ኃጢአትም ሆነ መልካም ሥራዎች በሰማይ ያለውን ሁሉን ቻይ እስከ መለወጥ የሚደርሱበት እንዲህ ያለ ኃይል ይሰጣሉ ወይ?

ከዚያም ኤሊሁ ሰብአዊ የሆነ ኅብረተሰብን ልብ እንዲሉ ይጠይቃቸዋል (ቊ. 8-16)። ኃጢአቶቻችንም ሆኑ መልካም ሥራ ዎቻችን በዙሪያችን ያሉ ሰዎችን ሊነኩ ይችላሉ (ቊ. 8)፣ ነገር ግን እግዚአብሔር በእነርሱ የሚነካ አይደለም። በእርግጠኝነት እግዚአብሔር ሰዎች በሚሠሩዋቸው ኃጢአቶች ያዝናል (ዘፍጥ. 6:6) ደግሞም በታማኝ ሰዎች መታዘዝ ይደሰታል (መዝ. 37:23)፤ ነገር ግን ድርጊቶቻችን እርሱን ሊበዘብዙት አይችሉም፣ እንዲሁም መጥፎ ተግባሮቻችን አያስፈራሩትም። ሰዎች ታዘዙትም አልታዘዙትም፣ የእግዚአብሔር ባሕርይ አንድ ዓይነት ነው። እግዚአብሔር የተሻለ ወደ መሆን አይለወጥም ምክንያቱም እርሱ ፍጹም ነው፣ ደግሞም እርሱ የከፋ ወደ መሆን አይለወጥም ምክንያቱም እርሱ ቅዱስ ነው።

እግዚአብሔር ለወፎችና ለምድር አራዊቶች እንክብካቤ ያደርጋል። እነርሱም ይታመኑበታል (ኢዮብ 35:11፤ ማቴ. 6:25-34)፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ ሰዎች አስቸጋሪ በሆነ የጭቆና ቀንበር ሥር እስከሚወድቁ ድረስ ወደ እግዚአብሔር አይጮኹም። መከራ እስኪመጣ ድረስ እግዚአብሔርን ይረሳሉ። ነገር ግን ጸሎታቸው ቅን እንዳልሆነ እግዚአብሔር ያውቃል። ስለዚህ አይመልስላቸውም (ቊ. 12-13)። ይህም የኢዮብ ጸሎት ለምን እንዳልተመለሰ ያብራራል፡- ይህም ልቡ ከእግዚአብሔር ጋር በትክክል የሚሄድ አልነበረም (ቊ. 14)።

ነገር ግን እግዚአብሔር ሸክሙን ባያቀልልለት እንኳ፣ ለታመነ በሥቃይ ውስጥ ላለ ሰው «መዝሙርን በሌሊት» ሊሰጥ ይችላል [ቊ. 10፤ መዝ. (42):8፤ (77):6]። «የቱም ሰው በቀን ሊዘምር

ይችላል፣» አሉ ቻለስ ስፐርጀን:: በመቀጠልም፣ «በቀኑ ብርሃን ኖታዎቹን ማንበብ በምንችልበት ወቅት መዘመር ቀላል ነው፤ ነገር ግን የሚነብበበት የብርሃን ጨረር በሌለበት መዘመር የሚችል የተካነ ዘማሪ ነው፣» አሉ:: ወደ መስቀል ከመሄዱ በፊት እግዚአብሔር ለኢየሱስ «በሌሊት መዘሙርን» ሰጥቶታል (ማቴ. 26:30) ደግሞም ለጳውሎስና ለሲላስ በፊልጵስዩስ እስር ቤት ውስጥ መዝሙር (የሐዋ. 16:25) ተሰጥቶአቸዋል:: ሸክማችንን ማቃለል የሚገባ መስሎ ካልታየው እግዚአብሔር የሚሸከሙብትን ጥንካሬ/ኃይል ሁልጊዜ ይሰጣቸዋል-እንዲሁም ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ የሚዘምሩትን መዝሙር ይሰጣቸዋል!

ኤሊሁ እግዚአብሔርን ሊያየው እንደማይችል ኢዮብ ያቀረበውን ተቃውሞ (ማጉረምረም) አጣጣለበት:: ዋናው ነገር *እግዚአብሔር ኢዮብን ማየቱ* እና ጉዳዩን ሙሉ በሙሉ ማወቁ ነው (ኢዮብ 35:14):: የኢዮብ ሁኔታ ባዶ በሆነ ንግግሩ እና በብዙ ቃሎቹ ሊለወጥ አይችልም (ቁ. 16)፣ ስለዚህ ኢዮብ ሊያደርገው የሚገባው ብቸኛው ነገር መጠበቅና መታመን ነበር (ቁ. 14)::

እግዚአብሔር ቸር ነው (ኢዮብ 33)፣ ደግሞም እግዚአብሔር ፍትሐዊ ነው (ኢዮብ 34-35)፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ታላቅ እና ኃይለኛም ጭምር ነው (ኢዮብ 36-37)፣ ደግሞም እግዚአብሔር ምን ያህል ታላቅ እንደ ሆነ ኢዮብ ሊገነዘብ እንደሚገባ ኤሊሁ አሰበ::

## እግዚአብሔር ታላቅ ነው (36-37)

«እግዚአብሔር ኃያል ነው» (ኢዮብ 36:5):: «እነሆ፣ እግዚአብሔር በኃይሉ ከፍ ከፍ ብሎአል» (ቁ. 22፣ አ.መ.ት):: «እነሆ፤ እግዚአብሔር ከአእምሯችን በላይ ታላቅ ነው» (ቁ. 26፣ አ.መ.ት):: በእነዚህ ሁለት ምዕራፎች፣ *ለሰዎች ባለው ምሕረት* የተሞላበት ዓላማ (ቁ. 1-25) እንዲሁም *በተፈጥሮ ውስጥ ባለው ታላቅ ኃይል* የእግዚአብሔርን ታላቅነት ኤሊሁ አጉልቶ ያሳያል (36:26-37:13):: ንግግሩንም አንድ የመጨረሻ ልመና ለኢዮብ በማቅረብ ይህም እግዚአብሔርን እንዲፈራና ንስሐ እንዲገባ በመጠየቅ ይደመድማል (ቁ. 14-24)::

**እግዚአብሔር ለሰው ያለው ምሕረት የሞላበት ዓላማ (ኢዮብ**



**36:1-25)::** የመጨረሻውን ሦስተኛ ንግግሩን እያደረገ ሳለ የኤሊሁ ታላቅነት ወደ አዲስ ከፍታ ደረሰ (ቁ. 1-4):: በዚሁ ጊዜ አድማጮቹ ዕረፍትን ያጡ ሳይሆኑ አይቀሩም፤ አለበለዚያ፣ ጥቂት ታገሠኝና እነግርሃለሁ» (ቁ. 2፣ አ.መ.ት) ማለት ለምን አስፈለገው? «እውቀቴን ከሩቅ አመጣለሁ» (ቁ. 3) የሚለው ዓረፍተ ነገር ወይ ብዙ እውቀት እንዳለው በመኩራራት እየተናገረ እንደ ሆነ አሊያም ደግሞ እውቀቱን በትክክል ከሰማይ እንደሚያገኘው እየገለጸ መሆኑን ይጠቁማል:: «በዕውቀቱ ፍጹም የሆነ ሰው ከአንተ ጋር ነው» ብሎ (ቁ. 4፣ አ.መ.ት)፣ የትሕትና ማስረጃ ነው ብሎ መቁጠር እጅግ ይከብዳል!

*ማብራሪያ* (ቁ. 5-15):: እግዚአብሔር ታላቅ እና ኃይለኛ የመሆኑ ነገር ሰውን ቸል ይለዋል ደግሞ ለግለሰቦች ግድ የለውም ማለት አይደለም:: «እግዚአብሔር ኀያል ነው፤ ግን ማንንም አይንቅም፤ ኃያል፣ በዐላማውም ጽኑ ነው» (ቁ. 5፣ አ.መ.ት):: ያ ዓላማ ምንድን ነው? ክፉዎችን መቅጣትና የተጠቁትን («ድሆች» ቁ. 6፣ 15) መርዳት ነው:: ኤሊሁ ዕብሪተኛ ከሆኑ ክፉዎች ጋር እንዲሁም ከተጨቆኑ ጻድቃን ጋር እግዚአብሔር የሚያደርገውን ግንኙነት ያቃርነዋል:: «እርሱ በደለኞችን በሕይወት አያኖርም ለችግረኞች ግን ፍርዱን ይሰጣል» (ቁ. 6)::

ኢዮብ እግዚአብሔር ቸል እንዳለ መሰለው፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ዓይኖቹን በጻድቃን ላይ ያደርጋል (ቁ. 7፤ 1ኛ ጴጥሮስ 3:12) ደግሞም በመጨረሻ ሁኔታዎቻቸውን ይለውጣል:: ከዐመድ ቁልል ወደ ላይ ከፍ ከፍ ያደርጋቸዋል (ሉቃስ 1:52-53) ደግሞም ከሰንሰለታቸው ነፃ ያደርጋቸዋል (ኢዮብ 36:7-8):: ልንኖርበት ትክክለኛ የሆነውን መንገድ በመስጠት ያርመን እና ያስተካክለን ዘንድ ይቀጣናል:: ትምህርታችንን ተምረን የምንታዘዝ ከሆንን፣ እንደ ገና ይባርከናል:: ነገር ግን የምናምፅ ከሆንን፣ ያጠፋናል (ቁ. 9-12)::

የልብ ምላሽ ቍልፍ ነገር ነው:: አስመሳዮች (ግብዞች) («በልባቸው አምላክ የለሽ የሆኑ» አ.መ.ት) እግዚአብሔርን በመቃወም ልባቸውን ባጠነከሩ መጠን ቍጣ ያነሣሣሉ:: እግዚአብሔር ምንም ያህል ቢቀጣቸውም፣ ለእርዳታ መጮኽን እንቢ ይላሉ:: ነገር ግን ልቦቻቸው ትሑት የሆኑ ሰዎች

ከእግዚአብሔር ዘንድ መልእክትን ያገኛሉ («በመከራቸውም ውስጥ ይናገራቸዋል» ቍ. 15፣ አ.መ.ት) ደግሞም ከኃጢአታቸው ይመለሳሉ። «ንጹሕ ያልሆኑ» የሚለው ሐረግ በቍጥር 14 ላይ በልዩ ልዩ የጣዖት አምልኮ ስፍራዎች ያሉ ወንድ ጋለሞታዎችን ያሳያል (ዘዳግ. 23:17)። ኤሊሁ ይህን ሥዕላዊ መግለጫ በጣም ጥልቀት ያለው ሐፍረትንና ኃጢአትን ለመግለጽ ይጠቀምበታል። ክፉዎች ገና በልጅነት (በወጣትነታቸው) የሚሞቱ ብቻ አይደሉም (ኢዮብ 36:14፤ 20:5፣ 11)፣ በመዋረድም ይሞታሉ።

*የሕይወት ማዛመጃ* (ቍ. 16-25)። ኢዮብ መወሰን አለበት። «ከመከራ መንጋጋ፣ ጭንቀት ወደሌለበት ወደ ሰፊ ስፍራ ያወጣሃል» [ቍ. 16፣ አ.መ.ት፤ መዝ. (18):19]። ምርጥ በሆኑ ምግቦች መሞላት ሲገባው፣ የኢዮብ ገበታ በመከራ ሞልቶአል። ኢዮብ እንዴት ምላሽ ሊሰጥ ይችላል?

ኤሊሁ በኢዮብ ፊት ብዙ አደጋዎችን ይመለከታል ደግሞም ያስጠነቅቀዋል። የመጀመሪያው ኢዮብ ከመከራ ለመውጣት አንዳንድ አቋራጮችን ይፈልጋል፣ በዚያም ደግሞ እግዚአብሔር ለእርሱ ያለውን መልእክት ይስታል። ኢዮብ አንድ ሰው ይህን «ሄዶ እንዲገዛለት» ሊስማማ ይችል ይሆናል፣ ነገር ግን የቱም የገንዘብ መጠን ይህን ሊገዛ አይችልም (ኢዮብ 36:18-19)። *«ዘ ዎል ስትሬት ጆርናል»* የተባለ ጋዜጣ እንዲህ ሲል ምርጥ በሆነ አባባል አስቀምጦታል፦ ገንዘብ ዓለም አቀፋዊ እንደ ሆነ የይለፍ ወረቀት ከሰማይ በቀር በየትኛውም ስፍራ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል መገልገያ መሣሪያ ነው፣ ደግሞም ከደስታ በቀር ሁሉንም ነገር እንደሚያቀርብ ዓለም አቀፋዊ መሣሪያ ነው።»

ሁለተኛው አደጋ የገዛ ሕይወቱን ማጥፋትም እንዳለ ኢዮብ ልብ ሊል ይገባል (ቍ. 20)። «ሌሊት» እና «ጨለማ» የሞት ሥዕላዊ መግለጫዎች ናቸው፣ ደግሞም ኢዮብ ዘወትር ለመሞት ያለውን ጥማት ይገልጻል (3:1-9፣ 20-23፤ 7:21፤ 10:18-22)። ብዙዎቹ መከራ የሚቀበሉ ሰዎች ያሉበትን ተስፋ-አልባ ሁኔታ ለማምለጥ እራሳቸውን ይገድላሉ፣ ነገር ግን ኢዮብ ይህን መንገድ ይከተላል የሚል አስጊ ነገር የለም። ኢዮብ የእምነት ሰው ነበር ደግሞም ሳይጋበዝ ወደ እግዚአብሔር መገኘት (ህልዎት) አይሄድም።

ኤሊሁ ሦስተኛ አደጋን ተመለከተ፣ ይህም ኢዮብ ተስፋው ሁሉ



ይሚጠጥና ወደ ኃጢአታዊ ሕይወት ይመለስ ይሆናል (36:21) የሚል ነው። በግል የእረኝነት አገልግሎቴ ማመናቸውን የሚመሰክሩበትን እምነት ጥለው ወደ ዓለም የተመለሱ ሰዎችን አማክሬአለሁ። «ሕይወት ይህን ያህል ከባድ ከሆነ» ይላሉ፣ «እኛም እንደዚሁ በቻልነው መጠን እራሳችንን ማስደሰት ይኖርብናል።» ከእግዚአብሔር ውጭ እውነተኛ የሆነ ደስታ አለመኖሩን ይረሳሉ፣ ከዚያም ደግሞ ኃጢአት የገዛ እራሱን መከራና ኀዘን ያመጣል።

በመጨረሻም፣ ኤሊሁ የእግዚአብሔርን ታላቅነት በተመለከተ አዲስ ራእይን አገኘ እንዲሁም እርሱን ማመስገን ጀመረ (ቍ. 22-25)። እግዚአብሔር በመከራችን ውስጥ ሊያስተምረን ይፈልጋል (ቍ. 22)፣ እንዲሁም ትምህርታችንን ለመማራችን አንዱ ማስረጃ ስለ መከራችን እንኳ እርሱን ማወደስና ማመስገን እንጀምራለን።» «ሰዎች በመዝሙር ያወደሱትን፣ የእርሱን ሥራ ማወደስ አትዘንጋ» (ቍ. 24)። «ጸሎት ነገሮችን እንደሚለውጥ» ሁሉ፣ እንዲሁ «ምስጋና ነገሮችን ይለውጣል።»

**እግዚአብሔር በተፈጥሮ ላይ ያለው ብርቱ ኃይል (ኢዮብ 36:26-37:24)።** «እነሆ፣ እግዚአብሔር ታላቅ ነው፣ እኛም አናውቀውም» (36:26)። ይህ የኤሊሁ የመጨረሻው የንግግሩ መሠረት አሳብ ክፍል ነው፤ እንዲሁም በፍጥረት ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ሥራ በተለይም በዓመቱ ወቅቶች እግዚአብሔር ዓለሙን የሚቈጣጠርበትን በሥዕላዊ መግለጫ ያሳያል።

*በልግ* (36:27-37:5)። በምሥራቅ ከበጋው ሙቀትና ድርቅ በኋላ፣ ምድሪቱም ሆነች ሕዝቡ ሁለቱም የበልጉን ዝናብ ዝግጁ ሆነው ይቀበሉታል። «ተፈጥሮአዊ የውኃ ዑደትን» (ትነት፣ የውኃ ወደ በረዶነት መለወጥ እንዲሁም የውኃ የበረዶ ክምችት) ደግሞም ይህ «ተፈጥሮአዊ ሂደት» እንዲሠራ የኤሌክትሪክሲቲ (መብረቅ) አስፈላጊ መሆንን በተመለከተ የኤሊሁን ማስተዋል ማግኘት ደስ ያሰኛል።

በሳይንቲስት (ተመራማሪ) አእምሮ ነገር ግን በገጣሚ ልብ፣ ኤሊሁ ነጐድጓድን በተመለከተ ማብራሪያ ሰጠ። ደመና እንዴት እንደሚሰባሰብ በመናገር ጀመረ (36:26-29)፣ ከዚያም በመብረቅ አማካይነት ኃይል እንዴት እንደሚለቀቅ መናገሩን ቀጠለ (ቍ. 30-32)፤ ከዚያም ደግሞ የነጐድጓድን ድምፅ በተመለከተ ተናገ

ሬ (36:33-37:5)። ለኤሊሁ፣ መብረቅ የእግዚአብሔር መሣሪያ ነው (36:32)፣ ደግሞም ነጐድጓድ የእግዚአብሔር ድምፅ ነው (37:2፣ 4-5)። በምሥራቅ፣ በብዙ ማይል ርቀት ላይ ዐውሎ ነፋስ ሲጠነሰስ ደግሞም ደስ በሚል እይታ እየቀረበ ሲመጣ ማየት ትችላላችሁ።

ለዐውሎ ነፋሱ ትዕይንት የኤሊሁ ምላሽ ምን ነበር? አንድ ነገር ለመጥቀስ ያህል፣ ዐውሎ ነፋሱ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት እና የእግዚአብሔርን መልካምነትን ያስታውሰዋል። «በእነዚህ በአሕዛብ ላይ ይፈርዳል፤ ብዙም ግብ ይሰጣል» (36:31)። በተጨማሪም በእርሱ ውስጥ በእግዚአብሔር ብርቱ ኃይል ላይ የመተማመን ስሜት ያሳድራል (37:1)። ዳዊት በመዝሙር 29 ላይ ተመሳሳይ ተሞክሮን አስፍሮአል።

*ክረምት* (ቊ. 6-10)። በአንዳንድ ነጥቦች፣ የበልግ ዝናብ፣ የክረምት የበረዶ ግግርና ትናንሽ በረዶ ይሆናል። ሠራተኞች ተግባራቸውን ማቆም ይኖርባቸዋል፣ ደግሞም የዱር አራዊት ወደ መጠለያ ጉረኖዎቻቸው ያፈገፍጋሉ። እግዚአብሔር በውኃዎች ላይ ይተነፍሳል፣ ደግሞም ይረጋሉ። የአየር ንብረት ባለሞያዎች «ሥነ አየር ጸባይ ክንውን» ብለው የሚጠሩትን፣ ኤሊሁ የሁሉን ቻዩ አምላክ ተአማራዊ ሥራ ይለዋል። እንዲህ ብለው በጻፉዋቸው አይዛቅ ዋትስ ከኤሊሁ ጋር ይስማማሉ፡-

*የጌታን መልካምነት እዘምራለሁ*
*ምድርን በምግብ የሞላውን፤*
*ፍጥረታትን በቃሉ ፈጠራቸው*
*ከዚያም አወጀ መልካምነታቸውን።*

*ከበታች ተክልም ሆነ አበባ የለም*
*ነገር ግን ክብርህ እንዲታወቁ አደረጋቸው፤*
*ደግሞም ደመና ተነሣ ውሽንፍሮችም ነፈሱ*
*ከዙፋንህ በወጣ ትእዛዝ።*



*ፀደይ* (ቊ. 11-13)። በመጨረሻም የሞቀ ነፋስ መንፈስ ይጀምራል፣ የበረዶው ግግርና ትናንሾቹ በረዶዎች ይቀልጣሉ፣ ደግሞም የዝናቡ ደመና እንደ ገና ይገለጣል። ኤሊሁ በዓለም የአየር ንብረት ላይ ነፋስ ጠቃሚ የሆነ ሚና የሚጫወት መሆኑን ያውቃል። ነፋስ ምን እንደሚያደርግ ማንም አስቀድሞ በትክክል ሊናገር አይችልም (ዮሐንስ 3:8)፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ነፋስን ሙሉ በሙሉ ይቈጣጠረዋል (መዝ. 148:8)። «የውኃው ዑደት» ውጤታማ በሆነ መልኩ ይሠራል፡- ደመናው በውኃ ይሞላል፣ መብረቁ ብልጭ ይላል፣ ዝናቡም ይወርዳል። እግዚአብሔር አንዳንዴ ለቅጣት ዐውሎ ነፋሶቹን ይልካል (ኢዮብ 37:13፤ ዘፍጥ. 6-8፤ ዘጸአ. 9:13-26፤ 1ኛ ሳሙ. 12:16-19)።

ነገር ግን በአብዛኛው፣ ዝናብ የፍቅር እና የምሕረት ስጦታው ነው (ኢዮብ 37:13)።

*በጋ* (ቊ. 14-18)። አሁን ደመናው በቊጥጥር ሥር ነው (ቊ. 16፣ አ.መ.ት)፣ ሁሉም ነገር ጸጥ ብሎአል። የበጋው ፀሐይ አየሩን አምቆታል፣ የደቡብ ነፋስ («ሲሮኮ» የሚባለው) ከበረሀ ይነፍሳል፣ ሰዎች ደግሞ «ከሙቀት የተነሣ በልብሳቸው ውስጥ የሚዝለፈለፉ» ሆነዋል (ቊ. 17፣ አ.መ.ት)። ሰማዩ ልክ እንደ ናስ መስታወት ነው፣ ማረፍ እንጂ ማንም ምንም ማድረግ አይፈልግም።

ነገር ግን ኤሊሁ በአራቱ ወቅቶች ውስጥ ግጥማዊ እና ሳይንሳዊ ትምህርት ከመስጠት የሚበልጥ ነገር እያደረገ ነበር። የእግዚአብሔርን ታላቅነት ደግሞም የተፈጥሮን አስደናቂ ነገሮች ልብ ማለት ከኢዮብ ይፈለጋል። *እንዲሁም ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር እና በዚህ ምድር ስላሉት ሥራዎቹ የሚያውቀው በእውነት ትንሽ እንደ ሆነ እንዲገነዘብ ይፈልጋል።* ኤሊሁ ኢዮብን ሦስት የዘመኑ ማነጋገሪያ ስለ ሆኑት ነገሮች ጥያቄዎችን ጠየቀው እነዚህም፡- ስለ ደመና፣ መብረቅ፣ ነፋስ እና ዝናብ-አልባ ስለሆነው ሰማይ ነበር። «እነዚህን ነገሮች ማብራራት ትችላለህ?» ሲል ጠየቀው፤ «ልትቈጣጠራቸው ትችላለህ?»

ይህም ኤሊሁን ወደ መጨረሻው ጥቃት አመራው፡- «የተፈጥሮን ዕለታዊ ነገሮች ለእኛ ማብራራት ካልቻልህ፣ እንግዲያውስ በእግዚአብሔር ፊት እራስህን ለመከላከል እንዴት ችሎት ማቋቋም

ትችላለህ?» ከዚያም ደግሞ እግዚአብሔርን ለመቋቋም መጣር በእግዚአብሔር ፍርድ መዋጥን እንደሚያመጣ በመንገር ኢዮብን አስጠነቀቀው (ቊጥር 20)። ቊጥር 21-22 «ከዝናብ በኋላ የሚሆንን ብሩህ ነጸብራቅ» (2ኛ ሳሙ. 23:4)፣ ሰማያዊውን ሰማይ፣ ብሩህ የሆነችን ፀሐይ «ወርቃማውን ውበት» እና የእግዚአብሔርን «አስፈሪ ክብር» (አ.መ.ት) ይዘረዝራል። «ሰው በሰማያት የሚያበራውን ብርሃን ሊመለከት አይችልም፣» አለ ኤሊሁ፣ «ሆኖም ግን፣ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ልትገናኘው ትፈልጋለህ» አለው።

የኤሊሁ የመደምደሚያ ቃሎች ምንም እንኳ እግዚአብሔርን በሙላት ልንረዳው ባንችልም፣ እርሱ ታላቅ እና ፍትሐዊ እንደ ሆነ ደግሞም ዓላማ ለሌላው ነገር ሰዎችን እንደማይጨቁን የምናውቅ መሆኑን ያስታውሰናል። ግላዊ ምላሻችን ምን ሊሆን ይችላል? «ስለዚህ ሰዎች ይፈሩታል።» ኢዮብ በዓለም ውስጥ የሚያደርጋቸውን የእግዚአብሔርን ሥራዎች ከተመለከተ በኋላ ወደዚሁ ዓይነት ድምዳሜ መጥቷል (ኢዮብ 28:24-28)።

ኤሊሁ እየተናገረ ሳለ፣ ራቅ ባለ ስፍራ ላይ እውነተኛ የሆነ ዐውሎ ነፋስ እየተነሣ ነበረ፤ ንግግሩን በጨረሰ ጊዜ ዐውሎ ነፋሱ *ጀመረና እግዚአብሔርም በዐውሎ ነፋሱ ውስጥ ነበር!*

ኢዮብ አሁን የጠየቀውን ነገር ሊያገኝ ነው፦ ይህም ከእግዚአብሔር ጋር በግል መገናኘት ነበር። ዝግጁ ነበር ወይ? *እኛስ ዝግጁ ነን ወይ?*



# ለግል ምልከታና ለቡድን ውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ልክ እንደ ኢዮብ፣ እግዚአብሔር ምናልባት ፍትሕ በጐደለው መልኩ እየመራህ እንዳለ የመሰለህ ጊዜን አስብ። በዚያን ጊዜ በእምነቶች ላይ የነበረውን ትግል ዘርዝር።

2. እግዚአብሔር ጻድቅ እና ሉዓላዊ ነው የሚለውን እውነትና ይህች ዓለም በፍትሕ መጓደል የተሞላች ናት የሚለውን እውነት እንዴት ታስታርቀዋለህ?

3. *መዝሙር* 9:15-16ን ያለውን አንብብ። መከራ ከምንለው ምን ያህሉ ያለመታዘዝ ውጤት እራሳችን በቆፈርነው ጉድጓድ ውስጥ መውደቅ እንደ ሆነ ታስባለህ።

4. እግዚአብሔር ሸክሞቻችንን ማቅለል አስፈላጊ አለመሆኑን ካየው፣ ሁልጊዜ የምንሸከምበትን ብርታት ይሰጠናል፣ ሲሉ ዌርዝቢ ተናግረዋል። በገዛ ሕይወትህ ወይም በምታውቀው ሰው ሕይወት ውስጥ ይህን እውነት እንዴት ተመልክተኸዋል?

5. ኤሊሁ ምናልባት ከሚያልፍበት መንገድ ማምለጫ አቋራጭ ኢዮብ ይፈልግ ይሆናል በሚል ፈርቶ ነበር። መከራን ለማስወገድ እኛ አንዳንድ ጊዜ የምንጠቀምባቸው አቋራጭ መንገዶች ምን ዓይነቶች ናቸው?

6. ኤሊሁ ምናልባት ኢዮብ ተስፋ ቈርጦ የኃጢአት ወደ ሆነ ሕይወት ይዘልቅ ይሆናል ብሎ ፈርቶ ነበር። አስቸጋሪ በሆኑ ጊዜያት ውስጥ ስናልፍ ይህ ፈተና የሚሆነው ለምንድን ነው?

7. ኤሊሁ ፍጥረታትን በወቅቶቻቸው የሚቈጣጠርበትን በመጥቀስ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ይገልጣል። የእግዚአብሔርን ታላቅነት የበለጠ የሚያስታውስህ የትኛው ወቅት ነው? ለምን ይህ ይሆናል?

8. መቈጣጠር አለመቻላችን በምን መልኩ ምቾትም ሆነ ኀዘን ሊሆን ይችላል?



# የዕረፍት ጊዜ

በቃላት ጋጋታው ሁሉና ከትሕትና ማጣቱ ጋር፣ ኤሊሁ ኢዮብ ሊሰማው የሚገባ አስፈላጊ የሆነ ጥቂት መልካም ነገሮችን ተናግሮአል። ኤሊሁ በኢዮብ 37-14-18 ውስጥ ወቅታዊ መነጋገሪያ ነገሮች የሆኑ ጥያቄዎችን መጠቀሙ እግዚአብሔር በኢዮብ 38-41 ውስጥ ለጠየቀው ጥያቄዎች ኢዮብን አዘጋጅቶታል። ከሦስቱ ጓደኞቹ በተቃረነ መልኩ፣ ኤሊሁ የኢዮብን ችግር በትክክል ልብ ብሎታል - እርሱ ሦስቱ ጓደኞቹ ይዘረዝሩት እንደ ነበሩት ኃጢአተኛ አልነበረም - ነገር ግን ዝንባሌው ስሕተት ነበረ። ኢዮብ እራሱን የሚያይበት ዓይነት «ቅዱስም» አልነበረም። ኢዮብ ቀስ በቀስ ወደ ተከላካይነት፣ ጤናማ ወዳልሆነ እራስን የማጽደቅ ዝንባሌ እየተረማመደ ነበር። ይህን ሁሉንም አውቃለሁ የሚል ዝንባሌ ነበር እግዚአብሔር በተገለጠ እና በጠየቀው ጊዜ ያጋለጠውና እንዲጠፋ ያደረገው።

ስለዚህ፣ ምንም እንኳ እግዚአብሔር ስለ ኤሊሁ ምንም ነገር ያልተናገረ ቢሆንም፣ ሰውዬው ጠቃሚ የሆነ አገልግሎት ለኢዮብ ሰጥቷል። አለ መታደል ሆኖ፣ ኢዮብ አልተቀበለውም።

ምዕራፍ አሥራ ሦስት

# የመጨረሻው ፈተና

## (ኢዮብ 38-42)

«እግዚአብሔርን አንድ ሚሊዮን ጥያቄዎች የምጠይቀው ነበሩኝ፤ ነገር ግን እርሱን ባገኘሁት ጊዜ፣ ሁሉም ከአእምሮዬ ሸሹ፤ ደግሞም ይህ ቁብ የሚሰጠው ጉዳይ አይመስልም ነበር።»

- ክርስቶፈር ሞርሊይ

ኤሊሁ ይዘረዝረው የነበረ ዐውሎ ነፋስ በመጨረሻው ተነሣ፣ ደግሞም እግዚአብሔር በዐውሎ ነፋስ ውስጥ ሆኖ ኢዮብን ተናገረው። ሦስቱ ጓደኞቹና ኤሊሁ እንዳደረጉት ያለ ለኢዮብ ችግሮች ምላሹ *ስለ እግዚአብሔር የሚነገር ነገር አልነበረም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር መገለጥ ነበር።* አራቱ ሰዎች የእግዚአብሔርን ታላቅነት በተመለከተ ተናግረዋል፣ ነገር ግን ኢዮብን በማሳመን ረገድ አልተሳካላቸውም። እግዚአብሔር ክብሩንና ኃይሉን በገለጠ ጊዜ፣ ኢዮብን ትሑት አደረገው ደግሞም ጸጥ ብሎ ወደ መገዛቱ አመጣው። ያም አቅጣጫን መቀየሪያ ነበር።

ስዊዘርላንዳዊው የሥነ ልቡና አዋቂ ዶ/ር ፖል ቱርኔር «ጊልት ኤንድ ግሬስ» (86) በሚለው መጽሐፉ እንዲህ ሲል ጽፎአል:- «የእግዚአብሔር መልስ ልክ የአንድ ንድፈ አሳብ መደምደሚያ የሆነ አሳብ፣ ዓረፍተ ነገር አይደለም፤ መልሱ እራሱ ነው። እርሱ እራሱን ለኢዮብ ገለጠለት፤ ኢዮብም ከእግዚአብሔር ጋር በግሉ ተገናኘ።»

እኛ እግዚአብሔር ፀሐይ በወጣችበት ሁኔታ ውስጥ እንዲያናግረን እንመርጣለን፣ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ፣ ከዐውሎ ነፋስ ውስጥ



ሊናገረን ያስፈልጋል። በዚህ መልኩ ነው እስራኤልን በሲና ተራራ ላይ (ዘጸአ. 19:16-19፣ ዕብ. 12:18) ደግሞም ከምእተ ዓመታት በኋላ ኤልያስን ያናገረው (1ኛ ነገሥት 19:8-11)። ሕዝቅኤል የእግዚአብሔርን ክብር በዐውሎ ነፋሱ ውስጥ ተመለከተ ደግሞም የእግዚአብሔር ድምፅ ሲናገረው ሰማ (ሕዝቅኤል 1-2)። ይህን በክብር የሆነ የእግዚአብሔርን መገለጥ መለማመድ ኢዮብን ለእግዚአብሔር መልእክት ዝግጁ አደረገው።

እግዚአብሔር ለኢዮብ ይናገረው የነበረ ነገር በፍጥረት ውስጥ ያለውን ሥራ በተመለከተ የሚናገር ሲሆን፣ ሰባ ሰባት ጥያቄዎችን የያዘ ነበር። ከእነዚህም ጥያቄዎች ጋር መለኮታዊ የሆነ ማብራሪያ አብሮ ተያይዞ ነበር። የዚህ ጥያቄ ሙሉው ዓላማ ኢዮብ የገዛ እራሱን አለመብቃት እንዲሁም እግዚአብሔርን ለመገናኘትና ከእርሱ ጋር እኩል ለመሟገት ያለመቻሉን እንዲገነዘብ ለማድረግ ነበር።

«ከዚያ በኋላ ጥራኝ፤ እኔም እመልስልሃለሁ፤ ወይም እኔ ልናገር፣ አንተ መልስልኝ» (ኢዮብ 13:22፣ አ.መ.ት)። አሁን ኢዮብ ላቀረበው ጥያቄ እግዚአብሔር ምላሽ እየሰጠ ነበር።

የእግዚአብሔር ንግግር በሦስት ጥያቄዎች አጠር ብለው መቅረብ ይችላሉ:-

1. «ስለ ፈጠርኳቸው ፍጥረታት ልታብራራልኝ ትችላለህ?» (38:1-18)።
2. «የፈጠርኳቸውን ነገሮች ማስተዳደር ትችላለህ?» (38:39-39:30)።

   *የኢዮብ የመጀመሪያ ምላሽ (40:1-5)*
3. «ፍጥረታትን በቁጥጥርህ ሥር ማዋል ትችላለህ?» (40:6-41:34)።

   *የኢዮብ ሁለተኛ ምላሽ (42:1-6)*

የመጀመሪያው ጥያቄ ፍጥረተ ዓለሙን ወደ መኖር ካመጣበት ከእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ ጋር የሚገናኝ ነበር። ሁለተኛው ለፍጥረቱ እንክብካቤ ከማድረግ እንዲሁም ሦስተኛው በሁለቱ ፍጥረታት ላይ (ምናልባትም በጉማሬ እና አዞ ላይ) የሚያነጣጥር ሲሆን፣ እነርሱን ለማስገዛት ችሎታው እንዳለው የሚጠይቅ ነበር። ኢዮብ እራሱን ማጽደቁን በተመለከተ ንስሐ በገባ ጊዜ፣

እግዚአብሔር ወደ ቀደመው ሁኔታ በተሐድሶ መለሰው (ቍ. 7-17)::

በዚህ ጊዜ እግዚአብአሔር «ጌታ» ተብሎአል ይህም ያህዌ አምላክ ማለት ሲሆን፣ (ከ12:9 በስተቀር) ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ጀምሮ በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ስም ነው:: በንግግራቸው ውስጥ፣ ሰዎቹ ሁሉ «እግዚአብሔር አምላክ» እና «ሁሉን ቻይ» የሚለውን ይጠቀሙ ነበር:: ነገር ግን «ያህዌህ» የሚለውን አይጠቀሙም ነበር:: ይህም ከምእተ ዓመታት በኋላ እግዚአብሔር ለእስራኤል የገለጠው ስም ነበር (ዘጸአ. 3:ከ13 ጀምሮ)፣ ይህም በእራሱ የሚኖር መሆኑን የሚገልጥ («ያለና የሚኖር እኔ ነኝ») መሆኑን የሚያሳይ እንዲሁም ከእስራኤል ጋር በግል የገባውን ቃል ኪዳን የሚያሳይ ስም ነው::

## እኔ የፈጠርኋቸውን ፍጥረታትን በተመለከተ ማብራሪያ መስጠት ትችላለህ? (38:1-3)

ኢዮብ ንግግሩ በጥበብ እና በእውቀት የተሞላ እንደ ሆነ እርግጠኛ ነበር፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር የመጀመሪያው ጥያቄ ያንን ከንቱ ስሜት እንዲያከትም አደረገው:: «ዕውቀት በጐደለው ቃል፣ ዕቅዴን የሚያጨልም ይህ ማን ነው?» (ኢዮብ 38:2፣ አ.መ.ት):: «ሊቪንግ ባይብል የሚባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ እንደዚህ ባለ መልኩ አሳጥሮ ያቀርበዋል:- «ለፍጥረታት የሚደረገውን ስጦታዬን ለመካድ ስለ ምን ድንቁርናህን ትጠቀማለህ?» እግዚአብሔር የኢዮብን ታማኝነትን ወይም ቅንነትን አልተጠራጠረም፤ እርሱ የተጠራጠረው በዓለም ያሉ ነገሮች ስለሚንዙባቸው መንገዶች ለማብራራት፣ ኢዮብ ያለውን ችሎታ ነበር:: ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር ምን ያህል የማያውቀው ነገር እንዳለ አልተገነዘበም:: ወደ እውነተኛ ጥበብ ለመምጣት የመጀመሪያው ደረጃ የገዛ እራሳችንን ድንቁርና ማወቅ ነው::

እግዚአብሔር *ስለ ምድር አፈጣጠር* በመናገር ይጀምራል (38:4-7) ደግሞም እራሱን የግንባታ ስፍራውን ከሚያጤን፣ አቅጣጫዎቹን ከሚነድፍ፣ መሠረቱን ከሚጥል፣ የማዕዘን ድንጋይን በስፍራው ከሚያኖር፣ እንዲሁም መዋቅሩን ከሚሠራ ከአንድ ቀያሽ ጋር ያመሳክራል:: ፍጥረት እጅግ ድንቅ ነው፣ ከዋክብቶች



ይዘምራሉ (1:6፤ 2:1) መላእክቶች ደግሞ በደስታ ይጮኻሉ፣ *ነገር ግን እግዚአብሔር በዚያ ትዕይንት ላይ የለም!* እንግዲያውስ ስለ እግዚአብሔር ሥራዎች ብዙ አውቃለሁ ብሎ እንዴት ይናገራል?

ገና ከመጀመሪያው፣ እግዚአብሔር ፍጥረቱ ሁሉ አስደሳች የሆነ የውብት ገነት እንዲሆን ዐቀደ፤ ነገር ግን ኃጢአት ፍጥረት ወደ አስቀያሚና አሳዛኝ የጦር ሜዳነት ለወጠው:: ሰው በእራስ ወዳድነቱ የተፈጥሮ ሀብቶችን እያባከነ፣ ምድርን፣ አየርን፣ ውኃን እንዲሁም ህዋን እየበከለ አሁን እንደምናውቀው ሕይወትን ለምን ያህል ጊዜ ፕላኔታችን ደግፋ ይዛለች ብለው የሳይንስ ተመራማሪዎች የሚደነቁበትን የእግዚአብሔርን ፍጥረት እያጠፋ ነው:: ማኅተመ ጋንዲ «በዓለም ላይ ለሰው ፍላጎት በቂ የሆነ ነገር አለ፣ ነገር ግን ለሰው ስግብግብ ፍላጎት በቂ የሆነ ነገር የለም» ማለቱ ትክክል ነበር::

ከዚያም ጌታ *ባሕርን* ወደ መመልከቱ ተሻገረ (38:8-11):: እዚህ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ተምሳሌታዊ መግለጫ *ግንባታ* ሳይሆን፣ *ውልደት* ነው:- ባሕሮች እርስ በርስ በምሥጢር ተጠላልፈዋል [ቍ. 8፤ ደግሞም መዝ. (139):13 ተመልከት] ደግሞም ከማኅፀን እንደሚወጣ ሕፃን ጥሶ ይወጣል:: በደመናና በጨለማ ተሸፍነዋል፣ ደግሞም ገደባቸው በእግዚአብሔር ተበጅቶላቸዋል:: «ይህን ሁሉ የሠራ ማን ነው?» ሲል እግዚአብሔር ኢዮብን ጠየቀው፣ ኢዮብ ደግሞ መልሱን አወቀው::

ቀጣዩ እግዚአብሔር የጠቀሰው የፍጥረት ገጽታ *ፀሐይ* ናት (ኢዮብ 38:12-15):: እዚህ ላይ እግዚአብሔር እራሱን ሠራዊቱን (ሰማያዊው ጭፍራ) እንደሚያዝዝ ጄኔራል አድርጎ ያቀርበዋል:: ኢዮብ እንድትወጣ እና ጨለማን እንድትገፍፍ ፀሐይን አዝዟት ያውቃልን? ብርሃን በመላው ዓለም በሚሠራጭበት ጊዜ፣ ማኅተም በሸክላ ወይም ከተዘጋ ቁም ሣጥን በተወሰደ ውብ የሆነ ልብስ ላይ እንደሚደረግ ሁሉ የምድርን አቀማመጥ ዝርዝር ሁኔታ ይገልጻል:: ነገር ግን ብርሃኑ በጨለማ የተደረገ ክፉ ድርጊትንም እንዲያከትም ያደርጋል (ዮሐንስ 3:19-21)፣ ወንጀለኛውንም ተጠቂውን ከማጥቃት ያስቆመዋል::

ቀጣዮቹ አሥራ አንድ ጥያቄዎች (ኢዮብ 38:16-24) *ሰፊ አቅጣጫዎች ካሉዋቸው ፍጥረታት ጋር የሚዛመዱ ናቸው::*

ኢዮብና ጓደኞቹ ከሚገምቱት በላይ ዛሬ ማንም ተራ ልጅ የአጽናፈ ዓለሙን ስፋትና ጥልቀት የበለጠ ያውቃል። ኢዮብ በባሕር ጥልቀት ውስጥ ተመላልሶ «የሲኦልን በሮች» ጐብኝቷልን? የውቅያኖስን ወለል ለማግኘት ምን ያህል ወደ ታች መውረድ እንዳለበት ያውቅ ነበር ወይ? (እስከ አሁን ድረስ ለመለካት የተቻለው ትልቁ ጥልቀት በሰላማዊ ውቅያኖስ ያለው ሲሆን 35,810 ጫማ ወይም 6.78 ማይልስ (10.85 ኪ.ሜትር) ገደማ ነው። ደግሞም ወደ ህዋ ለመድረስ *ቮየጀር 2* የተባለው ተጓዥ ቡድን 4.4 ቢሊዮን ማይልስ (7.05 ቢልዮን ኪ.ሜትር) ለመጓዝ 12 ዓመታት ፈጅቶበታል፤ እንዲሁም 1989 (እ.አ.አ) ከኔፕቲዩን የደመና መታጠፊያ በ3,000 ማይልስ (4.800 ኪ.ሜ) ውስጥ አልፏል!

ከቍጥር 19-21፣ የምሥራቅን እና የምዕራብን ዳርቻ ማስላት ይችል እንደ ሆነ ወይም አድማስ ለመለካት የሚከብድበት/የሚበዛበት እንደ ሆነ እግዚአብሔር ኢዮብን ጠየቀው። ከዚያም እግዚአብሔር እስኪፈልጋቸው ድረስ ግግር በረዶ እና ወራጅ በረዶ የሚከማቹበትን ከፍታ (ቍ. 22-23፤ ዘጸአ. 9:18-26፤ ኢያሱ 10:11) ወይም እግዚአብሔር መብረቅንና ነፋሳትን የሚያስቀምጥበትን ስፍራ (ኢዮብ 38:24) በተመለከተ የሚገባው እንደ ሆነ እግዚአብሔር ኢዮብን ጠየቀው። እርግጠኛ ለመሆን፣ የእግዚአብሔር ቃል ሙሉ በሙሉ ምጸታዊ ነው፤ ነገር ግን የእርሱ ኵሩነትን ለማስቆም እንዲሁም በንስሐ እንዲንበረከክ የሚያደርገው አስፈላጊ የነበረው ነገር ይኸው ነበር።

ኢዮብ ስለ *ዝናብ* ምን ያህል ያውቃል (ቍ. 25-28)? የእግዚአብሔርን ዓላማዎች ለማሳካት እንዴት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ያውቃልን? መብረቅ የት እና መቼ እንደሚባርቅ ሊናገር ይችላልን? ዝናብን እና ጤዛን ማዝነብ በዚህም ምድር የሚያስፈልጋትን ውኃ እንዲሰጥ ማድረግ ይችላልን? ማንም በማይኖርበት ስፍራ ላይ እግዚአብሔር ዝናብን ለምን እንደሚልክ ማብራራት ይችላልን? እንግዲያውስ እግዚአብሔር ከፀደይና ከበልግ ዝናብን መልሶ ወደ ክረምት *ዐመዳይና ውርጭ* (ቍ. 29-30) መቀየር ይችላል። ዝናብ እንዴት እንደሚዘንብ ኢዮብ ካላወቀ፣ በረዶ እንዴት ሊወለድ እንደሚችል ሊረዳ ይችላልን?

በዚህ ጊዜ፣ ምናልባት ኢዮብ የሞት ቅጣት እንዲተላለፍበት



ይፈልግ ይሆናል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር በዚሁ ገፋበት። እግዚአብሔር የኢዮብን ትኩረት በሰማያት ባሉ ነገሮች ላይ በሰባቱ ከዋክብት፣ ኦሪዮን በተባለው ኮከብ ላይ፣ የተለያዩ ኅብረ ክዋክብት («ማዛሮት») እንዲሁም ከልጆቹ ጋር ደብ፣ «አርክቱረስ» በሚባለው ኮከብ ላይ አደረገው። ኢዮብ እነዚህ በሰማይ ላይ ያሉ ፍጥረታት የሚመሩበትን ሕግ ያውቃልን? ደግሞስ እነዚህን ከዋክብቶች እና ፕላኔቶች ሊቈጣጠር እንዲሁም በተገቢው ወቅታቸው እንዲታዩ ሊያደርግ ይችላልን? ሰው ስለ ሰማያት ሊያጠና ይችል ይሆናል፣ ነገር ግን ሊቈጣጠራቸው አይችልም።

«ይህንስ በምድር ላይ እንዲሠለጥን ማድረግ ትችላለህን?» የሚለው ጥያቄ (ቍ. 33) «ኒው አሜሪካን ስታንዳርድ ቨርዥን» በሚባለው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ «በምድር ላይ የሚሠለጥኑበትን ሕግ መወሰን ትችላለህ ወይ?» በሚል ተተርጒሞአል። ኤን አይ ቪ ደግሞ እንዲህ ይነበባል፦ «የሰማያትን ሥርዓት ታውቃለህ? ይህንስ በምድር ላይ እንዲሠለጥን ማድረግ ትችላለህን?» ደግሞም ዘ ሊቪንግ ባይብል (ሕያው ቃል) የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ፣ «. . . ሰማያት ምድርን እንዴት በተጽዕኖዎቻቸው ውስጥ እንደሚያስገቡዋት ታውቃለህን?» ይላል። እዚህ ላይ የሥነ ከዋክብት ጥናት ባለሙያዎች እንደሚከራከሩለት በምድር ላይ በሚሆኑ ክስተቶች ከዋክብቶችና ፕላኔቶች ቀጥተኛ የሆነ ተጽዕኖ አላቸው የሚል አሳብ አለ ወይ? ከቶ የለም። ዓረፍተ ነገሩ እንዲህ ባለ መልኩ አጠር ብሎ ሊቀርብ ይችላል፦ «ኢዮብ ሆይ፣ ስለ ሰማያውያን አካላት ማለትም አንዳንዶች በምድር ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ብለው ስለሚያስቡዋቸው ነገሮች የምታውቅ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ያለህበትን ሁኔታ ለመቀየር ለምን ያንን ሥልጣን አትጠቀምም?» እግዚአብሔር «ቅዱስ በሆነ አሽሙር እየተናገረ» ነበር፣ ደግሞም አንዳንድ መሠረታውያን እውነቶችን እየተናገረ አልነበረም።

በቍጥር 34-38፣ እግዚአብሔር የኢዮብን ትኩረት ወደ ደመና ወሰደው። ኢዮብ የሰማያትን ሕግ ስላወቀ፣ ደመና ዝናብን እንዲሰጥ ሊያዝዘው ይችላልን? አገልጋዩ የሆነ መብረቅ፣ ስለ ተግባሩ አፈጻጸም ዘገባን ይሰጠዋልን? ኢዮብ የደመናትን የሥራ አፈጻጸም ሁኔታ መከታተያ ቅጽ በመውሰድ ልክ እንደ ማሰሮ

ዝናብ ለመስጠት ሊጠቀምበት ይችላልን?

እነዚህን ነገሮች ሁሉ መፍጠር አንድ ነገር ነው፣ ለሰው ልጆች ጥቅም እንዲሰጡ ማድረግ ደግሞ ሌላ ነገር ነው። ከዚያም ጌታ በምድር ላይ ላሉ ነገሮች የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ የሚሰጥበትን ሥራውን በተመለከተ ተከታታይ ጥያቄዎችን ወደ ማቅረቡ አመራ። ሕይወት ከሌላቸው ነገሮች ሕይወት ወዳላቸው ነገሮች አመራ።

**«ፍጥረታቴን ማስተዳደር ትችላለህን?» (38:39-39:30)**

እግዚአብሔር በኢዮብ ምናብ ላይ ስድስት እንስሶች፣ (እነዚህም:- አንበሳ፣ ፍየል፣ አጋዘን፣ የሜዳ አህያ፣ ጐሽ እና ፈረስ) እንዲሁም አምስት አዕዋፋት (እነርሱም:- ቍራ፣ ሰጐን፣ ሺመላ፣ ጭልፊት እና ንስር) ሰብስቦ አመጣ። ስለ እነዚህ ፍጡራን እያሰበ ሳለ፣ ኢዮብ ይህን ጥያቄ መመለስ ይኖርበታል:- «እንዴት እንደሚኖሩና ማን እንደሚንከባከባቸው ታውቃለህን?» በእርግጥ፣ የኢዮብ ምላሽ አላውቅም የሚል መሆን አለበት።

የእግዚአብሔር አዘጋጂነት በእርግጥ አስገራሚ ነው [መዝ. (104) ተመልከት]። በጥበቡ እና በኃይሉ እግዚአብሔር መላው ፍጥረተ ዓለሙን ይቈጣጠራል ደግሞም ፍጡራን ሁሉ እንክብካቤ ማግኘታቸውን ያረጋግጣል። «አንተ እጅህን ትከፍታለህ፣ ሕይወት ላለውም ሁሉ መልካምን ታጠግባለህ» [መዝ. (145):16]። እኛ የሰው ልጆች የሕይወትን ማሽን ስኬታማ በሆነ መልኩ ለማንቀሳቀስ እንቸገራለን፣ ነገር ግን እግዚአብሔር መላው ሕዋን ሳይንቲስቶቻችን ሳይንሳዊ ሕግጋትን በመሠረቱበት እንዲህ ባለ ግልጽ መንገድ ይመራል።

ኢዮብ የአንበሳ ግልገሎችን ወይም የቍራ ጫጩቶችን እንዴት መመገብ እንደሚችል ያውቃልን? (ኢዮብ 38:39-41)። የተራቡ መሆናቸውን እንኳ ያውቃልን? ለእነርሱ ምግብ ከየት ያገኛላቸዋል? ቁራዎች አንበሶች የጣሉትን በድን እንዴት እንደሚያገኙት ያውቃሉ፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለወፎች (ንጹሕ ላልሆኑት ቁራዎች እንኳ!) እንዴት ምግባቸውን እንደሚያገኙ አስተምሯቸዋል።

ከዚያም እግዚአብሔር ከሞት ርእስ ወደ ውልደት ርእስ ተሸጋገ



ረ። በውኑ ኢዮብ የፍየሎችንና የአጋዘንን የእርግዝና ጊዜ እንዲሁም ልጆቻቸውን እንዴት እንደሚወልዱ ያውቃልን? (39:1-4)። የተወለዱት ልጆች እንዴት በደኅና ያድጋሉ ደግሞስ እናቲቱ ከመኖሪያቸው መውጫ ጊዜያት መድረሱን እንዴት ታውቃለች? በግ ጠባቂዎችና ገበሬዎች እንስሶቻቸውን በእርግዝና ጊዜ እና ሲወልዱም ይረዷቸዋል፣ ነገር ግን የዱር አውሬዎች ልጆቻቸውን ያለ ምንም እርዳታ ይወልዳሉ።

የሜዳ አህያ (ቍ. 5-8)፣ በተጨማሪ «የበረሃ አህያም» ተብላ የምትጠራ ሲሆን፣ በበረሃው ውስጥ ነፃ ሆና ትንቀዋለላለች እንዲሁም ለማዳ መሆንን እምቢ ብላለች። ከሰዎች እርዳታ ውጭ ትኖራለች፣ ምክንያቱም ለእራስዋ እንዴት እንክብካቤ ማድረግ እንዳለባት እግዚአብሔር አስተምሯታል። «አውሮክስ» በመባል የሚጠራው ጎሽ እንስሳ ዓለም ውስጥ ያለ ሌላው «የተገለለ» እንስሳ ነበር (ቍ. 9-12)፣ እርሱም ከሰው ሥልጣን በታች መሆንን እምቢ ያለ ነው። በክብት ማደሪያ ውስጥ ልታውለውና፣ ልታስረው በቀንበርህም ልትጠምደው አትችልም ወይም ደግሞ እህልህን እንዲያበራይልህ ልታደርግ አትችልም።

«በዚያን ጊዜ ኢዮብ ሆይ፣ ሲል እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ ጠየቀው:- «እነዚህን እንስሳት በማስገዛቱ ረገድ የማይሳካልህ ከሆነ፣ እኔን በችሎት ላይ በምታገኝበት ጊዜ፣ በመሟገቱ ረገድ እንዴት ይሳካልሃል? ምን ያህልስ ብርቱ ነኝ ብለህ ታስባለህ?»

ከዚያም እግዚአብሔር የሁለት አዕዋፋትን ሁኔታ ወደ ማብራራቱ አመራ፣ እነዚህም ሺመላ ጣዎስ («ጣዎስ») እና ሰጐን ናቸው (ቍ. 13-18)። እግዚአብሔር በዚህ አንቀጽ ውስጥ ኢዮብን ምንም ጥያቄ አልጠየቀውም፤ የሰጐንን ግራ የሆነ አካል እና ባሕርይ ብቻ ነው ያስታወሰው፣ ምናልባትም ደግሞ ይህንን ኢዮብ ሊያብራራ ይችል እንደ ሆነ ጠየቀው።

ሺመላ አገልግሎት በደንብ የሚሰጡ ውብ የሆነ ክንፎች አላት፣ ሰጎን ግን በክንፎቿ ልታደርገው የምትችለው አየሩን ማርገብገብ ብቻ ነው! እግዚአብሔር ወፏን እንደትበርር ነገር ግን ከፈረስ በላይ መሮጥ የምትችል አድርጎ ለምን ሠራት? ዕንቁላሎችዋን የሚያደቡ ገዳዮች በቀላሉ ሊያገኙዋቸው በተጋለጠ ቦታ ላይ ጎጆዋን የምትሠራ ወፍን ለምን ሠራ? ከብዙዎቹ አዕዋፋት ጋር በተቃረነ

መልኩ ስለ ምን ልጆችዋን በተመለከተ ጠንቃቃ ሳትሆን ቀረች?

ቀጣዩ የሚነገርለት እንስሳ ፈረስ ነበር (ቍ. 19-25)፣ እርሱም ስለ ጥንካሬውና ድፍረቱ በታላቅ ሁኔታ የሚሞገስና ዋጋ የሚሰጠው እንስሳ ነበር። ይህ በእርሻ ላይ ያለ ፈረስ መግለጫ ሳይሆን፣ በጦርነት ላይ ያለ ፈረስ መግለጫ ነው፤ ደግሞም ወደ ጦርነት ለመግባት በመጓጓት ሲፈነጭ እና ሲጐደፍር በምናባችሁ ልትመለከቱ ትችላላችሁ። የመለከቱን ድምፅ በሰማ ጊዜ፣ ዝም ብሎ መቆም አይችልም፣ ነገር ግን «መሬቱን እያፈራረሰው» ያለ እስኪመስል ድረስ እጅግ ይሮጣል። አደጋ እንዲጋፈጥ እንዲሁም በጦር ሜዳ ላይ በውጤታማነት እንዲያገለግል የሚያስፈልገውን ጥንካሬና ችሎታ አላብሶ ፈረስን የፈጠረው ኢዮብ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ነው።

ስለ እንስሳቱ የተሰጠው መግለጫ በሁለቱ ወፎች፣ በጭልፊት እና በንስር (ቍ. 26-30) ተደመደመ። ከቦታ ቦታ እንዲዘዋወሩ እና ጐጆዎችን እንዲሠሩ ደመነፍሳዊ የሆነ ጥበብን ለወፎች የሰጠ ማን ነበር? ኢዮብ አይደለም! ንስሮች ከፍ ባሉ ዛፎች ጫፍ ላይ ጐጆ ቻቸውን ይሠራሉ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ልዩ የሆነ የማየትን ችሎታ ስለ ሰጣቸው ከሩቅ ግዳያቸውን ሊያዩትና ቍልቍል በር ረው ሊይዙት ይችላሉ። እግዚአብሔር እንደዚህ ባለ መንገድ ፈጥሮአቸዋልና በድኖችን በቀላሉ በማግኘት እራሳቸውንም ሆነ ልጆቻቸውን ለመመገብ ይችላሉ።

### የኢዮብ የመጀመሪያው ምላሽ (40:1-5)

እግዚአብሔር እርሱን ወደ ፍርድ ቤት ለመውሰድ እና በጉዳዩ ላይ ለመከራከር ኢዮብ ያለውን ፍላጎት በሚያንጸባርቅ ቋንቋ ተጠቀመ። «በውኑ የሚከራከር ሰው ሁሉን ከሚችል አምላክ ጋር ይከራከራልን? ከእግዚአብሔር ጋር የሚዋቀስ እርሱ ይመልስለት» (ኢዮብ 40:2)። እግዚአብሔር ጉዳዩን አቀረበ፤ ከዚያም ጉዳዩን እንዲያቀርብ ለኢዮብ ዕድል ሰጠው። ነገር ግን ኢዮብ የሚያቀርበው ጉዳይ አልነበረውም! የመጀመሪያ ቃሎቹ «እነሆ፣ እኔ ወራዳ ሰው ነኝ!» የሚል ሲሆን «እኔ ለዓይን የማልሞላና የማልጠቅም ሰው ነኝ፣» ከእግዚአብሔር ጋር ለመከራከር ምንም መብት የለኝም፤» ማለት ነው። ኢዮብ አፋቸውን እንዲዘጉ



ለጓደኞቹ ነግሯቸው ነበር (21:5)፣ ደግሞም ኢዮብ በመጣ ጊዜ ሉ ሎች አፋቸውን ዘግተው ነበር (29:9)፣ አሁን ግን ሲናገረው የማይገባ ነገር እናገር ይሆናል ብሎ ስለ ሰጋ ኢዮብ እጁን በአፉ ላይ መጫን አስፈልጎት ነበር (ምሳሌ 30:32፤ ሮሜ 3:19)። *በእግዚአብሔር ፊት ጸጥ እስካላልን ድረስ፣ ሊደረግልን የሚገባውን ነገር ሊያደርግልን አይችልም።* ለእራሳችን ጥብቅና እስከ ቆምን እና ከእግዚአብሔር ጋር እስከ ተከራከርን ድረስ፣ ሥራችንን ሊሠራልን እና በእኛ አማካይነት በውስጣችን ዕቅዶቹን መተግበር አይችልም።

ነገር ግን ኢዮብ በተሰበረ ልብ ዝም ብሎ መናዘዝ በሚገባው ቦታ አልነበረም፣ ዝም ብሎ ነበር ነገር ግን ገና እጁን አልሰጠም፤ ስለዚህም፣ እግዚአብሔር መናገሩን ቀጠለ።

### «ፍጥረቴን ማስተዳደር ትችላለህን?» (40:6-41:34)

አሁንም እንደ ገና ሰፊ የሆነውን የፍጥረትን ነባራዊ ሁኔታ ይዞ ኢዮብን በመግጠም ፈንታ፣ እግዚአብሔር ሁለት ፍጡራንን ብቻ በመምረጥ ልብ ይላቸው ዘንድ ኢዮብን ጠየቀው። ይህም እግዚአብሔር እንዲህ የሚለው ይመስላል። «አጽናፈ ዓለሙን ሁሉ ማወቅና መቈጣጠር ለአንተ እጅግ ይበዛብሃል። ይሁን እንጂ፣ ምርጥ ከሆኑት ሥራዎች ሁለቱ ይኸውልህ። በእነርሱ ምን ማድ ረግ ትችላለህ?»

አሁን አንገብጋቢው ጉዳይ የእግዚአብሔር ኃይል አይደለም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ፍትሕ ነው (ኢዮብ 40:8)። ኢዮብ እግዚአብሔር እርሱን በያዘበት አያያዝ (6:29፤ 27:1-6) እና በክፉ ዎች ላይ ባለመፍረዱ (21:29-31፤ 27:1-17) ፍትሐዊ አይደለም አለ። በ40:9-14 (አ.መ.ት) እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ጠየቀ:- «ኢዮብ ሆይ፣ እንደ እግዚአብሔር ክንድ ያለ ክንድ አለህን? ድምፅህስ እንደ እርሱ ድምፅ ሊያንጐደጕድ ይችላልን? እንግዲያስ ክብርንና ልዕልናን ተጐናጸፍ፣ ግርማ ሞገስንም ተላበስ፤ ቍጣህን አፍስስ፤ ትዕቢተኛውን ሁሉ ተመልክተህ አዋርደው፤ ትዕቢተኛ ውን ሰው ሁሉ ተመልክተህ ዝቅ አድርገው፤ ክፉዎችንም በቆሙበት ስፍራ አድቅቃቸው። ሁሉንም በአንድ ላይ ከዐፈር ደባልቃቸው፤ ፊታቸውንም በመቃብር ውስጥ ሸፍን። እኔም ቀኝ

እጅህ እንደምታድንህ፣ በዚያን ጊዜ አረጋግጬ እቀበላለሁ!»

ይሁን እንጂ፣ ኢዮብ በዓለም ኃጢአተኞች ላይ እንዲፈርድ እግዚአብሔር ዕድሉን ከመስጠቱ በፊት በሁለቱ ግሩም ፍጥረታት፣ በጉማሬ (ቍ. 15- 24) እና በአዞ (41:1-34) ላይ ክብርንና ልዕልናን እንዲጎናጸፍ ጠየቀው። ኢዮብ እነርሱን በማስገዛቱ ረገድ ከተሳካለት፣ እንግዲያውስ ኃጢአተኛ በሆነ ዓለም ላይ ፍርድን ለማስተላለፍ ብቃት ያለው ይሆናል።

**ጉማሬ (ኢዮብ 40:15-24)፡፡** ምንም እንኳ አንዳንዶች ዝሆን ወይም የውኃ ውስጥ ጎሽ እንደ ሆነ የሚያስቡ ቢሆኑም፤ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ስለ እርሱ ማብራሪያ የተሰጠበት እንስሳ ጉማሬ እንደ ሆነ ይስማማሉ። «ብሄሞት» የሚለው ቃል «ከሁሉ የላቀ - አውሬ» ለሚል ቃል ዕብራይስጣዊ የሆነ ትርጉም አለው። የዛሬዎቹ በታላቅ መንገድ በዘመናዊ መሣሪያዎች ለአደን የሚሄዱ አዳኞች በጉማሬ የአካል መጠንም ሆነ ጥንካሬ ምናልባት አይርበተበቱም ይሆናል፣ ነገር ግን በቀስትና በጦር መሣሪያዎች ዘመን ይህ አውሬ አዳጋች የሆነ ጠላት ነበር።

እርሱ የጉማሬም ሆነ የሰው (ቍ. 15) የሁለቱም ፈጣሪ ይሁንና የተለያዩ አድርጎ የሠራቸው መሆኑን እግዚአብሔር ለኢዮብ አስታወሰው። ጉማሬ ሣር ይመገባል ደግሞም ብርቱና ኃይለኛ ነው፤ ኢዮብ ብዙ ጥሩ ጥሩ ምግቦችን ይመገባል፣ ይሁንና ደካማና ከጉማሬ ጋር መታገል የማይቻል ነበር። የሰው አካል (በማወዳደር አነጋገር) ደካማና በቀላሉ የሚጎዳ ሆኖ ሳለ፤ ጉማሬ ኃይለኛ የሆነ አካል አለው፣ ጡንቻዎቹ ጠንካራ ናቸው እንዲሁም አጥንቶቹ እንደ ብረት ሐዲድ ጠንካሮች ናቸው። እንዲሁም ሰው የዕለት ምግቡን ለማግኘት ሲደክም ሳለ ከፍ ካሉ ቦታዎች የመጡ ተክሎችን ይመገባል። ጉማሬ በወንዝ ውስጥ ይኖራል፣ ከውኃው ሥር ይደበቃል። የውኃ ሙላት አያስደነግጠውም፤ እንዲሁም፣ አዳኞች አያስፈራሩትም። በኢዮብ ዘመን፣ ጉማሬን መያዝ የማይቻል ነገር ነው ማለት ይቻላል፣ ነገር ግን ሰውን ለመማረክ ምን ያህል ቀላል ነገር ነው!

«እንግዲህ ኢዮብ ሆይ፣» ሲል እግዚአብሔር ጠየቀው፣ «ይህን ታላቅ ፍጡር ልትማርከውና ልታስገዛው ትችላለህን? የምትችል ከሆነ፣ እንግዲያውስ በዓለም ላይ ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ልትፈርድ



የምትችልበት ኃይልም ሆነ ጥበብ እንዳለህ እምናለሁ።»

**አዞ (ኢዮብ 41:1-34)፡፡** ሌዋታን የሚለው ቃል ከዕብራይስጥ ቃል የተገኘ ትርጉም ለውጥ ሲሆን፣ የዚህ ቃል ሥርወ ቃሉ «መጠምዘዝ፣ መጥመልመል» ማለት ነው። ሰዎች በሜድትራኒያን ባሕር ይኖራሉ ተብሎ የሚታሰብን በባሕር ውስጥ ያሉ ተተናኳይ አውሬዎች ለመግለጽ ይጠቀሙበታል። መዝሙር 104:25-26 ምናልባት ዓሣነባሪን ወይም ዶልፊንን ሊያመለክት ይችላል። አይሁድ ጠላቶቻቸውን (ኢሳ. 27:1)፤ በተለይም ግብፅን [መዝ. (74):13-14] ለመግለጽ ቃሉን ይጠቀሙበታል። ራእይ 12:9 ሰይጣንን «የቀደመ እባብ» በሚል መልኩ ይጠቅሰዋል። በአፈ ታሪክ፣ ሌዋታን የውኃ አካላትን የሚገዛ እና ሰውን የማይፈራ ባለ ብዙ - ራስ የባሕር ተቈጣጣሪ አውሬ ነው።

«ሌዋታንን መያዝ ትችላለህን?» ሲል ጌታ ጠየቀ። «የምትችል ከሆነ፣ ምን ታደርገዋለህ?» (ኢዮብ 41:1-11 ተመልከት)። መልካም፣ ባጠመድኸው አዞ ምን ታደርገዋለህ? የቱንም ያህል ከአንተ ጋር የሚስማማ ቢመስልም ከእርሱ ለማዳ እንስሳ ልታደርገው አትችልም (ቍ. 3-5)፤ ደግሞም ነጋዴዎችም ሊገዙህ አይፈልጉም (ቍ. 6)። ልታሠለጥነው ብትሞክር፣ በፍጥነት ታቆማለህ፣ ሁለተኛም ከዚያም ከቶ አትሞክርም (ቍ. 8-9)! እግዚአብሔር ተግባራዊ የሆነ መደምደሚያ አበጀ፡- «አዞን መያዝ የማትችል ከሆነ፣ በፊቴ እንዴት ልትቆም ትችላለህ?» (ቍ. 10-11)።

በቍጥር 12-24፣ የዚህ ታላቅ ፍጡር ኃይለኛ የሆኑ እጆችና እግሮች፣ ጽኑ የሆኑ ጥርሶች እና ጠንካራ የሆኑ መዳፎች እንዲሁም የማይበገር ቆዳውን በተመለከተ ሥነ ግጥማዊ ማብራሪያዎችን እግዚአብሔር ሰጥቷል (ቍ. 12-17)። አዞ ከውኃ በሚወጣበትና ውኃን በሚያተራምስበት ጊዜ፣ ፀሐይ በትነቱ ላይ ታንጸባርቃለች፤ ደግሞም ከአውሬው አፍ የሚወጣ እሳትና ጢስ ይመስላል (ቍ. 18-21)። ዕቃ ጦሩ እጅግ ጠንካራ ከመሆኑ የተነሣ ወደ የትኛውም ስፍራ ያለ ፍርሃት ይሄዳል (ቍ. 22-24)።

ምዕራፉ የሌዋታን ቍጣንና ድፍረት በማብራራት ይደመደማል (ቍ. 28-34)። ሰዎች ከእርሱ በፍርሃት ይሸሻሉ (ቍ. 25)፣ ነገር ግን እርሱ ከእነርሱ አይሸሽም። በቍጥር 26-29፣ እንደ ገለባ

ቍራጭ ወይም የበሰበሰ እንጨት አድርጎ በመቁጠር ሌዋታን የሚስቅባቸውን እንደ ደረቅ ሣርና የበሰበሰ እንጨት የሚቈጥራቸው ስምንት ልዩ ልዩ መሣሪያዎች እግዚአብሔር ይጠቅሳቸዋል:: ልክ ይህ ፍጡር በዙሪያው ካሉ ነገሮች ሁሉ የሚፈራው ምንም ነገር እንደ ሌለው ሁሉ፣ እንዲሁ ከበታቹ ያሉ ነገሮችንም ሁሉ አይፈራም፤ ምክንያቱም የበታች አካላቱ ልክ ሹል በሆኑ የሸክላ ቍርጥራጮች የተሸፈነ ያህል ከጥቃት የተጠበቀ ነው (ቍ. 30):: በምድር ላይም ሆነ በውኃ ውስጥ የሚፈራው ጠላት የለም (ቍ. 31-32)፣ ምክንያቱም ውኃውን እንደሚፈላ ምንቸት ያደርገዋልና:: በውኃ ውስጥ በሚዋኝበት ጊዜ፣ ቀላዩን እንደ ሰው ሽበት ነጭ ያስመስለዋል!

## የኢዮብ ሁለተኛው ምላሽ (42:1-6)

ኢዮብ እንደ ተሸነፈ ያውቃል:: ከእግዚአብሔር ጋር በጉዳዩ ላይ ሊከራከር የሚችልበት መንገድ አልነበረም:: የእግዚአብሔርን ቃሎች እራሳቸውን በመጥቀስ (ኢዮብ 42:3-4)፣ ኢዮብ በእግዚአብሔር ፊት እራሱን ዝቅ አደረገ፣ እግዚአብሔር ዕ ቅዶቹንም በሚፈጽምበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ኃይሉንና ፍትሕን ተቀበለ (ቍ. 2):: ከዚያም ቃሎቹ ስሕተት እንደ ሆኑና ስለማያውቃቸው ነገሮች እንደ ተናገረ ኢዮብ አምኖ ተቀበለ (ቍ. 3):: እግዚአብሔር ፍትሕ የጐደለውና እርሱ በተገቢው መንገድ ያልያዘው ስለ መሆኑ ያቀረበውን ክስ አነሣ:: እግዚአብሔር የሚሠራው ሁሉ ልክ እንደ ሆነ፣ ደግሞም ሰው በእምነት ሊቀበለው እንደሚገባ ተገነዘበ::

ኢዮብ ለእግዚአብሔር እንዲህ ሲል ተናገረ:- «ጥያቄዎችህን መመለስ አልችልም! ማድረግ የምችለው ስለ ትምክሕቴ መናዘዝ፣ እራሴን ዝቅ ማድረግ እና ንስሐ መግባት ነው::» እስከ አሁን ድ ረስ፣ ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር የነበረው እውቀት ቀጥተኛ ያልሆነና በግል በሚሆን መገለጣዊ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ አልነበረም፤ ነገር ግን ተቀየረ:: ኢዮብ እግዚአብሔርን በግል ተገናኘው ደግሞም እራሱን «አፈርና አመድ» እንደ ሆነ አድርጎ ተመለከተ (ቍ. 6፤ 2:8፣ 12፤ ዘፍጥ. 18:27)::

ቻርለስ ስፐርጀን፣ «የንስሐ በር የደስታን አዳራሽ ይከፍታል፣» በማለት ተናገረ፣ ለኢዮብ ይህ እውነት ሆነ:: በመጽሐፉ ስቃይ (የሚስቅል) አሳብ ውስጥ፣ *ኃጢአተኛው ኢዮብ የእግዚአብሔር አገልጋይ ኢዮብ ሆነ* (ኢዮብ 42:7-9):: በእነዚህ ቍጥሮች ውስጥ የብሉይ ኪዳን ልዩ ማዕረግ በሆነው «ባሪያዬ» (1:8፤ 2:3 ተ መልከቱ) በሚል መጠሪያ እግዚአብሔር ኢዮብን ጠራው:: ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚያገለግለው እንዴት ነው? መከራን በትዕግሥት በመቀበል እንጂ፣ እግዚአብሔርን በመራገም አይደለም፣ በዚያም ደግሞ ዲያብሎስን ጸጥ በማስኘት ነው! በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መከራ መቀበል እግዚአብሔር ለመረጣቸው ጥቂት ሰዎች የሚሰጠው አገልግሎት ነው::

ነገር ግን አገልጋዩ (የእግዚአብሔር ባሪያ) ኢዮብ ለማላጁ ኢዮብ ሆነ:: ስለ እርሱ እውነተኛውን ነገር ባለመናገራቸው ምክንያት በኢዮብ ሦስት ጓደኞች ላይ እግዚአብሔር ተቈጣ (42:7)፣ ደግሞም እነርሱን ይቅር ይላቸው ዘንድ ከኢዮብ ጋር መታረቅ አለባቸው:: *ኢዮብ በእግዚአብሔርና በሦስቱ ጓደኞቹ መካከል አስታራቂ ሆነ!* ጓደኞቹ ይቅር በማለትና ለእነርሱ በመጸለይ ኢዮብ በረከቶቹን በገዛ ሕይወቱ ውስጥ ተመልሰው እንዲመጡ አደረገ (ቍ. 10):: ሌሎቹን ይቅር ማለትን እንቢ በምንልበት ጊዜ፣ እራሳችን ብቻ እንጐዳለን::

ኢዮብ በፊት ከነበረው ሁለት እጥፍ ሀብትና ንብረት ተሰጥቶት ዘመኑን ደመደመ:: አሥሩ ከእግዚአብሔር ጋር አሥሩ ደግሞ በቤ ቱ ውስጥ የሚኖሩ ሃያ ልጆች ነበሩት:: ( እርሱና ሚስቱ እንደ ገና ታርቀው አንድ ላይ ሆኑ::) ጓደኞችና ዘመዶች ኢዮብ የቤት እንስሳትን ለመግዛት ያስቻለውን «ለመቋቋሚያ የሚሆን እርዳታ ገንዘብ» አመጡ፤ በመጨረሻ ደግሞ ኢዮብ ቀድሞ ከነበሩት ሁለት እጥፍ የቤት እንስሳት ነበሩት:: እንደ ገና ሀብታም ሰው ሆነ:: «የእጥፉ» ቀመር ለኢዮብ ዕድሜም የሚሠራ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ታሪኩ በሚጀምርበት ጊዜ የሰባ ዓመት ሰው መሆኑ ግድ ነበር:: [መዝ. (90):10]፣ ደግሞም ዕድሜ ዕጥፍ እንዲሆንለት እግዚአብሔ ር ለኢዮብ ፈቀደለት (ኢዮብ 42:16)::

በምሥራቅ፣ በተለይ ውብ ሴቶችን በመውለዳቸው ወላጆች ኩራት ይሰማቸው ነበር:: ኢዮብ ደግሞ ሦስት ውብ ሴቶች ልጆች ነበሩት:- እነርሱም ጀሚማህ («እርግብ»)፣ ኬዚያ (ቀረፋ)

እንዲሁም ኬረን-ሀፑች («የዓይን ቀለም ቀንድ») የሚባሉ ናቸው። ጀሚማ አደብ የገዛች ነበረች፣ ኬዚያ የሽቱ ጠረን ያላት ነበረች፣ እንዲሁም ኬረን- ሀፑች ማስዋቢያዎች ነበሯች!

«ከሽምግልናና ዕድሜን ጠግቦ» መሞት የእያንዳንዱ ሰው ግብ ነበር። ረጅም ዕድሜ ከመኖር ያለፈ ትርጉም አለው፤ በመልካም የሚደመደም የባለጠግነትና የተሟላ ሕይወትን ማሳለፍ ማለት ነው። ይህም አብርሃምና ይስሐቅ የሞቱበት ሁኔታ ነው (ዘፍጥ. 25:8፤ 35:29)፣ ደግሞም ንጉሥ ዳዊት የሞተበት ሁኔታ ነው (1ኛ ዜና 29:28)።



# ለግል ምልከታና ለቡድን ውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔርን አግኝታችሁት ሁለት ጥያቄዎችን ማቅረብ የምትችሉ ቢሆን፣ እነዚያ ጥያቄዎች ምንድን ናቸው?

2. «መከራ እየተቀበልን ባለንበት ጊዜ፣ ስለ እግዚአብሔር ብዙ ማወቅ አያስፈልገንም፣ የበለጠ ማወቅ የሚያስፈልገን እራሱን እግዚአብሔርን ነው፣» ለሚለው ዓረፍተ ነገር (አባባል) ምላሻችሁ ምንድን ነው?

3. እግዚአብሔር ሀልዎቱን /መገኘቱን/ ለአንተ በሰላም ጊዜም ሆነ በችግር ጊዜ የገለጠበትን ሁኔታ አብራራ።

4. ስለ እግዚአብሔር ሀልዎት እንዲሁም በዓለም ላይ ስላለው ታላቅነት የበለጠ ሊያሳውቁህ የሚችሉ የእንስሳት ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ለምን እነርሱ ሊያስታውሱህ ቻሉ?

5. ለእግዚአብሔር ምላሽ ለመስጠት ዕድሉን ባገኘ ጊዜ፣ በኢዮብ አእምሮ ውስጥ ይመላለስ የነበረው ምንድን ነው ብለህ ትገምታለህ?

6. ዶ/ር ዌርዝቢ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡- «እግዚአብሔር የሚያደርገው የቱም ነገር ትክክል እንደ ሆነ እና ሰው በእምነት ሊቀበለው እንደሚገባ ኢዮብ ተገንዝቦአል፡፡» ለዚህ ዓረፍተ ነገር የምትሰጠው ምላሽህ ምንድን ነው?

7. የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመቀበልና በመከራ ውስጥ እርሱን በመታመን ረገድ የንስሐ ሚና ምንድን ነው?

8. ጉዳዩን ከእግዚአብሔር ጋር ከፈታ በኋላ፣ ኢዮብ ችግሩን ከጓደኞቹ ጋር መፍታት አስፈልጎት ነበር፡፡ በአስቸጋሪ ጊዜ ውስጥ በምናልፍበት ጊዜ በሕይወታችን ውስጥ ኢዮብን በምን መልኩ ነው እንደ መስታወት ማየት የሚኖርብን?

9. የሰይጣን የመጀመሪያው ክርክሩ በረከትን ስላገኘ ነው እግዚአብሔርን የታዘዘው የሚለው ከነበረ፣ በመከራ ውስጥ ኢዮብ ያደረገው ጉዞ በሰማያዊ ችሎት ፊት የሚያረጋግጠው ምንን ነበር?



# መደምደሚያ

ይህን የኢዮብን መጽሐፍ የመጨሻውን ምዕራፍ በተሳሳተ መንገድ ሁሉም መከራና ችግሮች በመፈታት ይደመድማሉ፣ ጥላቻዎች ሁሉ ይቅር ይባላሉ፣ እያንዳንዱ ሰውም፣ ከዚያ በኋላ በደስታ ይኖራል» በሚል መንገድ መተርጐም አይኖርብንም፡፡ ሁልጊዜ እንዲህ አይሆንም፡፡ ይህ ምዕራፍ ምንም ነገር ቢደርስብን፣ እግዚአብሔር ሁልጊዜ የመጨረሻውን ምዕራፍ ይጽፋል ሲል ያረጋግጥልናል፡፡ ስለዚህ፣ ልንፈራ አይገባንም፡፡ ያለንበት ሁኔታ የቱንም ያህል ሥቃይ የሞላበት ቢሆንም፣ ትክክለኛ የሆነውን ነገር እንደሚያደርግ ልንታመንበት ይገባል፡፡

ነገር ግን የኢዮብ ትልቁ በረከት የጤናው እና የሀብቱ ዳግም መመለስ ወይም የቤተሰቡ እና ከሰዎች ጋር የነበረው ወዳጅነት ዳግመኛ መመሥረት አልነበረም፡፡ ትልቁ በረከቱ እግዚአብሔርን በተሻለ መንገድ ማወቁ፤ እንዲሁም ሥራዎቹንም በተሻለ መንገድ መገንዘቡ ነበር፡፡ ልክ ያዕቆብ እንደ ጻፈው፣ «እነሆ፣ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፣ ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል፣ ጌታም እንደ ፈጸመለት አይታችኋል፤ ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና» (ያዕ. 5:11)፡፡ ደግሞም ዕብራውያን 12:11፣ «ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፣ ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል» የሚለውን ያስታውሰናል፡፡

«በመላው የኢዮብ ታሪክ ውስጥ፣ የእግዚአብሔርን ትዕግሥት እንዲሁም የሰውን ጽናት እንመለከታለን፡፡ እነዚህ በኅብረት ሲተ ገበሩ፣ ጉዳዩ ይረጋገጣል፡፡ ይህም ከእሳት እንደሚወጣ ወርቅ፣ የሕይወትን አክሊል እንደ መወሰድ ነው፣» በማለት ጂ. ካምፐቤል ሞርጋን ጽፈዋል፡፡ («ዘ አንሰርስ ኦፍ ጂሰስ ቱ ጆብ፣ 117)፡፡

ወደ ሕይወታችን ማንኛውም ነገር እንዲመጣ እግዚአብሔር ቢፈቅድም፣ እርሱ ሁልጊዜ የእራሱ የሆነ «መደምደሚያ» አለው፡፡ እርሱ የመጨረሻውን ምዕራፍ ይጽፋል፣ ያ ደግሞ ሁሉንም ነገር ዋጋ ያለው ያደርገዋል፡፡

ስለዚህ፣ ታጋሽ ሁን!

## የአዲስ ኪዳን የ«. . .ሁን» ተከታታይ መጻሕፍት፣

1. ለጌታ የተገዛህ ሁን (የማቴዎስ ወንጌል)
2. ተግተህ አገልግል (የማርቆስ ወንጌል)
3. ርኅሩኅ ሁን (የሉቃስ ወንጌል ምዕ. 1-13)
4. የበረታህ ሁን (የሉቃስ ወንጌል ምዕ. 14-24)
5. ሕያው ሁን (የዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 1-12)
6. የተለወጣችሁ ሁኑ (የዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 13-28)
7. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተመላለስ (የሐዋ. ምዕ. 1-12)
8. ደፍረህ መስክር (የሐዋ. ምዕ. 13-28)
9. ተስማማ (ሮሜ)
10. ጠቢብ ሁን (1ኛ ቆሮንቶስ)
11. ተጽናና (2ኛ ቆሮንቶስ)
12. አርነት መውጣት (ገላትያ)
13. ፍለጋ የሌለውን ባለጠግነት ውረስ (ኤፌሶን)
14. ደስተኛ ሁን (ፊልጵስዩስ)
15. ፍጹም ሁን (ቈላስይስ)
16. ለምጽአቱ ተዘጋጅ (1ኛ እና 2ኛ ተሰሎንቄ)
17. ታማኝ ሁን (1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስ፣ ቲቶና ፊልሞና)
18. በማየት ሳይሆን በእምነት ተመላለስ (ዕብራውያን)
19. ተስፋ አድርግ (1ኛ ጴጥሮስ)
20. ንቃ (2ኛ ጴጥሮስ፣ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ፣ ይሁዳ)
21. እውነተኛ ሁን (1ኛ ዮሐንስ)
22. በብስለት ማደግ (ያዕቆብ)
23. ድል አድራጊ ሁን (የዮሐንስ ራእይ)

## የብሉይ ኪዳን የ«. . .ሁን» ተከታታይ መጻሕፍት፣

1. የምታመልክ ሁን (መዝሙረ ዳዊት ምዕ. 1-89)
2. አመስጋኝ ሁን (መዝሙረ ዳዊት ምዕ. 90-150)
3. የተካንህ ሁን (መጽሐፈ ምሳሌ)
4. እርካታ ይኑርህ (መክብብ)
5. ቅዱስ ሁን (ዘሌዋውያን)
6. የተሰጠህ ሁን (ሩት/አስቴር)
7. ቈራጥ ሁን (ነህምያ)
8. ወሳኝ ሁን (ኤርምያስ)
9. ታጋሽ ሁን (ኢዮብ)